# ዳ ን ኤ ል ና

# አሥራ ሁለቱ

# ደቂቅ ነቢያት

አሳታሚ፡-
ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

አዲስ አበባ።

www.ethiopianorthodox.org

## መግለጫ:-

«እስመ አልቦ ዘይገብር እግዚአብሔር ዘኢከሠተ ወዘኢነገረ ለአግብርቲሁ ነቢያት» ልዑል እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለአገልጋዮቹ ነቢያት አስቀድሞ ሳይገልጥ ምንም ነገር አያደርግም /አሞጽ ፫ : ፯/ ተብሎ እንደተነገረው ነቢይነት በፍላጐት ወይም በምኞት የማይገኝ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ። ምክንያቱም ጌታ በወንጌል «ኢይክል ሰብእ ነሢአ ጸጋ ለሊሁ እመ ኢተውህበ እምሰማይ» ማንም ሰው ከላይ ከልዑል እግዚአብሔር ካልተሰጠው በስተቀር ምንም ነገር ሊኖረው አይችልም በማለት አስተምሯልና ነው ። /ዮሐ ፫ : ፳፯/

ነቢያት ቍጥራቸው ብዙ ቢሆንም፣ እንደ ቀኖና መጻሕፍት አቆጣጠር ዐበይት ነቢያትና ደቂቅ ነቢያት ተብለው በሁለት ክፍል ተመድበዋል ። ዐበይት ነቢያት የሚባሉት አራት ሲሆኑ ደቂቅ ነቢያት የሚባሉት ደግሞ አሥራ ሁለት ናቸው። በዝርዝርም ሲገለጹ:-

### ዐበይት ነቢያት:-

ሀ. ኢሳይያስ
ለ. ኤርምያስ
ሐ. ሕዝቅኤል
መ. ዳንኤል ሲሆኑ

### ደቂቅ ነቢያት የሚባሉት ደግሞ:-

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ሆሴዕ | ሠ. አብድዩ | በ. ሶፎንያስ |
| ለ. አሞጽ | ረ. ዮናስ | ተ. ሐጌ |
| ሐ. ሚክያስ | ሰ. ናሆም | ኀ. ዘካርያስ |
| መ. ኢዮኤል | ቀ. ዕንባቆም | ነ. ሚልክያስ ናቸው። |

❖ **ዳንኤል** የአይሁድ ንጉሣዊ ቤተሰብ በመሆኑ ቤተሰቦቹ ወደባቢሎን በተማረኩ ጊዜ ገና በልጅነቱ ተማርኮ ወርዶአል። በባቢሎን ሳለም ለነቢይነት የተጠራ ሲሆን በነቢይነት የነበረበትም ዘመን ከ ፮፻፭ - ፭፻፴፮ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው ። ዳንኤል እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ በስደት ሀገር እንደ ዮሴፍ ወልደ ያዕቆብ ያለሹመት ያደረበት ጊዜ አልነበረም።

ዳንኤል መንግሥተ ባቢሎን ከወደቀ በኋላ በመንግሥተ ፋርስ እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ኖሮአል። ነቢዩ ስለ መሲሕ « የሰው እጅ ሳይነካው ከረጅም ተራራ የወረደ ድንጋይ መንግሥታትን ሁሉ ይፈጫል» በማለት ክርስቶስን በእብን፣ ድንግል ማርያምን በደብር መስሎ ተናግሯል። /ዳን ፪ : ፴፬ - ፴፭/ በመቀጠልም «በሌሊት ራእይ አየሁ እነሆ! የሰው ልጅ...የሚመስል ከሰማይ ደመና ጋር መጣ . . . ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር፣ መንግሥትም ተሰጠው፣ ግዛቱም የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ነው ። መንግሥቱም የማይጠፋ ነው» ። በማለት የመሲሕን ሥጋዌና ዘለዓለማዊ መንግሥት ተናግሯል። /፯ : ፲፫ - ፲፬/

❖ ዐሥራ ሁለቱ ደቂቅ ነቢያት:- ከሆሴዕ እስከ ሚልክያስ ያሉት ነቢያት ደቂቅ መባላቸው የዐበይት ነቢያት ልጆች በመሆናቸው ወይም በዘመን ከዐበይት ነቢያት የሚያንሱ በመሆናቸው አይደለም። ወይም በቀኖናዊ መዐርግ ሁለተኛ ስለሆኑ አይደለም። ጽሑፋቸው ከዐበይት ነቢያት ጽሑፍ አነስተኛ በመሆኑ ብቻ ደቂቅ ነቢያት ተብለዋል።

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

❖ **1.ሆሴዕ** በአራቱ ነገሥተ ይሁዳ ማለትም በዖዝያን፣ በኢዮአታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ የነበረ ሲሆን፣ ዘመኑም ከ ፯፻፹፯ - ፯፻፳፯ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው:: ሆሴዕ የዐሥሩ ነገድ ነቢይ ሲሆን መልእክቱም ለዐሥሩ ነገድ ነው:: የመጽሐፈ ሆሴዕ ዋና መልእክት ፍቅረ እግዚአብሔርን መግለጥ በመሆኑ የብሉይ ኪዳን ዮሐንስ የሚል ስያሜ ከመተርጉማን ተሰጥቶታል:: /፪ : ፳፩ - ፳፫/፣ መጽሐፈ ሆሴዕ ስለ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት፣ ወደ ግብጽ መሰደድና መመለሱ፣ ስለሞቱና ትንሣኤው በኅብረ አምሳል ተናግሯል፤በሐዲስ ኪዳንም በብዛት ተጠቅሶ ይገኛል::/ሆሴዕ ፮ : ፩ - ፫ ፤ ፲፩ : ፩ - ፪፤ ማቴ ፪ : ፲፬ - ፲፭ ፤ ሮሜ ፱ : ፳፭ - ፳፮ /::

❖ **2. አሞጽ** ፤ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አሞጽ በሚል ስም የሚጠሩ ሦስት ሰዎች አሉ፤ እነሱም የነቢዩ ኢሳይያስ አባት፤ የምናሴ ልጅ ንጉሥ አሞጽና ከደቂቅ ነቢያት አንዱ አሞጽ ናቸው ::/ኢሳ ፩ : ፩ ፤ 2ነገሥ ፳፩ : ፲፰ - ፲፱/ አሞጽ ለነቢይነት የተጠራው ከ ፯፻፹፯ - ፯፻፴፭ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በነበረው በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያንና ከ ፯፻፺ - ፯፻፵፱ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በነበረው የእስራኤል ንጉሥ በዳግማዊ ኢዮርብአም ዘመነ መንግሥት ነበር:: አሞጽ ከነቢያት ወገን ሳይሆን በግብርና ሥራ ላይ ሳለ ጥሪ ደርሶታል :: /፯ : ፲፬ - ፲፮/ አሞጽ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ጊዜ ስለሚሆነው ተአምር ተናግሯል:: ሕዝብና አሕዛብ በክርስቶስ አንድ እንደሚሆኑ መናገሩንም ቅዱሳን ሐዋርያት ጠቅሰውታል:: /፭ : ፳ ፤ ፱ : ፲፩ - ፲፪ ፤ የሐዋ. ሥራ ፲፭ : ፲፭ - ፲፰ /፤

❖ **3. ሚክያስ** ከ ፯፻፵፱ - ፯፻፺፯ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በነበሩት በሦስቱ የይሁዳ ነገሥታት በኢዮአታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥታት የነበረ ሲሆን የሆሴዕና የኢሳይያስ የዘመን ጓደኛ ነው:: ኢሳይያስ በኢየሩሳሌም ሲያስተምር፣ ሚክያስ ደግሞ በምዕራባዊው ይሁዳ ያስተምርና ትንቢት ይናገር ነበር:: ስለ መሲሕ የተናገሩት ትንቢት፣ያስተማሩት ትምህርት ብዙውን ጊዜ ይመሳሰላል::/ሚክ.፬ : ፩ - ፭ ፤ ኢሳ ፪ : ፩ - ፬/ ኢሳይያስ « ድንግል ትፀንሳለች» ብሎ ደረቅ ትንቢት እንደተናገረ ሚክያስም «አንቺ ቤተልሔም ! የኤፍራታ ምድር ከይሁዳ አእላፋት አታንሽም፣ ሕዝቤ እስራኤልን የሚጠብቃቸው ንጉሥ ከአንቺ ይወለዳልና» በማለት ደረቅ ትንቢት ተናግሯል:: / ኢሳ. ፯ : ፲፬! ሚክ. ፭ : ፩ - ፭/

❖ **4. ኢዮኤል** የሁለቱ ነገድ ነቢይ ሲሆን በ፰፻፴ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እንደነበረ ይታወቃል:: ስለመንፈስ ቅዱስ መውረድና በዕለተ ስቅለት ስለሚፈጸመው ተአምር፣ የምሥራች ወንጌልም እንደሚሰበክ በግልጥ ተናግሯል:: /፪ : ፳፰ - ፴፪/ መጽሐፈ ኢዮኤል በዕብራይስጥ ቀኖና መጻሕፍት ከሆሴዕ ቀጥሎ ሲሆን በሰባ ሊቃናትና በግእዙ ቀኖና ከሚክያስ በኋላ ነው::

❖ **5. አብድዮ** ለነቢይነት የተጠራው በኢዮራም ዘመነ መንግሥት ፰፻፺ - ፰፻፵፫ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እንደነበር ስለ ኤዶምያስ የተናገረውን ትንቢት በአንደኛ ነገሥት ፰ : ፳ - ፳፪ እና በ፪ኛ ዜና መ. ፳፩ : ፰ - ፲ ላይ የተመዘገበውን ማነጻጸር ያስፈልጋል:: ለነቢይነት ከመጠራቱ አስቀድሞ የንጉሥ አክአብ የቤት አዛዥ ስለነበር ብዙኃን ነቢያትን ከኤልዛቤል እጅ አድኗል:: በቀጣይም የነቢዩ [illegible] /፩ኛ ነገ. ፲፰ : ፩ - ፲፱ / ስለ መሲሕም «ወይከውን መድኃኒት በደብረ ጽዮን» በጽዮን ተራራ መድኃኒት ይሆናል በማለት የክርስቶስን አዳኝነት ተንብይዋል :: አብድዩ ቍ.፲፯

❖ **6. ዮናስ** ከራሱ መጽሐፍ ውጭ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጠቀሰ ነቢይ ነው :: /፪ ነገ. ፲፬ : ፳፭/ ዮናስ የእስራኤል ነቢይ ሲሆን፣ የነበረበትም ዘመን በዳግማዊ ኢዮርብአም ዘመነ መንግሥት ፰፻፳፭ - ፯፻፹፬ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው:: ከአሞጽም ጋር በዘመን ይገናኛሉ:: በትውፊት እንደሚነገረው ዮናስ ነቢዩ ኤልያስ ከሞት ያስነሣው የሠራፕታ መበለት ልጅ ነው:: /፩ነገ ፲፰ : ፲ - ፳፬/ ዮናስ ሦስት ሌሊትና ሦስት መዓልት በከርሠ ዐንበሪ መቆየቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት ሌሊትና ሦስት መዓልት በከርሠ መቃብር ለመቆየቱና መነሣቱ ምሳሌ ሆኖ በራሱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተጠቅሶአል፤ /ማቴ.፲፪ : ፴፱ - ፵ ፤ ሉቃ ፲፩ : ፳፱ - ፴/ ዮናስ ያስተማረው ከምድረ እስራኤል ውጪ በነነዌ ስለሆነ፣ ነቢየ አሕዛብ ይባላል:: ይህም እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚያቋቁም የሚያመለክት ነው :: መጽሐፈ ዮናስ በዕብራይስጡ ቀኖና መጻሕፍት የደቂቅ ነቢያት አምስተኛ ሲሆን በግእዝና በሰባ ሊቃናት ስድስተኛ ነው::

❖ **7. ናሆም** እንደ ዮናስ በነነዌ ላይ ትንቢት የተናገረ ነቢይ ነው፤ በዮናስ የተነገረው የነነዌ ጥፋት ከናሆም በኋላ በ607 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ተፈጽሞአል :: ናሆም ለነቢይነት የተጠራው በ፯፻፴ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነበር :: ቅፍርናሆም የናሆም ሰፈር ማለት ስለሆነ የነቢዩ የትውልድ ሀገር እየተባለ የሚጠራው ቦታ ቅፍርናሆም መሆኑ ታውቋል:: የናሆም ትንቢታዊ መልእክት በነነዌ ላይ ያተኮረ በመሆኑ እንደ ዮናስ የአሕዛብ ነቢይ እየተባለ ይጠራል:: ትንቢተ ናሆም በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ከሚክያስ ቀጥሎ ሲሆን በግእዝና በሰባ ሊቃናት ቀኖና መጻሕፍት ከዮናስ በኋላ ገብቶአል::

❖ **8. ዕንባቆም** ከ፯፻፰ - ፭፻፺፯ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በዘመነ ኢዮአቄም ያስተምርና ትንቢት ይናገር የነበረ ነቢይ ነው :: ዳንኤልና ሕዝቅኤል በባቢሎን ጊውዋንን ሲያስተምሩ፣ ኤርምያስና ዕንባቆም በኢየሩሳሌም ትሩፋንን ያስተምሩ ነበር:: ዕንባቆም ስለ መሲሕ«እግዚአብሔርሰ ይመጽእ እምቴማን፣ ወቅዱስኒ እምደብረ ፋራን» እግዚአብሔር ከቴማን፣ቅዱሱም ከደብረ ፋራን ይመጣል» በማለት ተናግሯል:: ዕን. ፫ : ፫ ፤

❖ **9. ሶፎንያስ** በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት ፯፻፴፱ - ፯፻፰ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ትንቢት ይናገር ነበር / ሶፎ ፩ : ፩/ ይኸውም ከኢየሩሳሌም የጥፋት ቀን ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ ነበር :: የሶፎንያስ አባት ኩሺ በመባሉ አፍራካዊ እንደ ሆነ የተረጐሙ ሊቃውንት አሉ፣ ሆኖም ቅድመ አያቱ ሴዴቅያስ በመሆኑ አይሁዳዊ እንጂ አፍሪካዊ እንዳልሆነ ይታወቃል ::/ሶፎ ፩ : ፩/ ሶፎንያስ «ናሁ አስተዳለወ እግዚአብሔር መሥዋዕቶ፣ ወቀደሰሙ ለኅሩያኒሁ» እነሆ እግዚአብሔር መሥዋዕቱን አዘጋጀ፣ የመረጣቸውንም ቀደሳቸው በማለት እግዚአብሔር በመሲሕ ክርስቶስ መሥዋትነት ምእመናንን ማዳኑን ተንብዮአል:: / ሶፎ ፩ : ፯/

❖ **10. ሐጌ** በባቢሎን የተወለደ ሲሆን ከመጀመሪያዎቹ ከባቢሎን ምርኮ ተመላሾች ጋር የመጣ ፣ ከምርኮ መልስ በኋላ የነበረ ነቢይ ነው:: ሐጌና ዘካርያስ ከሚጠት በኋላ የአይሁድን ማኅበራዊ ሕይወት በአንድነት ያስተካከሉ፣ ስለ ቤተ መቅደሱ እንደ ገና መታነጽ ሕዝቡን ያተጋ ነበር :: ፪ኛው ቤተ መቅደስ የተሠራው

www.ethiopianorthodox.org

ከ ፭፻፳ - ፭፻፲፰ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ነቢዩ ሐጌ ዋና ረዳት ነበር፡፡ /ሐጌ፩ : ፰ ዕዝ. ፭ : ፩ / ነቢዩ ሐጌ የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ ያየ ሰው ስለ ነበር በሁለተኛው ቤተ መቅደስ ሕንጸት ጊዜ ሽማግሌ እንደሚሆን ግልጥ ነው /ሐጌ ፪: ፫/ ነቢዩ ሐጌ « ከፊተኛው ይልቅ የዚህ የሁለተኛው ቤት ክብር ይበልጣል» በማለት በሁለተኛው ቤተ መቅደስ አንጻር በክርስቶስ ስለምትሠራውና በደሙ ስለምትከብረው ቤተ ክርስቲያን ተንብዮአል ፡፡ /ሐጌ ፪ : ፱ - ፲/

◆ **11. ዘካርያስ** በዒዋዊ ሀገር በባቢሎን ተወልዶአል፣ አባቱ በራክዩ በባቢሎን ስለሞተ ከአያቱ ሐዶ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶአል፡፡ እርሱና አያቱ በዘሩባቤል መሪነት ከመጀመሪያው ግሩፕ ጋር ከምርኮ ተመልሰዋል፡፡ /ነሕ. ፲፪ - ፩ - ፯/ ዘካርያስ ትንቢቱን የጀመረው በ፭፻፳ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው፡፡ ዘካርያስ የገዥው ዘሩባቤል፣ የነቢዩ ሐጌና የሊቀ ካህናቱ ኢያሱ ወልደ ዮሴዴቅ የዘመን ጓደኛ ነበር፡፡ /ዘካ. ፫ : ፩ - ፬ ፤ ፮: ፲፩ ፤ ዕዝ ፭ : ፩ - ፪/ እንደ አይሁድ ትውፊት ዘካርያስ የሐጌ ቅርብ ወዳጅ ነበር፣ መቃብራቸውም ጎን ለጎን ነው ፡፡ ዘካርያስ ስለ መሲሕ በርካታ ግልጥ /ደረቅ/ ትንቢቶችን ማለትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱን፣ በሠላሳ ብር መሸጡን ፣ በጦር መወጋቱን፣ ሕማማተ መስቀልን መቀበሉን፣ በደብረ ዘይት ዳግም ምጽአቱን በግልጥ ተናግሯል፡፡/፱ : ፱- ፲ ፤ ፲፩ : ፪ ፤ ፲፪ : ፲ ፤ ፲፫ : ፮ - ፯ ፤ ፲፬ : ፬/

◆ **12. ሚልክያስ** ሚልክያስ ከጸሐፍት ነቢያት መጨረሻው ነቢይ ነበር፡፡ ከሐጌና ዘካርያስ በኋላ ከ ፬፻፶ - ፬፻ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በነቢይነት ቆይቶአል፡፡ በሚልክያስ ጊዜ አይሁድ ከባቢሎን ተመልሰው ነበር፡፡ ዕዝራና ነህምያ ቤተ አይሁድን በሚያስተካክሉበት ጊዜ ሚልክያስም ተባባሪያቸው ነበር፡፡ በሚልክያስ ዘመን ሕዝቡና ካህናቱ ቤተ እግዚአብሔርን፣ ሥርዐተ መሥዋዕቱን ያቃልሉ ነበር፣ ዐሥራቱና በኩራቱን ሲሰርቁ ነበር ፣ ፍችና ሁለተኛ ጋብቻ ልማድ ሆኖ ነበር፡፡ ነቢዩ ይህን በተመለከተ ገሥጸአቸዋል፡፡ /ሚል.፩ : ፮ - ፰ ፤ ፪ : ፩ - ፫ : ፫ -፲፬/ ሚልክያስ ስለ መሲሕ «ወይመጽእ ግብተ ውስተ ጽርሑ እግዚአብሔር ዘአንትሙ ተኀሥሡ» እናንተ የምትፈልጉት እግዚአብሔር ድንገት ወደ አዳራሹ ይመጣል በማለት ተናግሯል፡፡ ስለ መሥዋዕተ ወንጌልም በግልጥ ተንብዮአል፡፡ /ሚል ፩ : ፲፩/

በመሆኑም ቀደም ሲል የብሉያት መጻሕፍት አንድምታ ትርጓሜ በተከታታይ እየታተሙ ለሚያስተምሩ መምህራን፣ ለሚማሩ ደቀ መዛሙርትና ሙያውን መረዳት ለሚሹ አንባቢያን እንደሚደርሱ በተገባው ቃል መሠረት የተጠቀሱት መጻሕፍተ ነቢያት አንድምታ ትርጓሜ በማሳተሚያ ድርጅታችን አማካኝነት ታትመው መቅረባቸውን ስናበሥር መንፈሳዊ ደስታ ይሰማናል ፡፡

«ዘተወክፈ ነቢየ መስመ ነቢይ አስበ ነቢይ ይነሥእ»

አባ ጳውሎስ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

፲፱፻፺፰ ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ዘዳንኤል ነቢይ

## መቅድም

ዳንኤል፡ ማለት፡ ፍትሐ፡ እግዚአብሔር፣ ዳኛ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው፤ የዳንኤል፡ እናትና፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅ፣ ኢኮንያን፡ የኤልያቄም፡ ልጆች፡ ናቸው፤ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ሲማረኩ፡ አብረው፡ ተማርከው፡ ሄደዋል፤ ስለምን ጻድቃንን፡ ከኃጥአን፡ ጋራ፡ ያስማርካቸዋል፡ ቢሉ፡ ስለ፡ ሦስት፡ ነገር፡ ነው፤ ተማርከው፡ ከሄዱበት፡ አገር ወደ፡ ኃጢአት፣ ወደ፡ ጣዖት፡ እንዳይሄዱ፡ ይመክሯቸዋል፤ ያስተምሯቸዋልና፤ አንድም፡ መስፍን፡ ሁነው፣ ይገዟቸዋልና፡ እንደ፡ ኤርምያስ፣ እንደ፡ መርዶክዮስ፡ እንደሱ፤ አንድም፡ መከራ፡ ከበዛ፡ ዘንድ፡ ጸጋ፡ ክብር፡ ይበዛልና፤

አመ፡ ሠላስ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ለኢዮአቄም፡ ንጉሠ፡ ይሁዳ፣

የይሁዳው፡ ንጉሥ፡ ኢዮአቄም፣ በነገሠ፡ በሦስተኛው፡ ዘመን፤ አንድም፡ አመ፡ ሠላስ፡ ወርኀ፡ ይላል፤ ኢዮአቄም፡ ያለው፡ ኢኮንያንን፡ ነው፤ ኢኮንያን በነገሠ፡ በሦስተኛ፡ ወር፡ ናቡከደነፆር፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ መጣ፤

ወይቤሎ፡ ንጉሥ፡ ለአዝፋኔዝ፡ ሊቀ፡ ሕፅዋኒሁ፡ ኀረይ፡ ሊተ፡ እምደቂቀ፡ ዔዎ፤

ንጉሥ፡ ባለሟሉን፡ አስፋኔዝን፡ ተማርከው፡ ከመጡ፡ ልጆች፡ የነገሥታት፡ ልጆች፡ የሆኑ፣ መልክ፡ መልካም፡ የሆኑ፣ ጥበብ፡ የሚስማማቸው፣ ዕውቀት፡ ያላቸው፣ ቢቆሙ፡ የማይታክቱትን፡ ምረጥልኝ፡ አለው፤

ወይምሀርዎሙ፡ መጽሐፈ፡ ወነገረ፡ ፋርስ፣

መጽሐፈ፡ ፍልስፍና፣

ወነገረ፡ ፋርስ፣

ጥበብ፤ አንድም፡ መጽሐፈ፡ ወግ፣ ታሪክ፣ ወነገረ፡ ፋርስ፡ ቋንቋ፡ ያስተምሯቸው፤ እኔ፡ ከምበላው፡ እኔ፡ ከምጠጣው፡ እየሰጡ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይሕርስዎሙ፡ ሠለስተ፡ ዓመተ፤

ሕሙግ፡ መብልዕ፡ የሐምግ፡ ልበ፡ እንዲል፣ ያልሆነ፡ ምግብ፡ ልቡና፡ ያደነቁራልና፡ እኔ፡ ከም በላው፣ እኔ፡ ከምጠጣው፡ እየ ሰጡ፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ይንከባ ከቧቸው፤ ሐራስን፡ ይዞ፡ ይሕ ርስዎሙ፡ አለ፤ ያን፡ ጊዜ፡ ብዙ፡ ልጆች፡ ተመረጡ፤ ዳንኤል፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅም፡ አብረው፡ ተመርጠዋል፤

ወወለጠ፡ አስማቲሆሙ፡ ሊቀ፡ ሕፅዋ ኒሁ፡ ለንጉሥ፤

የንጉሥ፡ አዛዥ፡ ቢትወደድ፡ የሚሆን፡ አስፋኔዝ፡ ስማቸ ውን፡ ለወጠ፤ ዛሬ፡ ባርያን፡ ገዝተው፡ ማርከው፡ ስሙን፡ እንዲለውጡ፣ ስማቸውንም፡ በአንባር፡ ያወጣል፤ ዳንኤል፡ ማለት፡ ፍትሐ፡ እግዚአብሔር፣ ዳኛ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነበር፤ ብልጣሶር፡ አለው፤ አምኃ፡ ቤል፡ አስበ፡ ቤል፡ ማለት፡ ነው፤ አናንያ፡ ማለት፡ ደመና፡ ማለት፡ ነበር፤ ሲድ ራቅ፡ አለው፤ ሠቃየ፡ አትክ ልት፡ ማለት፡ ነው፤ አዛርያ፡ ማለት፡ ረድኤት፡ ማለት፡ ነበር፤ ሚሳቅ፡ አለው፤ ፀሐቂ፡ ተጋሂ፡ ፍንው፡ ለግብረ፡ መል እክት፡ ማለት፡ ነው፤ ሚሳ ኤል፡ ማለት፡ ሰምዓኒ፡ እግዚ አብሔር፡ ማለት፡ ነበር፤ አብ ደናጎ፡ አለው፤ ገብረ፡ ዳጎን፡ ማለት፡ ነው፤

ወአጥብዓ፡ ዳንኤል፡ በልቡ፣

ዳንኤል፡ በልቡ፡ ጥሬ፡ እን ብላ፡ በማለት፡ ጨከነ፤

ወአስተብቍዖ፡ ወይቤሎ፡ ሀበነ፡ ዘርዓ፡ ምድር፣

አስፋኔዝ፡ አሚሳድን፡ ተወራጅ፡ ሹሞላቸዋል፤ ዳንኤል፡ ማለ ደው፤ እንዲህ፡ አለው፤ ሽን ብራ፡ ጥሬ፡ ስጠን፡ አለው፤ ይህስ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይሆ ናል፡ ብሎ፡ ባቄላ፡ ጥሬ፡ ስጠን፡ አለው፤ ስለምን፡ ቢሉ፡ ተጠ ይፎ፣ ዛሬ፡ እኛ፡ በሃይማኖት፡ የማይመስለንን፡ መብሉን፡ መጠ ጡን፡ እንድንጠየፍ፡ ጥሬውን፡ እንዳንጠየፍ፤ አንድም፡ በተ ድላ፡ በደስታ፡ ከተማሩት፡ ትም ህርት፡ በመከራ፡ የተማሩት፡ ትምህርት፡ ይጠቅማል፡ ብሎ፤ አንድም፡ መከራ፡ ከበዛ፡ ዘንድ፡ ጸጋ፡ ክብር፡ ይበዛልና፤



ወለእመ፡ ርእየክሙ፡ ንጉሥ፡ ድግዱ ጋኒክሙ፡ እምእለ፡ ይበልዑ፡ እማዕደ፡ ንጉሥ፡ እፈርህ፡ አነ፡ ከመ፡ ኢይኴ ንነኒ፡ ንጉሥ፡ ርእስየ፣

ከንጉሥ፡ ግብር፡ ከሚበሉ፡ ሰዎች፡ ተለይታችሁ፡ ከስታችሁ፡ ንጉሥ፡ ያያችሁ፡ እንደሆነ፡ ከታች፡ ባቴን፡ ከላይ፡ አንገ ቴን፡ ይቀጣኛል፡ ብዬ፡ እኔ፡ እፈራለሁ፡ አላቸው፤

አመክሮሙ፡ ለአግብርቲከ፡ አሡረ፡ ዕለተ፤

እኛን፡ ባሮችህን፡ አሥር፡ ቀን፡ ፍተነን፡ አሉት፤ የነሱን፡ ድርጎ፡ እርሱ፡ እየተቀበለ፡ ለነዚያ፡ ጥሬ፡ እየሰጠ፡ አሥር፡ ቀን፡ ተቀመጠ፤

ወእምድኅረ፡ አሡር፡ ዕለት፡ ኀየሰት፡ ነፍስቶሙ፡ ወሠነየት፡ ራእዮሙ፡ እም እለ፡ ይበልዑ፡ እማዕደ፡ ንጉሥ፤

ከአሥር፡ ቀን፡ በኋላ፡ የን ጉሥ፡ ግብር፡ ከሚበሉ፡ ይልቅ፡ ሰውነታቸው፡ አምሮ፡ መልካ ቸው፡ ጠርቶ፡ ታየ፤ ከዚህ፡ በኋላ፡ የነሱን፡ ድርጎ፡ እርሱ፡ እየተቀበለ፡ ለነዚያ፡ ጥሬ፡ ባቄላ፡ እየሰጠ፡ ተቀመጠ፤ ወይሕር ስዎሙ፡ ፫ተ፡ ዓመተ፡ ያለው፡ ከተፈጸመ፡ በኋላ፡ ንጉሥ፡ አስመጥቶ፡ ጠየቃቸው፤

ወዘኃሠሠ፡ ንጉሥ፡ ምክረ፡ ወጥበበ፡ ረከበ፡ በነቤሆሙ፡ ትእሥርተ፡ እደ፡ እምጥቱ፡ ሰብአ፡ ሰገል፡ ወሰብአ፡ ሥራይ፡ እለ፡ ሀለዉ፡ ውስተ፡ መንግሥቱ፤

በሚገዛው፡ አገር፡ ካሉ፡ ሥር፡ ከሚምሱ፣ ቅጠል፡ ከሚበጥሱ፡ ይልቅ፡ ንጉሥ፡ የፈለገውን፡ ምክሩን፡ ጥበቡን፡ ከነዚያ፡ ዘንድ፡ አሥር፡ እጥፍ፡ በልጦ፡ አገኘ፤ አስመጥቶ፡ በጠየቃቸው፡ በሁለተኛው፡ ዘመን፡ ንጉሥ፡ ሕልም፡ አይቶ፡ ሕልሙም፡ ትርጓሜውም፡ ተዘነጋው፤ ስለ ምን፡ ቢሉ፡ የማለዳ፡ እንቅልፍ፡ ነበረበትና፤ አንድም፡ የዳንኤ ልን፡ ክብር፡ የሚገልጥ፡ መን ፈስ፡ ቅዱስ፡ አዘንግቶታል፤ ከበላው፡ አብልቶ፣ ከጠጣው፡ አጠጥቶ፡ የሚያኖራቸው፡ ጠቢ ባን፡ መፈክራን፡ ነበሩት፤ አስ መጥቶ፡ ሕልም፡ አይቼ፡ ሕል ሙም፡ ትርጓሜውም፡ ተዘንግ ቶኛልና፡ ንገሩኝ፡ አላቸው፤ የነ ገራችሁኝ፡ እንደሆነ፡ እሾማ ችኋለሁ፤ እሸልማችኋለሁ፤ ድርጎ፡ እዳርጋችኋለሁ፤ ያልነ ገራችሁኝ፡ እንደሆነ፡ እቀጣች ኋለሁ፡ አላቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

ንጉሥ፡ ይንግር፡ ሕልሞ፡ ወንሕነ፡ ናየ
ድዕ፡ ፍካሬሁ፨

ንጉሥ፡ ሕልሙን፡ ንገረን፨
ትርጓሜውን፡ እኛ፡ እንነግርሃ
ለን፡ አሉት፤ አንተስ፡ ከፈር
ዖን፡ ትበልጣለህ፨ እኛስ፡ ከዮ
ሴፍ፡ እናንሳለን፤ ዮሴፍ፡ የተ
ረጐመለት፡ ሕልሙን፡ ቢነግ
ረው፡ አይደለም፡ አሉት፤ እኔስ፡
ነገሩ፡ ተዘንግቶኛል፡ አላቸው፤
ባይሆንም፡ ቀን፡ ስጡን፡ አሉት፤
ኋላስ፡ ልብ፡ ወለድ፡ ነገር፡
ትሻላችሁ፤ ጊዜው፡ ሳያልፍ፡
አሁን፡ ትዝ፡ ትዝ፡ ሲለኝ፡
ንገሩኝ፡ አላቸው፤ ይኸማ፡ እን
ደምን፡ ይሆንልናል፡ አሉት፤
እንግዲያ፡ ከበላሁት፡ አብልቼ፡
ከጠጣሁት፡ አጠጥቼ፡ የማኖ
ራችሁ፡ ለዚህ፡ ብዬ፡ ነው፡
እንጂ፡ እንኪያ፡ ፈረስን፡ ናችሁ፡
እጋልባችሁ፤ በቅሎን፡ ናችሁ፡
አሰግራችሁ፤ ጦርን፡ ናችሁ፡
እወረውራችሁ፤ ጋሻን፡ ናችሁ፡
እመክታችሁ፡ ለዚህ፡ ብዬ፡ አይ
ደለም፡ አክብሬ፡ የማኖራችሁ፨
ንሳ፡ በሰይፍ፡ በላቸው፡ አለ፤
ወወጽአ፡ አርዮክ፡ ሰያፊ፡ ወአ
ኃዘ፡ ይቅትሎሙ፡ ለጠቢባነ፡
ባቢሎን፤ ታዛዥ፡ ወጥቶ፡
ጠቢባነ፡ ባቢሎንን፡ ያጠፋ
ቸው፡ ጀመረ፤ ዳንኤል፡ ቀርቦ፡
ጠየቀ፤ በይነ፡ ምንት፡ ወጽአ፡
ትእዛዝ፡ ዕፁብ፡ እምኀበ፡

ንጉሥ፤ እንዲህ፡ ያለ፡ ጭንቅ፡
ትእዛዝ፡ ከንጉሥ፡ ዘንድ፡
ስለምን፡ ታዘዘ፡ አለ፤ ንጉሥ፡
ሕልም፡ አይቶ፡ ሕልሙም፡
ትርጓሜውም፡ ተዘንግቶት፡
ነው፡ አሉት፤ ይኸንንስ፡ ሕል
ሙንም፡ ትርጓሜውንም፡ እኔ፡
እነግረዋለሁ፡ ይዘኸኝ፡ ግባ፡
አለው፤ ይዞት፡ ገባ፤ ለነዚያ፡
የነሳውን፡ ቀን፡ ለሱ፡ ሦስት፡
ቀን፡ ሰጠው፤ ፫ቱ፡ ደቂቅን፡
ይዞ፡ ቀኖና፡ ገባ፨ ለዳንኤል፡
ዕለቱን፡ ተገልጦለታል፤ ስለ
ምን፡ ቢሉ፡ ጥሬ፡ እንብላ፡ በማ
ለት፡ ጨክኖ፡ ነበርና፤ ስለተገ
ለጠለት፡ ግን፡ ዕለቱን፡ አልወ
ጣም፤ ስለምን፡ ቢሉ፡ ሱባዔ፡
ለማስከበር፡ ለሠለስቱ፡ ደቂቅ፡
በሦስተኛው፡ ቀን፡ ተገለጠላቸው፤
ሕልሙንም፡ ትርጓሜውንም፡
አግኝቸዋለሁና፡ ይዘኸኝ፡ ግባ፡
አለው፤ ይዞት፡ ገባ፤ አንተኑ፡
ብልጣሶር፡ ዘትፌክር፡ ሕል
ምየ፨ ሕልሜን፡ የምትተረጕ
ምልኝ፡ አንተ፡ ብልጣሶር፡
ነህ፡ አለው፤ እግዚአብሔር፡
እንጂ፡ ምሥጢር፡ የገለጠለት፡
ይተረጕማል፡ ብሎ፡ አምልኮተ፡
እግዚአብሔርን፡ ሰበከለት፤ በል፡
ንገረኝ፡ አለው፤ ከዕለታት፡
አንድ፡ ቀን፡ በሰገነት፡ ተቀም
ጠህ፡ ሳለ፡ የሴት፡ ወይዘሮ፨
የወንድ፡ መኰንን፡ ሲወጣ፡



ሲገባ፡ ሲታጠቅ፡ ሲፈታ፡ አይ
ተህ፡ እኔ፡ ይህን፡ ዓለም፡
እንደ፡ ገል፡ ቀጥቅጬ፡ እንደ፡
ሰም፡ አቅልጬ፡ ገዛሁት፤ ከኔ፡
በኋላ፡ የሚነሳው፡ ንጉሥ፡ ከኔ፡
የሚበልጥ፡ ይሆን? ወይስ፡
ከኔ፡ የሚያንስ፡ ይሆን፡ ብለህ፡
አሰብህ፤ በዚያው፡ ሌሊት፨
ርእሱ፡ ዘወርቅ፡ እንግድዓሁ፡
ወእደዊሁ፡ ወመዝራዕቱ፡ ዘብ
ሩር፡ ሐቌሁ፡ ወከርሡ፡ ዘብ
ርት፡ ቁየጺሁ፡ ዘሐፂን፡ መን
ፈቀ፡ እግሩ፡ ዘልሕኵት፡ ወመ
ንፈቀ፡ እግሩ፡ ዘሐፂን፨ ምስል፡
ቁሞ፡ አንተን፡ አንተን፡ ሲመ
ለከት፡ አየህ፤ አቄልቁሎ፡ አቄ
ልቁሎ፡ ነው፡ ቢሉ፡ እንደ፡
አፍራሪቆ፡ ድንኳን፡ ሁኖ፡
አይቶታል፤ አግድሞ፡ አግድሞ፡
ነው፡ ቢሉ፡ እንደ፡ በርኖስ፡
አዝራር፨ እንደ፡ ነፍጥ፡ መሽ
ቢያ፨ እንደ፡ አልጋ፡ ዙፋን፡
ሁኖ፡ አይቶታል፤ ይኸነንም፡
አይተህ፡ ሳለ፡ ከረጅም፡ ተራራ፡
እጅ፡ ሳይነካው፡ ታላቅ፡ ደን
ጊያ፡ ተፈንቅሎ፡ ወርዶ፡ በፊት፡
ሸክላውን፨ ቀጥሎ፡ ብረቱን፨
ቀጥሎ፡ ብርቱን፨ ቀጥሎ፡ ብሩን፨
ቀጥሎ፡ ወርቁን፨ ቀጥቅጦ፡
ተራራ፡ አህሎ፡ በዓለም፡ ሲመላ፡
አየህ፡ አለው፤

እሙን፡ ሕልሙ፨ ሕልሙ፡
ዕውነት፡ ነው፤ ትርጓሜውን፡

ንገረኝ፡ አለው፤ ራሱ፡ የወርቅ፡
የተባልህ፡ አንተ፡ ነህ፤ ወርቅ፡
ከሁሉ፡ በላይ፡ ነው፤ አንተም፡
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ነህና፡ ደረቱ፡
እጁ፡ ክንዱ፡ የብር፡ ነው፡ የተ
ባለ፡ ዳርዮስ፡ ነው፤ ከወርቅ፡
ብር፡ ያንሳል፤ እሱም፡ ከአንተ፡
በታች፡ ነውና፨ ወገቡ፡ ሆዱ፡
የብርት፡ ነው፡ የተባለ፡ ቂሮስ፡
ነው፤ የብርት፡ ድምፁ፡ ከሩቅ፡
ይሰማል፤ የሱም፡ ዜና፡ መን
ግሥቱ፡ ከሩቅ፡ ተሰምቷልና፡
ጭንና፡ ጭኑ፡ የብረት፡ ነው፡
የተባለ፡ እስክንድር፡ ነው፤
ብረት፡ ጽኑ፡ ነው፤ እሱም፡
ጽኑ፡ ንጉሥ፡ ነውና፡ እኩሌታ፡
እግሩ፡ የሸክላ፡ እኩሌታ፡ እግሩ፡
የብረት፡ የተባሉ፡ እስክንድር፡
ያነገሣቸው፡ ነገሥታት፡
ናቸው፤ በብረት፡ የተመሰሉት፡
በጥሊሞስ፡ አንጥያኮስ፡ ብርቱ
ዎች፨ በሸክላ፡ የተመሰሉት፡
ሶልፎስ፡ ደማጥርያኖስ፡ ደካ
ሞች፡ ናቸው፤ ይህስ፡ አይደለም፤
ወበመዋዕሊሆሙ፡ ለእሉ፡ ይመ
ጽእ፡ አምላከ፡ ሰማይ፡ ይላል፡
ብሎ፡ በመንግሥት፡ ያወርዱ
ታል፤ ርእሱ፡ ዘወርቅ፡ የተባለ፡
መንግሥተ፡ ባቢሎን፡ ነው፤
እንግድዓሁ፡ ዘብሩር፡ የተባለ፡
መንግሥተ፡ ሜዶን፡ ነው፤
ሐቌሁ፡ ዘብርት፡ የተባለ፡ መን
ግሥተ፡ ፋርስ፡ መንግሥተ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሮም፡ ነው። ቀዋሚ፡ ዘሐ ፂን፡ የተባለ፡ መንግሥተ፡ ዕርዕ፡ ነው። መንግሥተ፡ ሮምን፡ ከዚህ፡ ያገቡ፡ እንደሆነ፡ ያነን፡ መንግሥተ፡ ፋርስ፡ ብቻ፡ ማለት፡ ነው። መንፈቀ፡ እግሩ፡ ዘልሕኵት፡ ወዘሐፂን፡ የተ ባሉ፡ እለ፡ ሕውሳን፡ በዘርዓ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ የሚላቸው፡ ቀይ፤ ጥቁር፤ ረጅም፡ አጭር፡ ሁነው፡ በሮም፡ የሚነግሡ፡ ነገሥታት፡ ናቸው። ይህን፡ ሁሉ፡ አድቅቆ፡ ተራራ፡ አህሎ፡ በዓለም፡ ሲመላ፡ ማየትህ፡ ጌታ፡ ከሰማየ፡ ሰማያት፡ ወርዶ፤ ከድንግል፡ ማርያም፡ ተወልዶ፡ እነዚህን፡ ሁሉ፡ አጥፍቶ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ መንግሥቱን፡ ይገልጣል። በሥጋ፡ ዕሩየ፡ መንበር፡ ይሆ ናል፡ አለው።

እሙን፡ ሕልሙ፡ ወርቱዕ፡ ፍካሬሁ፤ ሕልሙ፡ እውነት፡ ነው። ትርጓሜውም፡ የቀና፡ ነው፡ ብሎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ሰገደ። ዳንኤልንም፡ ቢትወደድ፡ አድ ርጎ፡ ሾመው። ወግዶ በዘመኑ እንዲሉ፤ ዳንኤልም፡ ተካሶ፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅን፡ ቀኛዝማች ነት፤ ግራዝማችነት፤ ከንቲባ ነት፡ አሹሟቸዋል። እሱ፡ በከ ተማ፡ እነሱ፡ በገጠር፡ የሚ ኖሩ፡ ሁነዋል። ስለምን፡ ቢሉ፤ ነገረ፡ ሠሪ፡ ለመጠበቅ። አን ድም፡ ትምህርት፡ እንዲሰፋ፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ በነገሠ፡ በአሥራ፡ ስምንት፡ ዘመን፡ በሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ ቀናን፡ ያሉ፡ ሰዎች፡ ርእሱ፡ ዘወርቅ፡ ተብሎ፡ የተ ተረጐመልህ፡ አንተ፡ እንጂ፡ ነህ። አሁንም፡ ስሳ፡ ክንድ፡ ቁመቱ፤ ስድስት፡ ክንድ፡ ደረቱ፡ ጣዖት፡ በሐቅለ፡ አዱራን፡ ይቁም፡ ብለህ፡ አዋጅ፡ ንገር። ሁሉ፡ ለሱ፡ ይስገድ፡ አሉት። እንደ፡ ነገሩት፡ ስሳ፡ ክንድ፡ ቁመቱ፤ ስድስት፡ ክንድ፡ ደረቱ፡ ጣዖት፡ በሐቅለ፡ አዱራን፡ አቆመ። ሁሉም፡ ሰገደለት፤ ዳንኤል፤ ሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ ሳይሰግዱ፡ ቀሩ።

ወይእዜኒ፡ ሀለዉ፡ ሠለስቱ፡ ዕደው፡ እለ፡ ሤምኮሙ፡ ላዕለ፡ ግብረ፡ በሐው ርተ፡ ባቢሎን፡ ዘኢያምለኩ፡ አምላከከ፡ ወኢሰገዱ፡ ለምስል፡ ዘወርቅ፡ ዘገበርከ፤

ለሠራኸው፡ ለወርቅ፡ ምስል፡ ያልሰገዱ፤ አምላክህን፡ ያላመ ለኩ፤ በባቢሎን፡ የሾምካቸው፡ ሦስት፡ ሰዎች፡ አሉ፡ ብለው፡ ነገሩት። ይህን፡ በሰማ፡ ጊዜ፡ ተቆ ጥቶ፡ ሲድራቅ፡ ሚሳቅ፡ አብደ ናጎን፡ ያመጧቸው፡ ዘንድ፡ አዘዘ፤ አመጧቸው።

ወይቤሎሙ፡ አማንክሙኑ፡ ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፡ ኢታመልኩ፡ አም ላኪየ፡ ወኢትሰግዱ፡ ለምስል፡ ዘወርቅ፡ ዘገበርኩ፤

ሲድራቅ፤ ሚሳቅ፤ አብደናጎ፡ በውነቱ፡ ፈጣሪዬን፡ አታመል ኩም? ለሠራሁትስ፡ ለወርቅ፡ ምስል፡አትሰግዱም? አላቸው።



ወአውሥእዎ፡ ወይቤልዎ፡ ኢንፈቅድ፡ ንሕነሰ፡ ንሰጠውከ፡ በዝ፡ ነገር፤

አምላክህን፡ እናመልካለን፡ ብለን፡ ልንመልስልህ፡ አንወድም፡ አሉት።

ሀሎ፡ አምላክነ፡ ውስተ፡ ሰማይ፡ ዘኪ ያሁ፡ ናመልክ፡ ንሕነ፡ ወይክል፡ አድኅ ኖተነ፡ እምእዴከ።

እኛ፡ የምናመልከው፡ ፈጣሪያ ችን፡ በሰማይ፡ አለ። ከአንተ፡ እጅ፡ እኛን፡ ማዳን፡ ይቻለዋል። ንጉሥ፡ ግዱን፡ ቁርጡን፡ ታውቅ፡ ዘንድ፡ አምላክህን፡ አናመልክም። ለሠራኸው፡ ለወ ርቅ፡ ምስል፡ አንሰግድም፡ አሉት። ያን፡ ጊዜ፡ ንጉሥ፡ ጦር፡ ነጠቀባቸው። ሰይፍ፡ መዘ ዘባቸው። እሳቱን፡ እጥፍ፡ ድርብ፡ አድርገው፡ ያነድዱ፡ ዘንድ፡ አዘዘ። ኃያላኑን፡ ጽኑዓኑን፡ እጃቸውን፡ እግራቸውን፡ አሥ ረው፡ ከእቶነ፡ እሳት፡ ይጥሏ ቸው፡ ዘንድ፡ አዘዘ። ከዚያ፡ እጃቸውን፡ እግራቸውን፡ አሥ ረው፡ ከነልባልባቸው፤ ከነጫ ማቸው፤ ከነቁንጽል፡ ቀሚሳ ቸው፤ ከነመጐናጠፊያቸው፤ ከነኩፌታቸው፡ በተራዳ፡ እየ ገፉ፡ ከእሳት፡ ጕድጓድ፡ ጣሏ ቸው። ስለምን፡ ቢሉ፡ አላልቦ፡ ይግደላቸው፡ ብለው። አንድም፡ የንጉሥ፡ ሹማምንት፡ ናቸውና፡ ከናዋርዳቸው፡ ብለው። ወቆመ፡ አዛርያ፡ ወጸለየ፤

አዛርያ፡ ቁሞ፡ ጸለየ። ዳንኤል፡ ጥሬ፡ እንብላ፡ በማለት፡ እንደ፡ ጨከነ፡ እሱም፡ እቶነ፡ እሳት፡ እንግባ፡ በማለት፡ ጨክኖ፡ ነበ ርና፡ ለአዛርያ፡ ሰጥቶ፡ ተና ገረ፡ እንጂ፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ በውስጥ፡ ዳንኤል፡ በአፍአ፡ ሁነው፡ ተናግረውታል።

ወኢኃደጉ፡ አስተዋድዮቶሙ፡ ወዐልያን፡ ኀበ፡ ንጉሥ፡ እንዲል፤ የንጉሥ፡ ሎሌዎች፡ በምት ሐት፡ እንጂ፡ አበረዱት፡ ብለው፡ ነገሩት። ደም፡ ደም፡ ያለውን፡ እንጨት፡ ቅንጭቡን፡ ቁልቋ ሉን፡ አደሮ፡ ማሩን፡ ድኙን፡ ዶጉን፡ ጨመሩ።

ወተሰዐለ፡ ነበልባል፡ ፺ ወ ፱፡ እመት፤

ነበልባሉ፡ አርብዓ፡ ዘጠኝ፡ ክንድ፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አለ። በምን፡ ታው ቋል፡ ቢሉ፡ ነቢዩ፡ ባወቀ፡ ተና ግሮታል።

ወወረደ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ወዘበጦ፡ ለነበልባለ፡ እሳት፡ ወረሰዮ፡ ከመ፡ ነፋስ፡ ቈሪር።

መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ወርዶ፡ ነበልባሉን፡ መታው፤ እንደጠል፡ አቀዘቀዘው፤ ያን፡ ጊዜ፡ እንደ፡ አንድ፡ ልብ፡ መካሪ፤ እንደ፡ አንድ፡ ቃል፡ ተናጋሪ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሁነው፡ እግዚአብሔርን፡ አመ
ሰገኑ፤ ናቡከደነፆር፡ ሲያመሰ
ግኑ፡ ሰምቶ፡ አደነቀ፤ ሹማ
ምንቱን፡ ሦስት፡ ሰዎች፡ አሥ
ረን፡ ከእቶኑ፡ እሳት፡ ጥለን፡
አልነበረም? እኔ፡ አራት፡ ሰዎች፡
የተፈቱ፡ ሁነው፡ በእቶኑ፡ እሳት፡
መካከል፡ ሲመላለሱ፡ አያለሁ፡
አላቸው፤

ወገጹ፡ ለራብዓይ፡ ከመ፡ ወልደ፡ እግዚ
አብሔር፡ ይመስል፤

አራተኛውስ፡ የእግዚአብሔር፡
የባሕርይ፡ ልጁን፡ ይመስላል፤
መንፈስ፡ ቅዱስ፡ አፉን፡ ጸፍቶ፡
ያናግረዋል፤ አንድም፡ ገብርኤ
ልን፡ ይመስላል፡ ገብርኤል፡
ማለት፡ አምላክ፡ ወሰብእ፡
ማለት፡ ነው፤ ከዚህ፡ በኋላ፡
ናቡከደነፆር፡ ከእቶኑ፡ እሳት፡
ቀርቦ፡ አንትሙ፡ ሲድራቅ፡
ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፡ ንዑ፡
ዑ፡ ባላቸው፡ ጊዜ፡ እንደ፡ ሳቢሳ፡
ጭ፡ ሁነው፡ ብር፡ ብር፡ እያሉ፡
ዐጥተዋል፤ አዋጁን፡ በአዋጅ፡
መልሶ፤

መቦ፡ ዘጸረፈ፡ ወነበበ፡ ላዕለ፡
ምላከ፡ ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡
ወአብደናጎ፡ ይትኰነን፡ ነፍሱ፡
ይትበርበር፡ ቤቱ፡ ብሎ፡
አዋጅ፡ ነገረ፤ ዕርገተ፡ አራዊ
ትንም፡ ተናገሯል፤ ወርኢኩ፡
ብእሴ፡ ዘይለብስ፡ ጠብደነ፡
ብሎ፡ የሥጋዌንም፡ ነገር፡ ተና
ግሯል፤ የአክላዐባጥራንንም፡
ነገር፡ ተናገሯል፤ የሐሳዊ፡
መሲሕን፣ የምጽአትንም፡ ነገር፡
ተናገሯል፤ ይህም፡ ተጽፎ፡
ሲነበብ፣ ሲተረጐም፣ ከነቢ
ያት፡ እስከ፡ ሐዋርያት፡ ደረሰ፤
ሐዋርያት፡ ለቀሌምንጦስ፡ ሰማ
ንያ፡ አንዱን፡ መጽሐፍ፡ ቈጥ
ረው፡ ሲሰጡት፣ አንድ፡ መጽ
ሐፈ፡ ዳንኤል፡ ብለው፡ ቈጥ
ረው፡ ሰጥተውታል፤ ይኸም፡
ለከንቱ፡ አልተጻፈም፤ እኛ፡ ልን
ገሠጽበት፡ እኛ፡ ልንመከርበት፡
ነው፤

ወኵሉ፡ ዘተጽሕፈ፡ ለተግ
ሣጽ፡ ዚአነ፡ ተጽሕፈ፡ ከመ፡
በትዕግሥትነ፡ ወበተወክሎ፡
መጽሐፍ፡ ንርከብ፡ ተስፋነ፡
እንዲል፡ ሮሜ.፲፭:፬፤

ይህ፡ አርእስት፡ ነው፤ ፫፻፡
ለመጻሕፍት፡ አርእስት፡ ሲሰጡ፣
አርስት፡ ሰጥተውታል፤ እሱ፡
ነገሩን፡ ወሀሎ፡ ፩ ብእሲ፡
ብሎ፡ ያመጣል::



## ምዕራፍ፡ ፩

### ጉባዔ፣

፩፤ አመ፡ ሠላስ፡ ዓመተ፡ መንግ
ሥቱ፡ ለኢዮቄም፡ ንጉሠ፡ ይሁዳ፡ መጽአ፡
ናቡከደነፆር፡ ንጉሠ፡ ባቢሎን፡ ኀበ፡
ኢየሩሳሌም፣

ኤልያቄም፡ ያለው፡ ኢኮንያንን፡
ነው፤ ስም፡ ይወራረሳሉ፤ የይ
ሁዳው፡ ንጉሥ፡ ኢኮንያን፡ በነ
ገሠ፡ በሦስተኛው፡ ወር፡ የባቢ
ሎን፡ ንጉሥ፡ ናቡከደነፆር፡ ወደ፡
ኢየሩሳሌም፡ መጣ፤ ዓመትን፡
ወርን፡ ሲል፡ ነው፤ ወርኀን፡
ዓመት፡ ሲል፡ ዕዝራ፡ ወእምድ
ኅረ፡ ዝንቱ፡ ወርኅ፡ ትሬእያ፡
ለምድር፡ እንዘ፡ ትትሐወክ፡
ብሏል፤ ከዚህም፡ ዓመትን፡
ወርን፡ ሲል፡ ወአመ፡ ሠላስ፡
ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ አለ፣ ይኸ
ውስ፡ ቢሆን፡ በታሪኩ፡ የያዘው፡
የእስራኤልን፡ ነበር፤ ስለምን፡
የሶስናን፡ አስቀደመ፡ ቢሉ፣
ፍትሐ፡ እግዚአብሔር፡ ከተገለ
ጠበት፡ ብሎ፡ ፍትሐ፡ እግዚአብ
ሔርማ፡ በእስራኤልስ፡ ተገልጦ፡
የለም፣ እሱን፡ ትተው፡ ኃጢ
አት፡ ቢሠሩ፣ ጣዖት፡ ቢያመ
ልኩ፡ አይደለም፤ የሚያስማር
ካቸው፡ ቢሉ፡ መጽሐፍ፡ ምሥ
ጢር፡ በጣልቃ፡ እንጀ፡ ተርቶ፡
አይጠነቅቅምና፡ እንዲህ፡ አለ፤
አንድም፣ የእስራኤልን፡ አያይዞ፡
የሚሄድ፡ ነውና፡ ጣልቃ፡ እን
ዳይገባበት፡ የሶስናን፡ ነገር፡ አስ
ቀደመ፤ የእስራኤልን፡ ነገር፡
ወደኋላ፡ አደረገ፤

ወቀተላ፣

እጅ፡ አደረጋት፤

፪፤ ወአግብአ፡ እግዚአብሔር፡ ውስተ፡
እዴሁ፡ ለኢዮአቄም፡ ንጉሠ፡ ይሁዳ፣

የይሁዳውን፡ ንጉሥ፡ ኢኮንያንን፡
እግዚአብሔር፡ በናቡከደነፆር፡
እጅ፡ ጣለው፤

ወንዋየ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ነሥአ፡
ወወሰዶ፡ ብሔረ፡ ሰናኦር፡ ቤተ፡ አምላኩ፣

የቤተ፡ እግዚአብሔሩን፡ ንዋየ፡
ቅድሳት፡ ማርኮ፡ ወደ፡ ቤተ፡
ጣዖቱ፡ አገባው፤ ፈጣሪዬ፡ ነው፡
የሚለው፡ የጣዖቱ፡ ቤት፡ ወደ፡
አለበት፡ ወደ፡ ሰናዖር፡ ወሰደው፤

ወንዋዮሂ፡ አብዓ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ መዝ
ገበ፡ አምላኩ፣

የንጉሡን፡ ገንዘብ፡ ወደ፡ ቤተ፡
ጣዖቱ፡ እቃ፡ ቤት፡ አገባ፣

፫፤ ወይቤሎ፡ ንጉሥ፡ ለአስፋኔዝ፡
ሊቀ፡ ሕፅዋኒሁ፣

የንጉሥ፡ አዛዥ፡ ቢትወደድ፡
የሚሆን፡ አስፋኔዝን፤

ከመ፡ ያምጽእ፡ እምደቂቀ፡ እስራኤል፡
እምአለ፡ ተዔወዉ፣

ከተማረኩ፡ ከእስራኤል፡ ልጆች፡
ያመጣለት፡ ዘንድ፡ እንዲህ፡
አለው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእምዘርዓ፡ መንግሥት፤

የነገሥታት፡ ልጆች፡ የሆኑ፤

፬፤ ቢጸ፡ ወራዙተ፤

ዕደው፡ ወራዙተ፡ ሲል፡ ነው፡ ሕፃናቱን፤ አንድም፡ በሙያ፡ በመልክ፡ የተካከሉ፤

እለ፡ አልቦሙ፡ ነውር፤

ነውር፡ ነቀፋ፡ የሌላቸው፤

ዘላኅይ፡ ገጸሙ፤

መልካቸው፡ ያማረ፡ የሆነ፤

ወየአምሩ፡ ኵሎ፡ ጥበበ፤

ጥበብ፡ የሚስማማቸው፤

ወይሌብዉ፡ ኵሎ፡ ምክረ፤

ምክር፡ የሚያውቁ፤

ወይሔልዩ፡ ጥዩቀ፤

እውነት፡ ነገር፡ የሚያስረዱ፤

እለ፡ ቦሙ፡ ኃይል፡ ይቁሙ፡ ቅድሜሁ፡ ለንጉሥ፤

በንጉሥ፡ ፊት፡ ቢቆሙ፡ የማይ ታክቱ፤ አንድም፡ አእምሮ፡ ያላ ቸውን፡ ምረጥልኝ፡ አለው፤

ወይምሀርዎሙ፡ መጽሐፈ፤

ወግ፡ ታሪክ፡ ያስተምሯቸው፡ ዘንድ፤

ወነገረ፡ ፋርስ፤

ቋንቋ፤ አንድም፡ መጽሐፈ፡ ፍል ስፍና፤ ወነገረ፡ ፋርስ፤ ጥንቆላ፡ ያስተምሯቸው፡ ዘንድ፤

፭፤ ወአዘዘ፡ሎሙ፡ ንጉሥ፡ ሲሳ ዮሙ፡ ኵሎ፡ አሚረ፡ የሀብዎሙ፤ እማ ዕደ፡ ንጉሥ፡ ዘዘዕለቶሙ፤

ዕለት፡ ዕለት፡ ንጉሥ፡ ከሚበ ላው፡ ምግባቸውን፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ይሰጧቸው፡ ዘንድ፡ ንጉሥ፡ አዘዘላቸው፤

ወእምነ፡ ወይን፡ ንጉሥ፡ ዘይሰቲ፤

ንጉሥ፡ ከሚጠጣው፡ ወይን፡ ይሰጧቸው፡ ዘንድ፡ አዘዘ፤

ወይኅርስዎሙ፡ ፫ተ፡ ዓመተ፤

ሦስት፡ ዓመት፡ ይንከባከቧቸው፡ ዘንድ፡ አዘዘ፤ ሐራስን፡ ይዞ፡ ይሕርስዎሙ፡ አለ፤ ሕሙግ፡ መብልዕ፡ የሐምግ፡ ልበ፡ እን ዲል፤ ያልሆነ፡ ምግብ፡ ልቡና፡ ያደነቁራልና፤

ወእምዝ፡ ይቁሙ፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ በንጉሥ፡ ፊት፡ ይቆሙ፡ ዘንድ፤

፮፤ ወሀለዉ፡ ምስሌሆሙ፡ እም ደቂቀ፡ ይሁዳ፡ ዳንኤል፡ ወአናንያ፡ ወአዛ ርያ፡ ወሚሳኤል፤

ከይሁዳ፡ ልጆች፡ የተወለዱ፤ ዳንኤል፤ አናንያ፡ አዛርያ፤ ሚሳ ኤል፡ ከነዚያ፡ ጋራ፡ ነበሩ፤

፯፤ ወወለጠ፡ አስማቲሆሙ፡ ሊቀ፡ ሕፅዋኒሁ፤

የንጉሥ፡ አዛዥ፡ ቢትወደድ፡ የሚሆን፡ አስፋኔዝ፡ ስማቸውን፡



ለወጠ፤ ዛሬ፡ ባርያን፡ ማርከው፡ አምጥተው፡ ስሙን፡ እንዲለ ውጡ፤ ስማቸውንም፡ በአንፃር፡ ያወጣል፤

ወሰዳንኤል፡ ሰመዮ፡ ብልጣሶር፤

ዳንኤል፡ ማለት፡ ፍትሐ፡ እግዚ አብሔር፤ ዳኛ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነበረ፤ ብልጣሶር፡ አለው፤ አስበ፡ ቤል፡ አምኃ፡ ቤል፡ ሲል፤

ወሰአናንያ፡ ሲድራቅ፤

አናንያ፡ ማለት፡ ደመና፡ ማለት፡ ነበር፤ ሲድራቅ፡ አለው፤ ወልደ፡ ሰቃዩ፡ አትክልት፡ ማለት፡ ነው፤

ወሰአዛርያ፡ ሚሳቅ፤

አዛርያ፡ ማለት፡ ረድኤት፡ ማለት፡ ነበር፤ ሚሳቅ፡ አለው፤ ፀሐቂ፤ ተጋሂ፤ ፍንው፡ ለግብረ፡ መል እክት፡ ማለት፡ ነው፤

ወሰሚሳኤል፡ አብደናጎ፤

ሚሳኤል፡ ማለት፡ ሰምዓኒ፡ እግ ዚአብሔር፡ ማለት፡ ነበር፤ አብ ደናጎ፡ አለው፤ ገብረ፡ ዳጎን፡ ማለት፡ ነው፤

፰፤ ወአጥብዓ፡ ዳንኤል፡ በልቡ፡ ከመ፡ ኢይብላዕ፡ እማዕደ፡ ንጉሥ፤

ከንጉሥ፡ ማዕድ፡ እንዳይበላ፡ ዳንኤል፡ ጥሬ፡ እንብላ፡ በማለት፡ በልቡ፡ ጨከነ፤ ስለምን፡ ቢሉ፡ ተጸይፎ፡ ዛሬ፡ እኛ፡ በሃይማኖት፡ የማይመስለንን፡ የእስላሙን፤ ጥሬውን፡ እንዳንጸየፍ፤ ሥጋ ውን፡ እንድንጸየፍ፤ አንድም፡ በተድላ፡ በደስታ፡ ከተማሩት፡ ትምህርት፡ በመከራ፡ የተማሩት፡ ትምህርት፡ ይጠቅማል፡ ብሎ፤ አንድም፡ መከራ፡ ከበዛ፡ ዘንድ፡ ጸጋ፡ ክብር፡ ይበዛልና፤

ወከመ፡ ኢይስተይ፡ እምወይኑ፤

ከወይኑ፡ እንዳይጠጣ፡ ጨከነ፤

ወአስተብቍዖ፡ ዳንኤል፡ ለሊቀ፡ ሕፅ ዋን፡ ከመ፡ ኢያብልዖ፤

ከንጉሥ፡ ማዕድ፡ እንዳያበላው፡ ዳንኤል፡ አዛዡን፡ ማለደው፤

፱፤ ወወሀቦ፡ እግዚአብሔር፡ ሣህለ፡ ወምሕረተ፡ ለዳንኤል፡ በቅድመ፡ ሊቀ፡ ሕፅዋን፤

እግዚአብሔር፡ ለዳንኤል፡ ባለ ሟልነትን፡ ይቅርታን፡ በአዛዡ፡ ፊት፡ ሰጠው፤

፲፤ ወይቤሎ፡ ሊቀ፡ ሕፅዋን፡ ለዳን ኤል፡ እፈርሆ፡ አነ፡ ለእግዚእየ፡ ንጉሥ፤

ሊቀ፡ ሕፅዋን፡ ዳንኤልን፡ እኔ፡ ጌታዬ፡ ንጉሥን፡ እፈራዋለሁ፡ አለው፤

እስመ፡ አዘዘ፡ ሲሳየክሙ፡ ዘትበልዑ፡ ወዘትሰትዩ፤

የምትበሉትን፡ የምትጠጡትን፡ ምግባችሁን፡ አዝዟልና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእመ፡ ርእየክሙ፡ ንጉሥ፡ ድግዱጋኒ
ክሙ፡ እምደቂቀ፡ ዜዋ፡ እለ፡ ቢጽክሙ፤

ተማርከው፡ ከመጡት፡ ከባልን
ጀሮቻችሁ፡ ተለይታችሁ፡ ንጉሥ፡
ከስታችሁ፡ ያያችሁ፡ እንደሆነ፤

እፈርህ፡ ኢይኩንነኒ፡ ንጉሥ፡ ርእስየ፤

ንጉሥ፡ ከላይ፡ አንገቴን፤ ከታች፡
ባቴን፡ ይቀጣኛል፡ ብዬ፡ እፈ
ራለሁ፤

፲፩፤ ወይቤሎ፡ ዳንኤል፡ ለአሜሳድ፡
ዘሤሞ፡ ሊቀ፡ ሕፅዋን፡ ዲበ፡ ዳንኤል፡
ወአናንያ፡ ወአዛርያ፡ ወሚሳኤል፤

ሊቀ፡ ሕፅዋን፡ በዳንኤልና፡ በአ
ናንያ፤ በአዛርያና፡ በሚሳኤል፡
ላይ፡ የሾመው፡ አሜሳድን፡ ዳን
ኤል፡ እንዲህ፡ አለው፤ አስፋ
ኔዝ፡ ተወራጅ፡ ሹም፤ አሜሳ
ድን፡ ሹሞላቸዋል፤

፲፪፤ አመክሮሙ፡ ለአግብርቲከ፡
ዐሡረ፡ ዕለተ፤

እኛን፡ ባሮችህን፡ ዓሥር፡ ቀን፡
ፈትነን፤

ወየሀቡነ፡

ሽምብራ፡ ጥሬ፡ ይስጡን፤ ይህስ፡
ተድላ፡ ደስታ፡ ይሆናል፡ ብሎ፡
እምፍሬ፡ ምድር፡ ይላል፤ ባቄላ፡
ጥሬ፡ ይስጡን፤

ወንብላዕ፡ ወማየ፡ ንስተይ

ጥሬ፡ እንብላ፤ ውሃ፡ እንጠጣ፤

፲፫፤ ወትርአይ፡ ነፍስተነ፡ ወነፍስ
ቶሙ፡ ለደቅ፡ እለ፡ ይሴሰዩ፡ እማዕደ፡
ንጉሥ፤

ከንጉሥ፡ ማዕድ፡ የሚመገቡ፡
ብላቴኖች፡ ሰውነትና፡ የኛን፡
ሰውነት፡ እይ፤

ወዘከመ፡ ርኢከ፡ ግበር፡ ምስለ፡ አግ
ብርቲከ፤

ከዚያ፡ በኋላ፡ ለኛ፡ ለባሮችህ፡
እንዳየህ፡ አድርግልን፤

፲፬፤ ወሰምዖሙ፡ ዘንተ፡ ነገረ፡ ወአ
መከሮሙ፡ ዓሡረ፡ ዕለተ፤

ይህን፡ ነገራቸውን፡ ሰምቶ፡ ዓሥር፡
ቀን፡ ፈተናቸው፤ የነዚያን፡ ድርጎ፡
እሱ፡ እየተቀበለ፡ ለነዚያ፡ ጥሬ፡
እየሰጠ፡ ዓሥር፡ ቀን፡ ተቀመጠ፤

፲፭፤ ወኃሊፎ፡ አሡር፡ ዕለት፡ ኀየ
ሰት፡ ነፍስቶሙ፡ ወሠነየ፡ ራእዮሙ፡
እምእልክቱ፡ ደቅ፡ እለ፡ ይሴሰዩ፡ እማ
ዕደ፡ ንጉሥ፤

ዐሥር፡ ቀን፡ ካለፈ፡ በኋላ፡ የን
ጉሥ፡ ግብር፡ ከሚበሉ፡ ብላቴ
ኖች፡ ይልቅ፡ ሰውነታቸው፡ ጠርቶ፡
መልካቸው፡ አምሮ፡ ታየ፤

፲፮፤ ወእምዝ፡ ይነሥእ፡ አሜሳድ፡
ሲሳዮሙ፡ ዘይበልዑ፡ ወወይነ፡
ዘይሰትዩ፤

ከዚያ፡ በኋላ፡ አሜሳድ፡ የሚበ
ሉትን፡የሚጠጡትን፡እየተቀበለ፤

ወይሁቦሙ፡ ዘርዓ፡ ምድር፡ ለ፬ቱ፡ ደቅ፤

ለአራቱ፡ ብላቴኖች፡ ጥሬ፡ ይሰ
ጣቸው፡ ነበር፤



፲፯፤ ወወሀቦሙ፡ እግዚአብሔር፡
ጥበበ፡ ወአእምሮ፤

እግዚአብሔር፡ ጥበብን፡ ዕው
ቀትን፡ ሰጣቸው፤

ወልቡና፡ በኵሉ፡ መጽሐፍ፤

ኵሎ፡ መጻሕፍተ፡ ሲል፡ ነው፤
መጽሐፉን፡ ሁሉ፡ ማወቅ፡ ሰጣ
ቸው፤ አንድም፡ ለብዎ፡ በኵሉ፡
መጽሐፍ፡ ይላል፤ በመጽሐፍ፡
ያለውን፡ ሁሉ፡ ማወቅ፡ ሰጣቸው፤

ወዳንኤል፡ ኮነ፡ ጠቢበ፡ ለኵሉ፡ ራእይ፡
ወፍካሬ፡ ሕልም፤

ዳንኤል፡ ራእይ፡ በማየት፡ ሕልም፡
በመተርጐም፡ ብልህ፡ አዋቂ፡ ሆነ፤

፲፰፤ ወእምዝ፡ ተፈጸሞ፡ መዋዕል፡
ዘአዘዘ፡ ንጉሥ፤

ወይሕርስዎሙ፡ ሠለስተ፡ ዓመተ፡
ያለው፡ ከተፈጸመ፡ በኋላ፤

አምጽእዎሙ፡ ኀቤሁ፤

ወደሱ፡ አመጧቸው፤

ወአብዖሙ፡ ሊቀ፡ ሕፅዋን፡ ቅድመ፡
ንጉሥ፡ ናቡከደነፆር፤

ሊቀ፡ ሕፅዋን፡ በንጉሡ፡ በናቡ
ከደነፆር፡ ፊት፡ አገባቸው፤ አን
ድም፡ ኀበ፡ ንጉሥ፡ ይላል፤ ንጉሡ፡
ወደአለበት፡ አገባቸው፤

፲፱፤ ወተናገሮሙ፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ ጠየቃቸው፤

ወኢተረክበ፡ በውስተ፡ ኵሉ፡ ከመ፡ ዳን
ኤል፤ ወአናንያ፤ ወአዛርያ፤ ወሚሳኤል፤

በመንግሥቱ፡ ሁሉ፡ እንደ፡ ዳን
ኤል፡ እንደ፡ አናንያ፡ እንደ፡ አዛ
ርያ፡ እንደ፡ ሚሳኤል፡ ያለ፡ ብልህ፡
አልተገኘም፤

ወቆሙ፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፤

በንጉሥ፡ ፊት፡ ቆሙ፤

፳፤ ወኵሎ፡ ነገረ፡ ጥበብ፡ ወም
ክር፡ ዘኃሠሠ፡ ንጉሥ፡ በኀቤሆሙ፤

ንጉሥ፡ ከሳቸው፡ ዘንድ፡ የፈለ
ገውን፡ የጥበብን፡ የምክርን፡
ነገር፡ ሁሉ፤

ረከበ፡ ትዕሥርተ፡ ዕደ፡ እምኵሉ፡ ሰብአ፡
ሥራይ፡ ወሰብአ፡ ሰገል፡ እለ፡ ሀለዉ፡
ውስተ፡ መንግሥቱ፤

በመንግሥቱ፡ ካሉ፡ ከሚጠነ
ቍሉ፤ ሥር፡ ከሚምሱ፡ ቅጠል፡
ከሚበጥሱ፡ ሰዎች፡ ይልቅ፡
ዓሥር፡ ዕጥፍ፡ በልጦ፡ አገኘ፤

፳፩፤ ወነበረ፡ ዳንኤል፡ እስከ፡ አሐቲ፡
ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ለቂሮስ፡ ንጉሥ፤

ዳንኤል፡እስከ፡ቂሮስ፡መንግሥት፡
አንዲት፡ ዓመት፡ ድረስ፡ኖረ።

## ምዕራፍ፡ ፪

፩፤ በካልዕ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፤

አስመጥቶ፡ ከጠየቃቸው፡ በሁ
ለተኛው፡ ዘመን፤

ሐለመ፡ ሕልመ፡ ናቡከደነፆር

ናቡከደነፆር፡ ሕልም፡ አለመ፤

ወደንገፀት፡ ነፍሱ፡ ወረስዓ፡ ሕልሞ፤

ልቡናው፡ ደነገጠች፤ ሕልሙን፡
ዘነጋው፤ ስለምን፡ ቢሉ፡ የማ
ለዳ፡ እንቅልፍ፡ ነበረበትና፤ አን
ድም፡ የዳንኤልን፡ ክብር፡ የሚገ
ልጥ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ አዘንግ
ቶታል፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፤ ወአዘዘ፡ ንጉሥ፡ ይጸውዑ፡ ሰብአ፡ ሥራይ፤

ሥር፡ የሚምሱትን፡ ቅጠል፡ የሚበጥሱትን፤

ወሰብአ፡ ሰገል፤

የሚጠነቁሉትን፡ ሰዎች፤

ወጠቢባነ፤

ብልሆችን፤

ወለባውያነ፤

ልበኞችን፤

ወማዕምራነ፤

አዋቆችን፡ ይጠሩ፡ ዘንድ፡ ንጉሥ፡ አዘዘ፤

ወይንግርዎ፡ ሕልሞ፡ ለንጉሥ፤

ለንጉሥ፡ ሕልሙን፡ ይነግሩት፡ ዘንድ፤

ወመጽኡ፡ ወቆሙ፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፤

መጥተው፡ በንጉሡ፡ ፊት፡ ቆሙ፤

፫፤ ወይቤሎሙ፡ ንጉሥ፡ ሐለምኩ፡ ሕልመ፤

ሕልም፡ አለምሁ፤

ወደንገፀት፡ ነፍስየ፤

ልቡናዬ፡ ደነገጠች፤

ወረሳዕኩ፡ ሕልምየ፤

ሕልሙም፡ ትርጓሜውም፡ ተዘንግቶኛልና፡ ንገሩኝ፤

፬፤ ወተናገርዎ፡ ጠቢባን፡ ለንጉሥ፡ በሱርስት፤

ጠቢባን፡ በሱርስት፡ ቋንቋ፡ ንጉሥን፡ ተናገሩት፤

ወይቤልዎ፡ ንጉሥ፡ ለዓለም፡ ሕየው፤

ንጉሥ፡ ሺህ፡ ዓመት፡ ያንግሥህ፡ አሉት፤

አንተ፡ ንግሮሙ፡ ለአግብርቲከ፡ ሕልመከ፤

አንተ፡ ለኛ፡ ለባሮችህ፡ ሕልምህን፡ ንገረን፤

ወናየድዓከ፡ ፍካሬሁ፤

ትርጓሜውን፡ እንነግርሃለን፤

፭፤ ወተሠጥዎሙ፡ ንጉሥ፡ ወይቤሎሙ፡ ለጠቢባን፡ ተረስአኒ፡ ነገሩ፤

ንጉሥ፡ መለሰላቸው፤ ጠቢባንን፡ ነገሩ፡ ተዘንግቶኛል፡ አላቸው፤

ወእምከመ፡ ኢታየድዑኒ፡ ሕልምየ፤

ሕልሜን፡ ባትነግሩኝ፤

ወኢትፈክሩ፡ ሊተ፡ ትመውቱ፤

ባትተረጕሙልኝ፡ ትሞታላችሁ፤

ወትትበረበሩ፡ ንዋየክሙ፤

ገንዘባችሁ፡ ይበዘበዛል፤

፮፤ ወእመሰ፡ አይዳዕክሙኒ፡ ሕልምየ፤

ሕልሜን፡ ግን፡ ብትነግሩኝ፤

ወፈከርክሙ፡ ሊተሂ፤

ብትተረጕሙልኝ፤

ትነሥኡ፡ ፍተክሙ፤፡

ድርጎ፡ እዳርጋችኋለሁ፤

ወዓስበክሙ፤

ደመወዛችሁን፡ እሰጣችኋለሁ፤

ወብዙኃ፡ አከብረክሙ፤

ፈጽሜ፡ አከብራችኋለሁ፤



ወዳዕሙ፡ ንግሩኒ፡ ሕልምየ፡ ወፈክሩ፡ ሊተ፤

ሕልሜን፡ ንገሩኝ፡ ተርጕሙልኝ፡ እንጂ፤

፯፤ ወአውሥእዎ፡ ዳግመ፡ ወይቤልዎ፡ ንጉሥ፡ ይንግሮሙ፡ ለአግብርቲሁ፡ ሕልሞ፤

መለሱለት፡ ዳግመኛ፡ እንዲህ፡ አሉት፤ ንጉሥ፡ ሕልምህን፡ ለኛ፡ ለባሮችህ፡ ንገረን፤

ወፍካሬሁሰ፡ ንሕነ፡ ንነግሮ፤

ትርጓሜውን፡ ግን፡ እኛ፡ እንነግርሃለን፤

፰፤ ወተሰጥዎሙ፡ ንጉሥ፡ ወይቤሎሙ፤

ንጉሥ፡ መለሰ፤ እንዲህ፡ አላቸው፤

አማን፡ አእመርኩ፡ አነ፡ ከመ፡ ታስተሐፍሩኒ፡ እስመ፡ ተረስዓኒ፡ ነገሩ፤

ነገሩ፡ ተዘንግቶኛልና፡ እንድታሳፍሩኝ፡ እኔ፡ በእውነቱ፡ አወቅሁ፤

፱፤ ወእምከመ፡ ይእዜ፡ ኢትነግሩኒ፡ ሕልምየ፤

ባይሆንም፡ ቀን፡ ስጠን፡ ብለውታል፤ ዛሬስ፡ ሕልሜን፡ ካልነገራችሁኝ፤

አእመርኩ፡ አነ፡ ከመ፡ ተሐሥሡ፡ ሊተ፡ ዘትፈጥሩ፡ ነገረ፡ ሐሰት፡ ቅድሜየ፤

በፊቴ፡ ልብ፡ ወለድ፡ ነገር፡ እንድትነግሩኝ፡ አወቅሁ፤

ወአይድዑኒ፡ ሕልምየ፡ ዘእንበለ፡ ይኅልፍ፡ ጊዜሁ፤

ጊዜው፡ ሳያልፍ፡ ትዝ፡ ትዝ፡ ሲለኝ፡ ሕልሜን፡ ንገሩኝ፤

ወአአምር፡ ከመ፡ ፍካሬሁኒ፡ ትነግሩኒ፤

ሕልሙን፡ ብትነግሩኝ፡ ትርጓሜውንም፡ እንድትነግሩኝ፡ አውቃለሁ፤

፲፤ ወአውሥኡ፡ ካዕበ፡ ጠቢባን፡ በቅድመ፡ ንጉሥ፤

ጠቢባን፡ ዳግመኛ፡ በንጉሥ፡ ፊት፡ ተናገሩ፤

ወይቤሉ፡ አልቦ፡ ሰብእ፡ በዲበ፡ ምድር፡ ዘይክል፡ አእምሮ፡ ነገሩ፡ ለንጉሥ፤

ንጉሥ፡ የተናገርከውን፡ ነገር፡ ማወቅ፡ የሚቻለው፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ሰው፡ የለም፤

ወአልቦ፡ ንጉሥ፡ ዓቢይ፡ ወመልአክ፡ ዘይሴአል፡ ዘከመዝ፡ ነገር፤

እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ የሚጠይቅ፡ ገናና፡ ንጉሥ፡ አለቃ፡ የለም፤

በኀበ፡ ጠቢባን፡ ወሰብአ፡ ሰገል፤

በጠቢባን፡ ዘንድ፡ በጠንቋዮችም፡ ዘንድ፤

ወሰብአ፡ ሥራይ፤

ሥር፡ በሚምሱ፤ ቅጠል፡ በሚበጥሱ፡ ሰዎች፡ ዘንድ፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ የሚጠይቅ፡ የለም፤

፲፩፤ እስመ፡ ዕፁብ፡ ዝነገር፡ ዘይሴአል፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ የሚጠይቀው፡ ይህ፡ ነገር፡ ጭንቅ፡ ነውና፤

ወአልቦ፡ ባዕድ፡ ዘይነግሮ፡ ለንጉሥ፡ ሕልሞ፤

ሕልሙን፡ ለንጉሥ፡ የሚነግረው፡ ሌላ፡ የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

ዘእንበለ፡ አማልክት፡ እለ፡ ኢኮነ፡ ንብረቶሙ፡ ምስለ፡ ኵሉ፡ ዘሥጋ፤

አነዋወራቸው፡ ከሥጋዊ፡ ከደማዊ፡ ጋራ፡ ካልሆነ፡ ከሥላሴ፡ በቀር፤ አንድም፡ ከመላእክት፡ በቀር፤ አንድም፡ አነዋወራቸው፡ ከሥጋዊ፡ ከደማዊ፡ ጋራ፡ ካል ሆነ፡ ከሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ በቀር፤

፲፪፤ ወሶቤሃ፡ ንጉሥ፡ ተምዓ፡ ዓቢየ፡ መዓተ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ንጉሥ፡ ፈጽሞ፡ ተቆጣ፤ ትርጓሜው፡ እንደ፡ ታሪኩ፡ ነው፤

ወይቤ፡ ቅትልዎሙ፡ ለኵሎሙ፡ ጠቢባነ፡ ባቢሎን፤

ጠቢባነ፡ ባቢሎንን፡ ሁሉ፡ ግደ ሏቸው፡ አለ፤

፲፫፤ ወጽአ፡ ትእዛዝ፡ እምነበ፡ ንጉሥ፤

ከንጉሥ፡ ዘንድ፡ ትእዛዝ፡ ታዘዘ፤

ወአኀዙ፡ ይቅትልዎሙ፤

ያጠፏቸው፡ ጀመር፤

ወኃሠሥዎሙ፡ ለዳንኤል፡ ወለአዕርክቲሁ፡ ይቅትልዎሙ፤

ዳንኤልን፡ ባልንጀሮቹን፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅን፡ ይገድሏቸው፡ ዘንድ፡ ፈለጓቸው፤

፲፬፤ ወተናገሮ፡ ዳንኤል፡ ለአርዮክ፡ ሊቀ፡ መበስላኒሁ፡ ለንጉሥ፤

የንጉሥ፡ አዛዥ፡ አለቃ፡ የሚ ሆን፡ አርዮክን፡ ዳንኤል፡ ተና ገረው፤

ዘወጽአ፡ ይቅትሎሙ፡ ለጠቢባነ፡ ባቢሎን፤

ጠቢባነ፡ ባቢሎንን፡ ይገድላቸው፡ ዘንድ፡ የወጣ፤

፲፭፤ ወተስእሎ፡ ወይቤሎ፡ ለአርዮክ፡ መልአከ፡ ንጉሥ

የንጉሥ፡ አለቃ፡ አርዮክን፡ ጠየ ቀው፤ እንዲህ፡ አለው፤

በእንተ፡ ምንት፡ ወጽአ፡ ትእዛዝ፡ ዕፁብ፡ እምነበ፡ ንጉሥ፤

ከንጉሥ፡ ዘንድ፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ጭንቅ፡ ትእዛዝ፡ ስለምን፡ ታዘዘ? አለው፤

ወነገሮ፡ አርዮክ፡ ለዳንኤል፤

አርዮክም፡ ንጉሥ፡ ሕልም፡ አይቶ፡ ሕልሙንም፡ ትርጓሜ ውንም፡ የሚነግረው፡ አጥቶ፡ ነው፡ ብሎ፡ ለዳንኤል፡ ነገረው፤

፲፮፤ ወቦአ፡ ዳንኤል፡ ወአስተብቍዖ፡ ከመ፡ የዐድሞ፡ እስከ፡ ሠሉስ፡ ዕለት፤

እስከ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ድረስ፡ ቀን፡ ይሰጠው፡ ዘንድ፡ ዳንኤል፡ ገብቶ፡ ማለደው፤

ወይንግሮ፡ ሕልሞ፡ ለንጉሥ፡ ወይፌክር፡ ሎቱ፤

የንጉሥን፡ ሕልሙን፡ ተርጕሞ፡ ይነግረው፡ ዘንድ፡ ለነዚያ፡ የነሳ ውን፡ ለእሱ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ሰጠው፤



፲፯፤ ወቦአ፡ ዳንኤል፡ ቤቶ፡ ወነገሮሙ፡ ለአእርክቲሁ፡ አናንያ፡ ወአዛርያ፡ ወሚሳኤል፡ ዘ፡ ነገረ፤

ዳንኤል፡ ወደቤቱ፡ ገብቶ፡ ለባል ንጀሮቹ፡ ለአናንያ፤ ለአዛርያ፤ ለሚሳኤል፡ ይህን፡ ነገር፡ ነገራ ቸው፤ ሠለስቱ፡ ደቂቅን፡ ይዞ፡ ሱባዔ፡ ገባ፤

፲፰፤ ወሰአሉ፡ ሣህለ፡ እምነበ፡ አምላከ፡ ሰማይ፡ በእንተ፡ ዘኀቡዕ፤

የተሠወረውን፡ ነገር፡ ይገልጥላ ቸው፡ ዘንድ፡ ሰማይን፡ ከፈጠረ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ይቅ ርታን፡ ለመኑ፤

ከመ፡ ኢይመውቱ፡ ዳንኤል፡ ወአእርክቲሁ፡ ምስለ፡ ኵሎሙ፡ ጠቢባነ፡ ባቢሎን፤

ዳንኤልና፡ ባልንጀሮቹ፡ ከጠቢ ባነ፡ ባቢሎን፡ ጋራ፡ እንዳይሞቱ፤

፲፱፤ ወእምዝ፡ ተከሥተ፡ ሎቱ፡ ለዳንኤል፡ በራዕየ፡ ሌሊት፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ ለዳንኤል፡ ዕለ ቱን፡ ተገለጠለት፤ ስለምን፡ ቢሉ፡ ጥሬ፡ እንኩዋ፡ በማለት፡ ጨክኖ፡ ነበርና፡ ስለ፡ ተገለጠለት፡ ግን፡ ዕለቱን፡ አልወጣም፤ ሱባዔ፡ ለማስከበር፡ ነው፤ ለሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ በሦስተኛው፡ ቀን፡ ተገል ጦላቸዋል፤

ወአእኰቶ፡ ዳንኤል፡ ለአምላከ፡ ሰማይ፤

ሰማይን፡ የፈጠረ፡ እግዚአብሔ ርን፡ ዳንኤል፡ አመሰገነው፤

፳፤ ወይቤ፡ ይትባረክ፡ ስመ፡ እግዚአብሔር፡ ለዓለም፡ ወእስከ፡ ለዓለም፤

የእግዚአብሔር፡ ስም፡ ለዘለዓ ለሙ፡ ይክበር፡ ይመስገን፡ አለ፤

እስመ፡ ሎቱ፡ ውእቱ፡ ጥበብ፡ ወምክር፡ ወኃይል፤

ጥበብ፡ ምክር፡ ኃይል፡ የሱ፡ ገንዘብ፡ ነውና፤

፳፩፡ ወውእቱ፡ ይዌልጥ፡ ዓመታተ፤

በጋውን፡ በክረምት፤ ክረምቱን፡ በበጋ፤ ዄዋዌን፡ በሚጠት፡ የሚለ ውጥ፡ እሱ፡ ነው፤ አንድም፡ ማቴ ዎስን፡ በማርቆስ፤ ማርቆስን፤ በሉቃስ፤ የሚለውጥ፡ እሱ፡ ነው፤ አንድም፡ ዓመተ፡ ደዌን፡ በዓ መተ፡ ጥኢና፤ ዓመተ፡ ጥኢናን፡ በዓመተ፡ ደዌ፡ የሚለውጥ፡ እሱ፡ ነው፤

ወመዋዕለ፡

ሌሊቱን፡ በመዓልት፤ መዓል ቱን፡ በሌሊት፡ የሚለውጥ፡ እሱ፡ ነው፤ አንድም፡ ሰኞን፡ በማክ ሰኞ፤ ማክሰኞን፡ በረቡዕ፡ የሚለ ውጥ፡ እሱ፡ ነው፤ አንድም፡ መዋ ዕለ፡ ሐዘንን፡ በመዋዕለ፡ ፍሥሐ፤ መዋዕለ፡ ፍሥሐን፡ በመዋዕለ፡ ሐዘን፡ የሚለውጥ፡ እሱ፡ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወያነብር፡ ነገሥተ፤

እንደ፡ ሕዝቅያስ፡ ያሉ፡ ነገሥታትን፡ በዙፋን፡ የሚያስቀምጥ፡ እሱ፡ ነው፤

ወይስእር፤

እንደ፡ ሰናክሬም፡ ያሉትን፡ የሚሽር፡ እሱ፡ ነው፤

ወይሁቦሙ፡ ጥበበ፡ ለጠቢባን፤

ለጠቢባን፡ ዕውቀትን፡ የሚገልጥላቸው፡ እሱ፡ ነው፤

ወምክረ፡ ለመካርያን፤

ለመካርያን፡ ምክርን፡ የሚገልጥላቸው፡ እሱ፡ ነው፤

፳፪፤ ወውእቱ፡ ይከሥት፡ ዘዕሙቅ፤

ንባቡን፡ የሚገልጥላቸው፡ እሱ፡ ነው፤

ወኅቡዕ፤

ትርጓሜውን፡ የሚገልጥላቸው፡ እሱ፡ ነው፤

ወየአምር፡ ኵሎ፡ ዘውስተ፡ ጽልመት፤

የተሠወረውን፡ የሚያውቅ፡ እሱ፡ ነው፤

ወኀቤሁ፡ ሀሎ፡ ብርሃን፤

ዕውቀት፡ ከሱ፡ ይገኛል፤

፳፫፤ አንተ፡ አምላክ፡ አበዊነ፡ እገኒ፡ ለከ፡ ወእሴብሐከ፤

የዮሴፍን፡ ሕልም፡ ለያዕቆብ፤ የፈርዖንን፡ ሕልም፡ ለዮሴፍ፡ የገለጥህ፡ የአባቶቻችን፡ ፈጣሪ፡ አንተ፡ ነህ፤ እገዛልሃለሁ፤ አመሰግንሃለሁ፤

እስመ፡ ወሀብከኒ፡ ጥበበ፡ ወአእምሮ፤

ጥበብን፤ ዕውቀትን፡ ገልጠህልኛልና፤

ወነገርከኒ፡ ዘአስተብቋዕኩከ፤

የለመንሁህን፡ ነግረኸኛልና፤

ወአይዳዕከኒ፡ ሕልሞ፡ ለንጉሥ፡ ወፍካሬሁ፤

የንጉሥ፡ ሕልሙን፡ ትርጓሜውን፡ ነግረኸኛልና፡ አመሰግንሃለሁ፤

፳፬፤ ወሖረ፡ ዳንኤል፡ ኀበ፡ አርዮክ፡ ዘአዘዞ፡ ንጉሥ፡ ከመ፡ ይቅትሎሙ፡ ለጠቢባን፡ ባቢሎን፤

ዳንኤል፡ ጠቢባን፡ ባቢሎንን፡ ያጠፋቸው፡ ዘንድ፡ ንጉሥ፡ ወደ አዘዘው፡ ወደአርዮክ፡ ሄደ፤

ወይቤሎ፡ ዳንኤል፡ ኢትቅትሎሙ፡ ለጠቢባን፡ ባቢሎን፤

ዳንኤል፡ የባቢሎንን፡ አዋቆች፡ አትግደላቸው፡ አለው፤

አብዓኒ፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፤

ኀበ፡ ንጉሥ፡ ሲል፡ ነው፤ ወደ፡ ንጉሥ፡ አስገባኝ፤

ወአነ፡ እነግሮ፡ ለንጉሥ፡ ፍካሬሁ፡ ወሕልሞ፤

እኔ፡ ሕልሙንም፡ ትርጓሜውንም፡ ለንጉሥ፡ እነግረዋለሁ፤



፳፭፤ ወሶቤሃ፡ ፍጡነ፡ አብኦ፡ ለዳንኤል፡ አርዮክ፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፤

ያን፡ ጊዜ፡ አርዮክ፡ ዳንኤልን፡ ወደ፡ ንጉሥ፡ ፈጥኖ፡ አስገባው፤

ወይቤ፡ ረከብኩ፡ ብእሴ፡ እምደቂቀ፡ ዔዋ፡ ይሁዳ፡ ዘይነግሮ፡ ለንጉሥ፡ ሕልሞ፡ ወፍካሬሁ፤

ለንጉሥ፡ ሕልሙንም፡ ትርጓሜውንም፡ የሚነግረው፡ ከይሁዳ፡ ከተማረኩ፡ ልጆች፡ ወገን፡ ሰው፡ አገኘሁ፡ አለ፤

፳፮፤ ወተሠጥዎ፡ ንጉሥ፡ ወይቤሎ፡ ለዳንኤል፡ ዘስሙ፡ ብልጣሶር፤

ንጉሥ፡ መለሰ፤ ስሙ፡ ብልጣሶር፡ የሚባል፡ ዳንኤልን፡ እንዲህ፡ አለው፤

ትክልኑ፡ ትንግረኒ፡ ሕልምየ፡ ዘርኢኩ፡ ወፍካሬሁኒ፤

ያየሁትን፡ ሕልሜን፡ ትርጓሜውንም፡ ትነግረኝ፡ ዘንድ፡ ትችላለህ?

፳፯፤ ወአውሥአ፡ ዳንኤል፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፤

ዳንኤል፡ በንጉሥ፡ ፊት፡ መለሰ፤

ወይቤ፡ ዝ፡ ነገር፡ ዘይሴአል፡ ንጉሥ፤

ይህ፡ ንጉሥ፡ የሚጠይቀው፡ ነገር፤

ኢኮነ፡ ለጠቢባን፤

ጠቢባን፡ ነን፡ ለሚሉ፤

ወኢለማዕምራን፤

አዋቆች፡ ነን፡ ለሚሉ፡ አይደለም፤

ወኢለሰብአ፡ ሰገል፤

ለሚጠነቁሉ፡ሰዎች፡አይደለም፤

ወኢለሰብአ፡ ሥራይ፡ ኢይክሉ፡ ይንግሩ፡ ነገሮ፡ ለንጉሥ፤

ሥር፡ የሚምሱ፡ ቅጠል፡ የሚበጥሱ፡ የንጉሥን፡ ነገር፡ መናገር፡ የሚችሉ፡ አይደለም፤

፳፰፤ ዳዕሙ፡ ሀሎ፡ አምላክ፡ ውስተ፡ ሰማይ፡ ዘይከሥት፡ ዘኅቡዕ፤

የተሠወረውን፡ የሚገልጥ፡ ፈጣሪ፡ በሰማይ፡ አለ፡ እንጂ፤

ወውእቱ፡ አርአዮ፡ ለንጉሥ፡ ናቡከደነፆር፡ ዘሀሎ፡ ይኩን፡ በደኃሪ፡ መዋዕል፤

በኋላ፡ ዘመን፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ ያለውን፡ ለንጉሥ፡ ለአንተ፡ ገልጦልሃል፤

ከመዝ፡ ውእቱ፡ ሕልምከ፡ ዘርኢከ፤

ያየኸው፡ ሕልምህ፡ እንዲህ፡ ነው፤

ወራእየ፡ ርእስከ፡ በውስተ፡ ምስካብከ፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ ተኝተህ፡ ሳለ፡ ራስህ፡ ሕልም፡ ሲያይ፡ አየህ፤ አንድም፡ ራስህ፡ ሕልም፡ ሲያይ፡ አየህ፤ አንድም፡ ዘውስተ፡ ነፍስከ፡ ይላል፡ የራስህን፡ ጥፋት፡ አየህ፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፱፤ እስመ፡ ሐለይከ፡ ምንተ፡ ይከውን፡ እምድኅሬከ፤

ከአንተ፡ በኋላ፡ የሚሆነውን፡ አስበሃልና፤

ወዘይከሥት፡ ኅቡዓ፡ አርአየከ፡ ዘሀሎ፡ ይኩን፤

የተሠወረውን፡ የሚገልጥ፡ አምላክ፡ በኋላ፡ ዘመን፡ የሚሆነውን፡ ገልጦልሃል፤ ከዕለታት፡ አንድ፡ ቀን፡ በሰገነት፡ ተቀምጠህ፡ ሳለ፡ የሴት፡ ወይዘሮ፤ የወንድ፡ መኰንን፡ ሲወጣ፡ ሲገባ፡ ሲታጠቅ፡ ሲፈታ፡ አይተህ፡ እኔ፡ ይህን፡ ዓለም፡ እንደ፡ ገል፡ ቀጥቅጬ፡ እንደ፡ ሰም፡ አቅልጬ፡ ገዛሁት፤ ከኔ፡ በኋላ፡ የሚነሣው፡ ንጉሥ፡ ከኔ፡ የሚያንስ፡ ይሆን? ወይስ፡ ከኔ፡ የሚበልጥ፡ ብለህ፡ አስበሃልና፤

፴፤ ወአነሂ፡ አኮ፡ በጥበብየ፡ እምኵሉ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ዘተከሥተ፡ ሊተ፡ ዘኅቡዕ፤

እኔም፡ ከሰው፡ ሁሉ፡ ይልቅ፡ የተሠወረው፡ ምሥጢር፡ በጥበቤ፡ የተገለጠልኝ፡ አይደለም፤

ዳዕሙ፡ ከመ፡ እንግር፡ ለንጉሥ፡ ፍካሬሁ፡ ከመ፡ ታእምር፡ ዘሐለይከ፡ በልብከ፤

በልብህ፡ ያሰብኸውን፡ ታውቅ፡ ዘንድ፡ ትርጓሜውን፡ ለአንተ፡ ለንጉሥ፡ እነግርህ፡ ዘንድ፡ ነው፡ እንጂ፤

፴፩፤ አንተ፡ ንጉሥ፡ ርኢከ፤

ንጉሥ፡ አንተ፡ አየህ፤

ወናሁ፡ ምስል፡ ፩ዱ፡ ዓቢይ፤

አንድ፡ ታላቅ፡ ምስል፡ ቁሞ፡ አየህ፤

ወገጹ፡ ይኔጽር፡ ቅድሜከ፤

ፊቱ፡ ወደአንተ፡ ሲመለከት፡ አየኸው፤ እኔ፡ አንተ፡ ነህ፤ አንተ፡ እኔ፡ ነኝ፡ ሲል፤

ወግሩም፡ ራዕዩ፡ ለውእቱ፡ ምስል፤

የምስሉም፡ መልኩ፡ ልዩ፡ ነው፤

፴፪፤ ርእሱ፡ ዘወርቅ፡ ጽሩይ፤

ራሱ፡ የጠራ፡ ወርቅ፡ ነው፡ ማለት፡ ርእሱ፡ ዘወርቅ፡ የተባልህ፡ አንተ፡ ነህ፤ ወርቅ፡ መክብበ፡ ንዋያት፡ ነው፤ አንተም፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ነህና፤

እደዊሁ፡ ወእንግድዓሁ፡ ወመዝራዕቱ፡ ዘብሩር፤

እጁ፤ ደረቱ፤ ክንዱ፡ የብር፡ ነው፤ የተባለ፡ ዳርዮስ፡ ነው፤ ከወርቅ፡ ብር፡ ያንሳል፤ እሱም፡



በመንግሥት፡ ከአንተ፡ ያንሳልና፤

ከርሡ፡ ወሐቌሁ፡ ዘብርት፤

ሆዱ፡ ወገቡ፡ የብርት፡ ነው፡ የተባለ፡ ቂሮስ፡ ነው፤ የብርት፡ ድምፁ፡ ከሩቅ፡ ይሰማል፤ የሱም፡ ዜና፡ መንግሥቱ፡ ከሩቅ፡ ይሰማልና፤

፴፫፤ አቍያጺሁ፡ ዘሐፂን፤

ጭኖቹ፡ የብረት፡ ናቸው፡ የተባለ፡ እስክንድር፡ ነው፤ ብረት፡ ጽኑዕ፡ ነው፤ እሱም፡ ጽኑ፡ ንጉሥ፡ ነውና፤

ወእምኔሁ፡ መንፈቀ፡ እገሪሁ፡ ዘሐፂን፡ ወመንፈቀ፡ እገሪሁ፡ ልሕኩት፤

ከዚህም፡ እኩሌታ፡ እግሩ፡ የብረት፡ ነው፤ እኩሌታ፡ እግሩ፡ የሸክላ፡ ነው፤ አቈልቍሎ፡ አቈልቍሎ፡ ነው፡ ቢሉ፡ እንደ፡ አፍራሪቆን፡ ድንኳን፡ ሁኖ፡ አይቶታል፤ አግድሞ፡ አግድሞ፡ ነው፡ ቢሉ፡ እንደ፡ ነፍጥ፡ መሸቢያ፤ እንደ፡ በርኖስ፡ አዝራር፤ እንደ፡ አልጋ፡ ዙፋን፡ ሁኖ፡ አይቶታል፤ በብረት፡ የተመሰሉ፡ በጥሊሞስ፡ አንጥያኮስ፡ ናቸው፤ በሸክላ፡ የተመሰሉ፡ ሰልፎስ፡ ደማጥርያኖስ፡ ናቸው፤

፴፬፤ ወእንዘ፡ ትኔጽር፡ ተበትከ፡ ዕብን፡ ዓቢይ፡ እምደብር፡ ዘእንበለ፡ እድ፤

ተመትረም፡ ይላል፤ ይኸን፡ ስትመለከት፡ ከረጅም፡ ተራራ፡ እጅ፡ ሳይነካው፡ ታላቅ፡ ደንጊያ፡ ተፈንቅሎ፤

ወወረደ፡ ዲበ፡ እገሪሁ፡ ዘሐፂን፡ ወዘልሕኩት፤

የብረትና፡ የሸክላ፡ ከሚሆን፡ ከእግሩ፡ ላይ፡ ወደቀ፤

ወሐረፆ፡ ለዝሉፉ፤

ፈጽሞ፡ አደቀቀው፤

፴፭፤ ወእምዝ፡ ተሐርፀ፡ በምዕር፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ በአንድ፡ ጊዜ፡ ደቀቀ፤

ልሕኩቱሂ፤

በፊት፡ ሸክላው፤

ወሐፂኑሂ፤

ቀጥሎ፡ ብረቱ፤

ወብርቱሂ፤

ቀጥሎ፡ ብርቱ፤

ወብሩሩሂ፤

ቀጥሎ፡ ብሩ፤

ወወርቁሂ፤

ቀጥሎ፡ ወርቁ፡ ደቀቀ፤

ወኮነ፡ ከመ፡ ፀበለ፡ ዓውድ፡ ዘማዕረር፡ ዘይነሥእ፡ ነፋስ፡ ኵሎ፤

ነፋስ፡ እንደሚበትነው፡ በመከር፡ አውድማ፡ እንዳለ፡ ትቢያ፡ ሆነ፤ አንድም፡ ነፋስ፡ አጠፋው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወኢተዓውቀ፡ መካኑ፤

ቦታው፡ አልታወቀም፤ አንድም፡ ቦታው፡ እንዳልታወቀ፡ ሆነ፤

ወዝኩ፡ ዕብን፡ ዘቀጥቀጦ፡ ለምስል፡ ኮነ፡ ደብረ፡ ዓቢየ፡ ወመልዓ፡ ኵሎ፡ ምድረ፤

ምስሉን፡ የቀጠቀጠው፡ ያ፡ ደንጊያ፡ ተራራ፡ አህሎ፡ ምድሩን፡ ሲመላ፡ አየኸው፤

፴፮፤ ዝውእቱ፡ ሕልምከ፤

ሕልምህ፡ ይህ፡ ነው፤

ወፍካሬሁኒ፡ እነግር፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፤

ትርጓሜውንም፡ በንጉሥ፡ ፊት፡ እናገራለሁ፤

፴፯፤ አንተ፡ ንጉሥ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘወሀበከ፡ አምላከ፡ ሰማይ፡ መንግሥተ፡ ጽኑዓ፤

ሰማይን፡ የፈጠረ፡ አምላክ፡ ጽኑዕ፡ መንግሥትን፡ የሰጠህ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ የምትሆን፡ ንጉሥ፡ አንተ፡ ነህ፤

ወኃይለ፡ ወክብረ፡ በኵሉ፡ ምድር፤

ኃይልን፤ ክብርን፡ በዓለሙ፡ ሁሉ፡ የሰጠህ፤

፴፰፤ ወበኵሉ፡ በሐውርት፡ ኀበ፡ ይነብሩ፡ ደቂቀ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፤

የሰው፡ ሁሉ፡ ልጆች፡ በሚኖሩበት፡ አገር፡ የሰጠህ፤

ወአርዌ፡ ገዳም፡ ወአዕዋፈ፡ ሰማይ፡ ወዓሣተ፡ ባሕር፡ ወሀበከ፡ ውስተ፡ እዴከ፤

አራዊት፤ አዕዋፍ፤ ዓሣተ፡ ባሕር፡ የሚኖሩበትን፡ በእጅህ፡ የሰጠህ፤

ወሤመከ፡ እግዚአ፡ ለኵሉ፤

ለሁሉ፡ ጌታ፡ አድርጎ፡ የሾመህ፤

አንተ፡ ውእቱ፡ ርእሱ፡ ዘወርቅ፤

ርእሱ፡ ዘወርቅ፡ የተባልህ፡ አንተ፡ ነህ፤

፴፱፤ ወእምድኅሬከ፡ ይቀውም፡ ካልዕ፡ ንጉሥ፡ ዘይቴሐት፡ እምኔከ፤

ከአንተ፡ በኋላ፡ ሁለተኛ፡ ሌላ፡ ንጉሥ፡ ይነግሣል፡ ያለው፡ ከአንተ፡ የሚያንስ፡ ዳርዮስ፡ ነው፤

ወውእቱ፡ ዝኩ፡ ዘብሩር፤

እንግድዓሁ፡ ዘብሩር፡ የተባለ፡ ይህ፡ ነው፤

ወዝኩሰ፡ ዘብርት፤

ሐቌሁ፡ ዘብርት፡ የተባለ፤

ሣልስ፡ መንግሥት፡ ዘይኴንን፡ ኵሎ፡ ምድረ፤

ዓለሙን፡ ሁሉ፡ የሚገዛ፡ ሦስተኛ፡ መንግሥት፡ ቂሮስ፡ ነው፤

፵፤ ወራብዕ፡ መንግሥት፡ ጽኑዕ፡ ውእቱ፡ ከመ፡ ሐፂን፤

አራተኛው፡ መንግሥት፡ እንደ፡ ብረት፡ ጽኑዕ፡ የሚሆን፡ እስክንድር፡ ነው፤



ወበከመ፡ ሐፂን፡ ያደክሞ፡ ለኵሉ፡ ወያደቅቆ፡ ከማሁ፡ ይመውዖ፡ ለኵሉ፡ ወያገርሮ፤

ብረት፡ ሁሉን፡ እንዲያደክም፡ እንዲያደቅ፡ እስክንድር፡ ሁሉን፡ ድል፡ ይነሳል፤ ይገዛል፤

፵፩፤ ወገቢኒ፡ ዘርኢከ፡ እገሪሁ፡ ወአፃብዒሁ፡ መንፈቁ፡ ልሕኵት፡ ወመንፈቁ፡ ሐፂን፤

እግሩ፤ ጣቱ፡ እኩሉ፡ ሸክላ፤ እኩሉ፡ ብረት፡ ሁኖ፡ ያየኸው፤

እስመ፡ መንግሥቱ፡ ንፉቅ፡ ውእቱ፤

መንግሥቱ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ ነውና፤

ወእምጕንዱ፡ ለሐፂን፡ ውስቴቱ፡ በከመ፡ ርኢከ፡ ሐፂን፡ ኢድሙር፡ ምስለ፡ ልሕኵት፤

ከጉልበቱ፡ በታች፡ በባቱ፡ ስፍራ፡ እኩሌታው፡ ሸክላ፡ እኩሌታው፡ ብረት፡ ሆኖ፡ ያየኸው፡ እንደ፡ ውሀና፡ እንደ፡ ወተት፡ ተቀላቅለው፡ ሳሉ፡ ሳይቀላቀሉ፡ ያየሃቸው፤

፵፪፤ ወአፃብዓ፡ እገሪሁኒ፡ መንፈቁ፡ ሐፂን፡ ወመንፈቁ፡ ልሕኵት፤

አፃብዓ፡ እገሪሁኒ፡ ለማለት፡ ደግሞታል፤ የእግሩም፡ ጣት፡ እኩሌታው፡ የሸክላ፤ እኩሌታው፡ የብረት፡ ሁኖ፡ ያየኸው፤

መንፈቀ፡ መንግሥቱ፡ ጽኑዕ፤

የመንግሥቱ፡ እኩሌታ፡ ጽኑዕ፡ ነው፡ ማለት፡ አንጥያኮስ፡ በጥሊሞስ፡ ጽኑዓን፡ ናቸው፤

ወመንፈቀ፡ መንግሥቱ፡ ይትቀጠቀጥ፤

የመንግሥቱ፡ እኩሌታ፡ ደካማ፡ ነው፡ ማለት፡ ሰልፎስ፡ ደማጥርያኖስ፡ ድኩማን፡ ናቸው፤

፵፫፤ ወዝኒ፡ ዘርኢከ፡ ሐፂን፡ ወልሕኵት፡ እንዘ፡ ኢድሙር፡ ከማሁ፡ ሕውሳን፡ እሙንቱ፡ ለዘርዓ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ወኢኮኑ፡ ድሙራነ፡ ዝንቱ፡ ምስለ፡ ዝኩ፡ በከመ፡ ርኢከ፡ ኢይደመር፡ ሐፂን፡ ምስለ፡ ልሕኵት፤

ተቀላቅለው፡ ሳሉ፡ ሳይቀላቀሉ፡ ያየኻቸው፡ የአዳም፡ ልጆች፡ በመሆን፡ ተቀላቅለው፡ ሳሉ፡ ያልተቀላቀሉ፡ ናቸው፤ ቀይና፡ ጥቁር፤ ረጅምና፡ አጭር፤ ክፉና፡ መልካም፡ ናቸው፤ አንድም፡ የእስክንድር፡ ልጆች፡ በመሆን፡ ሳይቀላቀሉ፡ መንግሥቱን፡ በመውረስ፡ የተቀላቀሉ፡ ናቸው፤

፵፬፤ ወበመዋዕሊሆሙ፡ ለእሙንቱ፡ ነገሥት፡ ይመጽእ፡ አምላከ፡ ሰማይ፤

በነዚህ፡ ዘመን፡ ሰማይን፡ የፈጠረ፡ አምላክ፡ ይመጣል፤

ወይነሥእ፡ መንግሥተ፡ ዘለዓለም፡ ዘኢየኀልቅ፡ ወዘኢይትወሀብ፡ ለካልዕ፡ ሕዝብ፤

ለሌላ፡ ወገን፡ የማይሰጥ፡ ለዘለዓለም፡ የማይፈጸም፡ መንግሥትን፡ እጅ፡ ያደርጋል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወመንግሥቱ፡ ይመውዕ፡ ወያገርር፡ ኵሎ፡ ነገሥተ።

መንግሥቱ፡ ድል፡ ይነሳል፡ ነገ ሥታቱን፡ ሁሉ፡ ያስገዛል።

ወውእቱ፡ ይቀውም፡ ለዓለም።

እሱ፡ ለዘለዓለም፡ ጸንቶ፡ ይኖራል።

፵፭። ወዘከመ፡ ርኢከ፡ እምደብር፡ ተበትከ፡ ወወረደ፡ ዕብን፡ ዘእንበለ፡ እድ።

ተመትረም፡ ይላል፣ ከተራራ፡ እጅ፡ ሳይነካው፡ ተፈንቅሎ፡ የወ ረደው፡ ደንጊያ።

ወሐረፀ፡ ልሕኵቶሂ፡ ወሐፂኖሂ፡ ወብ ርቶሂ፡ ወብሩሮሂ፡ ወወርቆሂ።

ሸክላውን፣ ብረቱን፣ ብርቱን፣ ብሩን፣ ወርቁን፡ ቀጥቅጦ፡ በዓ ለም፡ ሲመላ፡ ያየኸው።

አምላክ፡ ዓቢይ፡ አርአዮ፡ ለንጉሥ፡ ዘሀሎ፡ ይኩን፡ ከመዝ።

በኋላ፡ ዘመን፡ ይደረግ፡ ዘንድ፡ ያለውን፡ ገናና፡ ጽኑዕ፡ የሚ ሆን፡ ፈጣሪ፡ ለንጉሥ፡ ለአንተ፡ ገልጦልሃል።

ወእሙን፡ ሕልሙ፡ ወርቱዕ፡ ፍካሬሁ።

ሕልሙ፡ እውነት፡ ነው። ትር ጓሜውም፡ የቀና፡ ነው። የዕ ብን፡ ምሳሌ፡ እንደ፡ ውዳሴ፡ ማርያም፡ ነው።

፵፮። ወሶቤሃ፡ ሰገደ፡ ንጉሥ፡ ናቡ ከደነፆር፡ በገጹ።

ያን፡ ጊዜ፡ ናቡከደነፆር፡ በግም ባሩ፡ ፍግም፡ ብሎ፡ ሰገደ።

ወለዳንኤልኒ፡ አክበሮ፡ ፈድፋደ።

ዳንኤልንም፡ ፈጽሞ፡ አከበረው።

ወወሀቦ፡ አምኃ፡ ወመሐና።

እጅ፡ መንሻ፡ አምኃ፡ ሰጠው።

፵፯። ወተሰጥዎ፡ ንጉሥ፡ ለዳን ኤል፡ ወይቤሎ።

ንጉሥ፡ መለሰለት፣ ዳንኤልን፡ እንዲህ፡ አለው።

አማን፡ አምላክክሙ፡ አምላከ፡ አማል ክት፡ ውእቱ።

ፈጣሪያችሁ፡ በእውነት፡ የካህ ናት፡ ፈጣሪ፡ ነው።

ወእግዚአ፡ አጋዕዝት።

የጌቶች፡ ጌታ፡ ነው።

ወንጉሠ፡ ነገሥት፡ ዘይከሥት፡ ዘኅቡዕ።

የተሠወረውን፡ የሚገልጥ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ነው።

እስመ፡ ክህልከ፡ አእምሮ፡ ዘኑኅ፡ ዘክዱን።

የተሠወረውን፡ ይህን፡ ማወቅ፡ ተችሎሃልና።

፵፰። ወአዕበዮ፡ ንጉሥ፡ ለዳንኤል።

ንጉሥ፡ ዳንኤልን፡ አከበረው፣ አገነነው።

ወብዙኃ፡ ፈተቶ።

ብዙ፡ ድርጎ፡ ዳረገው።



ወወሀቦ፡ አብያተ።

ቤት፡ ንብረት፡ ሰጠው። አንድም፡ ዓቢያተ፡ ቢል፡ ገናና፡ ገናና፡ ነገር፡ አደረገለት።

ወሤሞ፡ ለኵሉ፡ በሐውርተ፡ ባቢሎን፡ መልአከ።

በባቢሎን፡ ሁሉ፡ ቢትወደድ፡ አድርጎ፡ ሾመው።

ወመኰንነ፡ ለኵሉ፡ ጠቢባነ፡ ባቢሎን።

በባቢሎን፡ ላሉ፡ አዋቆች፡ ሁሉ፡ ገዥ፡ አድርጎ፡ ሾመው።

፵፱። ወሰአለ፡ ዳንኤል፡ በኀበ፡ ንጉሥ።

ወግዶ፡ በዘመኑ፡ እንዲሉ፣ ዳን ኤል፡ ከንጉሥ፡ ተካሰ።

ወሤሞሙ፡ ለሲድራቅ።

ሲድራቅን፡ ቀኛዝማችነት።

ወሚሳቅ።

ሚሳቅን፡ ግራዝማችነት።

ወአብደናጎ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ ግብረ፡ በሐ ውርተ፡ ባቢሎን።

አብደናጎን፡ በባቢሎን፡ አገር፡ ሥራ፡ ላይ፡ ሁሉ፡ ከንቲባነት፡ ሾመው።

ወዳንኤልሰ፡ ውስተ፡ ዓፀደ፡ መንግሥት።

ዳንኤል፡ ግን፡ በከተማ፡ የሚ ኖር፡ ሆነ። እነሱ፡ በውጭ፣ እሱ፡ በከተማ፡ የሚኖሩ፡ ሁነ ዋል። ስለምን፡ ቢሉ፡ ነገረ፡ ሠሪ፡ ጠላት፡ ለመጠበቅ፡ ነው። አን ድም፡ ትምህርት፡ ይሰፋል፡ ብሎ።

## ምዕራፍ፡ ፫

### ጉባዔ።

፩። ወአመ፡ ፲ቱ ወ፰ቱ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ለናቡከደነፆር፡ ንጉሥ።

ናቡከደነፆር፡ በነገሠ፡ በአሥራ፡ ስምንተኛው፡ ዘመን።

ገብረ፡ ምስለ፡ ዘወርቅ፡ ኑኁ፡ ፰ በእ መት፣ ወግድሙ፡ ስድስ፡ በእመት።

ስድስት፡ ክንድ፡ ደረቱ፣ ስልሳ፡ ክንድ፡ ቁመቱ፡ የወርቅ፡ ምስል፡ ሠራ። ሐተታ፡ የኢዮአቄም፡ መን ግሥት፡ አሥራ፡ አንድ፡ ነው። ከዚያ፡ ስምንት፡ ያመጧል፣ የሴ ዴቅያስ፡ አሥራ፡ አንድ፡ ነው። የናቡከ ደነፆር፡ ሃያ፡ አምስት፡ ነው። ንጉሠ፡ ነገሥት፡ የሆነበት፡ በአሥራ፡ ስምንት፡ ዘመን፡ ምስል፡ አቆመ። በአሥራ፡ ዘጠኝ፡ ራእይ፡ አየ። ሰባት፡ ዓመት፡ እሪያ፡ ሆነ። ከዚያ፡ ተመልሶ፡ አሥራ፡ ስምንት፡ ዘመን፡ ገዝቷል። አርባ፡ ይሆናል። አንድም፡ ከኢዮአቄም፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ያመጧል፣ ወተቀንያ፡ ፫ ዓመተ፡ ይላልና፣ የሴዴቅያስ፡ አሥራ፡ አንድ፡ የቀረው፡ አንድ፡ ነው። በአሥራ፡ ስምንት፡ ምስል፡ አቆመ። በአ ሥራ፡ ዘጠነኛው፡ ራእይ፡ አየ።

www.ethiopianorthodox.org

ሰባት፡ ዓመት፡ እሪያ፡ ሆነ፤ ተመ
ልሶ፡ አሥራ፡ አራት፡ ዓመት፡
ገዝቷል፤ አንድም፡ የኢዮአቂ
ምን፡ ትቶ፡ የሴዴቅያስ፡ አሥራ፡
አንድ፡ ከዚያ፡ ከሃያ፡ አምስቱ፡
ጨምሮ፡ በዚህ፡ በአሥራ፡ ስም
ንቱ፡ ምስል፡ አቆመ፤ በአሥራ፡
ዘጠኝ፡ ራእይ፡ አየ፤ ሰባት፡
ዓመት፡ እሪያ፡ ሆነ፤ ተመልሶ፡
አሥር፡ ዓመት፡ ገዝቷል፤
አንድም፡ የሴዴቅያስን፡ ትቶ፡
ከኢዮአቄም፡ ሰባት፡ ዓመት፡
ያመጧል፤ ይህን፡ ከዚያ፡
ጨምሮ፡ ተመልሶ፡ ሰባት ዓመት፡
ገዝቷል፡ ምስል፡ ያቆመበት፡
ነገር፡ እንዴት፡ ነው፡ ቢሉ፡
በሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ ቀናን፡ ያሉ፡
ሰዎች፡ ርእሱ፡ ዘወርቅ፡ ተብሎ፡
የተተረጐመልህ፡ አንተ፡ ነህ፤
አሁንም፡ ስሳ፡ ክንድ፡ ቁመቱ፣
ስድስት፡ ክንድ፡ ደረቱ፡ ጣዖት፡
በሐቅለ፡ አዱራን፡ ይቁም፡
ብለህ፡ እዘዝ፡ አሉት፤

ወአቀሞ፡ ውስተ፡ ሐቅለ፡ ዱራ፡ በሀ
ገረ፡ ባቢሎን፣

በባቢሎን፡ አውራጃ፡ ዱራን፡
በሚባል፡ ምድረ፡ በዳ፡ አቆመው፤
ዱራን፡ አዱራን፡ ይላል፤

፪፤ ወናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፡ ለአከ፡
ያስተጋብኡ፡ መኳንንተ፡ ወመላእክተ፡
ወመሳፍንተ፡ ወመገብተ፣

ንጉሥ፡ ናቡከደነፆር፡ መኳንን
ቱን፣ አለቆችን፣ መሳፍንቱን፣
ሹማምንቱን፡ ይሰበስቡ፡ ዘንድ፡
ላከ፤

ወዓበይተ፡ ወነገሥተ፡ ወኵሎ፡ መላ
እክተ፡ በሐውርት፣

ትልልቆችን፡ ነገሥታቱን፣ የሀ
ገሩን፡ አለቆች፡ ሁሉ፡ ይሰበ
ሰቡ፡ ዘንድ፡ ላከ፤

ይምጽኡ፡ ለመድቅሐ፡ ውእቱ፡ ምስል፡
ዘአቀሞ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፣

ንጉሥ፡ ናቡከደነፆር፡ ያቆመ
ውን፡ ምስል፡ ለማመስገን፡
ይመጡ፡ ዘንድ፤

፫፤ ወተጋብኡ፡ መኳንንት፣

ቀኝአዝማች፡ ግራአዝማች፡
ተሰበሰቡ፤

ወመላእክት፣

ቀኝ፡ ቢትወደድ፡ ግራ፡ ቢት
ወድድ፤

ወመሳፍንት፣

ደጅ፡ አዝማች፤

ወመገብት፣

ሹማምንቱ፡ ራቅ፡ ማሠሪያ፤



ዓበይት፣

ትልልቆች፡ የወንድ፡ መኰንን፣
የሴት፡ ወይዘሮ፤

ወሐበይት፣

የሻለቆች፤

ወነገሥት፣

ነገሥታቱ፡ ተሰበሰቡ፤

ወመላእክተ፡ በሐውርት፣

እንደ፡ ቆብ፡ አስጥል፡ ኃይሉ፣
እንደ፡ ጥቁር፡ ከበቴ፡ ያሉ፡
ተሰበሰቡ፤

ለመድቅሐ፡ ውእቱ፡ ምስል፡ ዘአቀመ፡
ናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፣

ንጉሥ፡ ናቡከደነፆር፡ ያቆመ
ውን፡ ምስል፡ ለማደስ፡ ለማ
መስገን፡ ተሰበሰቡ፤

ወቆሙ፡ ቅድመ፡ ምስል፣

በምስሉ፡ ፊት፡ ቆሙ፣ ዛሬ፡ ክር
ስቲያን፡ ንጉሥ፡ አዲስ፡ ቤተ፡
ክርስቲያን፡ አሠርቶ፡ ቆሞ፡ እን
ዲያስቀድስ፤

፬፤ ወከልሐ፡ ዓዋዲ፡ በሕቁ፣

አዋጅ፡ ነጋሪ፡ ቃሉን፡ አሰምቶ፡
ጮኸ፤

ለክሙ፡ ይብሉክሙ፡ አሕዛብ፡ ወሕ
ዝብ፡ ወበሐውርት፣

ሕዝብም፡ አሕዛብም፡ በሀገር፡
ያላችሁ፡ ሁሉ፡ ንጉሥ፡ እን
ዲህ፡ አሏችሁ፤

፭፤ እምከመ፡ ሰማዕክሙ፡ ቃለ፡
ቀርን፡ ወዕንዚራ፣

የነጋሪቱን፣ የበገናውን፡ ድምፅ፡
ከሰማችሁ፡ በኋላ፤

ወመሰንቆ፣

መሰንቆውን፤

ወብዕዛ፣

ዛጉፉን፤

ወማኅሌተ፣

አታሞውን፤

ወኵሎ፡ ንዋየ፡ ተውኔት፤

የእግር፡ አታሞውን፡ ከሰማችሁ፡
በኋላ፤

ግነዩ፡ ወስግዱ፡ ለምስል፡ ዘወርቅ፡ ዘአ
ቀመ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፣

ንጉሥ፡ ናቡከደነፆር፡ ለአቆ
መው፡ ለወርቁ፡ ምስል፡ ስገዱ፣
ተገዙ፤

፮፤ ለዘኢገነየ፡ ወለዘኢሰገደ፡ በጊዜሃ፡
ይወድይዎ፡ ውስተ፡ ዕቶነ፡ እሳት፡
ዘይነድድ፣

ያልተገዛውን፣ ያልሰገደውን፡
ያን፡ ጊዜ፡ ከሚነድ፡ እሳት፡ ጉድ
ጓድ፡ ውስጥ፡ ይጥሉታል፤

፯፤ ወእምዝ፡ ሶበ፡ ሰምዑ፡ አሕ
ዛብ፡ ቃለ፡ ቀርን፡ ወዕንዚራ፡ ወመሰንቆ፣

ከዚህ፡ በኋላ፡ አሕዛብ፡ የነጋሪ
ቱን፡ የበገናውን፡ የመሰንቆውን፡
ድምፅ፡ በሰሙ፡ ጊዜ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወብዕዛ፡ ወማኅሌተ፡ ወንዋየ፡ ተውኔት፤

ዛጉፋን፡ የእግሩን፡ አታሞ፡ በሰሙ፡ ጊዜ፤

ገነዩ፡ ኵሉ፡ አሕዛብ፡ ወሕዝብ፡ ወበሐውርት፤

ሕዝቡም፡ አሕዛቡም፡ መንደር፡ መንድረው፡ የሚኖሩ፡ ሁሉ፡ ተገዙ፤

ወሰገዱ፡ ለምስል፡ ዘወርቅ፡ ዘአቀመ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፤

ናቡከደነፆር፡ ለአቆመው፡ ለወርቁ፡ ምስል፡ ሰገዱ፤

፰፤ ወእምዝ፡ መጽኡ፡ ሰብአ፡ ፋርስ፡ ወአስተዋደይዎሙ፡ ለአይሁድ፡ ኀበ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ የፋርስ፡ ሰዎች፡ መጥተው፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅን፡ ከንጉሥ፡ ናቡከደነፆር፡ ጋራ፡ አጣሏቸው፤

፱፤ ወይቤልዎ፡ ለንጉሥ፡ ለዓለም፡ ሕየው፤

ንጉሥ፡ ሽህ፡ ዓመት፡ ያንግሥህ፡ አሉት፤

፲፤ አንተ፡ ንጉሥ፡ አዘዝከ፡ በቃልከ፡ ትእዛዘ፡ ለኵሉ፡ አሕዛብ፤

ንጉሥ፡ አንተ፡ ለአሕዛብ፡ ሁሉ፡ በቃልህ፡ ትእዛዝ፡ አዝዘህ፡ ነበር፤

እምከመ፡ ሰምዑ፡ ቃለ፡ ቀርን፡ ወዕንዚራ፡ ወማኅሌተ፡ ወመሰንቆ፡ ወከበሮ፡ ወኵሎ፡ ተውኔተ፤

ነጋሪቱን፤ በገናውን፤ አታሞውን፤ መሰንቆውን፤ ከበሮውን፡ ሁሉ፡ ከሰሙ፡ በኋላ፤

ይግነዩ፡ ወይስግዱ፡ ለምስል፤

ለምስል፡ ይሰግዱ፡ ይገዙ፡ ዘንድ፡ አዝዘህ፡ ነበር፤

፲፩፤ ወለዘኢገነየ፡ ወለዘኢሰገደ፡ ለምስል፡ ዘወርቅ፡ ይደይዎ፡ ውስተ፡ ዕቶነ፡ እሳት፡ ዘይነድድ፤

ለወርቁ፡ ምስል፡ ያልሰገደውን፤ ያልተገዛውን፡ ከሚነድ፡ ከእሳት፡ ጕድጓድ፡ ውስጥ፡ ይጥሉት፡ ዘንድ፡ አዝዘህ፡ ነበር፤

፲፪፤ ወይእዜኒ፡ ሀለዉ፡ ፫ቱ፡ ዕደው፡ አይሁድ፡ እለ፡ ሤምኮሙ፡ ለግብረ፡ በሐውርተ፡ ባቢሎን፤

በባቢሎን፡ ባሉ፡ አገሮች፡ ሥራ፡ የሾምካቸው፡ ሦስት፡ ሰዎች፡ አሉ፤

ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፡ እለ፡ አበዩ፡ ትእዛዘከ፡ ኦ፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ እሊህም፡ ትእዛዝህን፡ እምቢ፡ ያሉ፡ ሲድራቅ፡ ሚሳቅ፡ አብድናጎ፡ ናቸው፤

ወኢያምለኩ፡ አምላከከ፡ ወኢሰገዱ፡ ለምስል፡ ዘወርቅ፡ ዘገበርከ፤

አምላክህን፡ ያላመለኩ፡ ለሠራኸው፡ ለወርቅ፡ ምስል፡ ያልሰገዱ፡ አሉ፡ አሉት፤

፲፫፤ ወሶቤሃ፡ ተምዐ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ንጉሥ፡ ናቡከደነፆ፡ ተቆጣ፤



ወአዘዘ፡ በመዓት፡ ያምጽእዎሙ፡ ለሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፤

ተቆጥቶ፡ ሲድራቅ፡ ሚሳቅ፡ አብደናጎን፡ ያመጧቸው፡ ዘንድ፡ አዘዘ፤

ወመጽኡ፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፤

በንጉሥ፡ ፊት፡ መጡ፤

፲፬፤ ወተሠጥዎሙ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፡ ወይቤሎሙ፤

ናቡከደነፆር፡ መለሰላቸው፡ እንዲህ፡ አላቸው፤

አማንከሙኑ፡ ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፡ ዘኢታመልኩ፡ አምላኪየ፡ ወኢትሰግዱ፡ ለምስል፡ ዘወርቅ፡ ዘገበርኩ፤

ሲድራቅ፡ ሚሳቅ፡ አብደናጎ፡ ፈጣሪዬን፡ የማታመልኩ፡ ለሠራሁት፡ ለወርቅ፡ ምስል፡ የማትሰግዱ፡ እውነታችሁ፡ ነውን፤

፲፭፤ ወይእዜኒ፡ እመ፡ ጥቡዓን፡ አንትሙ፤

አሁንም፡ እናንተ፡ የጨከናችሁ፡ እንደሆነ፡ አይ፤ አንድም፡ ጨካኞች፡ እንደሆናችሁ፡ እስቲ፡ አይ፤ (እስቲ፡ አያለሁ)፤

እምከመ፡ ሰማዕክሙ፡ ቃለ፡ ቀርን፡ ወዕንዚራ፡ ወመሰንቆ፡ ወማኅሌተ፡ ወከበሮ፡ ወብዕዛ፡ ወኵሎ፡ ተውኔተ፤

የነጋሪቱን፡ ድምፅ፡ በገናውን፡ መሰንቆውን፡ አታሞውን፡ ከበሮውን፡ ዛጉፋን፡ የእግር፡ አታሞውን፡ ይኸን፡ ሁሉ፡ ከሰማችሁ፡ በኋላ፤

እስኩ፡ ለእመ፡ ኢትስግዱ፡ ለምስል፡ ዘወርቅ፡ ዘገበርኩ፤

ለሠራሁት፡ ለወርቁ፡ ምስል፡ እስቲ፡ ለምን፡ አትሰግዱ፤ አንድም፡ እስቲ፡ አትሰግዱ፡ እንደሆነ፡ አይ፤

ወእምከመ፡ ኢትሰግዱ፡ ለምስል፡ በጊዜሃ፡ ይወድዩክሙ፡ ውስተ፡ ዕቶነ፡ እሳት፡ ዘይነድድ፤

ለምስሉም፡ ካልሰገዳችሁ፡ ያን፡ ጊዜ፡ የሚነድ፡ እሳት፡ በአለበት፡ ጕድጓድ፡ ይጥሏችኋል፤

ወመኑ፡ ውእቱ፡ እግዚአብሔር፡ ዘያድኅነክሙ፡ እምእዴየ፤ ሎቱ፡ ስብሐት፤

ከኔ፡ እጅ፡ የሚያድናችሁ፡ እግዚአብሔር፡ ማን፡ ነው፤

፲፮፤ ወአውሥእዎ፡ ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፡ ለናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፤

ሲድራቅ፡ ሚሳቅ፡ አብደናጎ፡ ለናቡከደነፆር፡ መለሱለት፤

ወይቤልዎ፡ ኢንፈቅድ፡ ንሕነሰ፡ ከመ፡ ንስጠውከ፡ በዝ፡ ነገር፤

እኛስ፡ ቤልን፡ እናመልካለን፡ ብለን፡ በዚህ፡ ነገር፡ ልንመልስልህ፡ አንወድም፤ አንድም፡ መኑ፡ ያድኅነክሙ፡ እምእዴየ፡ ብሏቸው፡ ነበርና፡ የሚያድነን፡ ወዳጅ፡ ዘመድ፡ አለን፡ ብለን፡ ልንመልስልህ፡ አንወድም፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፯። ሀሎ፡ አምላክነ፡ ውስተ፡ ሰማይ፡ ዘናመልክ፡ ንሕነ፡ ወይክል፡ አድኅኖተነ፡ እምእዴከ፤

እኛ፡ የምናመልከው፡ ፈጣሪያችን፡ በሰማይ፡ አለ። ከአንተ፡ እጅ፡ እኛን፡ ማዳን፡ ይቻለዋል።

ወእምዕቶነ፡ እሳት፡ ዘይነድድ፤

ከሚነድ፡ ከዕቶን፡ እሳትም፡ እኛን፡ ማዳን፡ ይቻለዋል።

ወያነግፈነ፡ እምእዴከ፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ ከአንተ፡ እጅ፡ ያስጥለናል።

፲፰። ከመ፡ ታእምር፡ ኦ፡ ንጉሥ፡ አምላከከሂ፡ ኢናመልክ፡ ወለምስልሂ፡ ዘወርቅ፡ ዘአቀምከ፡ ኢንሰግድ፤

ንጉሥ፡ ግዱን፡ ቁርጡን፡ ታውቅ፡ ዘንድ፡ አምላክህን፡ አናመልክም፤ ለአቆምኸውም፡ ለወርቅ፡ ምስል፡ አንሰግድም።

፲፱። ወሶቤሃ፡ ተምዓ፡ ናቡከደነፆር፡ በሕቁ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ናቡከደነፆር፡ ፈጽሞ፡ ተቆጣ፤ ሠይፍ፡ መዘዘባቸው፤ ጦር፡ ነጠቀባቸው።

ወተወለጠ፡ ርእየተ፡ ገጹ፡ በላዕለ፡ ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፤

በሲድራቅ፡ በሚሳቅ፡ በአብደናጎ፡ ላይ፡ መልኩ፡ ተለወጠ።

ወአዘዘ፡ ያንድዱ፡ እቶነ፡ እሳት፡ ምስብዒተ፡ እስከ፡ በሕቁ፡ ይውዒ፤

በእጅጉ፡ ፈጽሞ፡ ይቃጠል፡ ዘንድ፡ ሰባት፡ እጥፍ፡ ድርብ፡ አድርገው፡ ዕቶን፡ እሳቱን፡ ያነድዱ፡ ዘንድ፡ አዘዘ።

፳። ወአዘዘ፡ ዕደወ፡ጽኑዓነ፡ ወኃያላነ፡ ይእሥርዎሙ፡ ለሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፤

ሲድራቅ፡ ሚሳቅ፡ አብደናጎን፡ ያሥሯቸው፡ ዘንድ፡ ኃያላን፡ ጽኑዓን፡ የሆኑ፡ ጕልማሶችን፡ አዘዘ።

ወይውርውዎሙ፡ ውስተ፡ ዕቶነ፡ እሳት፡ ዘይነድድ፤

ከሚነድ፡ ከዕቶን፡ እሳት፡ ውስጥ፡ ይጥሏቸው፡ ዘንድ።

፳፩። ወሶቤሃ፡ እሙንቱ፡ ዕደው፡ አሠርዎሙ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ጕልማሶች፡ አሠረው።

ምስለ፡ ድርማንቃቲሆሙ፤

ከነልባልባቸው።

ወምስለ፡ አሣእኒሆሙ፤

ከነጫማቸው።

ወምስለ፡ አልባሰ፡ አቍያጺሆሙ፤

ከነቍንፅል፡ ቀሚሳቸው።

ወምስለ፡ አክሊላቲሆሙ፤

ከነኮፌታቸው፡ አክሊላቲሆሙ፡ ባለው፡ ቆጸናቲሆሙ፡ የሚል፡ ይገኛል።

ወምስለ፡ አልባሲሆሙ፤

ከነመጎናጠፊያቸው።

ወወረውዎሙ፡ ውስተ፡ ዕቶነ፡ እሳት፡ ዘይነድድ፤

በተራዳ፡ እየገፉ፡ በዕቶን፡ እሳት፡ ውስጥ፡ ጣሏቸው፤ የንጉሥ፡



ሹማምንት፡ ናቸውና፡ እናዋርዳቸው፡ ብለው። አንድም፡ አላልቦ፡ ይግደላቸው፡ ብለው።

እስመ፡ ኀየለ፡ ቃለ፡ ንጉሥ፤

የናቡከደነፆር፡ ቃል፡ በርትቷልና። አንድም፡ እስመ፡ ኃያል፡ ቃለ፡ ንጉሥ፤ የናቡከደነፆር፡ ቃል፡ ኃያል፡ ነውና። አንድም፡ እስመ፡ ኀየለ፡ ቃለ፡ ንጉሥ፤ የንጉሥ፡ የጌታ፡ ቃል፡ ኢታምልክ፡ ያለው፡ ቃሉ፡ ጸንቷልና። አንድም፡ እስመ፡ ኃያል፡ ቃለ፡ ንጉሥ፤ የንጉሥ፡ የጌታ፡ ቃል፡ ኃያል፡ ነውና።

፳፪። ወአንደዱ፡ እሳተ፡ ዕቶን፡ በሕቁ፤

በጕድጓዱ፡ ያለውን፡ እሳት፡ ፈጽመው፡ አነደዱ፤

፳፫። ወወረዱ፡ እሉ፡ ፫ቱ፡ ደቂቅ፡ ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፡ ማዕከለ፡ ዕቶነ፡ እሳት፡ ዘይነድድ፡ እንዘ፡ ዕሡራን፡ እደዊሆሙ፡ ወእገሪሆሙ፤

እኒህ፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ ሲድራቅ፡ ሚሳቅ፡ አብደናጎ፡ እጃቸውን፡ እግራቸውን፡ ታሥረው፡ በሚነደው፡ እሳት፡ መካከል፡ ወደጕድጓዱ፡ ወረዱ።

፳፬። ወአንሶሰዉ፡ ማዕከለ፡ እሳት፤

በእሳቱ፡ መካከል፡ ተመላለሱ።

ወአዕኰቱ፡ እግዚአብሔርሃ፡ ወባረክዎ፤

እግዚአብሔርን፡ በውስጥ፡ በአፍዓ፡ አመሰገኑት።

፳፭። ወቆመ፡ አዛርያ፡ ወጸለየ፡ ከመዝ፤

አዛርያ፡ ቆመ፤ እንዲህ፡ ብሎ፡ ጸለየ፤ ዳንኤል፡ ጥሬ፡ እንብላ፡ በማለት፡ እንደ፡ ጨከነ፡ አዛርያም፡ ዕቶነ፡ እሳት፡ እንግባ፡ በማለት፡ ጨክኖ፡ ነበርና፤ ወቆመ፡ አዛርያ፡ ብሎ፡ ለአዛርያ፡ ብቻ፡ ሰጥቶ፡ ተናገረ፡ እንጂ፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ በውስጥ፡ ዳንኤል፡ በአፍአ፡ ሁነው፡ ተናግረውታል።

ወከሠተ፡ አፉሁ፡ ማዕከለ፡ እሳት፡ ወይቤ፤

በእሳት፡ መካከል፡ ነገር፡ ጀመረ፤ እንዲህ፡ አለ።

፳፮። ይትባረክ፡ እግዚአብሔር፡ አምላከ፡ አበዊነ፤

የአባቶቻችን፡ የአብርሃም፡ የይስሐቅ፡ የያዕቆብ፡ ፈጣሪ፡ ይክበር፡ ይመስገን። አንድም፡ ለአባቶቻችን፡ ኤርትራን፡ ዮርዳኖስን፡ የከፈለላቸው፤ ለኛም፡ ዕቶነ፡ እሳትን፡ ያበረደልን፡ የአባቶቻችን፡ ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር፡ ይክበር፡ ይመስገን።

እኩት፡ ወስቡሕ፡ ስምከ፡ ለዓለም፤

ስምህ፡ ለዘለዓለም፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው። እኛ፡ ብናመሰግንህ፡ ምስጋና፡ የሚጨመርልህ፤

www.ethiopianorthodox.org

እኛ፡ ባናመሰግንህ፡ ምስጋና፡ የሚከፈልብህ፡ አይደለም።

፳፯። እስመ፡ ጻድቅ፡ አንተ፡ እግዚኦ፡ በኵሉ፡ ዘአምጻእከ፡ ላዕሌነ።

ብነ፡ ሲል፡ ነው። በኛ፡ ላይ፡ በአመጣኸው፡ ሁሉ፡ አቤቱ፡ በእውነት፡ ፈርደህ፡ አምጥተህብናልና።

ዕሙን፡ ኵሉ፡ ግብርከ።

ሥራህ፡ ሁሉ፡ የታመነ፡ ነው።

ወርቱዕ፡ ኵሉ፡ ፍናዊከ።

ሥራህ፡ ሁሉ፡ የቀና፡ ነው።

ወጽድቅ፡ ኵሉ፡ ኵነኔከ።

ሕግህ፡ እውነተኛ፡ ሕግ፡ ነው። አንድም፡ ዕሙን፡ ኵሉ፡ ግብርከ፡ ኢታመልክ፡ አፍቅሮ፡ በጽ። ወርቱዕ፡ ኵሉ፡ ፍናዊከ። ስምንቱ፡ ቃላት። ወጽድቅ፡ ኵሉ፡ ኵነኔከ። አምስቱ፡ መቶ፡ ሰባ፡ ወነበቦ። አንድም፡ ዕሙን፡ ኵሉ፡ ግብርከ፡ ጌዋዌ፡ የታመነ፡ ነው። ወርቱዕ፡ ኵሉ፡ ፍናዊከ። ሚጠት፡ የቀና፡ ነው። ወጽድቅ፡ ኵሉ፡ ኵነኔከ። ፍርድህ፡ እውነት፡ ነው።

፳፰። ወገበርከ፡ ፍትሐ፡ ወርትዐ፡ በኵሉ፡ ዘገበርከ፡ ለነ።

በኛ፡ ላይ፡ ባደረግኸው፡ ሁሉ፡ ፍትሕ፡ ርትዕን፡ አደረግህ።

ወዲበ፡ ሀገረ፡ አበዊነ፡ ኢየሩሳሌም፡ ቅድስት።

ክብርት፡ በምትሆን፡ በአባቶቻችን፡ አገር፡ በኢየሩሳሌምም፡ እውነት፡ ፈርደህ፡ አመጣህባት።

እስመ፡ በኵነኔ፡ ጽድቅከ፡ አምጻእከ፡ ዘ፡ ኵሎ፡ በእንተ፡ ኃጢአትነ።

ስለ፡ ኃጢአታችን፡ ይህን፡ ሁሉ፡ እውነት፡ ፈርደህ፡ አምጥተህብናልና።

፳፱። እስመ፡ አበስነ፡ ወጌገይነ፡ ዘኃደግናከ።

አንተን፡ በሕግ፡ በአምልኮት፡ የተውንህ፡ እኛ፡ ፈጽመን፡ በድለናልና።

አመፅነ፡ በኵሉ፡ ወኢሰማዕነ፡ ትእዛዘከ።

በዘጠኙ፡ ቃላት፡ በደልን። ኢታምልክን፡ አልሰማንም። አንድም፡ አመፅነ፡ በኵሉ፡ በፀሐይ፡ በጨረቃ፡ በዕፀው፡ በአዕባን፡ በደልን።

ወኢሰማዕነ፡ ትእዛዘከ።

ትእዛዝህን፡ አልሰማንም።

፴። ኢዓቀብነ፡ ወኢገበርነ፡ በከመ፡ አዘዝከነ።

እንዳዘዝኸን፡ አላደረግንም። አልጠበቅንም።

ከመ፡ ይኩን፡ ሠናየ፡ ላዕሌነ።

ለኛ፡ በጎ፡ ይሆንልን፡ ዘንድ። አንድም፡ ከመ፡ ይኩን፡ ሠናይ፡ መጠበቁ፡ ለኛ፡ በጎ፡ ይሆንልን፡ ዘንድ።



፴፩። ኵሎ፡ ዘአምጻእከ፡ ላዕሌነ፡ ወኵሎ፡ ዘገበርከ፡ ዲቤነ፡ በኵነኔ፡ ጽድቅከ፡ ገበርከ።

በኛ፡ ላይ፡ ያመጣኸውን። በኛ፡ ላይ፡ ያደረግኸውን፡ ሁሉ፡ እውነት፡ ፈርደህ፡ አመጣህብን።

፴፪። ወመጠውከነ፡ ውስተ፡ እደ፡ ፀርነ፡ ኃጥአን፡ ወዓላውያን።

ኃጥአን፡ ዓላውያን፡ በሚሆኑ፡ በጠላቶቻችን፡ እጅ፡ ጣልኸን። ምግባር፡ የላቸውምና፡ ኃጥአን። ሃይማኖት፡ የላቸውምና፡ ዓላውያን፡ አላቸው።

እለ፡ ርኁቃን፡ ወግሁሣን፡ እምኔከ።

ከአንተ፡ ፈጽመው፡ በራቁ።

ወንጉሥ፡ ዓማፂ፡ ወእኩይ፡ እምኵሉ፡ ምድር።

አመፀኛ፡ በደለኛ፡ በሚሆን፡ ከሰው፡ ሁሉ፡ በሚከፋ፡ በናቡከደነፆር፡ እጅ፡ ጣልኸን። ከሰው፡ ሁሉ፡ የሚከፋ፡ አለው። አነ፡ ውእቱ፡ ዘአሠርቅ፡ ፀሐየ፡ ያለ። ከሱ፡ በቀር፡ ሌላ፡ የለምና። አንድም፡ ከሰው፡ ሁሉ፡ በሚከፋ፡ በብልጣሶር፡ እጅ፡ ጣልኸን። ከሰው፡ ሁሉ፡ የሚከፋ፡ አለው። በጽዋው፡ ቀድታችሁ፡ አጠጡበት። በጸሕሉ፡ ፈትፍታችሁ፡ አብሉበት፡ ያለ፡ ከሱ፡ በቀር፡ ሌላ፡ የለምና።

፴፫። ወይእዜኒ፡ አኮ፡ ድልወት፡ ለነ፡ ንክሥት፡ አፉነ።

አሁንም፡ አፋችንን፡ ገልጠን፡ እናመሰግንህ፡ ዘንድ፡ አይገባንም። አንድም፡ አኮ፡ መጠንነ፡ ይላል። አፋችንን፡ ገልጠን፡ እናመስግንህ፡ ዘንድ፡ መጠናችን፡ አይደለም።

ኃፍረት፡ ወዝንጓጌ፡ ኮነሙ፡ ለአግብርቲከ፡ ለእለ፡ ይፈርሁከ።

ለሚፈሩህ፡ ለባሮችህ፡ ኃፍረት፡ መሸሚጠጫ፡ ሆናቸው። አንድም፡ ኮነነ፡ ይላል። ለምንፈራህ፡ ለባሮችህ፡ ኃፍረት፡ መሸሚጠጫ፡ ሆነን።

፴፬። ወኢትመጥወነ፡ ለግሙራ፡ በእንተ፡ ስምከ።

ስምየኒ፡ መሐሪ፡ ወመስተሣህል፡ ስላልኸው፡ ስለ፡ ስምህ፡ አሳልፈህ፡ አትስጠን።

ወኢትሚጥ፡ ኪዳነከ።

መሐላህን፡ አትለውጥ። አንድም፡ ኪዳነነ፡ ይላል። መሐላችንን፡ አትለውጥ።

፴፭። ወኢታርኅቅ፡ ምሕረተከ፡ እምኔነ።

ይቅርታህን፡ ከኛ፡ አታርቅ።

www.ethiopianorthodox.org

በእንተ፡ አብርሃም፡ ፍቁርከ፤

ብየ፡ አርክ፡ በዲበ፡ ምድር፡ አብ
ርሃም፡ ፍቁርየ፡ ብለህ፡ ስለተ
ናገርህለት፡ ስለ፡ ወዳጅህ፡ ስለ፡
አብርሃም፡ ብለህ፡ መሐላህን፡
አትለውጥ፤

ወበእንተ፡ ይስሐቅ፡ ቍልዔከ፤

እምይስሐቅ፡ ይሰመይ፡ ለከ፡
ዘርዕ፡ ስላልኸው፡ ስለ፡ ወዳጅህ፡
ስለ፡ ይስሐቅ፡ ብለህ፤

ወበእንተ፡ እስራኤል፡ ቅዱስከ፤

እምይእዜሰ፡ ኢይኩን፡ ስምከ፡
ያዕቆብ፡ አላ፡ ይኩን፡ ስምከ፡
እስራኤል፡ ብለህ፡ ስለ፡ አከበ
ርኸው፡ ስለ፡ እስራኤል፡ ብለህ፡
መሐላህን፡ አትለውጥ፤

፴፮፤ እለ፡ ተናገርኮሙ፡ ወትብሎሙ፡
ከመ፡ ታብዝኅ፡ ዘርዖሙ፡ ከመ፡ ኮከበ፡
ሰማይ፡ ወከመ፡ ኆፃ፡ ዘድንጋገ፡ ባሕር፤

ዘጽንፈ፡ ባሕር፡ ሲል፡ ነው፤
ልጆቻቸውን፡ እንደ፡ ሰማይ፡
ኮከብ፤ እንደ፡ ባሕር፡ አሸዋ፡
ታበዛላቸው፡ ዘንድ፡ ስለ፡ ተናገ
ርኻቸው፡ እንዲህ፡ ስላልኻቸው፡
ስለ፡ አብርሃም፤ ስለ፡ ይስሐቅ፤
ስለ፡ ያዕቆብ፡ ብለህ፡ መሐላ
ህን፡ አትለውጥ፤

፴፯፤ እስመ፡ ውሑዳን፡ ጥቀ፡ እሙ
ንቱ፡ እምኵሉ፡ አሕዛብ፤

ከአሕዛብ፡ ሁሉ፡ እነሱ፡ እጅግ፡
ጥቂቶች፡ ነበሩና፤ አንድም፡ እኅዝ፡
ውሑዳን፡ ይላል፤ ይኸውም፡
እንዲህ፡ ያልኻቸው፡ ከአሕዛብ፡
እጅግ፡ አንሰው፡ ሳሉ፡ ነው፤

ወኮነ፡ ሕሡራነ፡ በኵሉ፡ ምድር፡ ዮም፡
በእንተ፡ ኃጢአትነ፤

ስለ፡ ኃጢአታችን፡ ዛሬ፡ በሀገሩ፡
ሁሉ፡ የተዋረድን፡ ሆነ፤

፴፰፤ አልቦ፡ በዝ፡ መዋዕል፡
መልአክ፤

አለቃህ፡ ኢያማልድህም? ትለኝ፡
እንደሆነ፡ እንደ፡ ኢያሱ፡ ያለ፡
አለቃ፡ የለም፤ ለምንት፡ አዕ
ድዎ፡ አዕደውኮ፡ ለገብርከ፡
ወናሁ፡ እስራኤል፡ ሜጠ፡
ዘባኖ፡ ቅድመ፡ ፀሩ፡ ብሎ፡
መዓቱን፡ መቅሠፍቱን፡ እንደ
መለሰ፤

ኢነቢይ፤

ነቢዩ፡ አያማልድህም? ትለኝ፡
እንደሆነ፡ በዚህ፡ ወራት፡ እንደ፡
ሙሴ፡ ያለ፡ ነቢይ፡ የለም፤ ጠስ
የኒ፡ እመጽሐፈ፡ ሕይወትከ፡
እምትጥስዮሙ፡ ለእሎንቱ፡
ብሎ፡ መዓቱን፤ መቅሠፍቱን፡
እንደመለሰ፤



ወኢንጉሥ፤

ንጉሡ፡ አያማልድህም? ትለኝ፡
እንደሆነ፡ በዚህ፡ ወራት፡ እንደ፡
ዳዊት፡ ያለ፡ ንጉሥ፡ የለም፤
ምንተ፡ ገብሩ፡ እሉ፡ አባግዕ፡
አነ፡ ኖላዊሆሙ፡ ዘአበስኩ፡ ዛቲ፡
ኃጢአት፡ ትኩን፡ ላዕሌየ፡ ወላ
ዕለ፡ ቤተ፡ አቡየ፡ ብሎ፡ መዓ
ቱን፤ መቅሠፍቱን፡ እንደመለሰ፤

ወኢቍርባን፡ ወኢመሥዋዕት፤

ቍርባንም፡ መሥዋዕትም፡ የለ፤

ወኢኅበ፡ ያጸንሕሑ፡ ዕጣነ፤

ዕጣን፡ የሚያሻትቱበት፡ ቤተ፡
መቅደስ፡ የለም፤ አንድም፡
የሚያሻትቱት፡ ዕጣን፡ የለም፤
አንድም፡ ዕጣንን፡ የሚያሻትቱ፡
ነቢያት፡ ካህናት፡ የሉም፤

ወኢብሔር፡ ኅበ፡ እለ፡ ይፈርዩ፡ በቅድ
ሜከ፡ ይርከቡ፡ ሣህለከ፤

ይቅርታህን፡ ያገኙ፡ ዘንድ፡ በፊ
ትህ፡ ምግባር፡ ትሩፋት፡ የሚ
ሠሩበት፡ እንደ፡ ኢየሩሳሌም፡
ያለ፡ አገር፡ የለም፤

፴፱፤ ዘእንበለ፡ በነፍስ፡ የዋህ፡ ወበ
መንፈስ፡ ትሑት፡ ተወከፍ፡ ለነ፤

በትሑት፡ ሰብእና፤ በቅን፡ ልቡና፡
ያቀረብነውን፡ ተቀበለን፡ እንጂ፤

፵፤ ከመ፡ ዘመሥዋዕተ፡ ሐራጊት፤

የሙሴን፤ የአሮንን፡ መሥዋ
ዕት፡ ትቀበል፡ እንደነበረ፤

ወአልህምት፤

የዳዊትን፡ የሰሎሞንን፡ መሥ
ዋዕት፡ ትቀበል፡ እንደነበረ፤

ወከመ፡ ዘአዕላፍ፡ አባግዕ፡ ስቡሐን፤

የኢዮስያስን፡ መሥዋዕት፡ ትቀ
በል፡ እንደ፡ ነበረ፡ ኢዮስያስ፡
በበዓለ፡ ፋሲካ፡ ዕልፍ፡ በግ፡
ሠውቷልና፤

ከማሁ፡ ይኩን፡ መሥዋዕቲነ፡ በቅድ
ሜከ፡ ዮም፤

መሥዋዕታችን፡ በፊትህ፡
አሁን፡ እንደ፡ ተናገርኩት፡
ይሁን፤ እንደ፡ ኢየሩሳሌም፡
ሰውነቱን፤ እንደ፡ ቤተ፡ መቅ
ደስ፡ ልቡናውን፤ እንደ፡
መሥዋዕቱ፡ጸሎቱን፤ እንደ፡
ሊቀ፡ ካህናቱ፡ ራሱን፡ አድ
ርጎ፡ ተናገረ፤

ወፍጹመ፡ ይኩን፡ በኀቤከ፤

በአንተ፡ ዘንድ፡ ፍጹም፡ ይሁን፤

ከመ፡ ኢይትኃፈሩ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡
ይትዌከሉከ፤

በአንተ፡ የሚያምኑ፡ ሁሉ፡
እንዳያፍሩ፤

www.ethiopianorthodox.org

፵፩፤ ወይእዜኒ፡ ንተልወከ፡ በኵሉ፡ ልብነ፡ ወንፈርሀከ፤

አሁንም፡ በሕግ፡ በአምልኮት፡ እንከተልሃለን፤ በፍጹም፡ ልቡና ችን፡ እንፈራሃለን፤

ወነኃሥሥ፡ ገጸከ፡ ዳዕሙ፡ ኢታስተ ሐፍረነ፤

አታሳፍረን፡ እንጂ፡ ገጸ፡ ረድ ኤትህን፡ እንሻለን፤

፵፪፤ ወግበር፡ ምስሌነ፡ በከመ፡ ተመይጦትከ፤

ለነ፡ ሲል፡ ነው፤ ተመየጡ፡ እት መየጠክሙ፡ እንዳልህ፡ አድር ግልን፤

ወበከመ፡ ብዝኃ፡ ምሕረትከ፡ አድኅነነ፡ በተአምሪከ፤

እንደ፡ ይቅርታህ፡ ብዛት፡ መጠን፡ በተአምራትህ፡ አድነን፤

ሀብ፡ ስብሐተ፡ ለስምከ፡ እግዚኦ፤

አቤቱ፡ ለስምህ፡ ምስጋና፡ ስጥ፡ ማለት፡ እንድናመሰግንህ፡ አድርገን፤

፵፫፤ ይትኃፈሩ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ አርአይዎሙ፡ ሥቃየ፡ ለአግብርቲከ፤

ባሮችህን፡ መከራ፡ ያሳዩዋቸው፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ይፈሩ፤

ወይትሐፈሩ፡ በኵሉ፡ ትዕግልቶሙ፡ ወይትቀጥቀጥ፡ ኃይሎሙ፤

በመቃማታቸው፡ ምክንያት፤ አንድም፡ ጣዖት፡ በማምለካ ቸው፡ ምክንያት፡ ይፈሩ፤ ይድ ክም፡ ኃይሎሙ፡ ይሕልቅ፡ ብዕ ሎሙ፡ ሲል፡ ነው፤ ኃይላቸው፡ ይድከም፤ ብዕላቸው፡ ይጥፋ፤

፵፬፤ ወያእምሩ፡ ከመ፡ አንተ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ባሕቲትከ፤

ፈጣሪ፡ አንተ፡ ብቻ፡ እንደ፡ ሆንህ፡ ይወቁ፤

ስቡሕ፡ በኵሉ፡ ምድር፤

በከላውዴዎን፤

ወበኵሉ፡ ዓለም፤

በባቢሎን፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፤ አንድም፡ ስቡሕ፡ በኵሉ፡ ምድር፡ በከላውዴዎን፡ በባቢ ሎን፡ ወበኵሉ፡ ዓለም፡ በኢየሩ ሳሌም፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፤ አንድም፡ ስቡሕ፡ በኵሉ፡ ምድር፤ በዚህ፡ ዓለም፡ ወበ ኵሉ፡ ዓለም፡ በመንግሥተ፡ ሰማይ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፤

## ጉባኤ

፵፭፤ ወኢኃደጉ፡ አስተዋድዮቶሙ፡ ወአልያን፡ ኀበ፡ ንጉሥ፤

የንጉሥ፡ ሎሌዎች፡ ነገር፡ መሥ ራቱን፡ አልተዉም፤

፵፮፤ ወውስተ፡ እሳቱ፡ ወደዩ፡ ተየ፡ ወፒሳ፤

ከእሳቱም፡ ድኙን፤ ሰሙን፤ አደሮ፡ ማሩን፡ ጨመሩ፤ አን ድም፡ የንጉሥ፡ ሎሌዎች፡ ነገር፡ መሥራቱን፡ አይተዉም፡ ነበር፤ ወዲህም፡ ድኙን፤ አደሮ፡ ማሩን፡ ይጨምሩ፡ ነበር፤ አን



ድም፡ እንዲያው፡ ዝም፡ ብለው፡ አጣሏቸው፡ እንጂ፡ ድኙን፤ አደሮ፡ ማሩን፡ ማድረግ፡ አይተ ዉም፡ ነበር፤ በምታት፡ እንጂ፡ አበረዱት፡ ብለው፡ ነገሩት፤ ደም፡ ደም፡ ያለውን፡ እንጨት፡ ጨምሩ፡ ብሏቸዋል፤

ወሰጠጽዮነ፤

ቅንጭቡን፤

ወቀለምጼዳ፤

ቍልቋሉን፤ አንድም፡ ወሰጠጽ ዮነ፡ ደጉን፤

ወቀለምጼዳ፤

የባሕሩን፡ አረፋ፡ የወይኑንም፡ ሐረግ፡ ጨመሩ፤

፵፯፤ ወተለዓለ፡ ነበልባል፡ እምዕ ቶን፡ ፵፡ ወ፱ተ፡ እመተ፤

ነበልባሉ፡ ከጕድጓዱ፡ አርባ፡ ዘጠኝ፡ ክንድ፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አለ፤ በምን፡ ታውቋል፡ ቢሉ፡ ነቢዩ፡ ባወቀ፡ ተናግሮታል፤ አንድም፡ ከጕድጓዱ፡ ዳር፡ ዛፍ፡ ነበረ፤ ቢሰፍሩት፡ አርባ፡ ዘጠኝ፡ ክንድ፡ ሁኗል፤ አንድም፡ አግድሞ፡ የበላውን፡ መሬቱን፡ ቢሰፍሩት፡ አርባ፡ ዘጠኝ፡ ክንድ፡ ሁኗል፤

፵፰፤ ወያንሶሱ፡ ወያውዒ፡ ዘረከበ፡ ኀበ፡ ዕቶናሙ፡ ለከለዳውያን፤

እሳቱ፡ እየተመላለሰ፡ በከለዳ ውያን፡ ጕድጓድ፡ ያገኘውን፡ ያቃ ጥል፡ ነበር፤ አንድም፡ ሰዎች፡ የንጉሥ፡ ፊቃደኞች፡ ናቸው፡ ይበሉን፡ ብለው፡ እየተመላለሱ፡ ቅንጭቡን፡ ቍልቋሉን፡ ይጥሉ፡ ነበር፤ ስለምን፡ የከለዳውያንማ፡ ሥርዓት፡ ግበ፡ አናብስት፡ አይ ደለም? ቢሉ፡ ተማክረው፡ አድር ገውታል፤ አንድም፡ ሥርዓት፡ አይከላከሉም፡ ነበርና፡ የሮም፡ ውግረት፤ የኢየሩሳሌም፡ ስቅ ለት፤ (ስቅላት) የፋርስ፡ ዕቶነ፡ እሳት፤ የባቢሎን፡ ግበ፡ አናብ ስት፡ ነው፤ አንድም፡ ኀበ፡ ዕቶ ኖሙ፡ ለፋርስ፡ ብሎ፡ ይጽፋል፤

፵፱፤ ወወረደ፡ መልአከ፡ እግዚአ ብሔር፡ ምስለ፡ እለ፡ አዛርያ፡ ውስተ፡ ዕቶነ፡ እሳት፡ ዘይነድድ፤

ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ የታ ዘዘ፡ መልአክ፡ ከአዛርያ፡ ጋር፡ ያሉ፡ ሦስቱ፡ ደቂቅ፡ ወዳሉ በት፡ ወደ፡ ዕቶነ፡ እሳት፡ ወረደ፤

ወዘበጠ፡ ለነበልባለ፡ እሳት፤

የእሳቱን፡ ነበልባል፡ መታው፤

www.ethiopianorthodox.org

፶፧ ወረሰዮ፡ ለነበልባለ፡ እሳት፡ ከመ፡ ነፋስ፡ ቈሪር፤

የእሳቱን፡ ነበልባል፡ እንደጠል፡ አቀዘቀዘው፧

ወኢለከፎሙ፡ ወኢምንትኒ፤

ምንም፡ ምን፡ አለበለባቸውም፧

ወኢሰሐጦሙ፤

አላፈናቸውም፧

ወኢያጽዓቆሙ፡ ወኢያመንደቦሙ፤

አላስጨነቃቸውም፡ አላስጠበባቸውም፧

፶፩፧ ወሶቤሃ፡ እሙንቱ፡ ፫ቲሆሙ፡ ኅቡረ፡ በ፩ልብ፡ ወበ፩ አፍ፡ ሰብሑ፡ ወአዕኰትዎ፡ ወባረክዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ በውስተ፡ ዕቶን፧

ያን፡ ጊዜ፡ ሦስቱ፡ በአንድነት፡ እንደ፡ አንድ፡ ልብ፡ መካሪ፤ እንደ፡ አንድ፡ ቃል፡ ተናጋሪ፡ ሁነው፡ እግዚአብሔርን፡ በጕድጓዱ፡ ውስጥ፡ አመሰገኑት፧

፶፪፧ ወይቤሉ፡ ይትባረክ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ አበዊነ፤

በመከራ፡ ላይ፡ መከራ፡ ቢጨምሩባቸው፡ በምስጋና፡ ላይ፡ ምስጋና፡ ይጨምራሉ፧ አንድም፡ የአባቶቻችን፡ የአብርሃም፤ የይስሐቅ፤ የያዕቆብ፡ ፈጣሪ፡ ይክበር፡ ይመስገን፤ ለአባቶቻችን፤ ኤርትራን፡ ዮርዳኖስን፡ የከፈለላቸው፡ ለኛም፡ ዕቶኑ፡ እሳትን፡ ያበረደልን፡ የአባቶቻችን፡ ፈጣሪ፡ ይክበር፡ ይመስገን፡ አሉ፧

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

እኛ፡ ብናመሰግነው፡ ምስጋና፡ የሚጨመርለት፤ እኛ፡ ባናመሰግነው፡ ምስጋና፡ የሚከፈልበት፡ አይደለም፧ ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፧

ወይትባረክ፡ ስመ፡ ስብሐቲሁ፡ ቅዱስ፤

ጽኑዕ፡ ክቡር፡ ልዩ፡ የሚሆን፡ የጌትነቱ፡ ስም፡ ይክበር፡ ይመስገን፧

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ በኵሉ፡ ዓለም፤

በዓለም፡ ሁሉ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፧

፶፫፧ ቡሩክ፡ አንተ፡ በጽርሐ፡ ቅድሳተ፡ ስብሐቲከ፤

ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ተብለህ፡ በምትመሰገንበት፡ በጽርሐ፡ አርያም፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፧

ስቡሕኒ፡ አንተ፡ ወእኩት፡ አንተ፡ ለዓለም፤

አንተ፡ ለዘለዓለም፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፧

፶፬፧ ቡሩክ፡ አንተ፡ ዘትሬኢ፡ ቀላያተ፡ ነቢረከ፡ ላዕለ፡ ኪሩቤል፤

በኪሩቤል፡ ላይ፡ ተቀምጠህ፡ ቀላያተ፡ ውቅያኖስን፤ ቀላያተ፡ ኤርትራን፤ ቀላያተ፡ ዮርዳኖስን፤ ቀላያተ፡ ዕቶኑ፡ እሳትን፤ ቀላያተ፡ ገሃነምን፡ የምታይ፡ አንተ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፧



ስቡሕኒ፡ አንተ፡ ወልዑል፡ አንተ፡ ለዓለም፤

አንተ፡ ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ነህ፤ ምስጉን፡ ነህ፧

፶፭፧ ቡሩክ፡ አንተ፡ በዲበ፡ መንበረ፡ መንግሥትከ፤

በጌትነትህ፡ ዙፋን፡ ላይ፡ ተቀምጠህ፡ የምትመሰገን፡ አንተ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፧

ስቡሕኒ፡ አንተ፡ ወቡሩክ፡ አንተ፡ ለዓለም፤

ክቡር፡ የምትሆን፡ አንተ፡ ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፧

፶፮፧ ቡሩክ፡ አንተ፡ በመልዕልተ፡ ሰማያት፤

ከሰባቱ፡ ሰማያት፡ በላይ፡ ያለህ፡ አንተ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፧

ስቡሕኒ፡ አንተ፡ ወክቡር፡ አንተ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ አንተ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፤ ስለምን፡ ስድስት፡ ነገር፡ ተናገሩ፤ ዝቅ፡ ብለው፡ አራት፡ አምስት፤ ከፍ፡ ብለው፡ ሰባት፡ ስምንት፡ ያልተናገሩ፡ ቢሉ፡ ዝቅ፡ ብለው፡ አራት፡ አምስት፤ ከፍ፡ ብለው፡ ሰባት፡ ስምንት፡ ቢናገሩ፡ ሰውማ፡ ስለምን፡ ማለቱን፡ ይተዋልን፤ እግዚአብሔር፡ እንዳመገባቸው፡ ተናገሩ፧ አንድም፡ እኛ፡ ከዕቶኑ፡ እሳት፡ በወደቅን፡ በስድስት፡ መቶ፡ ዘመን፡ ጌታ፡ ሰው፡ ይሆናል፡ ሲሉ፡ በዘመናቸው፡ የነበረ፡ ዳንኤል፡ በአራት፡ መቶ፡ ዘጠና፡ ዘመን፡ ሰው፡ ይሆናል፡ አለ፧ አይጣላም፧ ቢሉ፡ አይጣላም፡ ዳንኤል፡ ከሚጠት፡ እስከ፡ ፅንስ፡ ቈጥሮ፡ እነዚህ፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ ከዔዋዌ፡ እስከ፡ ዕርገት፡ ድረስ፡ ቈጥረው፡ ነው፧ ይህም፡ በነገሥታቱ፡ ዘመን፡ ይታወቃል፧ ናቡከደናፆር፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ የሆነበት፡ ሃያ፡ አምስት፤ የዮርማሮዴቅ፡ ሃያ፡ ሁለት፤ የብልጣሶር፡ ሃያ፡ ሦስት፤ ይህ፡ ሰባ፡ ዘመን፡ ይሆናል፧ ጌታ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ የኖረው፡ ሠላሳ፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ከሦስት፡ ወር፡ ነው፧ በሰባው፡ ዘመን፡ ላይ፡ ሲጨምሩት፡ መቶ፡ ሦስት፡ ይሆናል፧ ከሴዴቅያስ፡ ሰባት፡ አምጥቶ፡ መቶ፡ አሥር፡ ይሆናል፧ መቶ፡ አሥሩን፡ አራት፡ መቶ፡ ዘጠናው፡ ላይ፡ ቢጨምሩ፡ ስድስት፡ መቶ፡ ይሆናል፧ አንድም፡ ወተለዓለ፡ ነበልባል፡ ፵ወ፱ተ፡ እመተ፡ ያለው፡ ለጊዜው፡ የዘሩባቤል፡ የዘመነ፡ መንግሥቱ፡ አምሳል፡ ነው፧ ዘመነ፡ መንግሥቱ፡ አርባ፡ ዘጠኝ፡ ነውና፡ ይህን፡

www.ethiopianorthodox.org

ስድስቱን፡ ከአርባ፡ ዘጠኙ፡ ሲጨምሩት፡ አምሳ፡ አምስት፡ ይሆናል፤ በአምስት፡ ሽህ፡ ከአምስት፡ መቶ፡ ዘመን፡ ጌታ፡ ሰው፡ ይሆናል፡ ሲሉ፤ አንድም፡ ዓለም፡ በተፈጠረ፡ በስድስተኛው፡ ሽህ፡ጌታ፡ሰው፡ይሆናል፡ ሲሉ፤

፲፯፤ ይባርክዎ፡ ኵሉ፡ ግብረ፡ እግዚእ፡ ለእግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔር፡ ፍጥረቶች፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

እኛ፡ ብናመሰግነው፡ ምስጋና፡ የሚጨመርለት፡ እኛ፡ ባናመሰግነው፡ ምስጋና፡ የሚከፈልበት፡ አይደለም፤ ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፲፰፤ ይባርክዎ፡ ሰማያት፡ ለእግዚአብሔር፤

ሰባቱ፡ ሰማያት፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፲፱፤ ይባርክዎ፡ መላእክተ፡ እግዚእ፡ ለእግዚአብሔር፤

ሠራዊተ፡ መላእክት፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፳፤ ይባርክዎ፡ ኵሉ፡ ማያት፡ ዘመልዕልተ፡ ሰማያት፡ ለእግዚአብሔር፤

ከጠፈር፡ በላይ፡ ያሉ፡ ውሆች፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፳፩፤ ይባርክዎ፡ ኵሉ፡ ኃይሉ፡ እግዚእ፡ ለእግዚአብሔር፤

ሊቃነ፡ መላእክት፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፳፪፤ ይባርክዎ፡ ፀሐይ፡ ወወርኅ፡ ለእግዚአብሔር፤

ፀሐይ፤ ጨረቃ፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤



፳፫፤ ይባርክዎ፡ ከዋክብተ፡ ሰማይ፡ ለእግዚአብሔር፤

በሰማይ፡ የሚመላለሱ፡ ከዋክብት፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፳፬፤ ይባርክዎ፡ ጠል፡ ወዝናም፡ ለእግዚአብሔር፤

ጠል፡ ዝናም፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፳፭፤ ይባርክዎ፡ ኵሉ፡ መንፈስ፡ ለእግዚአብሔር፤

አራቱ፡ ነፋሳተ፡ ምሕረት፤ ስምንቱ፡ ነፋሳተ፡ መዓት፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፳፮፤ ይባርክዎ፡ እሳት፡ ወላህብ፡ ለእግዚአብሔር፤

እሳት፡ አካሉ፤ ላህብ፡ ነበልባሉ፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፳፯፤ ይባርክዎ፡ ሌሊት፡ ወመዓልት፡ ለእግዚአብሔር፤

አሥራ፡ ሁለቱ፡ ሰዓተ፡ መዓልት፤ አሥራ፡ ሁለቱ፡ ሰዓተ፡ ሌሊት፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፳፰፤ ይባርክዎ፡ ጠል፡ ወዓውል፡ ለእግዚአብሔር፤

ክፉ፡ ጠል፡ አለ፤ አውል፡ ህቡጤዛ፡ ማለት፡ ነው፤ እነዚህ፡ እግዚአብሔርን፡ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፳፱፤ ይባርክዎ፡ ቍር፡ ወአስሐትያ፡ ለእግዚአብሔር፤

ቍር፡ ብትን፤ አስሐትያ፡ ግግሩ፤ ወይትፈለጥ፡ ከመ፡ ሥባሬ፡ ማኅው፡ በሊሃት፡ የሚለው፡ ነው፤ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

www.ethiopianorthodox.org

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፷፤ ይባርክዎ፡ በርህ፡ ወጽልመት፡ ለእግዚአብሔር፤

**ሕፀፅ፡ ምልዓት፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤**

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፷፩፤ ይባርክዎ፡ ደደክ፡ ወመርቄ፡ ለእግዚአብሔር፤

**ቀቅ፡ ዋዕይ፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤ አንድም፡ ቈላ፡ ደጋ፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤**

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፷፪፤ ይባርክዎ፡ በረድ፡ ወጊሜ፡ ለእግዚአብሔር፤

**በረድ፡ ጉም፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤ ወርኢኩ፡ መዝገበ፡ በረድ፡ እንዲል፤ ለበረድ፡ ቦታ፡ አለው፤ ጊሜ፡ ላህበ፡ ምድር፡ ነው፤**

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፷፫፤ ይባርክዎ፡ መብረቅ፡ ወደመና፡ ለእግዚአብሔር፤

**መብረቅ፡ ደመና፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤ መብረቅ፡ የሚለው፡ መልአኩ፡ አሸዋውንና፡ ድኙን፡ ሲያማታው፡ መብረቅ፡ ይፈጠራል፤ ወተት፡ በገፉት፡ ጊዜ፡ ቅቤ፤ አስታና፡ አስታ፡ ባማቱት፡ ጊዜ፡ እሳት፡ እንዲወጣው፡ መብረቅ፡ ይፈጠራል፤ ደመና፡ ላህበ፡ ምድር፡ ነው፤ አንድም፡ ከባሕር፡ እርጥብ፡ ጢስ፤ ከየብስ፡ ደረቅ፡ ጢስ፡ ይወጣል፤ ወይመውቁ፡ በፀሐይ፡ ወይከውኑ፡ ፪ሆሙ፡ ፩ደ፡ ደመና፡ እንዲል፤ አንድ፡ ደመና፡ ይሆናሉ፤**

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፷፬፤ ትባርኮ፡ ምድር፡ ለእግዚአብሔር፤

**ምድር፡ እግዚአብሔርን፡ ታመሰግነዋለች፤ ለይቶ፡ በሴት፡ አን**



**ቀጽ፡ ጠራት፤ ሴት፡ ከወንድ፡ ዘርዕ፡ ተቀብላ፡ ልጅ፡ እንድታስገኝ፤ ምድርም፡ ከገበሬ፡ እጅ፡ ዘርዕ፡ ተቀብላ፡ አዝርዕትን፤ አትክልትን፡ ታስገኛለችና፤**

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፷፭፤ ይባርክዎ፡ አድባር፡ ወአውግር፡ ለእግዚአብሔር፤

**ተራራዎች፡ ኮረብታዎች፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤**

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፷፮፤ ይባርክዎ፡ ኵሉ፡ ዘይበቍል፡ ውስተ፡ ምድር፡ ለእግዚአብሔር፤

**አዝርዕት፡ አትክልት፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤**

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፷፯፤ ይባርክዎ፡ ቀላያት፡ ለእግዚአብሔር፤

**ቀላያት፡ እንደ፡ ጣና፤ እንደ፡ ምጽዋ፡ ያሉ፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤**

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፷፰፤ ይባርክዎ፡ ባሕር፡ ወአፍላግ፡ ለእግዚአብሔር፤

**ባሕር፡ አልፎ፡ አልፎ፡ የቆመው፤ አፍላግ፡ ፈሳሾች፡ እንደ፡ ዓባይ፡ እንደ፡ በሽሎ፡ ያሉ፡ ያመሰግኑታል፤**

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፷፱፤ ይባርክዎ፡ አንበር፡ ወኵሉ፡ ዘይትሐወስ፡ ውስተ፡ ማይ፡ ለእግዚአብሔር፤

**አሣ፡ አንበሪ፤ አዞ፡ ጉማሬ፡ ተሃዋስያን፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤**

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

**ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤**

፸፤ ይባርክዎ፡ ኵሉ፡ አዕዋፈ፡ ሰማይ፡ ለእግዚአብሔር፤

**በሰማይ፡ የሚመላለሱ፡ አዕዋፍ፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤**

www.ethiopianorthodox.org

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፹፩፤ ይባርክዎ፡ ኵሉ፡ አራዊት፡ ወእንስሳ፡ ለእግዚአብሔር፤

እንስሳት፡ አራዊት፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤ እንስሳት፡የሚላቸው፡ የሚበሉ፤ አራዊት፤ የሚላቸው፡ የማይበሉ፡ ናቸው፤ ፈረስ፡ በቅሎም፡ አይበሉምና፡ አራዊት፡ ይባላሉን፡ ብሎ፡ አራዊት፡ የሚላቸው፡ ሥጋ፡ ነጭተው፡ ደም፡ ተጐንጭተው፡ የሚኖሩ፡ ናቸው፤ እንስሳት፡ የሚላቸው፡ ሣር፡ ነጭተው፡ ውሃ፡ ተጐንጭተው፡ የሚኖሩ፡ ናቸው፤ እነዚህ፡ ሁሉ፡ እሱ፡ ባወቀ፡ ያመሰግኑታልና፤ አንድም፡ እነዚህን፡ የፈጠረ፡ ተብሎ፡ ይመሰገንባቸዋልና፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፹፪፤ ይባርክዎ፡ ደቂቀ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ለእግዚአብሔር፤

ከሁሉ፡ ሰው፡ ይበልጣልና፡ በላይ፡ አመጣው፤ የአዳም፡ ልጆች፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፹፫፤ ይባርክዎ፡ እስራኤል፡ ለእግዚአብሔር፤

ከሰው፡ ሁሉ፡ ወልድየ፡ ዘበኵርየ፡ ያላቸው፡ እስራኤል፡ ይበልጣሉና፡ በላይ፡ አመጣቸው፡ እስራኤል፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፹፬፤ ይባርክዎ፡ ካህናቲሁ፡ እግዚእ፡ ለእግዚአብሔር፤

ደቂቀ፡ አሮን፡ ከሁሉ፡ በላይ፡ ናቸውና፡ በመጨረሻ፡ አመጣቸው፤ የአሮን፡ ልጆች፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፹፭፤ ይባርክዎ፡ አግብርቲሁ፡ እግዚእ፡ ለእግዚአብሔር፤

ደቂቀ፡ ጌድሶር፡ ደቂቀ፡ ሜራሪ፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤



ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፹፮፤ ይባርክዎ፡ መንፈስ፡ ወነፍስ፡ ጻድቃን፡ ለእግዚአብሔር፤

መንፈስ፡ ልቡናቸው፤ ወነፍስ፡ ጻድቃን፡ ሰውነታቸው፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤ አንድም፡ ወይሬስዩ፡ ርእሶሙ፡ ከመ፡ መንፈስ፡ እንተ፡ ኃለፈት፡ የሚላቸው፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፹፯፤ ይባርክዎ፡ ጻድቃን፡ ወትሑታነ፡ ልብ፡ ለእግዚአብሔር፤

ትሑት፡ ሰብእና፤ ቅን፡ ልቡና፡ ያላቸው፤ አንድም፡ ወጣንያን፡ ፍጹማን፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤

፹፰፤ ይባርክዎ፡ አናንያ፡ ወአዛርያ፡ ወሚሳኤል፡ ለእግዚአብሔር፤

ከሁሉ፡ ሰማዕታት፡ ይበልጣሉና፡ በላይ፡ አመጣቸው፤ አናንያ፡ አዛርያ፡ ሚሳኤል፡ እግዚአብሔርን፡ ያመሰግኑታል፤

ስቡሕኒ፡ ውእቱ፡ ወልዑልኒ፡ ውእቱ፡ ለዓለም፤

ለዘለዓለሙ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነው፤ ይህም፡ አንድ፡ ስቡሕኒ፡ ጨምሮ፡ ቢቈጥሩት፡ ሠላሳ፡ ሦስት፡ ይሆናል፤ ጌታ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ሠላሳ፡ ሦስት፡ ዘመን፡ ለመኖሩ፡ ምሳሌ፡ ነው፤

፹፱፤ እስመ፡ አድኃነነ፡ እምእደ፡ ሲኦል፡ ወእሞት፡ ባልሐነ፤

እምአፈ፡ ሲኦል፡ ሲል፡ ነው፤ ከመቃብር፡ ከሞተ፡ ሥጋ፡ አድኖናልና፤ አንድም፡ ከሲኦል፡ ከሞተ፡ ነፍስ፡ አድኖናልና፤

ይህም፡ ምሳሌ፡ ነው፤ ሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ የጻድቃን፡ ብሊት፤ በአፍአ፡ ያሉት፡ የኃጥአን፡ ብሊት፤ ግበ፡ አናብስት፡ የእደ፡ እግዚአብሔር፤ በአፍአ፡ ያሉትን፡ እሳት፡ በላቸው፡ ይላል፤ ነፍሶሙሰ፡ ለጻድቃን፡ ውስተ፡ እደ፡ እግዚአብሔር፡ ወኢለከፎሙ፡ ሥቃይ፡ እንዲል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወእምዕቶነ፡ እሳት፡ ዘይነድድ፡ አንገፈነ፤

ከሚነድ፡ ከዕቶን፡ እሳት፡ አዳነን፤

ወአውፅዓነ፡ እማዕከለ፡ ነበልባል፤

ከነበልባሉ፡ መካከል፡ አወጣን፤

ግነዩ፡ ለእግዚአብሔር፡ እስመ፡ ኄር፤

ቸር፡ ነውና፡ ለእግዚአብሔር፡ ተገዙ፤

፺፤ ባርክዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ኵልክሙ፡ እለ፡ ትፈርህዎ፡ ለእግዚአብሔር፤

እግዚአብሔርን፡ የምትፈሩት፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔርን፡ አመስግኑት፤

ወግነዩ፡ ለአምላከ፡ አማልክት፤

ለካህናት፡ ፈጣሪ፡ ለእግዚአብሔር፡ ተገዙ፤

ሰብሕዎ፡ ወግነዩ፡ ሎቱ፤

አመስግኑት፡ ለሱ፡ ተገዙ፤

እስመ፡ ለኵሉ፡ ዓለም፡ ምሕረቱ፤

ቸርነቱ፡ ለዓለም፡ ሁሉ፡ ነውና፤

፺፩፤ ወሰምዖሙ፡ ናቡከደነፆር፡ እንዘ፡ ይሴብሕዎ፡ አንከረ፤

ናቡከደነፆር፡ ሲያመሰግኑ፡ ሰምቶ፡ አይቶ፡ አደነቀ፤

ወተንሥአ፡ ፍጡነ፡ ወይቤሎሙ፡ ለመገብቱ፤

ፈጥኖ፡ ተነሣ፤ ሹማምንቱን፡ መኳንንቱን፡ እንዲህ፡ አላቸው፤

አኮኑ፡ ፫ተ፡ ዕደወ፡ ወደይነ፡ ማዕከለ፡ ዕቶነ፡ እሳት፡ ዕሡራነ፤

ሦስት፡ ሰዎች፡ አሥረን፡ ከዕቶን፡ እሳት፡ ጥለን፡ አልነበረምን፤

ወይቤልዎ፡ እወ፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ አዎን፡ አሉት፤

፺፪፤ ወይቤ፡ ንጉሥ፡ አንሰ፡ እሬኢ፡ ገዞ፡ ፬ተ፡ ዕደወ፡ ፍቱሐነ፤

ንጉሥ፡ እንዲህ፡ አለ፤ እኔ፡ የተፈቱ፡ አራት፡ ሰዎች፡ አያለሁ፤

ወያንሶስዉ፡ ማዕከለ፡ እሳት፤

በእሳት፡ መካከል፡ ይመላለሳሉ፤

ወአልቦ፡ ዘለከፎሙ፤

የለበለባቸው፡ የለም፤

ወገጹ፡ ለራብዓይ፡ ከመ፡ ወልደ፡ እግዚአብሔር፡ ይመስል፤

አራተኛውስ፡ የእግዚአብሔር፡ የባሕርይ፡ ልጁን፡ ይመስላል፤ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ አፉን፡ ጸፍቶ፡ ያናግረዋል፤ አንድም፡ ገብርኤል፡ ማለት፡ አምላክ፡ ወሰብእ፡ ማለት፡ ነውና፤ አንድም፡ ሙሴን፡ ይመስላል፤ አንድም፡ ፀሐይን፡ ይመስላል፡ አለ፤ የባለጌ፡ አነጋገር፤ ባለጌ፡ መልከ፡ መልካም፡ ያየ፡ እንደሆነ፡ የንጉሥ፡ ልጅ፡ ይመስላል፡ እንዲል፤



፺፫፤ ወእምዝ፡ ሖረ፡ ናቡከደነፆር፡ ኀበ፡ ኆኅተ፡ እሳት፡ ዘይነድድ፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ ናቡከደነፆር፡ የሚነድ፡ እሳት፡ ወደ፡ አለበት፡ ወደ፡ ዕቶን፡ እሳት፡ ደጅ፡ ሄደ፤

ወይቤ፡ ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፡ አግብርቲሁ፡ እግዚአብሔር፡ ልዑል፡ ንዑ፡ ፃዑ፤

የልዑል፡ እግዚአብሔር፡ አገልጋዮች፡ ሲድራቅ፡ ሚሳቅ፡ አብደናጎ፡ ኑ፡ ውጡ፡ አለ፤

ወወጽኡ፡ ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፡ እማዕከለ፡ እሳት፤

ሲድራቅ፡ ሚሳቅ፡ አብደናጎ፡ እንደ፡ ሳቢሳ፡ ነጭ፡ ሁነው፤ በክንፈ፡ ጸጋ፡ ብር፡ ብር፡ እያሉ፡ ከእሳቱ፡ መካከል፡ ወጡ፤

፺፬፤ ወተጋብዑ፡ መላእክት፡ ወመጋብት፡ ወመኳንንት፡ ወኃያላኒሁ፡ ለንጉሥ፤

አለቆች፡ ሹማምንቱ፤ መኳንንቱ፤ የንጉሥ፡ አርበኞች፡ ተሰበሰቡ፤

ወርእይዎሙ፡ ለእሙንቱ፡ ዕደው፤

እነዚህን፡ ሰዎች፡ አይዋቸው፤

ከመ፡ ኢቀረቦሙ፡ እሳት፡ ሥጋሆሙ፤

እሳቱ፡ ወደ፡ ሰውነታቸው፡ እንዳልቀረበ፤

ወኢለከፎሙ፡ ስእርተ፡ ርእሶሙ፤

የራሳቸውን፡ ጠጉር፡ እንዳለበለባቸው፤

ወኢተወለጠ፡ ርእየተ፡ ገጾሙ፤

መልካቸው፡ እንዳልተለወጠ፤

ወአልቦ፡ ሳዕሴሆሙ፡ ጼና፡ ዘእሳት፤

መዓዛ፡ እሳት፡ በነሳቸው፡ ላይ፡ እንደሌለ፡ አዩ፤

፺፭፤ ወሰገደ፡ ንጉሥ፡ ለእግዚአብሔር፡ በቅድሜሆሙ፤

ንጉሥ፡ ለእግዚአብሔር፡ በፊታቸው፡ ሰገደ፤

አውሥአ፡ ናቡከደነፆር፡ ወይቤ፤

ናቡከደነፆር፡ መለሰ፤ እንዲህ፡ አለ፤

ይትባረክ፡ እግዚአብሔር፡ አምላከ፡ ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፡ ዘፈነወ፡ መልአኮ፡ ወአድኃነ፡ ነፍሰ፡ አግብርቲሁ፡ እለ፡ ተወከሉ፡ ቦቱ፤

መልአኩን፡ ሰዶ፡ ያመኑበት፡ የባሮቹን፡ ሰውነት፡ ያዳነ፡ የሲድራቅ፡ የሚሳቅ፡ የአብደናጎ፡ ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር፡ ይክበር፡ ይመስገን፡ አለ፤

ወሜጡ፡ ቃለ፡ ንጉሥ፤

የንጉሥን፡ ቃል፡ የመለሱ፤ ከዚህ፡ ቀድሞ፡ ዘኢሰገደ፡ ለምስል፡ ዘወርቅ፡ ይትበርበር፡ ቤቱ፡ ወይትኰነን፡ ነፍሱ፡ ብሎ፡

www.ethiopianorthodox.org

ነበር፤ አሁን፡ ግን፣ እመቦ፡ ዘፀረፈ፡ ላዕለ፡ አምላከ፡ ሲድራቅ፡ ይትበርበር፡ ቤቱ፡ የሚል፡ ነውና፤ አንድም፡ ወሜጡ፡ ቃለ፡ ለንጉሥ፡ ይላል፤ አምላከከሂ፡ ኢናመልክ፡ ብለው፡ ለንጉሥ፡ ቃልን፡ የመለሱ፤ አንድም፡ ወሜጡ፡ ቢል፡ ኢንፈቅድ፡ ንሰ ጠውከ፡ በዝ፡ ነገር፡ ብለው፡ ለንጉሥ፡ ቃልን፡ የመለሱ፤ አን ድም፡ የጌታን፡ አምልኮቱን፡ ያጸኑ፤ አንድም፡ የጌታን፡ ቃል፡ ያስመለሱ፡ ኢታምልክ፡ ባዕደ፡ አምላከ፡ ዘእንበሌየ፡ ያለውን፣

ወወሀቡ፡ ነፍሶሙ፡ ለእሳት፡ ከመ፡ ኢያ ምልኩ፡ ወኢይስግዱ፡ ለካልዕ፡ አም ላክ፡ ዘእንበለ፡ አምላኮሙ፣

ከፈጣሪያቸው፡ በቀር፡ ለጣዖት፡ እንዳይሰግዱ፡ እንዳያመልኩ፡ ሰው ነታቸውን፡ ለእሳት፡ የሰጡ፤

፺፮፤ ወአነሂ፡ አዘዝኩ፡ ለኵሉ፡ አሕ ዛብ፡ ወነገድ፡ ወበሐውርት፣

እኔም፡ ለአሕዛብ፡ ሁሉ፡ በየነ ገዱ፡ በየሀገሩ፡ አዘዝሁ፤

እመቦ፡ ዘጸረፈ፡ ወዘነበበ፡ ሕሡመ፡ ላዕለ፡ አምላከ፡ ሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደ ናጎ፡ ይትከሠት፡ ነፍሱ፡ ወይትበርበር፡ ቤቱ፣

በሲድራቅ፡ በሚሳቅ፡ በአብደ ናጎ፡ ፈጣሪ፡ ላይ፡ ክፉ፡ ነገር፡ የተናገረ፡ ቢኖር፡ ሰውነቱ፡ ይቀጣ፡ ዘንድ፡ ቤቱ፡ ይበዘበዝ፡ ዘንድ፡ አዘዝሁ፤

እስመ፡ አልቦ፡ ካልዕ፡ አምላክ፡ ዘያድ ኅን፡ከመዝ፣

እንደዚህ፡ የሚያድን፡ ሌላ፡ ፈጣሪ፡ የለምና፤

፺፯፤ ወሶቤሃ፡ ሤሞሙ፡ ንጉሥ፡ ለሲድራቅ፡ ወሚሳቅ፡ ወአብደናጎ፡ ላዕለ፡ ግብረ፡ በሐውርተ፡ ባቢሎን፣

ያን፡ ጊዜ፡ ንጉሥ፡ በባቢሎን፡ ባሉ፡ አገሮች፡ ሥራ፡ ላይ፡ ሲድ ራቅን፡ ሚሳቅን፡ አብደናጎን፡ ቀኝ፡ አዝማችነት፣ ግራዝማች ነት፣ ከንቲባነት፡ ሾማቸው፤

ወአዕበዮሙ፡

አከበራቸው፣ አገነናቸው፤

ወአኰነኖሙ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ አይሁድ፡ እለ፡ ውስተ፡ መንግሥቱ፡ ሀለዉ፣

በሚገዛው፡ አገር፡ ባሉ፡ በአይ ሁድ፡ ላይ፡ አሠለጠናቸው፤ አን ድም፡ ኵሎ፡ አይሁደ፡ ሲል፡ ነው፤ በሚገዛው፡ አገር፡ ያሉ፡ አይሁድን፡ ሁሉ፡ አስገዛቸው፤ የሕልሙን፡ አጻፉ፡ ከዚህ፡ ይና ገሩታል፤ በሰፊ፡ ሜዳ፡ ዛፍ፡ በቅሎ፡ ኑኁ፡ (ቁመቱ) እስከ፡ ሰማይ፡ ደርሶ፣ ጫፉ፡ ጽንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ፡ ደርሶ፣ ቅጠሉ፡ ጽፍቅ፡ ሁኖ፡ ፍሬው፡ ንብብር፡



ሁኖ፣ ከበላዩ፡ አዕዋፍ፡ ተቀ ምጠውበት፤ ከበታቹ፡ አራዊት፡ ተጠግተውበት፡ አይቷል፤ ይህ ንን፡ያየበት፡ምክንያት፡ምንድር ነው፡ ቢሉ፣ አነ፡ ውእቱ፡ ዘአ ሠርቅ፡ ፀሐየ፡ ብሎ፡ ነበርና፡ ስለዚህ፡ ነው፤

፺፰፤ ይቤ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፡ ለኵሉ፡ አሕዛብ፡ ወነገድ፣

ናቡከደነፆር፡ ለአሕዛብ፡ ለነገዱ፡ ሁሉ፡ እንዲህ፡ አለ፤

ወበሐውርት፡ ወለኵሉ፡ ምድር፣

ለሀገሩ፡ ለዓለሙ፡ ሁሉ፡ እን ዲህ፡ አለ፤

ሰላም፡ ይብዛኁ፡ ለክሙ፣

ተድላ፡ ደስታ፡ ይብዛላችሁና፣

፺፱፤ ተአምረ፡ ወመንክረ፡ ዘገብረ፡ሊተ፡ እግዚአብሔር፡ ልዑል፡ አደመኒ፡ ቅድሜየ፡ እንግርክሙ፣

ልዑል፡ እግዚአብሔር፡ ያደረገ ልኝን፡ ተአምራቱን፡ ድንቅ፡ ሥራ ውን፡ በፊቴ፡ እነግራችሁ፡ ዘንድ፡ ወደድሁ፤

፻፤ እስመ፡ ዓቢይ፡ ወጽኑዕ፡ ውእቱ፡ መንግሥቱ፡ መንግሥት፡ ዘለዓለም፣

የዘለዓለም፡ የሚሆን፡ መንግ ሥቱ፡ ጽኑዕ፡ ነውና፤

ወምኵናኑኒ፡ ለትውልደ፡ ትውልድ፣

አገዛዙም፡ለልጅ፡ልጅ፡ነውና።

## ምዕራፍ፡ ፬

፩፤ አነ፡ ናቡከደነፆር፡ እንዘ፡ እት ፌሣሕ፡ በቤትየ፡ ወእጼሎ፣

እኔ፡ ናቡከደነፆር፡ በቤቴ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ አድርጌ፡ ሳለ፤

ሐለምኩ፡ ሕልመ፡ ወገረመኒ፣

ሕልም፡ አለምሁ፡ እጅግ፡ አስፈራኝ፤

፪፤ ወደንገፀኒ፡ ልብየ፡ በውስተ፡ ምስካብየ፣

በመኝታዬ፡ ሳለሁ፡ ልቡናዬ፡ ደነገጠብኝ፤

እምራእየ፡ ርእስየ፡ ተሀውከኒ፡ ሕሊናየ፣

የራሴን፡ ራእይ፡ ከማየት፡ የተ ነሣ፡ ሕሊናዬ፡ ታወከብኝ፤ አን ድም፡ ራሴ፡ ሕልም፡ ሲያይ፡ አይቼ፡ ሕሊናዬ፡ ታወከብኝ፤ አንድም፡ የራሴን፡ ጥፋት፡ አይቼ፤

፫፤ ወአነ፡ አዘዝኩ፡ ይባዑ፡ ኀቤየ፡ ኵሎሙ፡ ጠቢባነ፡ ባቢሎን፡ ከመ፡ ይን ግሩኒ፡ ፍካሬሁ፡ ለሕልምየ፣

የሕልሜን፡ ትርጓሜ፡ ይነግ ሩኝ፡ ዘንድ፡ በባቢሎን፡ ያሉ፡ አዋቆች፡ ሁሉ፡ ወደኔ፡ ይመጡ፡ ዘንድ፡ እኔ፡ አዘዝኩ፣

www.ethiopianorthodox.org

፬። ወመጽኡ፡ ሰብአ፡ ሰገል፡ ወሰብአ፡ ሥራይ፤

ጥንቆላ፡ ያላቸው፡ ሰዎች፡ ሥር፡ የሚምሱ፡ ቅጠል፡ የሚበጥሱ፡ ሰዎች።

ወማዕምራን፡ ወመፈክራን፤

አወቅን፡ አወቅን፡ የሚሉ፡ ሕልም፡ የሚተረጕሙ፡ መጡ።

ወነገርክዎሙ፡ አነ፡ ሕልምየ፡ ቅድሜሆሙ፡ ወኢያይድዑኒ፡ ፍካሬሁ፤

እኔ፡ ሕልሜን፡ በፊታቸው፡ ነገርኋቸው። ትርጓሜውን፡ አልነገሩኝም።

፭። እስከ፡ አመ፡ ቦአ፡ ዳንኤል፡ ዘስሙ፡ ብልጣሶር፡ በስመ፡ አምላኪየ፤

በፈጣሪዬ፡ ስም፡ ስሙን፡ ብልጣሶር፡ ያልሁት፡ ዳንኤል፡ እስቲገባ፡ ድረስ። አንድም፡ በስመ፡ አምላኩ፡ ይላል።

ዘመንፈስ፡ እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፡ ላዕሌሁ፤

መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ያደረበት፡ ብልጣሶር፡ እስቲገባ፡ ድረስ።

፮። ወእቤ፡ ብልጣሶር፡ መልአኮሙ፡ ለአጸይደን፤

ብልጣሶር፡ ያልሁት፡ የጠቢባን፡ አለቃ፡ ዳንኤል፡ እስቲገባ፡ ድረስ።

ወአነ፡ አእመርኩ፡ ከመ፡ መንፈሰ፡ እግዚአብሔር፡ ዲቤከ፤

መንፈስ፡ ቅዱስ፡ እንዳደረብህ፡ እኔ፡ አወቅሁ፡ አልሁት።

ወኵሉ፡ ዘኅቡዕ፡ ኢይሰዓነከ፤

የተሠወረው፡ ሁሉ፡ አይሳንህም።

ስማዕ፡ ነገረ፡ ሕልምየ፡ ዘርኢኩ፡ ወንግረኒ፡ ፍካሬሁ፤

ያየሁትን፡ የሕልሜን፡ ነገር፡ ስማ፡ ትርጓሜውን፡ ንገረኝ፡ አልሁት።

፯። ርኢኩ፡ በውስተ፡ ምስካብየ፡ ወናሁ፡ ዕፅ፡ ዓቢይ፡ በውስተ፡ ማዕከለ፡ ምድር፡ ወነዊህ፡ ጥቀ፤

ተኝቼ፡ ሳለ፡ በሰፊ፡ ሜዳ፡ እጅግ፡ ረጅም፡ የሆነ፡ ታላቅ፡ ዛፍ፡ እነሆ፡ አየሁ።

፰። ወዓቢይ፡ ዕፁ፡ ወጽኑዕ፤

ዛፉ፡ ትልቅ፡ ጽኑዕ፡ ነው።

ወበጽሐ፡ ቆሙ፡ እስከ፡ ሰማይ፡ ወአዕፁቂሁ፡ እስከ፡ አጽናፈ፡ ምድር፤

ቁመቱ፡ እስከ፡ ሰማይ፡ ደርሶ፤ ጫፉ፡ ጽንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ፡ መልቶ።

፱። ወሠናይ፡ ቆጽሉ፡ ወፍሬሁኒ፡ ብዙኅ፤

ቅጠሉ፡ ጽፍቅ፡ ፍሬው፡ ንብብር፡ ሁኖ፡ አየሁ፡ አልሁት።

ወኵሉ፡ ይሴሰይ፡ እምኔሁ፤

ሁሉ፡ ከሱ፡ ሲመገብ።



ወያጸልሉ፡ ታሕቴሁ፡ አራዊተ፡ ገዳም።

የምድረ፡ በዳ፡ አራዊት፡ ከበታቹ፡ ተጠግተውበት።

ወይነብሩ፡ ውስተ፡ አዕፁቂሁ፡ አዕዋፈ፡ ሰማይ፤

ከበላዩ፡ አዕዋፍ፡ ተቀምጠውበት።

ወእምኔሁ፡ ይበልዕ፡ ኵሉ፡ ዘሥጋ፤

ሥጋዊ፡ ደማዊ፡ ሁሉ፡ ከዚያ፡ ሲበላ፡ አየሁ፡ አልሁት።

፲። ወርኢኩ፡ በራእየ፡ ሌሊት፡ በውስተ፡ ምስካብየ፤

በመኝታዬ፡ ሳለሁ፡ ሌሊት፡ በራእይ፡ አየሁ።

ወናሁ፡ ኤር፡ ቅዱስ፡ እምሰማይ፡ ወረደ፤

ቃል፡ ቅዱስ፡ ሲል፡ ነው። አንድም፡ መልአክ፡ ቅዱስ፡ ሲል፡ ነው። እነሆ፡ መልአክ፡ ከሰማይ፡ ወረደ።

ወከልሐ፡ በኃይል፤

ቃሉን፡ አሰምቶ፡ ተናገረ።

፲፩። ወከመዝ፡ ይቤ፡ ግዝምዎ፡ ለዝንቱ፡ ዕፅ፤

ይህን፡ እንጨት፡ ቁረጡት፡ አለ።

ወምትሩ፡ አዕፁቂሁ፤

ጫፉንም፡ ቁረጡት።

ወንግፉ፡ ቈፅሎ፡ ወዝርዉ፡ ፍሬሁ፤

ቅጠሉን፡ አርግፉ። ፍሬውን፡ በትኑ፡አለኝ፡አልሁት፡አላቸው።

ወይትሐወኩ፡ አራዊት፡ ዘታሕቴሁ፡ ወአዕዋፍኒ፡ ዘውስተ፡ አዕፁቂሁ፤

ከታች፡ የተጠጉበት፡ አራዊት፡ ከላይ፡ የተቀመጡበት፡ አዕዋፍ፡ ይታወኩ፡ አለ።

፲፪። ዳዕሙ፡ ሥርዎ፡ ወጉንዶ፡ ኅድጉ፡ ውስተ፡ ምድር፤

ነገር፡ ግን፡ ሥሩን፡ ግንዱን፡ አትንኩት።

በመዋቅሕተ፡ ሐፂን፡ ወብርት።

ዕሥርዎ፡ ያለበት፡ ነው። በብረት፡ በብርት፡ ጠርቁት።

ውስተ፡ ሐመልማል፡ ዘአፍአ፡ ወበጠለ፡ ሰማይ፡ ይንበር፤

በአፍአ፡ ባለ፡ በለመለመ፡ ቅጠል፡ ውስጥ፡ በጠል፡ ተነክሮ፡ ይኑር።

ወምስለ፡ አራዊት፡ መክፈልቱ፡ ይኩን፡ ውስተ፡ ሣዕረ፡ ገዳም፤

ዕድል፡ ፈንታው፡ ከአራዊት፡ ጋር፡ በሳር፡ ውስጥ፡ ይሁን።

፲፫። ወይትወለጥ፡ ልቡ፡ እምሰብእ፡ ወልበ፡ አርዌ፡ ይትወሀቦ፤

አእምሮው፡ ከሰው፡ ይለይ። የአውሬ፡ ዕውቀት፡ ይሰጠው።

፲፬። ወጄቱ፡ ዓመት፡ የኃልፍ፡ ላዕሌሁ፡ በኵነኔ፡ ልዑል፡ ወበቃለ፡ ቅዱስ፡ ትእዛዝ፤

በመልአኩ፡ ትእዛዝ፡ በልዑል፡ በእግዚአብሔር፡ ፍርድ፡ ሰባቱ፡ ዓመት፡ በሱ፡ ላይ፡ ያልፋል።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ፡ ያእምሩ፡ ኵሉ፡ ሕያዋን፡ ከመ፡ እግዚአብሔር፡ ይኴንን፡ መንግሥተ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ወለዘፈቀደ፡ ይሁቦ፤

እግዚአብሔር፡ የሰውን፡ ሁሉ፡ መንግሥት፡ እንዲገዛ፡ ለወደደውም፡ እንዲሰጠው፡ በሕይወት፡ ሥጋ፡ ያሉ፡ ሁሉ፡ ያውቁ፡ ዘንድ፤

ወበትዕቢቱ፡ ለሰብእ፡ የኀሥሮ፤

ሰውን፡ በትዕቢቱ፡ ያዋርደዋል፤

፲፭፤ ከመዝ፡ ሕልምየ፡ ዘሐለምኩ፡ አነ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፤

እኔ፡ ናቡከደነፆር፡ ያለምሁት፡ ሕልም፡ እንዲህ፡ ነው፤

ወአንተሰ፡ ብልጣሶር፡ ንግረኒ፡ ፍካሬሁ፤

ብልጣሶር፡ አንተ፡ ግን፡ ትርጓሜውን፡ ንገረኝ፤

እስመ፡ ኵሎሙ፡ ጠቢባነ፡ መንግሥትየ፡ ስዕኑ፡ ነጊሮትየ፡ ፍካሬሁ፤

በመንግሥቴ፡ ያሉ፡ አዋቆች፡ ሁሉ፡ ትርጓሜውን፡ መናገር፡ ተስኗቸዋልና፤

ወአንተሰ፡ ዳንኤል፡ ትክል፡ ነጊሮትየ፡ ፍካሬሁ፡ እስመ፡ መንፈስ፡ እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፡ ላዕሌከ፤

መንፈስ፡ ቅዱስ፡ አድሮብሃልና፡ ዳንኤል፡ አንተ፡ ግን፡ ትርጓሜውን፡ መናገር፡ ይቻልሃል፤

፲፮፤ ወሶቤሃ፡ ዳንኤል፡ ዘስሙ፡ ብልጣሶር፡ ሐለየ፡ መጠነ፡ አሐቲ፡ ሰዓት፤

ስሙ፡ ብልጣሶር፡ የተባለ፡ ዳንኤል፡ ያን፡ ጊዜ፡ አንድ፡ ሰዓት፡ ያህል፡ አሰበ፤ ስለምን፡ ቢሉ፡ ባይገለጥለት፤ አንድም፡ እንዴት፡ እሪያ፡ ትሆናለህ፡ ብዬ፡ ልተርጉምበት፡ ብሎ፤

ወተሰጥወ፡ ብልጣሶር፡ ወይቤ፤

ብልጣሶርም፡ መለሰ፤ እንዲህ፡ አለ፤

እግዚእየ፡ ይኩን፡ ሕልምከ፡ ላዕለ፡ ጸላዕትከ፡ ወፍካሬሁኒ፡ ለፀርከ፤

ጌታዬ፡ ሕልምህ፡ በጠላቶችህ፡ ላይ፡ ይሁን፤ ትርጓሜውም፡ በጠላትህ፡ ላይ፡ ይሁን፤

፲፯፤ ዕፅ፡ ዘርኢከ፡ ዓቢይ፡ ወጽኑዕ፤

ጽኑዕ፡ ረጅም፡ ሁኖ፡ ያየኸው፡ ዛፍ፤

ወበጽሐ፡ ኑኁ፡ ሰማየ፡ ወስፍሐ፡ እስከ፡ አጽናፈ፡ ምድር፤

ቁመቱ፡ እስከ፡ ሰማይ፡ ደርሶ፡ ጫፉ፡ ከጽንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ፡ ደርሶ፡ ያየኸው፤

፲፰፤ ወቈጽሉኒ፡ ዕፉቅ፡ ወፍሬሁኒ፡ ብዙኅ፤

ቅጠሉ፡ ዕፍቅ፡ ፍሬው፡ ንብብር፡ ሁኖ፡ ያየኸው፤



ወኵሉ፡ ይሴሰይ፡ እምኔሁ፤

ሁሉ፡ ከሱ፡ ሲመገብ፡ ያየኸው፤

ወይነብሩ፡ ታሕቴሁ፡ አራዊተ፡ ገዳም፤

ከታች፡ አራዊት፡ ተጠግተውበት፤

ወያጸልሉ፡ ኀበ፡ አዕፁቂሁ፡ አዕዋፈ፡ ሰማይ፤

አዕዋፍ፡ ከላዩ፡ ላይ፡ ተቀምጠውበት፡ ያየኸው፡ ዛፍ፤

፲፱፤ አንተ፡ ውእቱ፡ ንጉሥ፡ ዘዓበይከ፡ ወጸናዕከ፡ ወፈድፈደ፡ ዕበይከ፤

ገናንነትህ፡ የበዛ፡ የፀናህ፡ የከበርህ፡ ንጉሥ፡ አንተ፡ ነህ፤

ወበጽሐ፡ እስከ፡ ሰማይ፤

ኑኁ፡ (ቁመቱ) እስከ፡ ሰማይ፡ መሆኑ፡ አንተም፡ ከሁሉ፡ በላይ፡ ነህ፤

ወኵነኔከ፡ እስከ፡ አጽናፈ፡ ምድር፤

ጫፉ፡ ጽንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ፡ መሆኑ፡ አገዛዝህ፡ ጽንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ፡ ድረስ፡ ነው፤

፳፤ ወዝኒ፡ ዘርኢከ፡ ንጉሥ፡ ኤር፡ ቅዱስ፡ ወረደ፡ እምሰማይ፡ ወይቤ፡ ግዝምዎ፡ ለዝ፡ ዕፅ፤

መልአኩ፡ ከሰማይ፡ ወርዶ፡ ይህን፡ እንጨት፡ (ዛፍ) ቁረጡት፡ ሲል፡ ንጉሥ፡ ያየኸው፤

ወዳዕሙ፡ ሥርዎ፡ ወጉንዶ፡ ኅድጉ፡ ውስተ፡ ምድር፤

ነገር፡ ግን፡ ሥሩን፡ ግንዱን፡ አትንኩት፡ ሲል፡ ያየኸው፤

ወበመዋቅሕተ፡ ሐፂን፡ ወብርት፤

ሰንሰለት፡ ብርት፡ ቸንክሩበት፡ ሲል፡ ያየኸው፤

ውስተ፡ ሐመልማል፡ ዘአፍአ፡ ይንበር፡ በጠለ፡ ሰማይ፤

ከአፍአ፡ በተገኘ፡ ከሰማይ፡ በወረደ፡ ጠል፡ ተነክሮ፡ ይኑር፡ ሲል፡ ያየኸው፤

ወምስለ፡ አራዊተ፡ ገዳም፡ መክፈልቱ፡ ይኩን፡ ወውስተ፡ ሣዕረ፡ ገዳም፡ ይትረአይ፡ እስከ፡ የኃልፍ፡ ፯ቱ፡ ዓመት፡ ላዕሌሁ፤

ሰባቱ፡ ዓመት፡ እስኪያልፍ፡ ድረስ፡ ዕድል፡ ፈንታው፡ ከአራዊት፡ ጋር፡ ይሁን፡ ሲል፡ ያየኸው፤ ወደሳርም፡ ሲሰማራ፡ ያየኸው፤

፳፩፤ ዝ፡ ውእቱ፡ ፍካሬሁ፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ ትርጓሜው፡ ይህ፡ ነው፤

ኵነኔ፡ ልዑል፡ በጽሐ፡ ለእግዚእየ፡ ንጉሥ፤

የልዑል፡ የእግዚአብሔር፡ ፍርድ፡ በጌታዬ፡ በንጉሥ፡ ደርሶብሃል፤

፳፪፤ ወይሰድዱከ፡ እምሰብእ፡ ወትነብር፡ ምስለ፡ አራዊተ፡ ገዳም፤

ከሰው፡ ለይተው፡ ይሰዱሃል፤ ከአራዊት፡ ጋር፡ ትኖራለህ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወትትረአይ፡ ሣዕረ፡ ከመ፡ ላህም፤

እንደ፡ ላም፡ ወደሳር፡ ትሰማ
ራለህ፤

ወትነብር፡ ኀበ፡ ጠለ፡ ሰማይ፤

በጠል፡ ተነክረህ፡ ትኖራለህ፤

ወ፯ቱ፡ ዓመት፡ የኀልፍ፡ ላዕሌከ፤

ሰባቱ፡ ዓመት፡ በአንተ፡ ላይ፡
ያልፋል፤

እስከ፡ ተአምር፡ ከመ፡ ልዑል፡ ይኴ
ንን፡ መንግሥተ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡
ወለዘፈቀደ፡ ይሁቦ፤

ልዑል፡ እግዚአብሔር፡ የሰውን፡
ሁሉ፡ መንግሥት፡ እንዲገዛ፡
ለወደደውም፡ እንዲሰጠው፡ እስክ
ታውቅ፡ ድረስ፤

፳፫፤ ወገዚኢ፡ ዘይቤ፡ ኅድጉ፡ ሥርዎ፡
ወጕንዶ፡ ለዕፅ፡ ውስተ፡ ምድር፤

ሥሩን፡ ግንዱን፡ በምድር፡
ተዉት፡ ያለው፤

መንግሥትከ፡ ለከ፡ ይፀንሐከ፤

በእደ፡ ዮርማሮዴቅ፡ ወልድከ፡
ያለበት፡ ነው፤ መንግሥትህ፡
በልጅህ፡ በዮርማሮዴቅ፡ እጅ፡
ይቆይሃል፤

እስከ፡ ተአምር፡ ኵነኔ፡ ዘእምሰማይ፤

ግዛት፡ የሚሰጥ፡ ከጌታ፡ እንደ
ሆነ፡ እስክታውቅ፡ ድረስ፤

፳፬፤ በእንተዝ፡ ንጉሥ፡ ያሥም
ርከ፡ ምክርየ፤

ንጉሥ፡ ስለዚህ፡ ነገር፡ ምክሬ፡
ደስ፡ ያሰኝህ፡ ማለት፡ በጀ፡ በለኝ፤

በምጽዋት፡ ወበጽድቅ፡ ትድኅን፤

በምጽዋት፡ በትሩፋት፡ ትድናለህ፤

ወኃጢአትከኒ፡ በምሒረ፡ ነዳይ፡ እስከ፡
ይሠሪ፤

ኃጢአትህ፡ ለድኃ፡ በመራራት፡
እስኪሠረይልህ፡ ድረስ፤ አን
ድም፡ ወይሠሪ፡ ለከ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ኃጢአተከ፡ ወጌጋየከ፡
ኃጢአትህን፡ በደልህን፡ እግዚ
አብሔር፡ ያሥተሰርይልሃል፤

፳፭፤ ዝ፡ ኵሉ፡ በጽሐ፡ ለናቡ
ከደነፆር፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ ይህ፡ ሁሉ፡ በአንተ፡
ደረሰብህ፤

፳፮፤ እምድኅረ፡ ፲ወ፪ ወርኅ፡
መጽአ፤

ክፉ፡ በአየሁበት፡ አገር፡ መል
ካም፡ አላይበትም፡ ብሎ፡ ዓመት፡
ከሌላ፡ አገር፡ ተቀምጧል፤
ዓመቱ፡ ካለፈ፡ በኋላ፡ መጣ፤

ወበጽሐ፡ ኀበ፡ ጽርሐ፡ መንግሥቱ፡
ዘባቢሎን፤

በባቢሎን፡ ካለ፡ ከከተማው፡
ቤት ደረሰ፤



፳፯፤ እንዘ፡ ያንሶሱ፡ ተሰጥወ፡
ንጉሥ፡ ወይቤ፤

በቤተ፡ መንግሥቱ፡ ሲመላለስ፡
ንጉሥ፡ ተናገረ፡ እንዲህ፡ አለ፤

አኮኑ፡ ዛቲ፡ ባቢሎን፡ ዓባይ፡ እንተ፡ ሐነ
ፅኩ፡ ለቤተ፡ መንግሥትየ፤

ዘውዴን፡ ቀጥቅጬ፤ ማርዳ
ዬን፡ ቆርጬ፤ ኤልካዬን፡ ሰብሬ፡
ያቀናኋት፡ ባቢሎን፡ አይደለ
ችም፤ አንድም፡ መንግሥቴን፡
ላጸናባት፤

በጽንዓ፡ ኃይልየ፤

ኃይሌን፡ ልገልጥባት፤

ወለትርሢተ፡ ክብርየ፤

ሽልማቴን፡ ላኖርባት፡ ያቀና
ኋት፡ አገር፡ አይደለችም፤ እን
ዴት፡ ለሰው፡ ወዳጅ፡ የለው፡
ዳንኤል፡ እሪያ፡ ትሆናለህ፡ ይበ
ለኝ፡ ብሎ፤

፳፰፤ እንዘ፡ ዓዲሁ፡ ቃል፡ ውስተ፡
አፈ፡ ንጉሥ፡ መጽአ፡ ቃል፡ እምሰማይ፤

አስቦ፡ ሳይናገረው፡ ተናግሮ፡
ሳይፈጽመው፡ ከሰማይ፡ ቃል፡
መጣ፤

ለከ፡ ይብለከ፡ ናቡከደነፆር፡ ንጉሥ፡
ኀለፈት፡ መንግሥትከ፡ እምኔከ፤

ናቡከደነፆር፡ መንግሥትህ፡ ከአ
ንተ፡ አለፈች፡ ይልሃል፤

፳፱፤ ወይሰድዱከ፡ እምሰብእ፡ ወት
ነብር፡ ምስለ፡ አራዊተ፡ ገዳም፤

ከሰው፡ ለይተው፡ ይሰዱሃል፡
ከአራዊት፡ ጋራ፡ ትኖራለህ፤

ወትትረአይ፡ ሣዕረ፡ ከመ፡ ላህም፤

እንደ፡ ላም፡ ወደሳር፡ ትሰማ
ራለህ፤

ወየኃልፍ፡ ላዕሌከ፡ ፯ቱ፡ ዓመት፤

ሰባቱ፡ ዓመት፡ በአንተ፡ ላይ፡
ያልፋል፤

እስከ፡ ተአምር፡ ከመ፡ ልዑል፡ ይኴ
ንን፡ መንግሥተ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡
ወለዘፈቀደ፡ ይሁቦ፤

ልዑል፡ እግዚአብሔር፡ የሰውን፡
ሁሉ፡ መንግሥት፡ እንዲገዛ፡
ለወደደውም፡ እንዲሰጠው፡ እስ
ክታውቅ፡ ድረስ፤

፴፤ ወውእተ፡ ጊዜ፡ በጽሐ፡ ለና
ቡከደነፆር፡ ዝ፡ ነገር፤

ያን፡ ጊዜ፡ በናቡከደነፆር፡ ይህ፡
ነገር፡ ደረሰበት፤

ወሰደድዎ፡ እምሰብእ፤

መልኩ፡ ቢለውጥባቸው፡ ከሰው፡
ለይተው፡ በአጥንት፡ በምር
ግት፡ እያሉ፡ አስወጥተው፡
ሰደዱት፤

ወተርእየ፡ ሣዕረ፡ ከመ፡ ላህም፤

እንደ፡ ላም፡ ወደሳር፡ ተሰማራ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወተሤረየ፡ ሥጋሁ፡ እምጠለ፡ ሰማይ፤

ሰውነቱ፡ በጠል፡ ተነከረ፤

እስከ፡ ልሕቀ፡ ስእርቱ፡ ከመ፡ ዘአን
በሳ፡ ወጽፈሪሁኒ፡ ከመ፡ ዘንስር፤

ጋማውን፡ የአንበሳ፤ ጥፍሩን፡
የንስር፡ እስቲያደርግለት፡ ድረስ፤

፴፩፤ ወእምድኅረ፡ እማንቱ፡ መዋ
ዕል፡ አነ፡ ናቡከደነፆር፡ አንሣዕኩ፡ አዕ
ይንትየ፡ ውስተ፡ ሰማይ፤

ከብዙ፡ ቀን፡ በኋላ፡ እኔ፡ ናቡ
ከደነፆር፡ አንገቴን፡ ወደ፡ ሰማይ፡
አቅንቼ፡ አየሁ፤

ወገብዓኒ፡ ልብየ፡ ወባረክዎ፡ ለልዑል፤

አእምሮዬ፡ ተመለሰልኝ፡ ልዑል፡
እግዚአብሔርን፡ አመሰገንሁት፤

ወአዕኰትክዎ፡ ለዘሕያው፡ ለዓለም፡ ወመ
ንግሥቱኒ፡ ለትውልደ፡ ትውልድ፤

አገዛዙ፡ ለዘለዓለም፡ የሚሆን፡
መንግሥቱም፡ ለልጅ፡ ልጅ፡
ጸንቶ፡ የሚኖር፡ እሱን፡ አመ
ሰገንሁት፤

፴፪፤ ወኵሎሙ፡ እለ፡ ይነብሩ፡
ውስተ፡ ምድር፡ ከመ፡ ወኢምንት፡
እሙንቱ፤

በዚህ፡ ዓለም፡ የሚኖሩ፡ ሰዎች፡
ሁሉ፡ በሱ፡ ዘንድ፡ እንደ፡ ኢም
ንት፡ ናቸው፤

ወይገብር፡ በከመ፡ ፈቀደ፡ በኃይለ፡
ሰማይ፤

በፀሐይ፤ በጨረቃ፤ አንድም፡
በመላእክት፡ የወደደውን፡ ያደ
ርጋል፤ አንድም፡ በልዑላኑ፤

ወበዘሂ፡ ይነብር፡ ዲበ፡ ምድር፤

በምድር፡ በሚኖሩ፤ በእንስሳት፡
በአራዊት፤ አንድም፡ በደቂቀ፡
አዳም፡ የወደደውን፡ ያደርጋል፤
አንድም፡ በትሑታኑ፤

ወአልቦ፡ ዘይትቃወማ፡ ለእዴሁ፤

ሥልጣኑን፡ የሚቃወማት፡
የለም፤

ወይቤሎ፡ ምንተ፡ ገበርከ፤

ምን፡ አደረግህ፡ የሚለው፡
የለም፤

፴፫፤ ይእተ፡ ጊዜ፡ ገብዓኒ፡ ልብየ፤

ያን፡ ጊዜ፡ አእምሮዬ፡ ተመለ
ሰልኝ፤

ወመጻዕኩ፡ ውስተ፡ ክብረ፡ መንግ
ሥትየ፤

ወደ፡ ክብረ፡ መንግሥቴ፡
መጣሁ፤

ወተሠውጠ፡ ሕሊናየ፡ ወራእይየ፤

ወተውህቦ፡ ልበ፡ አርዌ፡ ብሎ፡
ነበርና፡ አእምሮዬ፡ መልኬ፡
ተመለሰልኝ፤ እኔ፡ ምን፡ ዕዳዬ፡

www.ethiopianorthodox.org



ቀድሞ፡ ከሰው፡ ሁሉ፡ በላይ፡
አድርጎኝ፡ ነበረ፤ ዛሬም፡ ከአ
ራዊት፡ በላይ፡ አድርጎኛል፡
ብሎ፡ ታበየ፤ ጋማው፡ እንዲ
መለጥ፡ ጥፍሩ፡ እንዲወልቅ፡
አደረገው፤ ከዚያው፡ በአለበት፡
ንስሓ፡ ገባ፤ ዳንኤል፡ ልቡናው፡
በጸጋ፡ እንደተመለሰ፡ አውቆ፡
ሂዳችሁ፡ አምጡት፡ አላቸው፤
ቢሄዱ፡ ከዛፍ፡ ሥር፡ ቁሞ፡
አገኙት፤ መልሰው፡ አምጥተ
ውታል፤

ወኃሠሡኒ፡ መገብትየ፡ ወመላእክትየ፤

ሹማምንቱ፡ አለቆቹ፡ ፈልገው፡
አመጡኝ፤

ጸናዕኩ፡ በውስተ፡ መንግሥትየ፤

በመንግሥቴ፡ ጸናሁ፤

ወተወሰኩ፡ ዕበየ፡ ፈድፋደ፤

እጅግ፡ ገነንኩ፤ ከበርሁ፤

፴፬፤ ወይእዜኒ፡ አነ፡ ናቡከደነፆር፡
እሴብሖ፡ ወአአኵቶ፡ ለእግዚአብሔር፤

አሁንም፡ እኔ፡ ናቡከደነፆር፡
በውስጥ፡ በአፍአ፡ እግዚአብ
ሔርን፡ አመሰግነዋለሁ፤

ወአሌዕሎ፡ ለንጉሠ፡ ሰማይ፤

ሰማይን፡ የፈጠረ፡ እሱን፡ ከፍ፡
ከፍ፡ አደርገዋለሁ፤

እስመ፡ ጽድቅ፡ ኵሉ፡ ግብሩ፡ ወርቱዕ፡
ፍናዊሁ፤

ሥራው፡ ሁሉ፡ እውነት፡ ነውና፤
ይኸውም፡ ሥራው፡ የቀና፡
ነውና፤

መንግሥቱ፡ ለዘለዓለም፡ ወምኵናኑኒ፡
ለትውልደ፡ ትውልድ፤

መንግሥቱ፡ ለዘለዓለም፡ ነው፤
አገዛዙም፡ ለልጅ፡ ልጅ፡ ነው፤

ወለኵሎሙ፡ እለ፡ የሐውሩ፡ በትዕቢት፡
ይክል፡ አኅሥሮቶሙ፤

በትዕቢት፡ ጸንተው፡ የሚኖ
ሩትን፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ማዋ
ረድ፡ ይቻለዋል።

## ምዕራፍ፡ ፭

፩፤ ወብልጣሶር፡ ንጉሥ፡ ገብረ፡
ምስሐ፡ ለመገብቱ፡

ብልጣሶር፤ ለሹማምንቱ፡ ምሳ፡
አደረገ፤

ወአስተጋብአ፡ ፲ቱ፡፻፡ ብእሴ፤

ቂሮስ፡ ዳርዮስን፡ ድል፡ ነስቶ፡
ሽህ፡ መኳንንት፡ ይዞ፡ በአዳ
ራሽ፡ ተገኝ፤

ወአስተየ፡ ወይነ፡ ለ፲ቱ፡፻፡ ዕደው፤

ለሽህ፡ ሰዎች፡ ወይን፡ አጠጣ፤
ምሳ፡ አደረገ፤

፪፤ ወእንዘ፡ ይሰቲ፡ ወይነ፡ ብል ጣሶር፡ ሰኪሮ፤

ብልጣሶር፡ ወይን፡ ሲጠጣ፡ ምክንያቱ፡ ሰክሮ፡ ነው፤ ዛሬ፡ እንጂ፡ እስራኤል፡ ለቂሮስ፡ ለዳ ርዮስ፡ ረድተው፡ ሊወጉህ፡ ነበረ፡ አሉት፤ ቢረዱስ፡ ምን፡ ጐድ ተው፤ ባይረዱስ፡ ምን፡ ጠቅ መው፡ ፈጣሪያቸው፡ አያድን፤ አይራዳ፤ አይታደግ፡ ብሎ፡ አያቱ፡ ናቡከደነፆር፡ አክብሮ፡ ያኖረው፡ የነበረውን፤

ይቤ፡ ያምጽኡ፡ ንዋየ፡ ወርቅ፡ ወብሩር፡ ዘአምጽአ፡ ናቡከደነፆር፡ አቡየ፡ እምቤተ፡ መቅደስ፡ ዘኢየሩሳሌም፤

በኢየሩሳሌም፡ ካለ፡ ከቤተ፡ መቅ ደስ፡ አባቴ፡ ናቡከደነፆር፡ ያመ ጣውን፡ የወርቁን፤ የብሩን፤ ጻሕል፡ ጽዋ፡ ያምጡ፡ አለ፤ አንድም፡ ይቤ፡ አምጽኡ፤ የወር ቁን፡ የብሩን፡ ጻሕህል፡ ጽዋ፡ ያመጡ፡ ዘንድ፡ አምጡ፡ አለ፤ ስለ፡ ምን፡ ቢሉ፡ በፊት፡ ድል፡ የተነሣ፡ በኋላ፡ ድል፡ ይነሣ ልና፤ አንድም፡ የእግዚአብሔ ርን፡ ቸርነት፡ ለመናገር፡ እስ ራኤል፡ የወጡ፡ በእግዚአብ ሔር፡ ኃይል፡ ነው፡ እንጂ፡ በሰው፡ ኃይል፡ አይደለም፡ ለማለት፤

ወይስተዩ፡ ቦቱ፡ ንጉሥ፡ ወመገብቱ፡ ወአንስቲያሁ፡ ወዕቍባቲሁ፤

ንጉሥ፡ ሹማምንቱ፤ ሚስቶቹ፤ ዕቍባቱ፡ ይጠጡበት፡ ዘንድ፡ አዘዘ፤

፫፤ ወአምጽኡ፡ ንዋየ፡ ወርቅ፡ ወብ ሩር፡ ዘአውጽኡ፡ እምቤተ፡ መቅደስ፡ ዘኢየሩሳሌም፤

በኢየሩሳሌም፡ ካለ፡ ከቤተ፡ መቅደስ፡ ያወጡትን፡ የብሩን፡ የወርቁን፡ የጻሕሉን፡ ጽዋ፡ አመጡ፤

ወሰትዩ፡ ቦቱ፡ ወይነ፡ ንጉሥ፡ ወመገ ብቱ፡ ወአንስቲያሁ፡ ወዕቍባቲሁ፤

ንጉሥ፡ ሹማምንቱ፤ ሚስቶቹ፤ ዕቍባቱ፡ በጽዋው፡ ወይን፡ ጠጡ በት፤ በጻሕሉ፡ ፈትፍተው፡ በሉበት፤

፬፤ ወአእኰቱ፡ አማልክቲሆሙ፡ ዘወርቅ፡ ወዘብሩር፡ ወዘብርት፡ ወዘሐ ፂን፡ ወዘዕፅ፡ ወዘልሕኵት፤

የወርቅ፤ የብር፤ የብርት፤ የብ ረት፤ የእንጨት፤ የሸክላ፡ የሚሆኑ፡ አማልክቶቻቸውን፡ አመሰገኑ፤

፭፤ ወበይእቲ፡ ሰዓት፡ ወጽአት፡ አፅባዕተ፡ እደ፡ ሰብእ፤

በዚያች፡ ሰዓት፡ የሰው፡ እጅ፡ ጣት፡ ወጣች፤ በሰው፡ እጅ፡ አምሳል፡ ስለ፡ ታየች፡ ነው፡ እንጂ፡ የሚ[illegible]



ወጸሐፈት፡ ቅድመ፡ ኆኅት፡ ኀበ፡ ምረገ፡ ዓረፍት፡ ዘቤተ፡ ንጉሥ፤

በደጃፉ፡ አንጻር፡ ባለ፡ በንጉሡ፡ ቤት፡ ግርግዳ፡ ካለ፡ ከኖራው፡ ላይ፡ ጻፈች፤ አንድም፡ ቅድመ፡ ማኅቶት፡ ይላል፤ በመብራቱ፡ አንጻር፡ ባለ፡ ከዓምዱ፡ ላይ፡ ጻፈች፤

ወርእየ፡ ንጉሥ፡ አፅባዕተ፡ እደ፡ ሰብእ፡ እንዘ፡ ትጽሕፍ፤

ንጉሥ፡ የሰው፡ እጅ፡ ስትጽፍ፡ አይቶ፤

፮፤ ወሰቤሃ፡ ጸልመ፡ ገጹ፡ ለንጉሥ፤

ያን፡ ጊዜ፡ የንጉሥ፡ ፊቱ፡ ጠቈረ፤

ወደንገፆ፡ ልቡ፡ ወተፈትሐ፡ መሌሊተ፡ ሐቌሁ፤

ልቡ፡ ደነገጠበት፤ ወገቡ፡ ተለያየ፤

ወተጐድዐ፡ ብረኪሁ፤

ጕልበቱ፡ ብርክርክ፡ አለ፤

፯፤ ወዓውየወ፡ ንጉሥ፡ በቃሉ፤

ንጉሥ፡ ቃሉን፡ አሰምቶ፡ ተናገረ፤

ከመ፡ ያምጽኡ፡ ሎቱ፡ መሠርያነ፤

ሥር፡ የሚምሱ፤ ቅጠል፡ የሚበጥሱ፤

ወሰብአ፡ ሰገል፤

ጥበብ፡ ያላቸውን፡ ሰዎች፡ ያመ [illegible]ት፡ ዘንድ፤

ወይቤሎሙ፡ ለጠቢባነ፡ ባቢሎን፤

ጠቢባን፡ ባቢሎንን፡ እንዲህ፡ አላቸው፤

ዘአንበቦ፡ ለዝንቱ፡ መጽሐፍ፡ ወነገረኒ፡ ፍካሬሁ፡ አለብሶ፡ ሜላተ፤

ይህን፡ መጽሐፍ፡ አንብቦ፤ ተር ጕሞ፡ የነገረኝን፡ ነጭ፡ ሐር፡ አለብሰዋለሁ፤

ወአዓንቆ፡ ባዝግና፡ ወርቅ፡ ውስተ፡ ክሣዱ፤

በአንገቱም፡ ዝርግፍ፡ ወርቅ፡ አሥርለታለሁ፤

ወእሠይሞ፡ መኰንነ፡ በውስተ፡ ሣል ስተ፡ እደ፡ መንግሥትየ፤

የመንግሥቴን፡ ሲሶ፡ እሰጠዋ ለሁ፤ አንድም፡ ቢትወደድ፡ አድ ርጌ፡ እሾመዋለሁ፤

፰፤ ወቦኡ፡ ኵሎሙ፡ ጠቢባነ፡ ባቢሎን፤

በባቢሎን፡ ያሉ፡ አዋቆች፡ ሁሉ፡ ገቡ፤

ወስዕኑ፡ አንብቦ፡ መጽሐፍ፤

መጽሐፉን፡ ማንበብ፡ ተሳናቸው፤

ወፍካሬሁኒ፡ ኢነገርዎ፡ ለንጉሥ፤

ትርጓሜውንም፡ ለንጉሥ፡ አል ነገሩትም፤

፱፤ ወደንገፀ፡ ብልጣሶር፡ ንጉሥ፡ ወጸልመ፡ ገጹ፤

እስከ፤ አሁን፡ ድረስ፡ ካህናቱ፡ ይነግሩኛል፡ ብሎ፡ ተስፋ፡ ነበ

www.ethiopianorthodox.org

ረው፤ ንባቡም፣ ትርጓሜውም፡ ቢጠፋው፡ ብልጣሶር፡ ፊጽሞ፡ ደነገጠ፤ ፊቱ፡ ጠቈረ፤

ወደንገፁ፡ መገብቱሂ፣

ሹማምንቱም፡ ደነገጡ፤

፲፤ ወቦአት፡ ንግሥት፡ ቤተ፡ ምሳሕ፣

ንግሥት፡ ያላት፡ የናቡከደነፆር፡ ሚስት፡ የዮርማሮዴቅ፡ እናት፡ የብልጣሶር፡ አያት፡ ናት፤ ከውጭ፡ ዛሬ፡ ልጁ፡ ምሳ፡ አድርጎ፡ ነበረ፤ ምሳው፡ ቀና ለት፡ ይሆን፡ ብላ፡ ጠየቀች፣ ምሳውስ፡ ቀንቶለት፡ ነበረ፣ ነገር፡ ግን፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ አይቶ፡ አዝኗል፤ ብለው፡ ነገ ሯት፤ ለዚህማ፡ ለአባቱ፡ ለና ቡከደነፆር፡ ርእሱ፡ ዘወርቅን፡ የተረጐመለት፡ ዳንኤል፡ ያለ፡ አይደለም፡ ብላ፡ ሴት፡ ፈጣን፡ ናትና፡ ቀሚሷን፡ አንጠልጥላ፡ (ሰብስባ) ከአደራሹ፡ ገባች፤

ወትቤሎ፡ ለንጉሥ፡ ለዓለም፡ ሕየው፣

ንጉሥ፡ ሽህ፡ ዓመት፡ ያንግ ሥህ፡ አለችው፤ አንድም፡ ወንድ፡ ልጅ፡ ለፈረስ፣ ሴት፡ ልጅ፡ ለበርኖስ፡ የምታደርስ፡ ያድርግህ፡ አለችው፤

ኢይደንግፅከ፡ ልብከ፡ ወኢይጽልም፡ ገጽከ፣

ልብህ፡ አይደንግጥ፡ ፊትህ፡ አይጥቆር፤

፲፩፤ ሀሎ፡ ፩ዱ፡ ብእሲ፡ ውስተ፡ መንግሥትከ፡ ዘቦ፡ ላዕሌሁ፡ መንፈስ፡ እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፣

በምትገዛው፡ ሀገር፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ያደረበት፡ አንድ፡ ሰው፡ አለ፤

ወበመዋዕለ፡ አቡከኒ፡ ተረክበ፡ ላዕ ሌሁ፡ ጥበብ፣

በአባትህም፡ ዘመን፡ ጥበብ፡ ከሱ፡ ተገኝቷል፤

ወነገሮ፡ ሕልሞ፡ ወፍካሬሁ፣

ሕልሙንም፡ ትርጓሜውንም፡ ነግሮታል፤

ወሤሞ፡ ንጉሥ፡ ናቡከደነፆር፡ አቡከ፡ መልአከ፡ ጠቢባን፡ ወማዕምራን፣

አዋቆች፡ ብልሆች፡ ነን፡ በሚሉ፡ ላይ፡ አለቃ፡ አድርጎ፡ ሹሞት፡ ነበር፤

ወሰብአ፡ ሰገል፣

ጥበብ፡ ባላቸው፡ ሰዎች፤

ወሰብአ፡ ሥራይ፣

ሥር፡ በሚምሱ፡ ቅጠል፡ በሚ በጥሱ፣ ሰዎች፡ ላይ፡ ሹሞት፡ ነበር፤



፲፪፤ እስመ፡ ፈድፈደ፡ መንፈስ፡ ዘላዕሌሁ፣

በሱ፡ ላይ፡ ያለ፡ ዕውቀት፡ በዝ ቷልና፤

ወጥበብ፡ ዘውስተ፡ ፍካሬ፡ ሕልም፤

ሕልም፡ የመተርጐም፡ ጥበብ፡ በዝቶለታልና፤

ወይነግር፡ ዘኅቡዕ፣

ንባቡን፣

ወይፌትሕ፡ ዘሥውር፣

ትርጓሜውን፡ ይናገራል፤

ዝውእቱ፡ ዳንኤል፣

ይህም፡ ዳንኤል፡ ነው፤

ወንጉሥ፡ ሰመዮ፡ ብልጣሶር፣

ንጉሥ፡ ስሙን፡ ብልጣሶር፡ ብሎታል፤

ወይእዜኒ፡ ለአክ፡ ይጸውዕዎ፡ ለከ፣

ከሱ፡ በቀር፡ ሌላ፡ የሚተረጐ ምልህ፡ የለምና፡ አሁንም፡ ይጠ ሩልህ፡ ዘንድ፡ እዘዝ፡ አለችው፤

ወይነግረከ፡ ፍካሬሁ፣

ትርጓሜውን፡ ይነግርሃል፤

፲፫፤ ወሶቤሃ፡ ጸውእዎ፡ ወቦአ፡ ዳንኤል፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፣

ያን፡ ጊዜ፡ ጠሩትና፡ ዳንኤል፡ በንጉሥ፡ ፊት፡ ገባ፤

ወይቤሎ፡ ንጉሥ፡ ለዳንኤል፣

ንጉሥ፡ ዳንኤልን፡ እንዲህ፡ አለው፤

አንተኑ፡ ዳንኤል፡ ዘእምደቂቀ፡ ዴዋ፡ ይሁዳ፡ ዘአምጽአ፡ ንጉሥ፡ እምይሁዳ፣

ያውቀዋል፡ ቢሉ፡ አባቴ፡ ከይሁዳ፡ ካመጣው፡ ምርኮ፡ ልጆች፡ ወገን፡ የምትሆን፡ ዳንኤል፡ አንተ፡ ነህን፡ አለው፤ አንድም፡ አያ ውቀውም፡ ቢሉ፡ ዳንኤል፡ የም ትባል፡ አንተ፡ ነህን፡ አለው፤

፲፬፤ ሰማዕኩ፡ በእንቲአከ፡ ከመ፡ መንፈስ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕሌከ፣

መንፈስ፡ ቅዱስ፡ እንዳደረብህ፡ የአንተን፡ ነገር፡ ሰምቻለሁ፤

ጥበብ፡ ወምክር፡ ወፍካሬ፡ ፈድፋደ፡ ተረክበ፡ ላዕሌከ፣

ጥበብ፡ ምክር፡ ትርጓሜ፡ ከሁሉ፡ ይልቅ፡ ከአንተ፡ እንደተገኘ፡ ሰምቻለሁ፤

፲፭፤ ወይእዜኒ፡ ቦኡ፡ ቅድሜየ፡ ጠቢባን፣

አሁንም፡ ብልሆች፤

ወሰብአ፡ ሰገል፣

ጥበብ፡ ያላቸው፤

ወማዕምራን፣

አዋቆች፤

www.ethiopianorthodox.org

ያንብቡ፡ ዘ፡ መጽሐፈ፡ ወያይድዑኒ፡ ፍካሬሁ፤

ይህን፡ መጽሐፍ፡ አንብበው፡ ትርጓሜውን፡ ይነግሩኝ፡ ዘንድ፡ በፊቴ፡ ገብተው፡ ነበር፤

ወስዕኑ፡ አንብቦቶ፡ ወፍካሬሁ፤

አንብቦ፡ መተርጐም፡ ተሳናቸው፤ ንባቡ፡ በዕብራይስጥ፤ ትርጓሜው፡ በሱርስት፡ ነውና፤

፲፮፤ ወሰማዕኩ፡ አነ፡ በእንቲአከ፡ ከመ፡ ትክል፡ ፈክሮ፤

መተርጐም፡ እንዲቻልህ፡ እኔ፡ ያንተን፡ ነገር፡ ሰማሁ፤

ወይእዜኒ፡ እመ፡ ክህልከ፡ አንብቦቶ፡ ለዝንቱ፡ መጽሐፍ፡ ወአይዳዕከኒ፡ ፍካሬሁ፡ ሜላተ፡ አለብሰከ፤

አሁንም፡ ይህን፡ መጽሐፍ፡ ማንበብ፡ ቢቻልህ፡ ትርጓሜውን፡ ብትነግረኝ፡ ኩፋር፡ አለብስሃለሁ፤

ወአዓንቀከ፡ ቃማ፡ ወርቅ፡ ውስተ፡ ክሣድከ፤

ዝርግፍ፡ ወርቅ፡ በአንገትህ፡ አሥርልሃለሁ፤

ወትኴንን፡ ሣልስተ፡ እደ፡ መንግሥትየ፤

የመንግሥቴን፡ ሲሶ፡ ትገዛለህ፤

፲፯፤ ወይቤ፡ ዳንኤል፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፤

ዳንኤል፡ በንጉሥ፡ ፊት፡ እንዲህ፡ አለ፤

ሀብትከኒ፡ ለከ፡ ይኩንከ፤

የገንዘብ፡ ፍቅር፡ የለውምና፡ ገንዘቡ፡ ለአንተ፡ ይሁን፡ አለ፤

ወፍተ፡ መንግሥትከሂ፡ ሀብ፡ ለባዕድ፤

የሹመትም፡ ፈቲው፡ የለውምና፡ ሹመቱን፡ ለሌላ፡ ስጥ፤

ወአነ፡ አነብቦ፡ ለዝንቱ፡ መጽሐፍ፡ ወእነግረከ፡ ፍካሬሁ፤

እኔ፡ ይህን፡ መጽሐፍ፡ አንብቤ፡ ትርጓሜውን፡ እነግርሃለሁ፤

፲፰፤ ኦ፡ ንጉሥ፡ እግዚአብሔር፡ ልዑል፡ ወሀቦ፡ መንግሥተ፡ ወክብረ፡ ወዕበየ፡ ወግርማ፡ ለናቡከደነፆር፡ አቡከ፤

ንጉሥ፡ ልዑል፡ እግዚአብሔር፡ መንግሥትን፤ ክብርን፤ ገናንነትን፤ መፈራትን፡ ለአባትህ፡ ለናቡከደነፆር፡ ሰጥቶት፡ ነበር፤

፲፱፤ ወእምነ፡ ዕበዩ፡ ዘወሀቦ፤

ከሰጠውም፡ ከገናንነቱ፡ የተነሣ፤

ኵሉ፡ አሕዛብ፡ ወበሐውርት፡ ወሕዝብ፡ ይርዕዱ፡ እምኔሁ፤

ሕዝቡ፡ አሕዛቡም፡ አገሩ፡ ሁሉ፡ ከሱ፡ የተነሣ፡ ይርዱ፡ ይንቀጠቀጡ፡ ነበር፤



ወይፈርሁ፡ እምቅድመ፡ ገጹ፤

ከፊቱ፡ የተነሣ፡ ይፈሩ፡ ነበር፤

ዘፈቀደ፡ ይቀትል፤

ሊገድለው፡ የወደደውን፡ ይገድል፡ ነበር፤

ወዘፈቀደ፡ ይቀሥፍ፤

ሊገርፈው፡ የወደደውን፡ ይገርፍ፡ ነበር፤

ወዘፈቀደ፡ ያከብር፤

ሊያከብረው፡ የወደደውን፡ ያከብር፡ ነበር፤

ወዘፈቀደ፡ የኀሥር፤

ሊያዋርደው፡ የወደደውን፡ ያዋርድ፡ ነበር፤

፳፤ ወአመ፡ አዕበየ፡ ልቦ፡ ወአጽንዐ፡ ነፍሶ፡ ከመ፡ ይትዓበይ፤

ይታበይ፡ ዘንድ፡ ሰውነቱን፡ በአጸና፤ ልቡናውን፡ በአስታበየ፡ ጊዜ፤

ወድቀ፡ እምዕበየ፡ መንግሥቱ፡ ወኃሥረ፡ እምክብሩ፤

ከገናንነቱ፡ ተለየ፤ ከክብሩ፡ ተዋረደ፤

፳፩፤ ወተሰደ፡ እምሰብእ፤

ከሰው፡ ተለይቶ፡ ሄደ፤

ወነበረ፡ ምስለ፡ ሐለስትዮታት፤

ከምድረ፡ በዳ፡ አህያዎች፡ ጋር፡ ኖረ፤ ከጠጣ፡ ከዝንጀሮዎች፡ ጋር፤

ወተርእየ፡ ሣዕረ፡ ከመ፡ ላህም፤

እንደ፡ ላም፡ ወደሳር፡ ተሰማራ፤

ወተሴረየ፡ ነፍስቱ፡ እምጠለ፡ ሰማይ፤

ሰውነቱ፡ በጠል፡ (በጤዛ)፡ ተነክሮ፡ ኖረ፤

እስከ፡ አእመረ፡ ከመ፡ ልዑል፡ ይኴንን፡ መንግሥተ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ወለዘፈቀደ፡ ይሁብ፤

ልዑል፡ እግዚአብሔር፡ የሰውን፡ መንግሥት፡ እንዲገዛ፡ ለወደደውም፡ እንዲሰጠው፡ እስቲያውቅ፡ ድረስ፤

፳፪፤ ወአንተኒ፡ ወልዱ፡ ብልጣሶር፡ ኢያትሐትከ፡ ልበከ፡ ቅድመ፡ እግዚአብሔር፤

የአራኙ፡ ልጅ፡ አጥባቂ፤ የዓባያ፡ ልጅ፡ ወዳቂ፤ የመጋዣ፡ ልጅ፡ አውላቂ፤ የትዕቢተኛ፡ ልጅ፡ ናቂ፡ እንዲሉ፤ አንተም፡ ልጁ፡ ብልጣሶር፡ ልቡናህን፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ አላወረድህም፤

ወዘንተ፡ ኵሎ፡ ኢያእመርከ፤

ይህን፡ ሁሉ፡ አላወቅህም፤

፳፫፤ ወተዓበይከ፡ ላዕለ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክከ፡ አምላከ፡ ሰማይ፤

ሰማይን፡ በፈጠረ፡ በፈጣሪህ፡ በእግዚአብሔር፡ ላይ፡ ታበይህ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወንዋየ፡ ቤቱ፡ አምጻእከ፡ ቅድሜከ፤

ንዋየ፡ ቅድሳቱን፤ ጻሕሉን፤ ጽዋውን፡ በፊትህ፡ አመጣህ፤

አንተ፡ ወመገብትከ፡ ወአንስቲያከ፡ ወዕቁባቲከ፡ ሰተይክሙ፡ ቦቱ፡ ወይነ፤

አንተ፡ ሹሞችህ፤ ሚስቶችህ፤ ዕቁባቶችህ፡ በጽዋው፡ ወይኑን፡ ቀድታችሁ፡ ጠጣችሁበት፤

ወአማልክቲከ፡ ዘወርቅ፡ ወዘብሩር፡ ወብርት፡ ወዘሐዊን፡ ወዕፅ፡ ወዕብን፤

የወርቅ፡ የብር፡ የብርት፡ የብረት፡ የእንጨት፡ የደንጋይ፡ የሚሆኑ፤

እለ፡ ኢይሰምዑ፡ ወኢይሬዕዩ፡ ወኢየአምሩ፡ አእኰትከ፤

የማይሰሙ፤ የማያዩ፤ የማያውቁ፡ ጣዖቶችህን፡ አመሰገንህ፤

ወለእግዚአብሔርሰ፡ ዘውስተ፡ እዴሁ፡ መንፈስከ፡ ወኵሉ፡ ፍናዊከ፡ ኢያዕኰትኮ፤

ሥራህ፡ ሰውነትህ፡ በእጁ፡ የተያዘ፡ እግዚአብሔርን፡ ግን፡ አላመሰገንኸውም፤

፳፬፤ ወበእንተዝ፡ እምኀቤሁ፡ ፈነወ፡ አፅባዕተ፡ እድ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ከሱ፡ ዘንድ፡ የመልእኩን፡ እጅ፡ ሰደደ፤

፳፭፤ ወዝ፡ መጽሐፍ፡ ዘተአዘዘ፡ ማኔ፡ ቴቄል፡ ፋሬስ፤

ዘተጽሕፈ፡ ሲል፡ ነው፤ የተጻፈውም፡ መጽሐፍ፡ ማኔ፡ ቴቄል፡ ፋሬስ፡ የሚል፡ ነው፤

፳፮፤ ወከመዝ፡ ፍካሬሁ፡ ማኔ፡ ብሂል፡ ሰፈራ፡ እግዚአብሔር፡ ለመንግሥትከ፡ ወሠለጣ፤

ትርጓሜውም፡ እንዲህ፡ ነው፤ ማኔ፡ ማለት፡ እግዚአብሔር፡ መንግሥትህን፡ ጨርሶ፡ ሰፈራት፡ ማለት፡ ነው፤ ላዳን፡ ከመላ፡ በኋላ፡ እንዳያክል፡ እንግዲህ፡ ወዲህ፡ መንግሥትህ፡ አታክልም፤

፳፯፤ ቴቄል፡ ደለዋ፡ በመዳልው፡ ወተረክበት፡ ሕፅፅተ፤

ቴቄል፡ ማለት፡ በሚዛን፡ መዘናት፤ ሻ፡ ብላ፡ ጐድላ፡ ተገኘች፡ ማለት፡ ነው፤ አንድም፡ በልቡና፡ መረመራት፤ ከሕግ፡ ከሥርዓት፡ ወጣች፡ ማለት፡ ነው፤

፳፰፤ ፋሬስ፡ ተሥዕረት፡ መንግሥትከ፡ ወተውህበት፡ ለሜዶን፡ ወፋርስ፤

ፋሬስ፡ ማለት፡ መንግሥትህ፡ አለፈች፡ ለፋርስ፡ ለሜዶን፡ ተሰጠች፡ ማለት፡ ነው፤

፳፱፤ ወአዘዘ፡ ብልጣሶር፡ ያልብስዎ፡ ሜላተ፡ ለዳንኤል፡ ወአልበስዎ፤

ምንም፡ ክፉ፡ ቢተረጉምበት፡ አሕዛብ፡ መሐላቸውን፡ አጥኝ፡ ናቸውና፡ ብልጣሶር፡ ዳንኤልን፡



ኩፋር፡ ያለብሱት፡ ዘንድ፡ አዘዘ፤ አለበሱት፤

ወአዕነቅዎ፡ ቃማ፡ ወርቅ፡ ዲበ፡ ክሣዱ፤

ዝርግፍ፡ ወርቅ፡ በአንገቱ፡ አሠሩለት፤

ወሰበኩ፡ ሎቱ፡ ከመ፡ ይኩን፡ ሣልስተ፡ እደ፡ መንግሥቱ፤

የመንግሥቱ፡ ሲሶ፡ ለሱ፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ አዋጅ፡ ነገሩለት፤

፴፤ ወበይእቲ፡ ሌሊት፡ ሞተ፡ ብልጣሶር፡ ንጉሠ፡ ከላውዴዎን፤

የከላውዴዎን፡ ንጉሥ፡ ብልጣሶር፡ በዚያች፡ ሌሊት፡ ሞተ፤ ሲበጻበጽበት፡ የዋለው፡ ጠጅ፡ መልከኛው፤ አንድም፡ ሹመቱን፡ ለዳንኤል፡ የሰጠበት፤ አንድም፡ ዳንኤል፡ ሲተረጉምለት፡ የሰማ፡ ሌላ፡ ከሚመሰገንበት፡ እኔ፡ ልመስገንበት፡ ብሎ፡ ቸብቸቦውን፡ ቆርጦ፡ በሳር፡ ጠቅሎ፡ ወስዶ፡ ለቂሮስ፡ ለዳርዮስ፡ ሰጥቷቸዋል፤

፴፩፤ ወዳርዮስ፡ ሜዶናዊ፡ ነግሠ፡ ህየንቴሁ፡ እንዘ፡ ፷ወ፪ቱ፡ ክረምቱ፤

የሜዶን፡ ሰው፡ ዳርዮስ፡ ስለሱ፡ ፈንታ፡ በስልሳ፡ ሁለት፡ ዘመኑ፡ ነገሠ፤ ይኸውም፡ የእግዚአብሔር፡ ቸርነቱ፡ ነው፤ የስልሳ፡ ሁለት፡ ዘመን፡ ሳለ፡ የሠላሳ፡ አንድ፡ ዘመን፡ ጉልማሳ፡ ብልጣሶርን፡ ገደለ፡ ለማለት፡፡

## ምዕራፍ፡ ፮

፩፤ ወአደሞ፡ ዳንኤል፡ በቅድሜሁ፡ ለዳርዮስ፤

ዳንኤል፡ ዳርዮስን፡ በፊቱ፡ ደስ፡ አሰኘው፤

ወሤመ፡ በውስተ፡ መንግሥቱ፡ ፻ወ፳፡ መሳፍንተ፡ ከመ፡ የሀልዉ፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ መንግሥቱ፤

ዳርዮስ፡ በሚገዛው፡ አገር፡ ሁሉ፡ ይኖሩ፡ ዘንድ፡ በሚገዛው፡ አገር፡ መቶ፡ ሃያ፡ መሳፍንት፡ ሾመ፤ አንድም፡ እሥራ፡ ባለው፡ ሃምሳ፡ ይላል፤

፪፤ ወእለ፡ ይትሌዓሉ፡ እምኔሆሙ፡ ፫ቱ፡ ነገሥት፤

ከነዚህም፡ የሚበልጡት፡ ሦስቱ፡ ነገሥታት፡ ናቸው፤

ወ፩ዱ፡ እምኔሆሙ፡ ዳንኤል፡ ከመ፡ ኀቤሁ፡ ያግብዑ፡ ነገሥት፡ ናሥታ፤

ነገሥታቱ፡ ይግባኙን፡ ወደሱ፡ ያቀርቡ፡ ዘንድ፡ ከነዚህም፡ አንዱ፡ ዳንኤል፡ ነው፤

ወኢያጽሕብዎ፡ ለንጉሥ፡ ወኢበምንትኒ፤

በማናቸውም፡ ነገር፡ ንጉሡን፡ እንዳይዘበዝቡት፤

፫፤ ወዳንኤል፡ የዓቢ፡ እምኔሆሙ፤

ከነዚህም፡ ዳንኤል፡ ይበልጣል፤

እስመ፡ ፈድፋደ፡ መንፈስ፡ ዘላዕሌሁ፤

በሱ፡ ላይ፡ ያለው፡ እውቀት፡ በዝቷልና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወሤሞ፡ ንጉሥ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ መንግሥቱ፤

ንጉሥ፡ በሚገዛው፡ አገር፡ ሁሉ፡ ሾመው፤

፬፤ ወኃሠሡ፡ ሎቱ፡ ምክንያተ፡ ለዳንኤል፡ መገብት፡ ወመኳንንት፡ በዘያስተዋድይዎ፤

በሚያጣሉት፡ ገንዘብ፡ ሹማምንቱ፡ መኳንንቱ፡ ለዳንኤል፡ ምክንያት፡ ፈለጉለት፤

ወኢረከቡ፡ ምክንያተ፡ ለዳንኤል፡ ወኢምንተኒ፡ ወኢጌጋየ፡ እስመ፡ ምዕመን፡ ውእቱ፤

የታመነ፡ ነውና፡ ለዳንኤል፡ ምንም፡ ምን፡ ምክንያት፡ በደል፡ አላገኙበትም፤

፭፤ ወይቤሉ፡ መገብት፡ ኢንረክብ፡ ሎቱ፡ ምክንያተ፡ ለዳንኤል፡ ዘእንበለ፡ በሕገ፡ አምላኩ፤

ሹማምንቱ፡ ከፈጣሪው፡ ሕግ፡ በቀር፡ ለዳንኤል፡ ሌላ፡ ምክንያት፡ አናገኝለትም፡ አሉ፤

፮፤ ወእምዝ፡ ተጋብኡ፡ መገብት፡ ወመኳንንት፡ ኀበ፡ ንጉሥ፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ ሹማምንቱ፡ መኳንንቱ፡ ከንጉሥ፡ ዘንድ፡ ተሰበሰቡ፤

ወይቤልዎ፡ ሕየው፡ ንጉሥ፡ ዳርዮስ፡ ለዓለም፤

ንጉሥ፡ ሺህ፡ ዓመት፡ ያንግሥህ፡ አሉት፤

፯፤ ወተማከሩ፡ ምክረ፡ መላእክት፡ ወመሳፍንት፡ ወመገብት፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ውስተ፡ መንግሥትከ፤

በምትገዛው፡ አገር፡ ያሉ፡ አዋቆች፡ መሳፍንቱ፡ ሹማምንቱ፡ ሁሉ፡ ምክርን፡ ተማከሩ፤

ወዓደሙ፡ ዕድሜ፡ ከመ፡ አልቦ፡ ዘይስእል፡ ኀበ፡ ኵሉ፡ አማልክት፡ ወሰብእ፡ እስከ፡ ሠሉስ፡ ዕለት፤

እስከ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ድረስ፡ ከጣዖታቱም፡ ከሰውም፡ ዘንድ፡ የሚለምን፡ እንዳይኖር፡ ቀን፡ ቀጠሩ፤

ዘእንበለ፡ ኀቤከ፡ ንጉሥ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ መንግሥትከ፤

ንጉሥ፡ በምትገዛው፡ አገር፡ ሁሉ፡ ስምዓኒ፡ ዳርዮስ፡ ስምዓኒ፡ ዳርዮስ፡ ከማለት፡ በቀር፤

ወእመ፡ አኮ፡ ይደይዎ፡ ውስተ፡ ግበ፡ አናብስት፤

ከሌላ፡ ግን፡ ቢለምን፡ ከአንበሳ፡ ጉድጓድ፡ ይጥሉት፡ ዘንድ፡ ቀጠሩ፤

፰፤ ይእዜኒ፡ ንጉሥ፡ አዝዝ፡ ዕድሜ፤

አሁንም፡ ንጉሥ፡ ቀን፡ ቅጠር፤

ወጸሐፍ፡ ከመ፡ ኢይዕበዩ፡ ፋርስ፡ ወሜዶን፡ ሥርዓተከ፤

የፋርስ፡ የሜዶን፡ ሰዎች፡ ሥርዓትህን፡ እምቢ፡ እንዳይሉ፡ ጻፍ፤

፱፤ ወሶቤሃ፡ አዘዘ፡ ዳርዮስ፡ ይጽሐፉ፡ ዘንተ፡ ሥርዓተ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ዳርዮስ፡ ይህን፡ ሥርዓት፡ ይጽፉ፡ ዘንድ፡ አዘዘ፤



፲፤ ወአእሚሮ፡ ዳንኤል፡ ከመ፡ ተአዘዘ፡ ዝንቱ፡ ሥርዓት፡ ቦአ፡ ቤቶ፤

ዳንኤል፡ ይህ፡ ሥርዓት፡ እንደ ታዘዘ፡ አውቆ፡ ወደቤቱ፡ ገባ፤

ወአርኃወ፡ መሳክወ፡ ጽርሑ፡ አንፃረ፡ ኢየሩሳሌም፡ በጊዜ፡ ፫ቱ፡ ሰዓት፡ ዘዕለት፡ ሰገደ፤

በኢየሩሳሌም፡ አንፃር፡ ያለ፡ የቤቱን፡ መስኮት፡ ከፍቶ፡ ከቀኑ፡ በሦስተኛው፡ ሰዓት፡ ሰገደ፤ አንድም፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ ሰገደ፤

ጸለየ፡ ወተጋነየ፡ ለእግዚአብሔር፡ በከመ፡ ያለምድ፡ ቅድመ፤

ቀድሞ፡ እንደ፡ አስለመደ፡ እግዚአብሔርን፡ ለመነ፤

፲፩፤ ወለዓይኒ፡ ግብር፡ ያስተሐይዕዎ፡ ዘልፈ፡ እሙንቱ፡ ዕደው፤

እኒህ፡ ሰዎች፡ በማናቸውም፡ ሥራ፡ ይመለከቱት፡ ነበረ፤

ወረከብዎ፡ ለዳንኤል፡ እንዘ፡ ያስተበቍዖ፡ ለአምላኩ፡ ወይጼሊ፤

ዳንኤልን፡ ፈጣሪውን፡ እየለመነ፡ ሲጸልይ፡ አገኙት፤

፲፪፤ ወሖሩ፡ ወይቤልዎ፡ ለንጉሥ፡ አኮኑ፡ አንተ፡ አደምከ፡ ከመ፡ ኢይስዓል፡ ኵሉ፡ ሰብእ፡ ኀበ፡ ኵሉ፡ አማልክት፡ ወሰብእ፡ እስከ፡ ሠላስ፡ ዕለት፤

ሄደው፡ ንጉሥን፡ እንዲህ፡ አሉት፤ ሰው፡ ሁሉ፡ እስከ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ድረስ፡ ከሰውም፤ ከጣዖታቱም፡ ሁሉ፡ እንዳይለምን፡ ቀን፡ ቀጥረህ፡ አልነበረምን፤

ዘእንበለ፡ ኀቤከ፡ ንጉሥ፤

ስምዓኒ፡ ዳርዮስ፡ ስምዓኒ፡ ዳርዮስ፡ ከማለት፡ በቀር፤

እመቦ፡ ዘተረክበ፡ ይደይዎ፡ ውስተ፡ ግበ፡ አናብስት፤

ከሌላ፡ ሲለምን፡ ቢገኝ፡ በአንበሳ፡ ጉድጓድ፡ ይጥሉት፡ ዘንድ፡ ቀን፡ ቀጥረህ፡ አልነበረምን፤

ወይቤ፡ ንጉሥ፡ እሙን፡ ዝነገር፤

ንጉሥ፡ ይህ፡ ነገር፡ እውነት፡ ነው፡ አለ፤

ወኢይትነሠት፡ ሥርዓተ፡ ፋርስ፡ ወሜዶን፤

የፋርስ፡ የሜዶን፡ ሥርዓት፡ አይፈርስም፤ አንድም፡ ቃሎሙ፡ ለፋርስ፡ ወሜዶን፡ ይላል፤ የፋርስ፡ የሜዶን፡ ሰዎች፡ ነገራቸው፡ አይፈርስም፤

፲፫፤ ወአውሥኡ፡ ወይቤሉ፡ ቅድመ፡ ንጉሥ፤

በንጉሥ፡ ፊት፡ መለሱ፡ እንዲህ፡ አሉ፤

ናሁ፡ ዳንኤል፡ ዘእምደቂቀ፡ ፄዋ፡ ይሁዳ፡ ዓበየ፡ ወኢሰምዓ፡ ትእዛዘከ፤

እነሆ፡ ከይሁዳ፡ ምርኮኞች፡ ልጆች፡ ወገን፡ የሚሆን፡ ዳንኤል፡ እምቢ፡ አለ፡ ትእዛዝህን፡ አልሰማም፤

ወጊዜ፡ ፫ቱ፡ ሰዓት፡ ዘዕለት፡ ሰአለ፡ ኀበ፡ አምላኩ፡ ስዕለቶ፤

ከቀኑም፡ በሦስተኛው፡ ሰዓት፡ ወደ፡ ፈጣሪው፡ ልመናውን፡ አቀረበ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፤ ወሰሚዖ፡ ንጉሥ፡ ዘንተ፡ ነገረ፡ ተከዘ፡ ጥቀ፤

ንጉሥ፡ ይህን፡ ነገር፡ ሰምቶ፡ እጅግ፡ አዘነ፤

ወተበአሰ፡ ከመ፡ ያድኅኖ፡ ለዳንኤል፤

ዳንኤልን፡ ያድነው፡ ዘንድ፡ ተከራከረ፤

እምነግህ፡ እስከ፡ ሠርክ፡ ፈቀደ፡ ያድኅኖ፡ ወስዕነ፤

ከጧት፡ እስከ፡ ሠርክ፡ ድረስ፡ ያድነው፡ ዘንድ፡ ወደደ፤ ማዳን፡ ተሳነው፤

፲፭፤ ወይቤሉ፡ እሙንቱ፡ ዕደው፡ ሶቤሃ፡ ለንጉሥ፤

እኒህ፡ ሰዎች፡ ንጉሥን፡ ያን፡ ጊዜ፡ እንዲህ፡ አሉት፤

አእምር፡ ንጉሥ፡ ከመ፡ ዕድሜ፡ ፋርስ፡ ወሜዶን፡ ዘዓደሙ፡ ወሠርዑ፡ ዓበየ፤

ንጉሥ፡ የፋርስ፡ የሜዶን፡ ሰዎች፡ የቀጠሩትን፡ ቀን፡ የሠሩትን፡ ሥራ፡ እምቢ፡ እንዳለ፡ እወቅ፤ አንድም፡ ዐበየ፡ ወኢሰዓለ፡ ኀቤከ፡ ንጉሥ፡ ይላል፤

፲፮፤ ወእምዝ፡ አዘዘ፡ ንጉሥ፡ ያምጽእዎ፡ ለዳንኤል፡ ወይደይዎ፡ ውስተ፡ ግበ፡ አናብስት፤

አገር፡ ቢያብር፡ ለንጉሥ፡ ያስቸግር፡ እንዲሉ፤ ከዚህ፡ በኋላ፡ ንጉሥ፡ ዳንኤልን፡ አምጥተው፡ በአንበሳ፡ ጉድጓድ፡ ይጥሉት፡ ዘንድ፡ አዘዘ፤

ወይቤሎ፡ ንጉሥ፡ ለዳንኤል፡ አምላክከ፡ ዘኪያሁ፡ ታመልክ፡ ዘልፈ፡ ለያድኅንከ፤

ንጉሥ፡ ዳንኤልን፡ ዘወትር፡ እሱን፡ የምታመልከው፡ ፈጣሪህ፡ ያድንህ፡ አለው፤

፲፯፤ ወወረውዎ፤

ወርውረው፡ ጣሉት፤

ወአምጽኡ፡ ዕብነ፡ ወከደኑ፡ ዲበ፡ አፈ፡ ግብ፤

ድንጋይ፡ አምጥተው፡ የጉድጓዱን፡ አፍ፡ ገጠሙት፤

ወኃተመ፡ ንጉሥ፡ በሕልቀቱ፡ ወበሕልቀተ፡ መገብቱ፡ ከመ፡ አልቦ፡ ዘይትሜየን፡ ላዕለ፡ ዳንኤል፤

በዳንኤል፡ ላይ፡ የሚተነኰል፡ እንዳይኖር፡ በሱ፡ በሹማምንቱም፡ ማኅተም፡ አተመ፤ ጸንቶ፡ ሲከራከርለት፡ አይተዋልና፡ በሕልቀተ፡ መገብቱ፡ ላለው፤ አንድም፡ ጸንተው፡ ሲመክሩበት፡ አይቷልና፡ አውጥተው፡ እንዳይገድሉት፡ በሕልቀቱ፡ ላለው፤

፲፰፤ ወአተወ፡ ንጉሥ፡ ቤቶ፡ ወኖመ፡ ዘእንበለ፡ ይደረር፤

ንጉሥ፡ ከቤቱ፡ ገብቶ፡ ግብር፡ ሳያገባ፡ ተኛ፤

ወኢያብኡ፡ ሎቱ፡ ዘይበልዕ፤

ግብር፡ አላገቡለትም፤

ወዓበዮ፡ ንዋም፤

እንቅልፍ፡ እምቢ፡ አለው፤



ወዓፀወ፡ እግዚአብሔር፡ አፉሆሙ፡ ለአናብስት፡ ወኢሠሐጥዎ፡ ለዳንኤል፤

እግዚአብሔር፡ የአናብስትን፡ አፍ፡ ዘጋ፤ ዳንኤልን፡ ስንኳን፡ ይበሉት፡ አልጫሩትም፤ (አልቧጨሩትም)፤

፲፱፤ ወእምዝ፡ ጌሠ፡ ንጉሥ፡ በጽባሕ፡ ቅድመ፡ ጎሕ፡ ወሮፀ፡ ኀበ፡ ግበ፡ አናብስት፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ ንጉሥ፡ ከጎሕ፡ አስቀድሞ፡ በማለዳ፡ ገሥግሦ፡ ሄደ፤ ፈጥኖ፡ ከአንበሳው፡ ጉድጓድ፡ ደረሰ፤

፳፤ ወበጺሖ፡ ኀበ፡ ግብ፡ ከልሐ፡ በዓቢይ፡ ቃል፤

ከጉድጓዱ፡ በደረሰ፡ ጊዜ፡ ቃሉን፡ አሰምቶ፡ ተናገረ፤

ወይቤ፡ ዳንኤል፡ ገብረ፡ እግዚአብሔር፡ ሕያው፡ አምላክከ፡ ዘኪያሁ፡ ታመልክ፡ ዘልፈ፡ ክህለኑ፡ አድኅኖተከ፡ እምአፈ፡ አናብስት፤

የእግዚአብሔር፡ አገልጋይ፡ ዳንኤል፡ ዘወትር፡ እሱን፡ የምታመልከው፡ ሕያው፡ የሚሆን፡ ፈጣሪህ፡ ከአናብስት፡ አፍ፡ አንተን፡ ማዳን፡ ተቻለውን፡ አለ፤

፳፩፤ ወይቤሎ፡ ዳንኤል፡ ለንጉሥ፡ ንጉሥ፡ ለዓለም፡ ሕየው፤

ዳንኤል፡ ንጉሥን፡ እንዲህ፡ አለው፤ ንጉሥ፡ ሽህ፡ ዓመት፡ ያንግሥህ፤ አንድም፡ ወንድ፡ ልጅ፡ ለፈረስ፤ ሴት፡ ልጅ፡ ለበርኖስ፡ የምታደርስ፡ ያድርግህ፤

፳፪፤ አምላኪየ፡ ፈነወ፡ መልአኮ፡ ወፈጸመ፡ አፈ፡ አናብስት፡ ወአድኃነኒ፤

ፈጣሪዬ፡ መልአኩን፡ ሰድዶ፡ የአናብስትን፡ አፍ፡ ዘጋ፤ አዳነኝ፤

ወኢሠሐጡኒ፡ ወኢክህሉኒ፤

አልጫሩኝም፤ አልቻሉኝም፤

እስመ፡ ተረክበ፡ ሊተ፡ ጽድቅ፡ በቅድሜሁ፤

በፊቱ፡ ጽድቅ፡ አምልኮት፡ ተገኝቶልኛልና፤

ወቅድሜከኒ፡ ኦ፡ ንጉሥ፡ ኢገበርኩ፡ እኩየ፤

ንጉሥ፡ በፊትህም፡ ክፉ፡ ነገር፡ አላደረግሁም፡ ማለት፡ በንጉሥ፡ ዕልወት፡ በእግዚአብሔር፡ ክህደት፡ አላደረግሁምና፤

፳፫፤ ወሶቤሃ፡ ተፈሥሐ፡ ንጉሥ፡ ጥቀ፡ በእንቲአሁ፡ ወአዘዘ፡ ያውጽእዎ፡ ለዳንኤል፡ እምግበ፡ አናብስት፤

ያን፡ ጊዜ፡ ንጉሥ፡ ስለሱ፡ እጅግ፡ ደስ፡ አለው፤ ዳንኤልንም፡ ከግበ፡ አናብስት፡ ያወጡት፡ ዘንድ፡ አዘዘ፤ ይህም፡ ምሳሌ፡ ነው፤ ዳንኤል፡ የጻድቃን፡ ብሊት፤ ግበ፡ አናብስት፡ የገሃነም፤ ዳንኤልን፡ አናብስት፡ እንዳልበሉት፡ ጻድቃን፡ ብሊትንም፡ ሥቃየ፡ ሲኦል፡

www.ethiopianorthodox.org

አላገኛቸውምና፡ የተበሉት፡ የኃጥአን፡ ብሊት፡ የሲኦል፡ ሥቃይ፡ አግኝቷቸዋልና፤

ወወጽአ፡ ዳንኤል፡ እምግብ፣

ዳንኤል፡ ከጉድጓዱ፡ ወጣ፤

ወኢተነክየ፡ ምንተኒ፣

ምንም፡ ምን፡ አልነካውም፤

ወኢተረክበ፡ ሕሱም፡ ላዕሌሁ፡ እስመ፡ ተአመነ፡ በአምላኩ፣

በፈጣሪው፡ አምኗልና፡ በሱ፡ ላይ፡ ክፉ፡ ነገር፡ ተገኝቶ፡ ምንም፡ ምን፡ የተጐዳው፡ የለም፤

፳፬፤ ወይቤ፡ ንጉሥ፡ ያምጽእዎሙ፡ ለእሙንቱ፡ ዕደው፡ እለ፡ አስተዋደይዎ፡ ለዳንኤል፣

ዳንኤልን፡ ያጣሉትን፡ ሰዎች፡ ያመጧቸው፡ ዘንድ፡ ንጉሥ፡ አዘዘ፤

ወወደይዎሙ፡ ውስተ፡ ግበ፡ አናብስት፡ ለእሙንቱ፡ ወለደቂቆሙ፡ ወለአንስቲያሆሙ፣

እነሱን፡ ልጆቻቸውን፡ ሚስቶቻቸውን፡ በአናብስት፡ ጉድጓድ፡ ጣሏቸው፤

ወዘእንበለ፡ ይብጽሑ፡ ምድረ፡ ግብ፡ አኃዝዎሙ፡ አናብስት፣

ምድር፡ ሳይነኩ፡ አናብስት፡ እየቀለቡ፡ ዋጧቸው፤

ወቀጥቀጥዎሙ፡ ኵሎ፡ አዕፅምቲሆሙ፣

አጥንታቸውን፡ ሁሉ፡ ቀጠቀጧቸው፤

፳፭፤ ወእምዝ፡ ጸሐፈ፡ ዳርዮስ፡ ንጉሥ፡ ለኵሉ፡ አሕዛብ፡ ወሕዝብ፡ ወበሐውርት፡ ወለኵሉ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ውስተ፡ ምድር፣

ከዚህ፡ በኋላ፡ ዳርዮስ፡ ለሕዝቡ፣ ለአሕዛቡም፣ ለሀገሩ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ለሚኖሩ፡ ሁሉ፡ ጻፈ፣

ሰላም፡ ይብዛኅ፡ ለክሙ፡ እምቅድመ፡ ገጽየ፣

በፊቴ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ይብዛላችሁና፣

፳፮፤ አዘዝኩ፡ ለኵሉ፡ መኳንንት፡ ዘውስተ፡ መንግሥትየ፣

በምግዛው፡ አገር፡ ላሉ፡ ለመኳንንቱ፡ ሁሉ፡ አዘዝሁ፣

ከመ፡ ይፍርሁ፡ ወይርዓዱ፡ እምቅድመ፡ ገጹ፡ ለአምላከ፡ ዳንኤል፣

ከዳንኤል፡ ፈጣሪ፡ ከገጸ፡ መዓቱ፡ የተነሣ፡ ይፈሩ፡ ይርዱ፡ ዘንድ፤

እስመ፡ ውእቱ፡ አምላክ፡ ሕያው፡ ዘይሄሉ፡ ለዓለም፤ ዘኢይማስን፡ መንግሥቱ፡ ወምኵናኑኒ፡ ለዝሉፉ፣

አገዛዙ፡ ጸንቶ፡ የሚኖር፡ መንግሥቱ፡ የማያልፍ፡ ለዘለዓለም፡ ጸንቶ፡ የሚኖር፡ ሕያው፡ አምላክ፡ እሱ፡ ነውና፤

፳፯፤ ያድኅንሂ፣

ከእቶን፡ እሳት፡ ያድናል፤



ወይረድእሂ፣

ከግበ፡ አናብስት፤ አንድም፡ ከግበ፡ አናብስት፡ ያድናል፣ በምግባር፡ ይረዳል፤

ወይገብር፡ ተአምራተ፡ ወመንክራተ፡ በሰማይ፣

በፀሐይ፣ በጨረቃ፤ አንድም፡ በልዑላኑ፣ አንድም፡ በመላእክት፣ አንድም፡ በአየር፡ ባሉ፡ አጋንንት፡ ተአምራት፡ ያደርጋል፤

ወበምድር፣

በዕፀው፡ በአዕባን፤ አንድም፡ በትሑታኑ፤ አንድም፡ በደቂቀ፡ አዳም፤ አንድም፡ በምድር፡ ባሉ፡ አጋንንት፡ ተአምራትን፡ ያደርጋል፤

ዘአድኃኖ፡ ለዳንኤል፡ እምአፈ፡ አናብስት፣

ዳንኤልን፡ ከአፈ፡ አናብስት፡ ያዳነው፡ እሱ፡ ነው፤

፳፰፤ ወዓብየ፡ ዳንኤል፡ በመንግሥተ፡ ዳርዮስ፡ ወበመንግሥተ፡ ቂሮስ፡ ፋርሳዊ፣

ዳንኤል፡ በዳርዮስ፡ መንግሥትና፡ በቂሮስ፡ መንግሥት፡ ከበረ፣ ገነነ፣ በነዚህ፡ መንግሥት፡ ቢትወደድ፡ እየሆነ፡ ገዝቷል።

## ምዕራፍ፡ ፯፤

፩፤ በቀዳሚ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ለብልጣሶር፡ ንጉሠ፡ ከላውዴዎን፣

የከላውዴዎን፡ ንጉሥ፡ ብልጣሶር፡ በነገሠ፡ በመጀመሪያው፡ ዘመን፤

ሐለመ፡ ዳንኤል፡ ሕልመ፣

ከዚህ፡ ቀድሞ፡ የሰውን፡ ሕልም፡ ይተረጉም፡ ነበረ፤ አሁን፡ ግን፡ ዳንኤል፡ ሕልም፡ አለመ፤

ወርእየ፡ ርእሰ፡ በውስተ፡ ምስካቢሁ፣

ራሱን፡ በሕልም፡ አየ፤ አንድም፡ ራሱ፡ ሕልም፡ ሲያይ፡ አየ፤ አንድም፡ ዘውስተ፡ ነፍሱ፡ ይላል፤ የራሱን፡ ጥፋት፡ አየ፤ የእስራኤል፡ ጥፋት፡ የሱ፡ ነውና፣

ወጸሐፈ፡ ሕልሞ፣

ሕልሙን፡ ጻፈ፤

፪፤ ወይቤ፡ አነ፡ ዳንኤል፡ ሐለምኩ፣

እኔ፡ ዳንኤል፡ ሕልም፡ አለምሁ፡ አለ፤

ወርኢኩ፡ ፬ተ፡ ነፋሳተ፡ ሰማይ፡ ይነፍሑ፡ ውስተ፡ ባሕር፡ ዓቢይ፣

በአራቱ፡ ሊቃነ፡ መላእክት፡ ምግብና፡ አምሳል፡ አራቱ፡ ነገሥተ፡ አሕዛብ፡ ሲነግሡ፡ አየሁ፤ ባሕር፡ ታዋኪ፡ ነው፤ ይህም፡ ዓለም፡

www.ethiopianorthodox.org

ታዋኪ፡ ነውና፣ በባሕር፡ ያለ፡ ካልወጣ፡ አይታወቅም፤ በዚህ፡ ዓለምም፡ ካልተደረገ፡ አይታ ወቅምና፤

፫፤ ወዓርጉ፡ ፬ቱ፡ አራዊት፡ ዓበ ይት፡ እምባሕር፡ ኅቡረ፣

አራቱ፡ ነገሥተ፡ አሕዛብ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ነገሡ፤

፬፤ ወቀዳማዊት፡ ከመ፡ አንበሳዊት፣

መጀመሪያዪቱ፡ በአንበሳ፡ አም ሳል፡ ናት፡ አለ፤ ናቡከደነፆር፡ ነው፤ ጋማውን፡ የአንበሳ፡ አድ ርጎለታልና፤

ወባቲ፡ ክንፍ፣

ጥፍር፡ አላት፤ ጥፍሩን፡ የን ስር፡ አድርጎለታልና፤

ወክነፊሃኒ፡ ከመ፡ ዘንስር፣

ጥፍሩም፡ እንደ፡ ንስር፡ ነው፤

ወርኢክዋ፡ እስከ፡ ተመልሐ፡ ክነፊሃ፣

ጋማው፡ እስቲመለጥ፣ ጥፍሩ፡ እስቲወልቅ፡ ደርሼ፡ አየሁ፤ ናቡ ከደነፆር፡ ቀድሞ፡ ሰውን፡ ሁሉ፡ አስገዝቶኝ፡ ነበር፤ ዛሬም፡ አራ ዊትን፡ሁሉ፡ አስገዝቶኛል፤ እኔ፡ ምን፡ ዕዳዬ፡ ብሎ፡ ታበየ፤ ጋማው፡ እንዲመለጥ፣ ጥፍሩ፡ እንዲወ ልቅ፡ አድርጎታል፤

ወተንሥአት፡ እምድር፣

ከአርዌ፡ መልክ፡ ተለይቶ፤ አን ድም፡ ወቀዳማዊት፡ ከመ፡ አንበ ሳዊት፡ ብለህ፡ መልስ፤ መጀመ ሪያዪቱ፡ መንግሥተ፡ ባቢሎን፡ ናት፤ ከመ፡ አንበሳዊት፡ አላት፤ ሥራቷ፡ ግበ፡ አናብስት፡ ነውና፣ ወባቲ፡ ክንፍ፡ ሥልጣን፡ አላት፣ ሥልጣኗም፡ እንደ፡ ናምሩድ፡ ነው፤ ሥልጣኗ፡ እስቲነሣት፡ ደርሼ፡ አየሁ፡ ተገገር፡ ሆነች፤

ወቆመት፡ በእግረ፡ ሰብእ፣

በተገገር፡ ሰው፡ አምሳል፡ ጸናች፣

ወልበ፡ ሰብእ፡ ተውህበ፡ ላቲ፣

ወተውህቦ፡ ልበ፡ አርዌ፡ ብሎ፡ ነበርና፡ የተገገር፡ ሰው፡ ሥር ዓት፡ ተሰጣት፤

፭፤ ወመጽአ፡ ካልዕ፡ አርዌ፡ ዘይመ ስል፡ ድበ፣

ተከትላ፡ የሚመስል፡ ሌላ፡ አርዌ፡ መጣ፡ አለ፣ ዳርዮስ፡ ነው፤

ወቆመ፣

ነገሠ፤

ወ፩፡ ገጹ፣

አራቱን፡ መዓዝን፡ አንድ፡ አድ ርጎ፡ ይገዛል፤

ወ፫ቱ፡ ዓፅመ፡ ገበዋት፡ ውስተ፡ አፉሁ፣

ሦስት፡ የጎን፡ አጥንቶች፡ በእጁ፡ ተይዘዋል፣ ማለት፡ ባቢሎንን፡ ሜዶንን፡ ፋርስን፡ ይገዛል፤



ዓፅመ፡ ገበዋት፡ አላቸው፤ የጎን፡ አጥንት፡ ሥጋ፡ የለውም፤ እነ ዚህም፡ ገንዘባቸውን፡ ተዘርፈ ዋልና፤ አንድም፡ ጐን፡ አጠገብ፡ ነው፤ በአጠገብ፡ ኗሪዎች፡ ናቸ ውና፤ አንድም፡ ጐን፡ ማረፊያ፡ ነው፤ ገንዘባቸውን፡ በልተው፡ አርፈው፡ ይኖራሉና፤ አንድም፡ ጐን፡ ጠማማ፡ ነው፡ ጠዋዕያን፡ ምግባር፡ ናቸውና፤

ወእቤላ፡ ከመዝ፡ ተንሥኢ፡ ወብልዒ፡ ሥጋ፡ ብዙኀ፣

እንዲህ፡ አልኋት፤ ተነስተሽ፡ የሰውን፡ ሁሉ፡ ገንዘብ፡ አብዝ ተሽ፡ ሰብስቢ፡ አልኋት፤

፮፤ ወእምድኅረ፡ ዝንቱ፡ ርኢኩ፡ ካልዓ፡ አርዌ፡ ከመ፡ ነምር፣

ከዚህ፡ በኋላ፡ በነምር፡ አምሳል፡ ሌላ፡ አውሬ፡ አየሁ፡ አለ፣ ቂሮስ፡ ነው፤

ወላዕሌሁ፡ ፬ቱ፡ ክንፍ፡ ከመ፡ ዖፍ፣

እንደ፡ ዖፍ፡ አራት፡ ክንፍ፡ አለው፡ ማለት፡ ባቢሎን፣ ፋርስ፣ ፅርዕ፣ ሜዶን፡ በሱ፡ ትእዛዝ፡ አሉ፤ አምስቱ፡ ቢል፡ ከሮምና፡ ከግብፅ፡ አንዳቸውን፡ አግብቶ፤

ወ፬ቱ፡ አርእስቲሁ፡ ለአርዌናሁ፣

የንጉሡ፡ ነገሥትነቱ፡ አህጉር፡ አራት፡ ናቸው፤ ባቢሎን፡ ሜዶን፡ ፅርዕ፡ በዝርዝሩ፡ ፋርስን፡ ማምጣት፡ ነው፤ አምስቱ፡ ቢል፡ ከሮምና፡ ከግብፅ፡ አንዳቸውን፡ አግብቶ፤

ወተውህበ፡ ሎቱ፡ መባሕት፣

መጥባሕትም፡ ይላል፤ ሥል ጣን፡ ተሰጠው፤

፯፤ ወእምድኅሬሁ፡ ርኢኩ፡ በራ እየ፡ ሌሊት፡ ራብዐ፡ አርዌ፡ ግሩመ፣

ከሱ፡ በኋላ፡ ግሩም፡ የሆነ፡ አራ ተኛ፡ አውሬ፡ ሌሊት፡ በራእይ፡ አየሁ፤ ራእየ፡ መዓልት፡ አለና፡ ራእየ፡ ሌሊት፡ አለ፤ በዝሆን፡ አምሳል፡ አይቶታል፡ እስክን ድር፡ ነው፤

ወመደንግፀ፡ ወኃያለ፡ ጥቀ፣

የሚያስደነግጥ፡ እጅግ፡ ኃያል፡ የሆነ፡ እስክንድርን፡ አየሁ፤

ወስነኒሁ፡ ዘሐፂን፣

ሥልጣኑ፡ ፅኑዕ፡ ነው፤

ወፅፈሪሁ፡ ዘብርት፣

ሠራዊቱ፡ ፅኑዓን፡ ናቸው፤

ይበልዕ፡ ወየሐርፅ፡ ወዘተርፈ፡ ይከይድ፡ በእግሩ፣

የሰውን፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ ይበ ላል፣ ከሱ፡ የቀረውን፡ ሠራዊ ቱን፡ እየሰደደ፡ ያጠፋል፤

ወውእቱ፡ የዓቢ፡ እምኵሎሙ፡ አራ ዊት፡ ዘቅድሜሁ፣

ከሱ፡ አስቀድመው፡ ከነበሩት፡ ነገሥታት፡ሁሉ፡እሱ፡ይበልጣል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወ፯ቱ፡ አቅርንቲሁ፤

ዐሥር፡ ነገሥታትን፡ ያነግሣል፡ አራቱ፡ ደጋግ፤ (ታላላቅ)፤ ስድ ስቱ፡ ታናናሽ፡ ናቸው፤

፰፤ ወነጸርኩ፡ አቅርንቲሁ፤

እስክንድር፡ ያነገሣቸው፡ ነገሥ ታቱን፡ አየሁ፤

ወናሁ፡ ካልዕ፡ ቀርን፡ ንዑስ፡ በቈለ፡ በማዕከሎሙ፤

እነሆ፡ በመካከላቸው፡ ታናሽ፡ ቀንድ፡ በቀለ፡ ማለት፡ አውፊ ፋኖስ፡ አንጥያኮስ፡ ነገሠ፤ አን ድም፡ ሐሳዊ፡ መሢሕ፡ ነገሠ፤

ወ፫ቱ፡አቅርንቲሁ፡ዘቅድሜሁ፡ተመልሑ፡ እምቅድመ፡ ገጹ፤

ከሱ፡ አስቀድመው፡ የነበሩ፡ ሰል ፎስ፡ ደማጥርያኖስ፡ በጥሊሞስ፡ ጠፉ፤ አንድም፡ የሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ስማቸው፡ ያልታወቀ፡ ነገሥታቱ፡ ጠፉ፤

ወውስቴቱ፡ አዕይንት፡ ከመ፡ አዕይንተ፡ ሰብእ፡ ውስተ፡ ውእቱ፡ ቀርን፡ ንዑስ፤

ቀርን፡ ብሎት፡ ነበርና፡ ሰው፡ እንደሆነ፡ ለማጠየቅ፡ እንደ፡ ሰው፡ ያለ፡ ዓይን፡ አለው፤ አንድም፡ የሰው፡ ዓይን፡ ተንኮለኛ፡ ነው፤ ተንኮለኝነት፡ አለው፤ አንድም፡ ለጌታ፡ ነቢያተ፡ ጽድቅ፡ እንዳ ሉት፡ ለአንጥያኮስም፡ ነቢያተ፡ ሐሰት፡ አሉት፤ አንድም፡ ለጌታ፡ ሄኖክ፤ ኤልያስ፡ እንዳሉት፤ ለሐሳዊ፡ መሢሕም፡ ሐሳዊ፡ ሄኖክ፤ ሐሳዊ፡ ኤልያስ፡ አሉት፤

ወአፉሁ፡ ይነብብ፡ ዓቢያተ፤

አንጥያኮስ፡ የእስራኤል፡ አም ላክ፡ ምን፡ አምላክ፡ ነው፡ እያለ፡ ይናገራል፤ አንድም፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ከሰማየ፡ ሰማያት፡ ወረ ድሁ፤ ከድንግል፡ ማርያም፡ ተወ ለድሁ፤ ጽርሐ፡ አርያም፡ ይሏ ችኋል፤ የኔ፡ ከተማ፡ ናት፡ እያለ፡ ይናገራል፤

፱፤ ወርኢኩ፡ እስከ፡ አንበሩ፡ መንበረ፤

መናብርተ፡ ሲል፡ ነው፤ እንደ፡ አትሮንስ፡ ሰሎሞን፡ እርከን፡ እርከን፡ አለውና፤ አንድም፡ የንጉሡ፡ ሲዘረጋ፡ የባለሟሎ ቹም፡ ይዘረጋልና፤ አንድም፡ በንጉሥ፡ ቤት፡ ዙፋን፡ አልጋ፤ ድንክ፡ አልጋ፡ አለና፡ መናብ ርት፡ ብሎ፡ አበዛ፤ አንድም፡ ነቢያት፡ ካህናት፡ መቃብያንን፡ እስቲያስተምሩ፡ ድረስ፤ ብሉየ፡ መዋዕል፡ እስቲያድርባቸው፤ ሐዋርያት፡ ምእመናንን፡ እስቲ ያስተምሩለት፤ ጌታ፡ እስቲያድ ርባቸው፤ አንድም፡ ሄኖክ፤ ኤል ያስ፡ ምእመናንን፡ እስቲያስተ ምሩለት፡ ብሉየ፡ መዋዕል፡ ጌታ፡ ክርስቶስ፡ …



ድረስ፡ ደርሼ፡ አየሁ፤ አንድም፡ በደብረ፡ ጽዮን፡ ዙፋን፡ እስቲዘረ ጋለት፡ ደርሼ፡ አየሁ፤ ብሉየ፡ መዋዕል፡ ክርስቶስ፡ አስቲቀመ ጥበት፡ ድረስ፡ ደርሼ፡ አየሁ፤

ወነበረ፡ ዲቤሁ፡ ብሉየ፡ መዋዕል፤

ብሉየ፡ መዋዕል፡ ጌታ፡ በዙፋኑ፡ ተቀመጠ፤

ወልብሱ፡ ፀዓዳ፡ ከመ፡ በረድ፤

ልብሱ፡ እንደ፡ በረድ፡ ነጭ፡ ነው፤ ንጹሐ፡ ባሕርይ፡ ነኝ፡ ሲል፤

ወስእርተ፡ ርእሱ፡ ከመ፡ ፀምር፡ ንጹሕ፤

የራሱ፡ ጠጉር፡ እንደ፡ ብዝት፡ ነጭ፡ ነው፤ ብሉየ፡ መዋዕል፡ ነኝ፡ ሲል፡ በሽበተ፡ ሰው፡ አም ሳል፡ ይታየዋል፤

ወመንበሩሂ፡ እሳት፡ ዘይነድድ፤

ዙፋኑም፡ የሚነድ፡ እሳት፡ ነው፤ በመዓት፡ አለሁባቸው፡ ሲል፤

ወሠረገላሁኒ፡ አፍሐም፡ ዘያንበለብል፤

ሠረገላውም፡ የሚያቃጥል፡ ፍሕም፡ ነው፤ የነዚያን፡ ደም፡ አፈስሳለሁ፡ ሲል፤

፲፤ ወፈለገ፡ እሳት፡ ይውኅዝ፡ ቅድሜሁ፤

በፊቱ፡ የእሳት፡ ፈሳሽ፡ ይፈስ ሳል፤ መቅሠፍተ፡ ኃጥአን፤ አን ድም፡ ሀብተ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ …

አዕላፈ፡ አዕላፋት፡ ይትለአክዎ፤

የብዙ፡ ብዙ፡ የሚሆኑ፡ መላእ ክት፡ ያገለግሉታል፤

ወትእልፊተ፡ አዕላፋት፡ ይቀውሙ፡ ዓውደ፡ ቅድሜሁ፤

የብዙ፡ ብዙ፡ የሚሆኑ፡ መላእ ክት፡ በፊቱ፡ ዙሪያውን፡ ይቆማሉ፤

ወነበረ፡ ዓውደ፡ ወከሠተ፡ መጻሕፍተ፤

ጌታ፡ በአደባባይ፡ ተቀመጠ፤ የአ ንጥያኮስን፡ ዕዳውን፡ አወቀበት፤ አንድም፡ የሐሳዊ፡ መሲሕን፡ ዕዳውን፡ አወቀበት፤ አንድም፡ በምጽአት፡ ጌታ፡ በአደባባይ፡ ተቀመጠ፤ ብሉዩን፤ ሐዲሱን፡ ገለጠ፤ ብሉይ፡ ሐዲስ፡ እየተነ በበ፡ በዚያ፡ ያለውን፡ የሠሩ፡ ወደመንግሥተ፡ ሰማያት፡ ይገ ባሉ፤ በዚያ፡ ያለውን፡ ያልሠሩ፡ ወደገሃነም፡ ይሄዳሉና፤ አንድም፡ ያን፡ ጊዜስ፡ ይህ፡ ሁሉ፡ የለም፡ ብሎ፡ ምግባረ፡ ጻድቃንን፤ ምግ ባረ፡ ኃጥአንን፡ መረመረ፤

፲፩፤ ወርኢኩ፡ ሶቤሃ፡ እምቃለ፡ ነገሩ፡ ዓቢይ፡ ዘይነብብ፡ ዝኩ፡ ቀርን፤

አንጥያኮስ፡ የእስራኤል፡ አም ላክ፡ ምን፡ አምላክ፡ ነው፤ ከማ ለቱ፡ የተነሣ፤ አንድም፡ ጌታ፡ አንጥያኮስ፡ ይጥፋ፡ ከማለቱ፡ የተነሣ፤ አንድም፡ ሐሳዊ፡

www.ethiopianorthodox.org

መሲሕ፡ ከሰማየ፡ ሰማያት፡ ወረድሁ፤ ከድንግል፡ ማርያም፡ ተወለድሁ፡ ከማለቱ፡ የተነሣ፤ አንድም፡ ጌታ፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ይጥፋ፡ ከማለቱ፡ የተነሣ፤

እስከ፡ ተአተተ፡ ወእስከ፡ ተቀትለ፡ ውእቱ፡ አርዌ፡ ወጠፍዓ፤

ያን፡ ጊዜ፡ አንጥያኮስ፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ እስቲጠፋ፡ ድረስ፡ ደርሼ፡ አየሁ፤

ወወሀቡ፡ ሥጋሆሙ፡ ያውዕዩ፡ በእሳት፤

ዕብራውያን፡ ለመከራ፡ በርት ተው፡ መገኘታቸውን፡ መናገር፡ ነው፤ አንድም፡ አንጥያኮስ፡ ቍስለ፡ ሥጋ፡ ታሞ፡ አንደበቱ፡ ተቆራርጦ፡ ሙቷልና፤ አንድም፡ የነአልዓዛርን፡ ሥጋቸውን፡ በእ ሳት፡ ያቃጥሉ፡ ዘንድ፡ ሰጡ፤ አንድም፡ የነሐሳዊ፡ መሲሕን፡ ሥጋቸውን፡ ሥላሴ፡ ለእሳተ፡ ገሃነም፡ ሰጡ፡ አለ፤ የሥጋው፡ ከነፍስ፡ ያደርሳቸዋልና፤

፲፪፤ ወቆመ፡ ርእሶሙ፡ ለእሉ፡ አራዊት፤

የሮማውያን፡ መንግሥት፡ ጸና፤ አንድም፡ አውፊፋኖስ፡ አንጥ ያኮስ፡ ነገሡ፤ አንድም፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ከመን ፈቅ፡ ጸና፤ አንድም፡ ተጸርዐ፡ ይሳል፤ ጠፋ፤

ወተውህበ፡ ሎሙ፡ ነዋህ፡ ሕይወት፡ እስከ፡ ዕድሜሆሙ፤

ለነአንጥያኮስ፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፤ አንድም፡ ለአይሁድ፡ አርባ፡ ዘመን፤ አንድም፡ ለሮማ ውያን፡ አራት፡ መቶ፡ ስድስት፡ ዘመን፡ ተሰጣቸው፤

፲፫፤ ወርኢኩ፡ በራእየ፡ ሌሊት፤

ራእየ፡ መዓልት፡ አለና፡ ራእየ፡ ሌሊት፡ አለ፤ ሌሊት፡ በራእይ፡ አየሁ፤

ወናሁ፡ መጽአ፡ ዓቢይ፡ በደመና፡ ሰማይ፡ ከመ፡ ወልደ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፤

ዓቢይ፡ ጌታ፡ ወልደ፡ ዕጓለ፡ እመ ሕያው፡ እንደ፡ መሆኑ፡ በም ልዓተ፡ ክብር፡ በስፍሐተ፡ ክብር፡ መጣ፤ አንድም፡ በሥጋ፡ ማር ያም፡ መጣ፤

ወበጽሐ፡ ኀበ፡ ብሉየ፡ መዋዕል፤

አብ፡ እስከሚገዛው፡ ይገዛል፤ አንድም፡ አብ፡ የሚፈርደውን፡ ይፈርዳል፤ አንድም፡ ወልደ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ እርሱ፡ በም ጽአት፡ በክበበ፡ ትስብእት፡ ይመ ጣል፤ በመለኮቱ፡ የሚፈርደውን፡ በሰውነቱ፡ ይፈርዳል፤ አንድም፡ ደመናውን፡ እየተረገጠ፡ ይመ ጣል፤ የደብረ፡ ታቦር፤ የዕር ገት፤ [illegible]



ርይ፡ ክብሩ፡ ነው፤ መመለክ፤ መሰገድ፡ የሚገባው፡ ነው፤

፲፬፤ ወተውህበ፡ ሎቱ፡ ምኵናን፡ ወክብር፡ ወመንግሥት፤

አገዛዝ፤ ክብር፤ መንግሥት፡ ተሰጠው፤

ወኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ ወበሐውርት፡ ወነ ገድ፡ ይትቀነዩ፡ ሎቱ፤

አሕዛብ፡ ሁሉ፡ መንደር፡ መንድ ረው፡ የሚኖሩ፡ ነገደ፡ አሕዛብ፤ ነገደ፡ እስራኤል፤ ነገደ፡ ሴም፤ ነገደ፡ ካም፤ ነገደ፡ ያፌት፡ ይገ ዙለታል፤

ወምኵናኑኒ፡ ምኵናን፡ ዘለዓለም፡ ዘኢየሐልቅ፤

አገዛዙ፡ ለዘለዓለም፡ የማይፈ ጸም፡ ነው፤

ወመንግሥቱኒ፡ ዘኢይማስን፤

መንግሥቱም፡ የማያልፍ፡ ነው፤

፲፭፤ ወርእደኒ፡ መንፈስየ፡ አነ፡ ዳንኤል፤

እኔ፡ ዳንኤል፡ ሰውነቴ፡ ራደ ብኝ፤ ተንቀጠቀጠብኝ፤

ወደንገፀኒ፡ ልብየ፡ እምራእየ፡ ርእስየ፤

ከራሴ፡ ራእይ፡ የተነሣ፡ ልቡ ናዬ፡ ደነገጠብኝ፤

፲፮፤ ወሖርኩ፡ ወተጠየቅዎ፡ ለ፩ዱ፡ እምእለ፡ ይቀውሙ፤

ሂጀ፡ ከጌታ፡ ጋር፡ ከቆሙ፡ መላ [illegible] ሁት፤

ወአይድዓኒ፡ ፍካሬሁ፡ ጥዩቀ፡ ወጠየቁ፡ ወኵሉ፡ ነገሮ፤

የተረዳ፡ ትርጓሜውን፡ ነገሩን፡ ሁሉ፡ ተረዳሁ፤

፲፯፤ ወይቤለኒ፡ እሉ፡ ፬ቱ፡ አራ ዊት፡ ዓበይት፡ ዘርኢከ፡ ፬ቱ፡ ነገሥታት፡ እሙንቱ፡ ይትነሥኡ፡ ዲበ፡ ምድር፤

ያየሃቸው፡ እኒህ፡ አራቱ፡ ዓበ ይት፡ አራዊት፡ አራት፡ ነገሥ ታት፡ ናቸው፤ እነዚህ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ይነግሣሉ፤

ወዓዲ፡ ይትአተቱ፤

ዳግመኛ፡ ይጠፋሉ፤

፲፰፤ ወይገብዕ፡ መንግሥት፡ ለቅ ዱሳነ፡ ልዑል፤

መንግሥት፡ ለመቃብያን፡ ይመ ለሳል፤ አንድም፡ ለምእመናን፡ ሃይማኖት፡ ይፀናል፤

ወይነሥኡ፡ መንግሥተ፡ ቅዱሳነ፡ ልዑል፤

መቃብያን፡ መንግሥቱን፡ እጅ፡ ያደርጋሉ፤

ወይነብርዋ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፤

ለዘለዓለም፡ ይኖሩባታል፤

፲፱፤ ወተጠየቅዎ፡ ካዕበ፡ በእንተ፡ ራብዕ፡ አርዌ፤

ዳግመኛ፡ የእስክንድርን፡ ነገር፡ ጠየቅሁት፤

እስመ፡ ነኪር፡ ውእቱ፡ እምኵሎሙ፡ አራዊት፡ ወግሩም፡ ውእቱ፡ ጥቀ፤

ከአራዊት፡ ሁሉ፡ ልዩ፡ ነውና፤ እጅግ፡ ግሩም፡ ነውና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወስነኒሁ፡ ዘሐፂን፡ ወጽፈሪሁ፡ ዘብርት፤

ሥልጣኑ፡ ሠራዊቱ፡ ጽኑዓን፡ ናቸውና፤

ይበልዕሂ፡ ወየሐርስ፡ ወዘተርፈ፡ ይከይድ፡ በእግሩ፤

የሰውን፡ ሁሉ፡ ገንዘብ፡ ይበላል፤ ከሱ፡ የተረፈውን፡ ሠራዊቱን፡ እየሰደደ፡ ያጠፋል፤

፰፤ ወበእንተ፡ ፲ቱ፡ አቅርንቲሁ፡ ዘውስተ፡ ርእሱ፤

በራሱ፡ ላይ፡ የበቀሉ፡ ያሥሩን፡ ቀንዶች፡ ነገር፡ ጠየቅሁት፡ ማለት፡ በሥልጣኑ፡ የተያዙ፡ ያሥሩን፡ ነገሥታት፡ ነገር፡ ጠየቅሁት፤

ወዝኩሂ፡ ካልዕ፡ ቀርን፡ ዘበቈለ፡ መርሆሙ፡ ለ፫ቱ፡ እምእልኩቱ፡ ፲ቱ፡ እለ፡ እምቅድሜሁ፤

ከሱ፡ አስቀድመው፡ የነበሩ፡ ከዐሥሩ፡ ሦስቱን፡ ነገሥታት፡ ያጠፋ፡ የአንጥያኮስን፡ ነገር፤ አንድም፤ የሐሳዊ፡ መሲሕን፡ ነገር፡ ጠየቅሁት፤

ወወድቁ፡ ፫ቱ፡ አቅርንት፡ እለ፡ እምቅድሜሁ፤

ከሱ፡ አስቀድመው፡ የነበሩ፡ ስልፎስን፡ ደማጥርያኖስን፡ በጥሊሞስን፡ እስቲያጠፋቸው፡ ድረስ፤

ወዝኩ፡ ዘቦ፡ አዕይንት፤

የሰው፡ ዓይን፡ ተንኮለኛ፡ ነው፤ ተንኮለኝነት፡ ያለው፡ የዚያን፡ የአንጥያኮስን፡ ነገር፤ አንድም፡ የሐሳዊ፡ መሲሕን፡ ነገር፤

ወአፉሁ፡ ይነብብ፡ ዓቢያተ፤

አንጥያኮስ፡ የእስራኤል፡ አምላክ፡ ምን፡ አምላክ፡ ነው፡ እያለ፤ አንድም፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ከሰማየ፡ ሰማያት፡ ወረድሁ፡ ከድንግል፡ ማርያም፡ ተወለድሁ፡ እያለ፤

ወርእሱ፡ የዓቢ፡ እምአብያጺሁ፤

አንዱ፡ ከአንዱ፡ በልጦ፡ ያየሁት፤

፳፩፤ ርኢክዎ፡ ለውእቱ፡ ቀርን፡ ይትቃተሎሙ፡ ለቅዱሳን፤

መቃብያንን፡ ሲወጋቸው፤

ወሞያሙ፤

ድል፡ ሲነሣቸው፡ አየሁት፤

፳፪፤ እስከ፡ መጽአ፡ ብሉየ፡ መዋዕል፤

ብሉየ፡ መዋዕል፡ ጌታ፡ በረድኤት፡ እስቲመጣ፡ ድረስ፤

ወፈትሐ፡ሎሙ፡ ለቅዱሳነ፡ ልዑል፤

ለመቃብያን፡ እስቲፈርድላቸው፡ ድረስ፤

ወበጽሐ፡ ዕድሜሁ፤

ጊዜ[illegible]



ወአጽንዓ፡ መንግሥቶሙ፡ ለቅዱሳን

የመቃብያንን፡ መንግሥት፡ እስቲያጸና፡ ድረስ፡ አየሁት፤

፳፫፤ ወይቤ፡ አርዌ፡ ራብዕ፤

አራተኛው፡ አውሬ፡ እስክንድር፡ ነው፤

ራብዕት፡ መንግሥት፡ ይእቲ፡ እንተ፡ ተዓቢ፡ እምኵሉ፡ መንግሥታት፤

ከመንግሥቱ፡ ሁሉ፡ የምትበልጥ፡ አራተኛ፡ መንግሥት፡ ናት፤

ወትበልዓ፡ ለኵላ፡ ምድር፡ ወትከይዳ፡ ወትቀጠቅጣ፤

አገሩን፡ ሁሉ፡ ፈጽማ፡ ታጠፋለች፤

፳፬፤ ወ፲ቱ፡ አቅርንቲሁ፡ ፲ቱ፡ መንግሥታት፡ ዘይትነሥኡ፡ ዲበ፡ ምድር፤

አሥሩ፡ ቀንዶች፡ በዚህ፡ ዓለም፡ የሚነሡ፡ አሥሩ፡ ነገሥታት፡ ናቸው፤

ወእምድኅሬሆሙ፡ ይትነሣዕ፡ ካልዕ፡ ንጉሥ

ከነዚያ፡ በኋላ፡ አንጥያኮስ፤ አንድም፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ይነግሣል፤

ወየአትቶሙ፡ ለእኩያን፡ እለ፡ እምቅድሜሁ፤

ከሱ፡ አስቀድሞ፡ የነበሩ፡ ክፉዎችን፡ ያጠፋቸዋል፤

ወየኃሥሮሙ፡ ለ፫ቱ፡ ነገሥት፤

ሦስቱን፡ ነገሥታት፡ ያዋርዳቸዋል፤

፳፭፤ ወይነብብ፡ በነገረ፡ ልዑል፤

አንጥያኮስ፡ የእስራኤል፡ አምላክ፡ ምን፡ አምላክ፡ ነው፡ እያለ፡ አንድም፤ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ከሰማየ፡ ሰማያት፡ ወረድሁ፡ ከድንግል፡ ማርያም፡ ተወለድሁ፡ እያለ፡ ይናገራል፤

ወየአትቶሙ፡ ለቅዱሳነ፡ ልዑል፤

መቃብያንንም፡ ያጠፋቸዋል፤

ወይኄይል፤

ይበረታል፡ አንጥያኮስ፤ አንድም፤ ሐሳዊ፡ መሲሕ፤

ወይዌልጥ፡ መዋዕለ፤

በዓለ፡ ሠዊትን፤ በዓለ፡ ፋሲካን፤ በዓለ፡ መፀለትን፡ ይለውጣል፤ አንድም፡ ጌታ፡ መዋዕለ፡ ደዌን፡ በመዋዕለ፡ ጥዒና፡ ይለውጣል፤ መዋዕለ፡ ጥዒናን፡ በመዋዕለ፡ ደዌ፡ ይለውጣል፤ አንድም፡ ሰኞን፡ በማክሰኞ፡ ማቴዎስን፡ በማርቆስ፡ ይለውጣል፤

ወሕገ፤

በጥሊሞስ፤ አንጥያኮስ፡ ሕገ፡ ኦሪትን፡ በሕገ፡ ጣዖት፡ ይለውጣል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይትወሀብ፡ ሎቱ፡ እስከ፡ ዕድሜሁ፡ ውስተ፡ እዴሁ፤

እስከ፡ ጊዜው፡ ድረስ፡ ሥል ጣን፡ ይሰጠዋል፤

ዓመት፤

አንድ፡ ዓመት፤

ወዓመታት፤

ሁለት፡ ዓመት፤ ሦስት ዓመት ይሆናል፤

ወመንፈቀ፡ ዓመት

መንፈቅ፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ከመ ንፈቅ፡ ሥልጣን፡ ይሰጠዋል፤

፳፮፤ ወነበረ፡ ዓውደ፡ ወሠዓሮ፡ ለመልአክ፤

አንጥያኮስ፡ በአደባባይ፡ ተቀ መጠ፤ አልዓዛርን፡ ከሹመቱ፡ ሻረው፤ አንድም፡ ጌታ፡ በአደባ ባይ፡ ተቀመጠ፤ አንጥያኮስን፡ ከሹመቱ፡ ሻረው፤ አንድም፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ በአደባባይ፡ ተቀመጠ፤ ከጌኖክና፡ ከኤል ያስ፡ አንዱን፡ ሻረው፤ አንድም፡ ጌታ፡ በአደባባይ፡ ተቀመጠ፡ ሐሳዊ፡ መሲሕን፡ ሻረው፤

ከመ፡ ያማስን፡ ለግሙራ፤

አንጥያኮስ፡ ፈጽሞ፡ መንግሥ ትን፡ ያጠፋ፡ ዘንድ፤ አንድም፡ ኢያማስን፡ ቢል፡ መንግሥቱን፡ እንዳያጠፋ፤

፳፯፤ መንግሥት፡ ወምኵናን፡ ወዕ በየ፡ መንግሥት፡ ዘመትሕተ፡ ሰማይ፡ ተውህበ፡ ለቅዱሳነ፡ ልዑል፤

መንግሥት፡ አገዛዝ፡ ከሰማይ፡ በታች፡ ያለ፡ የመንግሥት፡ ገና ንነት፡ ለመቃብያን፡ ተሰጠ፤

ወመንግሥቱሂ፡ መንግሥት፡ ዘለዓለም

መንግሥቱም፡ የዘለዓለም፡ መን ግሥት፡ ነው፤

ወኵሎሙ፡ መንግሥታት፡ ይትቀነዩ፡ ሎቱ፡ ወይትኤዘዙ፡ እስከ፡ ዝየ፤

ለአንጥያኮስ፡ ለሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ይገዙለታል፤ ሦስት፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፡ ይገዙለታል፤ አን ድም፡ የዚህ፡ ዓለም፡ ነገሥታት፡ ለጌታ፡ ይገዙለታል፤ መገዛታ ቸው፡ እስከዚህ፡ ነው፡ አይ ባልም፤

፳፰፤ ወአሜሃ፡ ይከውን፡ ማኅለ ቅተ፡ ሕዝብ፤

ያን፡ ጊዜ፡ የሕዝቡ፡ ጥፋት፡ ይሆናል፤

ወአነ፡ ዳንኤል፡ ሕሊናየ፡ ተሐውከኒ፡ ጥቀ፡ በሕቁ፤

እኔ፡ ዳንኤል፡ ሕሊናዬ፡ ፈጽሞ፡ ታወከብኝ፤

ወተወለጠ፡ ራእይየ፤

መልኬ፡ ተለወጠ፤

ወዐቀብኩ፡ ነገሮ፡ ውስተ፡ ልብየ፤

ነገሩን፡ በልቡናዬ፡ አወጣው፡ አወርደው



## ምዕራፍ፡ ፰

### ጉባዔ

፩፤ ወአመ፡ ፲ወ፫፡ ዓመተ፡ መንግ ሥቱ፡ ለብልጣሶር፡ ንጉሥ፡ አስተርአ የኒ፡ ሊተ፡ ራእይ፡ አነ፡ ዳንኤል፡ ርኢኩ፤

ብልጣሶር፡ በነገሠ፡ በአሥራ፡ ሦስት፡ ዘመን፡ ለኔ፡ ለዳንኤል፡ ራእይ፡ ታየኝ፤ አሥራ፡ አንድ፡ ዓመት፡ አላየም፡ ቢሉ፡ አዎን፡ አላየም፤ ዕውቀቱ፡ የጸጋ፡ ነው፡ እንጂ፡ የባሕርይ፡ ነውን? አን ድም፡ አይቷል፡ ወደኛ፡ አልመ ጣልንም፤ ይህስ፡ አይደለም፡ ይህም፡ ባልመጣልንም፡ ነበር፡ ብሎ፡ ተናግሮት፡ ሳይጸፍ፡ ቀር ቷል፡ ተናግሮት፡ ሳይጸፍ፡ የቀ ረው፡ ይበልጣልና፤

እምድኅረ፡ አስተርአየኒ፡ ሊተ፡ ዘቀዳሚ፤

አስቀድሜ፡ ያየሁት፡ ዕርገተ፡ አራዊትን፡ ካየሁ፡ በኋላ፡ ለእኔ፡ ለዳንኤል፡ ራእይ፡ ታየኝ፤

፪፤ ወርኢኩ፡ እንዘ፡ ሀሎኩ፡ ውስተ፡ ሱሳ፡ ዘባሪ፡ ዘብሔረ፡ ኤላም፤

በፋርስ፡ አንፃር፡ ባለች፡ የኤ ላም፡ ክፍል፡ በምትሆን፡ በሱሳ፡ ሳለሁ፤

ወርኢኩ፡ በራእይ፡ ወሀሎኩ፡ ውስተ፡ ዑባል፤

ዑባል፡ ዛፍ፡ ዱር፡ ፈፋ፡ ወንዝ፡ ነው፤ በዑባል፡ ሳለሁ፡ በራእይ፡

፫፤ ወአንሣዕኩ፡ አዕይንትየ፡ ወርኢኩ፤

አንገቴን፡ አቅንቼ፡ አየሁ፤

ወናሁ፡ ፩፡በሐኵ፡ ይቀውም፡ ቅድመ፡ ዑባል፤

በዛፉ፡ አንፃር፡ አንድ፡ የበግ፡ አውራ፡ ቁሞ፡ አየሁ፡ በሐኵ፡ ያለው፡ ዳርዮስን፡ ነው፤

ወሎቱ፡ ፪ቱ፡ አቅርንት፡ ነዊሃን፤

ፋርስን፡ ሜዶንን፡ ይገዛል፤

ወ፩ዱ፡ ይነውኅ፡ እምካልዑ፤

ከሜዶን፡ ፋርስ፡ ይበልጣል፤ ወዘይነውህ፡ ድኅረ፡ በቈለ፡ ይላል፤ ብሎ፡ ሜዶንን፡ ከገዛ፡ በኋላ፡ ፋርስን፡ ገዛ፤

፬፤ ወርኢክዎ፡ ለውእቱ፡ በሐኵ፡ ይወግዕ፡ በአቅርንቲሁ፡ ለመንገለ፡ ባሕር፡ ወሰሜን፡ ወደቡብ፤

አራቱን፡ መዓዝን፡ ሲወጋ፡ አየሁ፡ ማለት፡ አራቱን፡ መዓዝን፡ ይገዛል፤

ወኢይቀውሙ፡ ኵሉ፡ አራዊት፡ ቅድሜሁ፤

ነገሥታቱ፡ ሁሉ፡ በፊቱ፡ አይ ቆሙም፤

ወአልቦ፡ ዘያመሥጥ፡ እምእዴሁ፤

ከእጁ፡ የሚያመልጥ፡ የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

ወገብረ፡ በከመ፡ ፈቀደ፡ ወዓብየ፤

እንደወደደ፡ አደረገ፡ ከበረ፡
ገነነ።

፭። ወአነ፡ ዳንኤል፡ ሀሎኩ፡ ውስተ፡
ሱሳ፡ እንዘ፡ እሔሊ፡ ዘንተ፤

እኔ፡ ዳንኤል፡ በሱሳ፡ ሳለሁ፡
ይህን፡ ሳወጣ፡ ሳወርድ።

ወናሁ፡ መጽአ፡ ፩ዱ፡ ዳቤላ፡ ዘጠሊ፡
እምዕራብ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ ገጸ፡ ምድር፤

እነሆ፡ ከምዕራብ፡ አንድ፡ የፍ
የል፡ አውራ፡ በምድር፡ መልቶ፡
መጣ።

ወአልቦ፡ ዘለከፋ፡ ለምድር፤

ምድርን፡ የነካት፡ የለም። ሁሉም፡
በፈረስ፡ በሠረገላ፡ እየተቀመጠ፡
መጥቷል። አንድም፡ እንደሱ፡
አድርጎ፡ ምድርን፡ የገዛት፡
የለም። አንድም፡ አገሩን፡ የነካ
በት፡ የለም። እንዲያው፡ ዝም፡
ብሎ፡ መጣ፡ እንጂ፤

ወቦ፡ ቀርን፡ ማዕከለ፡ አቅርንቲሁ፤

በቀንዶቹ፡ መካከል፡ ቀንድ፡ አለ፡
አለ። አውፊፉኖስ፡ አንጥያኮስ።

፮። ወሖረ፡ ኀበ፡ ዝኩ፡ በሐኵ፡ ዘቦ፡
አቅርንት፡ ዘርኢክ፡ ይቀውም፡ ውስተ፡
ዑባል።

በፊፋው፡ ቁሞ፡ ካየሁት፡ ቀንድ፡
ወደአለው፡ ወደ፡ በጉ፡ አውራ፡
ሄዶ፡ ማለት፡ ወደ፡ ዳርዮስ፡ ሄደ።

ወሮፀ፡ ኀቤሁ፡ በኃይሉ፤

በኃይሉ፡ ወደሱ፡ ፈጥኖ፡ ሄደ።
አንድም፡ ምስለ፡ ኃይሉ፡ ይላል፤
ከሠራዊቱ፡ ጋራ፡ ሄደ።

፯። ወርኢክዎ፡ በጺሖ፡ ኀበ፡ ዝኩ፡
በሐኵ፤

ከዳርዮስ፡ ዘንድ፡ ደርሶ፡ አየሁት፤

ወአብደ፡ ላዕሌሁ፤

ሮፀ፡ ሲል፡ ነው። ፈጥኖ፡ ወደሱ፡
ሄደ። አንድም፡ የስንፍና፡ ሥራ፡
ሠራበት።

ወአውደቆ፡ ለዝኩ፡ በሐኵ

ዳርዮስን፡ አጠፋው።

ወቀጥቀጦን፡ ለ፪ሆን፡ አቅርንቲሁ፤

ፋርስን፡ ሜዶንን፡ ገዛ፤

ወአልቦ፡ ኃይል፡ ለዝኩ፡ በሐኩ፡ ከመ፡
ይቁም፡ ቅድሜሁ፤

በፊቱ፡ ይቆም፡ ዘንድ፡ ለዳር
ዮስ፡ ኃይል፡ አልነበረውም፤

ወነጽሖ፡ ዲበ፡ ምድር፡ ወኬዶ፤

በምድር፡ ላይ፡ ጥሎ፡ ረገጠው፡
ማለት፡ አጠፋው።

ወአልቦ፡ ዘያድኅኖ፡ እምእዴሁ፡ ለው
እቱ፡ በሐኵ፤

ዳርዮስን፡ ከእስክንድር፡ እጅ፡
የሚያስጥለው፡ የለም። አንድም፡
እምእዴሁ፡ ለውእቱ፡ ዳቤላ፡
ዘጠሊ፡ ይላል።



፰። ወዝኩ፡ ዳቤላ፡ ዘጠሊ፡ ዓብየ፡
ጥቀ፤

እስክንድር፡ እጅግ፡ ከበረ፡ ገነነ፤

ወሶበ፡ ቀተሎ፡ ለዝኩ፡ በሐኵ፡ ሠበረ፡
ቀርኖ፡ ዓቢየ፤

ገደሎም፡ ይላል፡ እሱን፡ ከገደ
ለው፡ በኋላ፡ ፋርስን፡ ገዛ። አን
ድም፡ ታላቅ፡ ሎሌውን፡ ገዛ።
አንድም፡ ባለሟሎቹን፡ ገዛ፤ ለዳ
ርዮስ፡ የአንበሳ፡ የነምር፡ የዝ
ሆን፡ ለማዳ፡ ነበሩት። ጦርነት፡
በገጠመ፡ ጊዜ፡ እነዚያን፡ ይሰዳ
ቸዋል። ድል፡ ይነሰዋል፤ እስክ
ንድር፡ በነዚያ፡ አምሳል፡ የአን
በሳ፡ የነምር፡ የዝሆን፡ ምስል፡
ሠርቶ፡ ባሩዱን፡ በውስጥ፡ አድ
ርጎ፡ በመዘውር፡ የሚተኮስ፡
አድርጎታል፤ ሲዋጉ፡ እነዚያን፡
ሰደዳቸው፤አንበሳው፡ ወደ፡ አን
በሳው፡ ነምሩ፡ ወደ፡ ነምሩ፡
ዝሆኑ፡ ወደ፡ ዝሆን፡ ዘመዶቻ
ችንን፡ ያገኘን፡ መስሏቸው፡ ወደ
ነሱ፡ ሄዱ፤ እየተተኮሰ፡ አጥ
ፍቷቸዋል። ዳርዮስና፡ እስክን
ድር፡ ሲዋጉ፡ ዳርዮስ፡ ሸሸ፤ የማ
ይችለውን፡ እየገጠመ፡ ዕለት፡
ዕለት፡ ያስፈጀናል፡ ብሎ፡ ቢት
ወደዱ፡ ወግቶ፡ ጣለው። እስክን
ድር፡ ደርሶ፡ ከወደቀበት፡ አን

ሥቶ፡ አንገቱን፡ ቀና፡ አድርጎ፡
ወንድሜ፡ እኔ፡ በላይ፡ ልሁን፡
እላለሁ፡ እንጂ፡ ሞትህንስ፡ አል
ወደውም፡ አለው፤ እኔስ፡ እን
ዳልተርፍ፡ ሁኜ፡ ተወግቻለሁ።
የወጋኝም፡ የገዛ፡ ሎሌዬ፡ ነውና፡
ይልቁንስ፡ ደሜን፡ መልስልኝ፡
አለው። በኋላ፡ እስክንድር፡ ዳር
ዮስን፡ የገደለውን፡ ሰው፡ ከሁሉ፡
በላይ፡ አደርገዋለሁ፡ ብሎ፡ አዋጅ፡
ነገረ፤ እኔ፡ ነኝ፡ አለው። ይዞ፡
ሰቀለው። ምነው፡ ንጉሥ፡ ከሁሉ፡
በላይ፡ አደርገዋለሁ፡ ብለህ፡ አል
ነበረም፡ አሉት። አሁንስ፡ ከሁሉ፡
በላይ፡ አደረግሁት፡ እንጂ፡
ከሁሉ፡ በታች፡ አደረግሁት፡ ብሎ፡
ቃሉ፡ ደብተራ፡ መልሶላቸዋል፤

ወእምድኅረዝ፡ ዓብየ፡ ዳቤላ፡ ጠሊ።

ከዚህ፡ በኋላ፡ እስክንድር፡ ከበረ፡
ገነነ፤

ወዓዲ፡ በቈሉ፡ ፬ቱ፡ አቅርንት፡ መትሕ
ቴሁ፡ በ፬፡ ነፋሳተ፡ ሰማይ፤

አራቱን፡ መዓዝን፡ ለመውጋት።
አንድም፡ ለመግዛት፡ ከሱ፡ በታች፡
አራቱ፡ ነገሥታት፡ ይነሣሉ።
በአራቱ፡ ሊቃነ፡ መላእክት፡ ምግ
ብና፡ አምሳል፡ አራቱ፡ ነገሥተ፡
አሕዛብ፡ ይነሣሉ።

www.ethiopianorthodox.org

፱፤ ወእምውስተ፡ ፩ዱ፡ እምኔሆሙ፡ በቊለ፡ ቀርን፡ ንዑስ፡፡

ከነዚህም፡ አንዱ፡ አውፊፋኖስ፡ አንጥያኮስ፡ ነው፤

ወዓብየ፡ ጥቀ፡፡

እጅግ፡ ከበረ፡ ገነነ፤

ወይወግዕ፡ ለመንገለ፡ ሰሜን፡ ወጽባሕ፡፡

አራቱን፡ መዓዝን፡ ይገዛል፤ አንድም፡ አራቱን፡ መዓዝን፡ ለመግዛት፡ ከበረ፡ ገነነ፤

፲፤ ወበጽሐ፡ በኃይል፡ ዓቢይ፡ እስከ፡ ኃይለ፡ ሰማይ፡፡

በጽኑዕ፡ ኃይል፡ መቃብያንን፡ እስከ፡ መግዛት፡ ደረሰ፤ አንድም፡ ጣዖት፡ እስከ፡ ማምለክ፡ ደረሰ፤ አንድም፡፡ ፀሐይ፡ ጨረቃን፡ እስከ፡ ማምለክ፡ ደረሰ፤

ወወድቀ፡ ውስተ፡ ምድር፡ እምነ፡ ኃይለ፡ ሰማያት፡ ወእምነ፡ ከዋክብተ፡ ሰማይ፡፡

ፀሐይ፡ ጨረቃን፡ ከዋክብትን፡ ከማምለኩ፡ የተነሣ፤ አንድም፡ መቃብያንን፡ ከመግዛቱ፡ የተነሣ፤ አንድም፡ ጣዖት፡ ከማምለኩ፡ የተነሣ፤ አንድም፡ ሰማያዊ፡ ሕግን፡ ከማፍረሱ፡ የተነሣ፡ ጠፋ፤

ወኬዳ፡ እስከ፡ ማዕከላ፡፡

እስከ፡ መካከሏ፡ ሂዶ፡ መቃብያንን፡ ይወጋል፤ አንድም፡ እስከ፡ መካከላ ፡ ይወጋል፤

፲፩፤ ሠርዌ፡ ዓበየ፡ ከመ፡ ያድኅን፡ ዜዋሁ፡፡

አንጥያኮስ፡ በፍቅር፡ የማረካቸው፡ ሦስቱን፡ ካህናት፡ ይሾሟቸው፡ ዘንድ፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አለ፤ አንድም፡ አልዓዛር፡ መቃብያንን፡ በነፍስ፡ ያድናቸው፡ ዘንድ፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አለ፤ አንድም፡ ዓበየ፡ ይላል፡ መቃብያንን፡ ያጸናቸው፡ ዘንድ፡ መሥዋዕተ፡ እሪያ፡ አልሠዋም፡፡ ለሥዕለ፡ ፀሐይ፡ አልሰግድም፡ አለ፤

ወእምኔሁ፡ ይተሐወኩ፡ መሣውዕት፡፡

ሠዋዕት፡ ሲል፡ ነው፡፡ ከሱ፡ የተነሣ፡ ካህናቱ፡ ይታወካሉ፡፡

ወኮነ፡ ወተሠልጠ፡፡

አንጥያኮስ፡ ነገሠ፡፡ በመንግሥት፡ ሠለጠነ፤ አንድም፡ ንጉሠ፡ ነገሥትነት፡ በሱ፡ ተጀመረ፡ በሱ፡ ተጨረሰ፡፡ አንድም፡ ክፋት፡ በሱ፡ ተጀመረ፡ በሱ፡ ተጨረሰ፡፡

ወማሰነ፡ መቅደሰ፡፡

ቤተ፡ መቅደስ፡ ፈረሰ፡፡

፲፪፡ ወተውህበ፡ ላዕለ፡ መሥዋዕተ፡ ኃጢአት፡፡

አፍአዊ፡ ኃጢአት፡ በሚያስተሠርዩበት፡ በመሥዋዕተ፡ ኦሪት፡ ላይ፡ መሥዋዕተ፡ ጣዖት፡ ተሰጠ፤ አንድም፡ ወተውህበ፡ ላዕለ፡



መሥዋዕተ፡ ኃጢአት፡ ይላል፡፡ በመሥዋዕተ፡ ኦሪት፡ ላይ፡ መሥዋዕተ፡ እሪያ፡ ተሰጠ፡፡

ወተገድፈት፡ ጽድቅ፡ ውስተ፡ ምድር፡፡

ሕግ፡ ጠፋች፡፡

ገብረ፡ ወተሠልጠ፡፡

ነገሠ፡ በመንግሥት፡ ሠለጠነ፤ አንድም፡ ንጉሠ፡ ነገሥትነት፡ በርሱ፡ ተጀመረ፡ በርሱ፡ ተጨረሰ፤

፲፫፤ ወሰማዕኩ፡ ፩ዱ፡ መልአክ፡ እምቅዱሳን፡ ዘይነግር፡፡

ከቅዱሳን፡ መላእክት፡ አንድ፡ መልአክ፡ ሲናገር፡ ሰማሁ፤

ወይቤ፡ በፊልሙኒ፡ ዘይነብብ፡፡

በመላእክት፡ ቋንቋ፤ አንድም፡ በምሥጢር፡ ሲናገር፡ ሰማሁ፤

እስከ፡ ማእዜኑ፡ ይቀውም፡ ዝ፡ ራእየ፡ ነቢያት፡፡

ይህ፡ ራእይ፡ የሚፈጸም፡ እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ ነው፤ አንድም፡ ይትገሃድ፡ ይትከሠት፡ ሲል፡ ነው፡፡ የአክዩ፡ አሶር፡ በዕብራውያን፡ ወዕብራውያን፡ የአክዩ፡ በአሶር፡ ብለው፡ ነቢያት፡ የተናገሩት፡ የሚፈጸም፡ መቼ፡ ነው፤

ወመሥዋዕት፡ እንተ፡ ተነሥተት፡፡

መሥዋዕቱም፡ የሚፈርስ፡ ሁኗል፡ ይህ፡ እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ ነው፤

ወኃጢአት፡ እንተ፡ አማሰነት፡፡

ኃጢአት፡ ሁሉን፡ አጠፋች፡፡ ይህ፡ እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ ነው፤

ወተውህበት፡ መቅደስ፡ ለኃጢአት፡፡

ቤተ፡ መቅደስ፡ ለመሥዋዕተ፡ ዕሪያ፡ ተሰጠች፡፡ ይህ፡ እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ ነው፤

ወኃይላ፡ ለመቅደስ፡ ተከይደ፡፡

ንዋየ፡ ቅድሳቷ፡ ጠፋ፡፡ ይህ፡ እስከ፡ መቼ፡ ድረስ፡ ነው፤

፲፬፤ ወይቤሎ፡ እስከ፡ ሠርክ፡ ወነግህ፡ ፲፻ወ፫፻ተ፡ መዋዕለ፡፡

እስከ፡ ሠርክ፡ ወነግህ፡ እምነግህ፡ እስከ፡ ሠርክ፡፡ እምሠርክ፡ እስከ፡ ነግህ፡ ይላል፡፡ ከነግህ፡ እስከ፡ ሠርክ፡ ድረስ፡ ነው፤ ምነው፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፡ አይደለም? ቢሉ፡ ያው፡ እየመሸ፡ እየነጋ፡ ነውና፡፡ ሽህ፡ ከሦስት፡ መቶ፡ ቀን፡ ከሆነ፡ በኋላ፤ አንድም፡ ሽህ፡ ከሦስት፡ መቶ፡ ቀን፡ ቆይቶ፤

ይነጽሕ፡ መቅደስ፡፡

ቤተ፡ መቅደስ፡ ከመሥዋዕተ፡ ጣዖት፡ ይነጻል፡፡ ምነው፡ ሀያ፡ ሁለት፡ ቀን፡ ይጐድለው፡ የለም፡ ቢሉ፡ መጣ፡ መጣ፡ ሲሉ፡ ትተውት፡ ሂደዋል፤ አንድም፡ እሱ፡ መጥቶ፡ ዝም፡ ብሎ፡ ተቀምጧል፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፭፤ ወእምዝ፡ ሶበ፡ ርኢኩ፡ አነ፡ ዳንኤል፡ ዘራእየ፡ ኃሠሥኩ፡ ፍካሬሁ፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ እኔ፡ ዳንኤል፡ ይህነን፡ ራእይ፡ በአየሁ፡ ጊዜ፡ ትርጓሜውን፡ መረመርሁ፤

ወመጽአ፡ ወቆመ፡ ቅድሜየ፡ ከመ፡ ራእየ፡ ብእሲ፤

በሰው፡ አምሳል፡ መጥቶ፡ በፊቴ፡ ቆመ፤

፲፮፤ ወሰማዕኩ፡ ቃለ፡ ብእሲ፡ በማዕከለ፡ ዑባል፤

በፈፋው፡ መካከል፡ የሰው፡ ቃል፡ ሰማሁ፤

ወጸውዐ፡ በዓቢይ፡ ቃል፡ ወይቤ፡ ገብርኤል፡ አለብዎ፡ ዝኩ፡ ራእየ፤

ቃሉን፡ አሰምቶ፡ ጠርቶ፡ ገብርኤል፡ ይህን፡ ራእይ፡ ልብ፡ አስደርገው፡ አለ፤

፲፯፤ ወመጽአ፡ ወቆመ፡ ጥቃ፡ ኀበ፡ እቀውም፡ አነ፤

መጥቶ፡ እኔ፡ ከቆምሁበት፡ አጠገብ፡ ቆመ፤

ወሶበ፡ መጽአ፡ ደንገፅኩ፡ ወወደቁ፡ በገጽየ፤

በመጣ፡ ጊዜ፡ ደንግጬ፡ በግምባሬ፡ ፍግም፡ ብዬ፡ ወደቅሁ፤

ወይቤለኒ፡ ለበውከኑ፡ ወልደ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፤

ዳንኤል፡ ይህነን፡ ራእይ፡ አወቅ ፍጡን፡ አለኝ፤

እስመ፡ ዓዲ፡ ኢኃልቀ፡ ዕድሜሁ፡ ለዝ፡ ራእይ፤

የዚህ፡ የራእዩ፡ ጊዜው፡ ገና፡ አልደረሰምና፤

፲፰፤ ወሶበ፡ ነበበኒ፡ ደንገፅኩ፡ ወወደቁ፡ በገጽየ፡ ውስተ፡ ምድር፤

በተናገረኝ፡ ጊዜ፡ ደንግጬ፡ በፊቴ፡ ፍግም፡ ብዬ፡ ወደቅሁ፤

ወአኃዘኒ፡ ወአንሥአኒ፡ ወአቀመኒ፡ ዲበ፡ ምድር፡ በእገርየ፤

አንሥቶ፡ ይዞ፡ በእግሬ፡ አቆመኝ፡ በምን፡ ያቆመው፡ ኑሯል፡ ብሎ፡ በእውቀት፡ አጸናኝ፡ ሲል፡ ነው፤

፲፱፤ ወይቤለኒ፡ ናሁ፡ አነ፡ እነግረከ፡ ዘይከውን፡ በደኃሪ፡ መዋዕል፡ መቅሠፍተ፡ ዓቢየ፤

በኋላ፡ ዘመን፡ የሚደረገውን፡ መከራ፡ እኔ፡ እነግርሃለሁ፡ አለኝ፤

እስመ፡ ዓዲ፡ ማኅለቅተ፡ ዕድሜሁ፡ ለራእይ፡ ኢበጽሐ፤

የራእዩ፡ ፍጻሜ፡ ገና፡ አልደረሰምና፤

፳፤ በሐኰ፡ ዘርኢከ፡ ዘቦ፡ አቅርንት፡ ንጉሠ፡ ፋርስ፡ ወሜዶን፡ ውእቱ፤

ቀንዶች፡ ያሉት፡ ያየኸው፡ አውራ፡ በግ፡ የፋርስና፡ የሜዶን፡ ንጉሥ፡ ዳርዮስ፡ ነው፤



፳፩፤ ወዳቤላ፡ ዘጠሊ፡ ንጉሠ፡ ዮናናውያን፡ ውእቱ፤

የፍየሉ፡ አውራ፡ የፅርዓውያን፡ ንጉሥ፡ እስክንድር፡ ነው፤ ንጉሠ፡ ዮናናውያን፡ ባለው፡ ንጉሠ፡ ኤሊኖን፡ ይላል፤

ወቀርኑ፡ ዓቢይ፡ ማዕከለ፡ አቀርንቲሁ፡ ውእቱ፡ ንጉሥ፡ ቀዳማዊ፡ ወዘተቀጥቀጠ፡ ኀበ፡ ቆመ፤

በቀንዱ፡ መካከል፡ ያለ፡ ቀንዱ፡ ደግ፡ የሆነ፡ ከቆመበት፡ የቀጠቀጠው፡ ቀዳማዊ፡ ንጉሥ፡ እስክንድር፡ ነው፤ አንድም፡ በቀንዱ፡ መካከል፡ ያለ፡ ቀንዱ፡ ደግ፡ የሆነ፡ ካለበት፡ የቀጠቀጠው፡ እስክንድር፡ ነው፤ አንድም፡ በቀንዱ፡ መካከል፡ ያለ፡ ቀንዱ፡ ደግ፡ የሆነ፡ ከቆመበት፡ የተቀጠቀጠ፡ ዳርዮስ፡ ነው፤ አንድም፡ በቀንዱ፡ መሐከል፡ ያለ፡ ቀንዱ፡ ደግ፡ የሆነ፡ ካለበት፡ የተቀጠቀጠው፡ ዳርዮስ፡ ነው፤

፳፪፤ ፬ቱ፡ አቅርንት፡ ታሕቴሁ፡ ዘበቈሉ፡ ፬ቱ፡ ነገሥት፡ ይትነሥኡ፡

ከሱ፡ በታች፡ አራት፡ ተወራጅ፡ ነገሥታት፡ ይነግሣሉ፤

ወአኮ፡ በኃይሎሙ፡ ዘይትነሥኡ፤

የሚነሡ፡ በኃይላቸው፡ አይደለም፤

፳፫፤ ወበደኃሪታ፡ መንግሥቶሙ፡ ትትቀጠቀጥ፤

መንግሥታቸው፡ በፍጻሜዋ፡ ጊዜ፡ ትጠፋለች፤ አንድም፡ ወበደኃሪታ፡ ለመንግሥቶሙ፡ ትትፌጸም፡ ኃጢአት፡ ይላል፤ በመንግሥታቸው፡ ፍጻሜ፡ ኃጢአት፡ ትፈጸማለች፤

ወ፩ዱ፡ እምውስቴቶሙ፡ ይትነሣእ፡ ንጉሥ፡ ዘኢየኀፍር፡ ገጸ፤

ከነዚህ፡ አንዱ፡ የሰው፡ ፊት፡ የማያፍር፡ አውፊፋኖስ፡ አንጥያኮስ፡ ይነሣል፤ አንድም፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ይነሣል፤

ወኢየአምር፡ ምሳሌ፤

በእገሌ፡ የተፈረደበት፡ ይፈረድብኛል፡ የማይል፡ አንጥያኮስ፤ አንድም፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፤ አንድም፡ ምሳሌ፡ ሕግን፡ የማያውቅ፡ ይነሳል፤

፳፬፤ ወጽኑዕ፡ ኃይሉ፤

ኃይሉ፡ ጽኑዕ፡ የሚሆን፤

ወያማስን፡ ዕፁባተ፤

ሕገ፡ ኦሪትን፡ ያጠፋል፤ አንድም፡ ዕፁባተ፡ በዕፁባት፡ ይላል፤ ሕገ፡ ኦሪትን፡ በሕገ፡ ጣዖት፡ ያጠፋል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወያረትዕ፡ ግብረ፤

ሕገ፡ ጣዖትን፡ ያቀናል፤ አን
ድም፡ ወኢያረትዕ፡ ይላል፤ ሕገ፡
ኦሪትን፡ አያቀናም፤

ወይገብር፡ ኃጢአተ፤

ኃጢአት፡ ይሠራል፤

ወያጠፍዖሙ፡ ለጽኑዓን፡ ወለቅዱሳን፡
ሕዝብ፤

ጽኑዓን፡ ክቡራን፡ የሚሆኑ፡
መቃብያንን፡ ያጠፋቸዋል፤ አን
ድም፡ ሦስቱን፡ ካህናት፡ ያጠ
ፋቸዋል፤

፳፭፤ ወያረትዕ፡ አርዑተ፡ ክሣድ፤

በመቃብያን፡ አገዛዝ፡ ያጸና
ባቸዋል፤

ወትምዕይንት፡ ውስተ፡ እዴሁ፤

በቃሉ፡ የእስራኤል፡ አምላክ፡
ምን፡ አምላክ፡ ነው፡ እያለ፡
ይናገራል፤ አንድም፤ ሐሳዊ፡
መሲሕ፡ ከሰማየ፡ ሰማያት፡
ወረድሁ፡ ከድንግል፡ ማርያም፡
ተወለድኩ፡ እያለ፡ ይናገራል፤

ወይትዔበይ፡ በልቡ፤

በልቡ፡ ይታበያል፡ ከኔ፡ በላይ፡
ማን፡ አለ፡ ይላል፤

ወበጕሕሉት፡ ያሐልቆሙ፡ ለብዙኃን፤

ብዙ፡ ሰዎችን፡ መቃብያንን፡ በተ
ንኮል፡ የጠፋቸዋል፡ አምላካች
ሁን፡ አምላክ፤ መሥዋዕታች
ሁን፡ መሥዋዕት፤ በዓላችሁን፡
በዓል፡ አደርጋለሁ፡ ብሎ፡
መጥቷልና፤

ወዲበ፡ መልአክ፡ ያቀውም፡ መልአከ፤

በአልዓዛር፡ ላይ፡ አለቃ፡ ይሾ
ማል፤ አንድም፤ በንጉሡ፡ ላይ፡
ንጉሠ፡ ነገሥት፡ ነኝ፡ ይላል፤

ወበያፌስ፡ ይቀጠቅጥ፡ እደ፤

በፋስ፡ የሰውን፡ እጅ፡ ይቀጠ
ቅጣል፤ አንድም፡ ወዘእንበለ፡
ያፌስ፡ ይቀጠቅጥ፡ እደ፡ ይላል፤
ሥልጣን፡ ገንዘቡ፡ ሳይሆን፡ የሰ
ውን፡ ሥልጣን፡ ያጠፋል፤

በእድ፡ ይቀጠቅጥ፡ እደ፤

በሥልጣን፡ የሰውን፡ ሥልጣን፡
ያጠፋል፤ አንድም፡ ወዘእንበለ፡
እድ፡ ይቀጠቅጥ፡ እደ፤ ሥል
ጣን፡ ገንዘቡ፡ ሳይሆን፡ የሰውን፡
ሥልጣን፡ ያጠፋል፤ አንድም፡
በእድ፡ ይትቀጠቀጥ፡ እዱ፡ በሥ
ልጣን፡ ሥልጣኑ፡ ይጠፋል፤
ቍስለ፡ ሥጋ፡ ታሞ፡ አንደበቱ፡
ተቆራርጦ፡ ሙቷልና፤ አንድም፡
ወዘእንበለ፡ እድ፡ ይትቀጠቀጥ፡
እዱ፡ ይላል፤ ሥልጣን፡ ገን
ዘቡ፡ ሳይሆን፡ ሥልጣኑ፡
ይጠፋል፤

፳፮፤ ወራዕየ፡ ሠርክ፡ ወነግህ፡
እሙን፡ ውእቱ፤

የነግህ፡ የሠርክ፡ ራእይ፡ የታ
መነ፡ ነው፤



ወአንተ፡ ዳንኤል፡ ሕትሞ፡ ለዝ፡ ራእይ፡
እስመ፡ ለብዙኅ፡ መዋዕል፤

ብዙ፡ ዘመን፡ ይኖራልና፡ ዳን
ኤል፡ ይህን፡ ራእይ፡ ጻፈው፤

፳፯፤ ወአነ፡ ዳንኤል፡ ደወይኩ፡ ወሰ
ከብኩ፡ መዋዕለ፤

እኔ፡ ዳንኤል፡ የእስራኤልን፡
መከራ፡ በአሰብሁ፡ ጊዜ፡ ብዙ፡
ቀን፡ ታምሜ፡ ተኛሁ፤

ወተንሣእኩ፡ ወገበርኩ፡ ግብረ፡ ንጉሥ፤

ተነሥቼ፡ የንጉሥን፡ ትእዛዝ፡
አደረግሁ፤ አንድም፡ የንጉሡ፡
ሰማይን፡ ትእዛዝ፡ አደረግሁ፡
አቍጣሮም፡ እንደሆን፡
አልታወቀ፤

ወአንከርኩ፡ ዘንተ፡ ራዕየ፤

ይህን፡ ራእይ፡ አደነቅሁ፤

ወአልቦ፡ ዘየአምሮ፤

ራእዩን፡ የሚያውቀው፡ የለም፤

## ምዕራፍ፡ ፱

### ጉባኤ

፩፤ በቀዳሚ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡
ለዳርዮስ፡ ወልደሱኢር፤

የሱኢር፡ ልጅ፡ ዳርዮስ፡ በነገሠ፡
በመጀመሪያው፡ ዘመን፡ ወልደ፡
ሱኢር፡ ባለው፡ ወልደ፡ አህሻዊ
ሮስ፡ የሚል፡ ይገኛል፤

ዘእምዘርአ፡ ሜዶን፡ ዘነግሠ፡ ላዕለ፡ መን
ግሥተ፡ ከላውዴዎን፤

በከላውዴዎን፡ መንግሥት፡ የነ
[illegible] ሜዶን፡ ልጅ፡ ወገን፡
የተወለደ፡ የሱኢር፡ ልጅ፡ ዳር
ዮስ፡ በነገሠ፡ በመጀመሪያ፡
ዘመን፤

፪፤ አነ፡ ዳንኤል፡ አእመርኩ፡ እም
ውስተ፡ መጻሕፍት፡ ኍልቈ፡ ዓመታት፡
ዘኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀበ፡ ኤርም
ያስ፡ በዘይሜለጥ፡ ሙስናሃ፡ ለኢየሩ
ሳሌም፡ ፸፡ ዓመት፤

ሰባ፡ ዘመን፡ ቆይቶ፡ የኢየሩ
ሳሌም፡ መከራዋ፡ በሚፈጸም፡
ገንዘብ፡ ወደ፡ ኤርምያስ፡ የመጣ፡
በመጻሕፍት፡ የተጻፈ፡ የዘመ
ኑን፡ ቍጥር፡ እኔ፡ ዳንኤል፡
አወቅሁ፤ ምነው፡ መጻሕፍት፡
ብሎ፡ አበዛ፡ በኤርምያስ፡ ብቻ፡
አይደለም፡ ቢሉ፡ ከሁለት፡ ስፍራ፡
ስለ፡ ተጻፈ፡ ወኃሊቆ፡ ፸፡ ዓመት፡
እትቤቀሎ፡ ለንጉሠ፡ ባቢሎን፡
ተብሎ፤ ወአመ፡ ኃልቀ፡ ፸፡
ዓመት፡ ይሔውፀክሙ፡ እግዚ
አብሔር፡ በሣህል፡ ተብሎ፡ ስለ፡
ተነገረ፤

፫፤ ወሜጥኩ፡ ገጽየ፡ ኀበ፡ እግዚአ
ብሔር፡ አምላኪየ፤

ገጹ፡ ልቡናዬን፡ ወደ፡ ፈጣሪዬ፡
ወደ፡ እግዚአብሔር፡ መለስሁ፤

ከመ፡ እኅሥሥ፡ ምሕረተ፡ ወሣህለ፡
በጸም፡ ወበሠቅ፡ ወበሐመድ፡ ወገነይኩ፤

ማቅ፡ ለብሼ፡ ትቢያ፡ ነስንሼ፡
በጾም፡ ይቅርታን፡ ቸርነትን፡
እሻ፡ ዘንድ፡ ለአንተ፡ ተገዛሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፬፤ ወእቤ፡ እግዚኦ፡ አምላክ፡ ዓቢይ፡ ወስቡሕ፤

አቤቱ፡ ገናና፡ የምትሆን፡ ፈጣሪ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፤

ዘተዓቅብ፡ ኪዳነከ፡ ወምሕረተከ፡ ለእለ፡ ያፈቅሩከ፡ ወለእለ፡ የዐቅቡ፡ ትእዛዘከ፤

ትእዛዝህን፡ ለሚጠብቁ፡ ለሚወዱህ፡ ይቅርታህን፡ መሐላሕን፡ የምታጸና፡ አቤቱ፡ ክቡር፡ ምስጉን፡ ነህ፡ እላለሁ፤

፭፤ አበስነ፡ ወዓመፅነ፡ ወጌገይነ፡ ወዓለውነ፤

ፈጽመን፡ በደልነ፡ ሳትነ፤

ወተግኅስነ፡ አምትእዛዝከ፤

ከሕገ፡ ኦሪት፤ አንድም፡ ከሕገ፡ ወንጌል፡ ራቅነ፤

ወእምፍትሕከ፤

ከአምልኮትህ፡ ራቅነ፤

፮፤ ወኢሰማዕናሆሙ፡ ለነቢያት፡ አግብርቲከ፤

ባሮችህ፡ ነቢያትን፡ አልሰማናቸውም፤

እለ፡ ነገርዎሙ፡ በስምከ፡ ለነገሥትነ፡ ወለመላእክቲነ፡ ወለአበዊነ፡ ወለኵሉ፡ ሕዝበ፡ ምድር፤

ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ብለው፡ ለነገሥታቱ፡ ለአለቆቻችን፡ ለአባቶቻችን፡ ለሕዝቡ፡ ሁሉ፡ የነገሩዋቸውን፡ ነቢያትን፡

፯፤ ወለከ፡ እግዚኦ፡ ጽድቅ፤

አቤቱ፡ ለአንተ፡ ቸርነት፡ ይገባሃል፤

ወለነ፡ኃፍረት፡ ለገጽነ፡ በዛቲ፡ ዕለት፤

በዚች፡ ቀን፡ ለኛ፡ ኃፍረት፡ ይገባናል፤

ለሰብአ፡ ይሁዳ፡ ወለእለ፡ ይነብሩ፡ ኢየሩሳሌም፤

በይሁዳ፡ በኢየሩሳሌም፡ ለሚኖሩ፤

ወለኵሎሙ፡ እስራኤል፡ እለ፡ ርሑቃን፡ ወቅሩባን፡ በኵሉ፡ ምድር፡ ኀበ፡ ዘረውኮሙ፡ ህየ፡ በማዕሌቶሙ፡ ዘዓለዉከ፤

እለ፡ ርሑቃን፡ አሥሩ፡ ነገድ፤ ወቅሩባን፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ናቸው፤ በወነጀሉህ፡ ወንጀላቸው፡ በበተንሃቸው፡ አገር፡ ሁሉ፡ ለአሥሩ፡ ነገድ፡ ለሁለቱ፡ ነገድ፡ ለእስራኤል፡ ሁሉ፡ ኃፍረት፡ ይገባቸዋል፤

፰፤ እግዚኦ፡ ለነ፡ ኃፍረት፡ ለገጽነ፤

አቤቱ፡ ለኛ፡ ኃፍረት፡ ይገባናል፤

ወለነገሥትነ፡ ወለመኳንንቲነ፡ ወለአበዊነ፡ እስመ፡ አበስነ፡ ለከ፤

አንተን፡ በድለንሃልና፡ ለነገሥታቱ፡ ለመኳንንቱ፡ ለአባቶቻችን፡ ኃፍረት፡ ይገባል፤

፱፤ እግዚኦ፡ አምላክ፡ ሣህል፡ ወምሕረት፡ እስመ፡ ክሕድነ፡ ወኢሰማዕነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክነ፤

የይቅር[illegible]



ችን፡ የእግዚብሔርን፡ ቃል፡ አልሰማንም፤

፲፤ ከመ፡ ንሑር፡ በሕግ፡ ዘወሀበነ፡ በቅድመ፡ ገጽነ፡ በእደ፡ አግብርቲሁ፡ ነቢያት፤

በባሮቹ፡ በነቢያት፡ ቃል፡ በአስተማረን፡ በሕግ፡ ጸንተን፡ እንኖር፡ ዘንድ፡ አልሰማንም፤

፲፩፤ ወኵሎሙ፡ እስራኤል፡ ዓለዉ፡ ሕገከ፤

እስራኤል፡ ሁሉ፡ ሕግህን፡ አፈረሱ፤

ወዓበዩ፡ ሰሚዓ፡ ቃለከ፤

ቃልህን፡ መስማት፡ እምቢ፡ አሉ፤

ወመጽአ፡ መርገም፡ ላዕሌነ፤

መከራ፡ በኛ፡ ላይ፡ መጣ፤

ወመሐላ፡ ዘጽሑፍ፡ ውስተ፡ ኦሪተ፡ ሙሴ፡ ገብረ፡ እግዚአብሔር

የእግዚአብሔር፡ አገልጋይ፡ ሙሴ፡ በኦሪት፡ ዘዳግም፡ የጻፈው፡ መሐላ፡ በኛ፡ ደረሰ፤

፲፪፤ እስመ፡ አበስነ፡ ሎቱ፡ ወዓቀመ፡ ቃሎ፡ እግዚአብሔር፡ ዘነበበ፡ ላዕሌነ፤

በድለናልና፡ እግዚአብሔር፡ በእኛ፡ የተናገረውን፡ ቃሉን፡ አጸና፤

ወዲበ፡ መኳንንቲነ፡ እለ፡ ኰነኑነ፤

[illegible] በመኳንንቱም፡ ላይ፡ [illegible]

ወአምጽኡ፡ ላዕሌነ፡ እኪተ፡ ዓቢየ፡ ዘኢኮነ፡ ከማሁ፡ በኵሉ፡ መትሐተ፡ ሰማይ፤

ከሰማይ፡ በታች፡ እንደዚህ፡ ያለ፡ ተደርጎ፡ የማያውቅ፡ ጽኑ፡ መከራ፡ በአመጡብን፤

ዘከመ፡ ኮነ፡ በኢየሩሳሌም፤

በኢየሩሳሌም፡ እንደ፡ ተደረገው፡ ተደርጎ፡ የማያውቅ፡ መከራ፡ በአመጡብን፤

፲፫፤ በከመ፡ ጽሑፍ፡ ውስተ፡ ሕገ፡ ሙሴ፡ ዝኵሉ፡ እኩይ፡ በጽሐነ፤

ሕጌን፡ ብትጠብቁ፡ አድናችኋለሁ፤ ባትጠብቁ፡ ሕያው፡ አነ፡ አማንየ፡ ብሎ፡ እንደ፡ ተጻፈ፡ ደረሰብን፤

ወኢተማኅለልነ፡ ለገጸ፡ እግዚብሔር፡ አምላክነ፡ ከመ፡ ንትመየጥ፡ እምኃጣውኢነ፤

ከኃጢአታችን፡ እንመለስ፡ ዘንድ፤ አንድም፡ ከኃጢአታችን፡ እንድንመለስ፡ በመሆን፡ የፈጣሪያችንን፡ ገጸ፡ ረድኤቱን፡ አለመንምና፤

ወነሃሊ፡ ኵሎ፡ ጽድቀከ፤

ቸርነትህን፡ እናስብ፡ ዘንድ፤

፲፬፤ ወተግሀ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ በኛ፡ መከራ፡ ለማምጣት፡ ተጋ፤ አንድም፡ በኛ፡ መከራ፡ ለማምጣት፡ ተግቷልና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአምጽአ፡ ላዕሌነ፡ መቅሠፍተ፤

በኛ፡ ላይ፡ መዓቱን፡ መቅሠፍ
ቱን፡ አመጣ፤ አንድም፡ አምጥ
ቶብናልና፤

እስመ፡ ጻድቅ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክነ፡
በኵሉ፡ ግብሩ፡ ዘገብረ፤

በሠራው፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ፈጣ
ሪያችን፡ እግዚአብሔር፡ እውነ
ተኛ፡ ስለሆነ፤ አንድም፤ የባሕ
ርይ፡ አምላክ፡ ነውና፤

ኢሰማዕነ፡ ቃሎ፤

እኛ፡ ግን፡ ቃሉን፡ አልሰማንም፤
አንድም፡ አልሰማንምና፤

፲፭፤ ወይእዜኒ፡ እግዚኦ፡ አምላክነ፡
ዘአውጻእኮሙ፡ ለሕዝብከ፡ እምድረ፡ ግብፅ፡
በእድ፡ ጽንዕት፡ ወገበርከ፡ ለነ፡ ስምዓ፡
እስከ፡ ዛ፡ ዕለት፤

በአሥር፡ መቅሠፍት፡ እስራኤ
ልን፡ ከግብፅ፡ ከአወጣሃቸው፡
ጀምሮ፡ እስከዚች፡ ቀን፡ ድረስ፡
ምስክር፡ ተአምራትህን፡ ያደረ
ግህ፡ ፈጣሪያችን፡ አቤቱ፤

አበስነ፡ ወአመፅነ፡ ወጌገይነ፤

አሁንም፡ ፈጣሪያችን፡ ፈጽመን፡
በደልነ፤ አንድም፡ በድለናልና፤

፲፮፤ እግዚኦ፡ በኵሉ፡ ምሕረትከ፡
ሚጥ፡ መዓተከ፡ ወመቅሠፍተከ፡ እምኔነ፤

አቤቱ፡ በፍጹም፡ ቸርነትህ፡ መዓ
ትህን፡ መቅሠፍትህን፡ ከኛ፡
አርቅ፤

ወእምሀገርከ፡ ኢየሩሳሌም፡ ወእምደ
ብረ፡ መቅደስከ፤

ከሀገርህ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ከመ
መስገኛህ፡ ቦታ፡ ከቤተ፡ መቅደስ፡
አርቅ፤

እስመ፡ አበስነ፡ ወጌገይነ፡ ወአበዊነኒ፡
በኢየሩሳሌም፤

በድለናል፡ ስተናልና፤ አባቶቻ
ችንም፡ በኢየሩሳሌም፡ በድለ
ዋልና፤

ወኃሥሩ፡ ሕዝብከ፡ በጽዕለት፡ በኵሉ፡
አድያሚነ፤

በመወሳሰኛችን፡ ላሉ፡ ሁሉ፡
ወገኖችህ፡ ለስድብ፡ ለተዋርዶ፡
ሁነዋልና፤

፲፯፤ ወይእዜኒ፡ እግዚኦ፡ አምላክነ፡
ስማዕ፡ ጸሎተ፡ ገብርከ፤

አሁንም፡ አቤቱ፡ ፈጣሪያችን፡
የኔን፡ የባሪያህን፡ ልመናዬን፡
ስማ፤

ወስእለቶ፤

ብዙ፡ ልመናዬን፤

ወአብርህ፡ ገጸከ፡ ላዕለ፡ መቅደስከ፡ ዘተ
መዝበረ፡ በእንቲአከ፡ እግዚኦ፤

አቤቱ፡ አንተን፡ ስላመለክን፡
በአንተ፡ ስላመነ፡ በፈረሰ፡ በቤተ፡
መቅደስ፡ ገጸ፡ ረድኤትህን፡
አብራ፤



፲፰፤ አምላኪየ፡ አፅምዕ፡ ዕዝነከ፡
ወስማዕ፤

ፈጣሪዬ፡ በጆሮህ፡ ልመናዬን፡
ጸሎቴን፡ ስማ፤

ወክሥት፡ አዕይንቲከ፡ ወርኢ፡ ሙስናነ፤

ዓይነ፡ ምሕረትህን፡ ልቡናህን፡
ግለጥ፡ ጥፋታችንን፡ እይ፡
ተመልከት፤

ወዘሀገርከ፡ እንተ፡ ተሰምየ፡ ስምከ፡
ላዕሌሃ፤

ስምህ፡ በሷ፡ ላይ፡ የተጠራ፡ የሀ
ገርህን፡ ጥፋት፡ እይ፤

ወአኮ፡ በጽድቅነ፡ ዘነቄሩ፡ ሣህለነ፡ ቅድሜከ፡
ዳዕሙ፡ በምሕረትከ፡ ብዙኅ፡ እግዚኦ፤

ዘናበጽሕ፡ ዘናቄርብ፡ ሲል፡ ነው፤
በምግባራችን፡ በትሩፋታችን፡
ልመናችንን፡ ወደ፡ አንተ፡ የም
ናደርስ፡ አይደለም፤ አቤቱ፡ በቸ
ርነትህ፡ ነው፡ እንጂ፤

፲፱፤ ስምዓነ፡ እግዚኦ፤

አቤቱ፡ ስማን፤

ተሣሃለነ፡ እግዚኦ፤

አቤቱ፡ ይቅር፡ በለን፤

አፅምዕ፡ እግዚኦ፡ ወግበር፤

አቤቱ፡ ልመናችንን፡ ስማ፡ ሚጠ
ትን፡ አድርግልን፤

ወኢታጕንዲ፡ በእንቲአነ፡ እግዚኦ፡
አምላክነ፤

አቤቱ፡ ፈጣሪያችን፡ ስለኛ፡ ሚጠ
ትን፡ አትዘግይ፤

እስመ፡ ተሰምየ፡ ስምከ፡ በላዕለ፡ ሀገርከ፡
ወዲበ፡ ሕዝብከ፤

ስምህ፡ በሀገርህ፡ በኢየሩሳሌም፡
በወገኖችህ፡ በእስራኤል፡ ላይ፡
ተጠርቷልና፤

፳፤ ወእንዘ፡ እነግር፡ ወእጼሊ፤

ይህን፡ ስናገር፡ ስጸልይ፤

እትነሀይ፡ በእንተ፡ ኃጢአትየ፡ ወኃጢ
አተ፡ ሕዝብየ፡ እስራኤል፤

እትአመን፡ ሲል፡ ነው፤ ኃጢአ
ቴን፡ የወገኖቼን፡ ኃጢአት፡ ሳስ
ተሠርይ፡ እታመናለሁ፡ ማለት፡
እንዲሠረይ፡ አደርጋለሁ፤

ወእገድፍ፡ ሣህልየ፡ ቅድመ፡ እግዚአብ
ሔር፡ አምላኪየ፡ በእንተ፡ ቤተ፡ መቅደሰ፡
ለአምላኪየ፤

አቁርብ፡ አበጽሕ፡ ሲል፡ ነው፤
ስለ፡ ፈጣሪየ፡ ማደሪያ፡ ስለ፡
ቤተ፡ መቅደስ፡ ልመናዬን፡ ወደ፡
እግዚአብሔር፡ አቀርባለሁ፤

፳፩፤ ወእንዘ፡ እነግር፡ ጸሎትየ፡
መጽአ፡ ብእሲ፡ ገብርኤል፡ ዘርኢኩ፡
በራዕይ፡ ቀዲሙ፡ እንዘ፡ ይሠርር፤

ይኸን፡ ስጸልይ፡ ቀድሞ፡ በራ
እይ፡ ያየሁት፡ ገብርኤል፡ ፈጥኖ፡
መጣ፤ በሰው፡ አምሳል፡ ስለ
ታየው፡ ብእሲ፡ አለ፤ አንድም፡
ቀድሞ፡ በራዕይ፡ ያየሁት፡ ገብ
ርኤል፡ ሲበር፡ መጣ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወገሠሠኒ፡ በጊዜ፡ መሥዋዕተ፡ ሠርክ፣

የሠርክ፡ መሥዋዕት፡ በሚሠዋበት፡ ጊዜ፡ ቀሰቀሰኝ፣ በባቢሎን፡ መሥዋዕት፡ ኑሮ፡ አይደለም፡ የኢየሩሳሌምን፡ መናገር፡ ነው፤

፳፪፤ ወአለበወኒ፡ ወተናገረ፡ ምስሌየ፣

ልብ፡ አስደረገኝ፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ተናገረ፤

ወይቤለኒ፡ ገብርኤል፡ ዳንኤል፡ ዳንኤል፣

ገብርኤል፡ ዳንኤል፡ ዳንኤል፡ አለኝ፤

ወዳእኩ፡ ወመጻእኩ፡ ከመ፡ አለቡከ፡ ይእዜ፡ ጥበበ፣

ሚጠትን፤ አንድም፡ ሥጋዌን፡ ልብ፡ አስደርግህ፡ ዘንድ፡ ዛሬ፡ መጣሁ፤

፳፫፤ በቀዳሚ፡ ጸሎትከ፡ ወጽአ፡ ቃል፣

በመጀመሪያ፡ ልመናህ፡ ንገረው፡ የሚለኝ፡ ቃል፡ ወጣ፤

ወመጻእኩ፡ እዜኑከ፡ እስመ፡ ብእሴ፡ ፍትወት፡ አንተ፣

ሊነግሩህ፡ የምትወድ፤ አንድም፡ ሊነግሩህ፡ የምትወደድ፡ ሰው፡ ነህና፡ ልነግርህ፡ መጣሁ፤

ወሐልዮ፡ ለነገር፡ ወለቡ፡ ዘርኢከ፣

ነገሩን፡ አስበህ፡ ያየኸውን፡ ልብ፡ አድርገው፤

፳፬፤ ፸፡ ሰንበታተ፡ አድሞሙ፡ ለሕዝብከ፣

ወገኖችህን፡ ሰባ፡ ሱባዔ፡ ቅጠራቸው፣ በሰባ፡ ሱባዔ፡ ጌታ፡ ይወለዳል፣ ብለህ፡ ንገራቸው፣ ሰባውን፡ አንድ፣ ሰባውን፡ አንድ፡ እያሉ፡ እስከ፡ ሰባት፡ ቢቆጥሩ፡ አራት፡ መቶ፡ ዘጠና፡ ይሆናል፣ በዘመኑ፡ የነበሩ፡ ሰለስቱ፡ ደቂቅ፡ ስድስት፡ መቶ፡ አሉ፣ አይጣላም፡ ቢሉ፡ አይጣላም፣ እነዚያ፡ ከዔዋዌ፡ እስከ፡ ዕርገት፡ ድረስ፡ ቈጥረው፡ ነው፣ እሱ፡ ከሚጠት፡ እስከ፡ ልደት፡ ቈጥሮ፡ ሐተታ፡ እንዳለፈው፡ ነው፣ ሰባውን፡ ሱባዔ፡ ከሶስት፡ ስፍራ፡ ተናገረው፡ እንደ፡ ሶስት፡ ምስክር፡ ጥፋ፡ በሥሉስ፡ ልማ፡ በሥሉስ፡ እንዲሉ፣ አንድም፡ ሰባቱን፡ ሱባዔና፡ ስልሳ፡ ሁለቱን፡ ሱባዔ፡ ቢያገናኙት፡ ስልሳ፡ ዘጠኝ፡ ይሆናል፤ እሱ፡ ሱባዔ፡ የገባበትን፡ ትቶ፣ አንድም፡ ጌታ፡ የተወለደበትን፡ ትቶ፤

ወለሀገርከ፡ ቅድስት፣

ክብርት፡ የምትሆን፡ ሀገርህ፡ ኢየሩሳሌምን፡ ቅጠራት፤

ከመ፡ ትሠለጥ፡ ኃጢአት፡ ወትትሐተም፡ ጌጋይ፣

በሚጠት፤ አንድም፡ በዘመነ፡ ሥጋዌ፡ ኃጢአት፡ እንድትጠፋ፡ ቅጠራት፤



ወይደመሰስ፡ አበሳ፣

በደል፡ ይጠፋል፤

ወትሠረይ፡ ዓመፃ፣

ኃጢአት፡ ትሠረያለች፤

ወትመጽእ፡ ጽድቅ፡ እንተ፡ ለዓለም፣

ለዘላለም፡ የምትሆን፡ ሚጠት፡ ትመጣለች፤ አንድም፡ ለዘለዓለም፡ የምትሆን፡ ወንጌል፡ ትነገራለች፤ አንድም፡ ትሩፋት፡ ትሠራለች፤

ወይትዓተብ፡ ራእየ፡ ነቢያት፣

ይትገሃድ፡ ይትከሠት፡ ሲል፡ ነው፤ ነቢያት፡ የአክዩ፡ አሶር፡ በዕብራውያን፣ ወዕብራውያን፡ የአክዩ፡ በአሶር፡ ብለው፡ የተናገሩት፡ ይገለጣል፤

ወይትቀባዕ፡ ቅዱሰ፡ ቅዱሳን፣

ቅዱሰ፡ ቅዱሳን፡ ጌታ፡ ይከብራል፣ የባሕርይ፡ ክብሩን፡ ገንዘብ፡ ያደርጋል፤

፳፭፤ አእምር፡ ወለቡ፡ እምፀዓተ፡ ቃሉ፡ ዘታወሥእ፣

ንገረው፡ የሚለኝ፡ ቃሉ፡ ከመውጣቱ፡ የተነሣ፡ የምትመልሰውን፡ እወቅ፤ አንድም፡ እምጻአተ፡ ቃል፡ ዘአወሥአከ፡ ንገረው፡ የሚለኝ፡ ቃል፡ ከመውጣቱ፡ የተነሣ፡ የምመልስልህን፡ እወቅ፤ አንድም፡ እምጸአተ፡ ቃሉ፡ ዘታወሥእ፡ ንገረው፡ የሚለኝ፡ አካላዊ፡ ቃሉ፡ ከመምጣቱ፡ የተነሣ፡ የምትመልሰውን፡ እወቅ፤ አንድም፡ እምጸአተ፡ ቃል፡ ዘአወሥአከ፣ አካላዊ፡ ቃል፡ ከመምጣቱ፡ የተነሣ፡ የምመልስልህን፡ እወቅ፤

ወትትሐነፅ፡ ኢየሩሳሌም፡ እስከ፡ ክርስቶስ፡ ንጉሥ፣

ኢየሩሳሌም፡ ጌታ፡ እስቲወለድ፡ ድረስ፡ በመፍረስ፡ በመታነፅ፤ ቤተ፡ መቅደስ፡ በመሆን፡ ቆይታ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ በመሆን፡ ትታነጻለች፤

ሰብአተ፡ ሰንበታተ፡ ስሳ፡ ወክልዔተ፡ ሰንበታተ፣

ሰባት፡ ሱባዔ፣ ስድሳ፡ ሁለት፡ ሱባዔ፡ ቆይታ፤

ይትመየጥ፡ ወይትሐነፅ፡ መርኅባ፣

አደባባይዋ፡ የቤተ፡ መቅደስ፡ አደባባይ፡ በመሆን፡ ይታነፃል፤ አንድም፡ አደባባይዋ፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ አደ ባባይ፡ ወደ፡ መሆን፡ ይመለሳል፤

ወዓረፍታ፣

ቅጽሯ፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ ቅፅር፡ በመሆን፡ ይታነጻል፤

ወይትከዓው፡ መዋዕል፣

ተድላ፡ ደስታ፡ ያለበት፡ ዘመን፡ ይመጣል፤

www.ethiopianorthodox.org

፳፮፤ ወእምድኅረ፡ ስሳ፡ ወክልዔቱ፡ ሰንበታት፡ ይጠፍዕ፡ ቅብዓት፡ ወፍትሕ፡ አልቦ፡ ኀቤሁ፤

ስቀለው፡ ስቀለው፡ ማለት፡ የለም፤ ከስልሳ፡ ሁለት፡ ሱባዔ፡ በኋላ፡ አፍአዊ፡ ቅብአ፡ ክህነት፡ ቅብዓ፡ መንግሥት፡ ይጠፋል፤ ሐተ ታው፡ እንዳሰፈጡ፡ ነው፤

ወያማስን፡ ሀገረ፡ መቅደስነ፤

ኢየሩሳሌምን፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ያጠፋል፤

ምስለ፡ ንጉሥ፡ ዘይመጽእ፤

ከአንጥያኮስ፡ ጋራ፡ የሚመጣ፡ ሠራዊት፡ ያጠፋዋል፤ አንድም፡ የንጉሥ፡ ጣዖት፤ አንድም፡ ከጥ ጦስ፡ ጋራ፡ የሚመጣ፡ ሠራዊት፤ አንድም፡ ጣዖት፤ አንድም፡ ከሐ ሳዊ፡ መሲሕ፡ ጋራ፡ የሚመጣ፡ ሠራዊት፡ ያጠፋታል፤ አንድም፡ ጣዖት፡ ያጠፋታል፤

ወይትመተሩ፡ በማየ፡ አይኅ፡ እስከ፡ ለዝሉፉ፤

እንደ፡ ማየ፡ አይኅ፡ ባለ፡ መቅሠ ፍት፡ እስከ፡ ዘለዓለም፡ ይጠፋሉ፤

ይትራገዙ፡ ወይትቃተሉ፤

ይቀራረዳሉ፡ ይዋጋሉ፤

ወይሠዓር፡ መሥዋዕት፤

መሥዋዕት፡ ይጠፋል፤

፳፯፤ ወይማስን፡ መዓዝኒሁ፡ ለግሙራ፤

የኢየሩሳሌም፡ አራቱ፡ መዓዝኗን፡ ያጠፋል፤ አንድም፡ አራት፡ መዓ ዝን፡ ያለው፡ ልብሰ፡ ተክህኖን፡ ያጠፋል፤ አንድም፡ አራት፡ መዓ ዝን፡ ያለው፡ ምሥዋዓ፡ ብር ቱን፡ ያጠፋል፤

ወይጸንዕ፡ ሥርዓቶሙ፡ ለብዙኃን፡ አሐቲ፡ ሰንበተ፡ ወመንፈቀ፡ ሰንበት፤

አንድ፡ ሱባዔ፡ ተኩል፡ ቆይቶ፡ የመቃብያን፡ ሥርዓታቸው፡ ይጸ ናል፤ የአንጥያኮስ፡ ሶስት፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፤ የጥጦስ፡ ሶስት፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፤ የሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ሶስት፡ ዓመት፡ ከመ ንፈቅ፤ ይኸን፡ አጠራቅሞ፡ አንድ፡ ሱባዔ፡ ተኩል፡ አለ፤ እንዲህስ፡ አድርጎ፡ ሱባዔ፡ አይቆጥርም፡ ብሎ፡ ጳውሎስ፡ ማመኑ፡ ጌታ፡ ባረገ፡ በስምንተኛይቱ፡ ዘመን፡ ነው፤ እንዲቱን፡ ዘመን፡ ሲያይ፡ እንዲኽ፡ አለ፤ አንድም፡ የምዕ መን፡ ሥርዓቷ፡ እስከ፡ ስም ንት፡ ዘመን፡ ቆይታ፡ ትጸናለች፤

ይሠዐር፡ መሥዋዕት፡ ወሞጻሕት፤

መሥዋዕት፡ ወይን፡ ይጠፋል፤

ወይማስን፡ ርኵሰሙ፡ በውስተ፡ መቅደስ፤

በቤተ፡ መቅደስ፡ ያለ፡ ... ይጠፋል፤



ወእስከ፡ ማኅለቅተ፡ ዓመታት፡ ይትወ ሀብ፡ ዕድሜሁ፡ ለሙስና፤

በመቃብያን፡ የታዘዘ፡ መከራ፡ እስቲፈጸም፡ ድረስ፡ ደርሶ፡ የአ ንጥያኮስ፡ ዘመን፡ ለጥፋት፡ ይሰ ጣል፤ አንድም፡ ሶስት፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፡ ሲፈጸም፡ አንጥያ ኮስ፡ ለጥፋት፡ ይሰጣል፤

## ምዕራፍ፡ ፲፤

ራእይ፡ ዘርእየ፡ ዳንኤል፤

ዳንኤል፡ ያየው፡ ራእይ፡ ይህ፡ ነው፤

፩፤ ወአመ፡ ሠላስ፡ ዓመተ፡ መን ግሥቱ፡ ለቂሮስ፡ ንጉሠ፡ ፋርስ፡ ተከ ሥተ፡ሎቱ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ለዳን ኤል፡ ዘተሰምየ፡ ስሙ፡ ብልጣሶር፤

ቂሮስ፡ በነገሠ፡ በሦስተኛው፡ ዘመን፡ ስሙ፡ ብልጣሶር፡ ለተ ባለ፡ ለዳንኤል፡ ቃለ፡ እግዚአብ ሔር፡ ተገለጠለት፤

ወእሙን፡ ነገሩ፤

ነገሩ፡ የታመነ፡ ነው፤

ወኃይል፡ ዓቢይ፡ ተውህበ፡ ሎቱ፡ በው ስተ፡ ራእይ፤

ራእይ፡በማየት፡ብዙ፡ምሥጢር፡ ብዙ፡ ዕውቀት፡ ተገለጠለት፤

፪፤ ወውእተ፡ አሚረ፡ አነ፡ ዳንኤል፡ ሀሎኩ፡ እላሁ፡ ፫ቱ፡ ሰንበታተ፡ መዋዕለ፤

ያን፡ ጊዜ፡ እኔ፡ ዳንኤል፡ ሦስት፡ ... ሱባዔ፡ ... ሳዝን፡ ... ነበርሁ፤

ኢፈቀድኩ፡ እብላዕ፡ እክለ፤

እህል፡ እበላ፡ ዘንድ፡ አልወ ደድሁም፤

ወኢቦአ፡ ውስተ፡ አፉየ፡ ሥጋ፡ ወወይን፤

ሥጋ፡ ወይን፡ ወደአፌ፡ አልገባም፤

፫፤ ወቅብዓ፡ ኢተቀባዕኩ፡ እስከ፡ ይትፈጸሙ፡ ፫ቱ፡ ሰንበታተ፡ መዋዕል፤

ሦስቱ፡ የቀን፡ ሱባዔ፡ እስቲፈ ጸም፡ ድረስ፡ ቅቤ፡ ዘይት፡ አልተ ቀባሁም፤

፬፤ ወኮነ፡ እምድኅረ፡ ፲ቱ፡ ወ፰ቱ፡ ዓመት፤

ከአሥራ፡ ስምንት፡ ዘመን፡ በኋላ፡ እንዲህ፡ ሆነ፤ አሥራ፡ ስምንት፡ ያለው፡ አሥሩ፡ የብልጣሶር፤ ስድስቱ፡ የዳርዮስ፤ ሁለቱ፡ የቂ ሮስ፡ ነው፤ አንድም፤ አሥራ፡ ሦስት፡ የብልጣሶር፡ የዳርዮስ፡ አንድ፤ የቂሮስ፡ ሦስት፤ ይህ፡ አስራ፡ ሰባት፡ ይሆናል፤ አስራ፡ ሰባተኛው፡ ሲፈጸም፡ አስራ፡ ስምንተኛው፡ ሲጀመር፡ ነው፤

በ፳፡ ወ፬ዱ፡ ጽባሕ፡ በረቡዓ፡ ሠርቀ፡ ወርኅ፡ ቀዳሚ፤

በ፳፡ ወ፬ዱ፡ ጽባሕ፡ ያለው፡ ከመጋቢት፡ አስራ፡ ሰባት፤ ከሚ ያዝያ፡ አራት፡ ቀን፡ አምጥቶ፤ መጋቢት፡ በገባ፡ በአስራ፡ ሰባት፤

www.ethiopianorthodox.org

ሚያዝያ፡ በባተ፡ በአራት፡ ቀን፡ እንዲህ፡ ሆነ፤ አንድም፣ በእሥራ፡ ወክልዔቱ፡ ጽባሕ፡ ይላል፣ ከመጋቢት፡ አስራ፡ ስምንት፣ ከሚያዝያ፡ አራት፡ ቀን፡ አምጥቶ፡ በእሥራ፡ ወክልዔቱ፡ ጽባሕ፡ ያለው፡ ይህ፡ ነው፤ አንድም፣ በእሥራ፡ ወአርባዕቱ፡ ጽባሕ፡ ይላል፤ ከመጋቢት፡ ሀያ፡ ቀን፣ ከሚያዝያ፡ አራት፡ ቀን፡ አምጥቶ፡ በእሥራ፡ ወአርባዕቱ፡ ጽባሕ፡ ያለው፡ ይህ፡ ነው፤ አንድም፡ በእሥራ፡ ወአርባዕቱ፡ ለሠርቀ፡ ወርኅ፡ ቀዳማይ፡ ይላል፣ ሚያዝያ፡ በባተ፡ በሀያ፡ አራት፡ ቀን፡ ራእይ፡ አይቷል፤

ወሀሎኩ፡ አነ፡ ኀበ፡ ፈለግ፡ ዓቢይ፡ ዘውእቱ፡ ጤግሮስ፣

ይኸውም፡ ጤግሮስ፡ ነው፣ እኔ፡ በትልቁ፡ ፈሳሽ፡ ውሀ፡ ሳለሁ፤

፭፤ አንሣዕኩ፡ አዕይንትየ፡ ወነጸርኩ፣

አንገቴን፡ አቅንቼ፡ አየሁ፣

ወናሁ፡ ፩ዱ፡ ብእሲ፡ ዘይለብስ፡ ጠብደነ፣

ግምጃ፡ የለበሰ፡ እነሆ፡ አንድ፡ ሰው፡ አየሁ፣ የባቢሎንን፡ ሰዎች፡ ደም፡ አፈስሳለሁ፡ ሲል፡ መልአክ፡ ቀይ፡ ግምጃ፡ ለብሶ፡ ታይቶታል፣

ወቅነቱ፡ ሐቌሁ፡ በወርቀ፡ ያፌዝ፣

ወገቡን፡ በወርቅ፡ ዝናር፡ ታጥቋል፤

፮፤ ወነፍስቱሂ፡ ከመ፡ ተርሴስ፣

ሰውነቱ፡ እንደ፡ ዕንቊ፡ ነው፤

ወገጹሂ፡ ከመ፡ ራእየ፡ መብረቅ፣

ፊቱ፡ እንደ፡ መብረቅ፡ የሚያስደነግጥ፡ ነው፤

ወአዕይንቲሁ፡ ከመ፡ ማኅቶተ፡ እሳት፣

ዓይኖቹ፡ እንደ፡ እሳት፡ ፋና፡ ናቸው፡ መስሎ፡ ይታየዋል፣ በዓይነ፡ መዓት፡ አለሁ፡ ሲል፤

እደዊሁ፡ ወእገሪሁ፡ ከመ፡ ብርት፡ ርሱን፣

እጁ፡ እግሩ፡ እንደ፡ ጋለ፡ ብረት፡ ነው፣ የነዚያን፡ ደም፡ አፈስሳለሁ፡ ሲል፤

ወቃለ፡ ነገሩ፡ ከመ፡ ድምፀ፡ አሕዛብ፡ ብዙኅ፣

የነገሩ፡ ፍሬ፡ እንደ፡ ብዙ፡ አሕዛብ፡ ድምፅ፡ ነው፣ ያስፈራል፣ አንድም፡ ፩ዱ፡ ብእሲ፡ የተባለ፡ ጌታ፡ ነው፣ ጠብደን፡ ሥጋ፡ ነው፣ ጌታን፡ ሥጋ፡ ለብሶ፡ አየሁት፣ ወርቅ፡ ዝናር፡ ታጥቆ፡ አየሁት፡ ማለት፡ ጽንዓ፡ ተዋሕዶውን፡ መናገር፡ ነው፣ ነፍስቱሂ፡ ከመ፡ ተርሴስ፡ ኤጲስ፡ ቆጾሳት፡ እንደ፡ ዕንቊ፡ ናቸው፣ ገጹሂ፡ ጳጳሳት፡ እንደመብረቅ፡ ያስፈራሉ፤



አዕይንቲሁ፣ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ እንደ፡ ፋና፡ ናቸው፤ እደዊሁ፡ ወእገሪሁ፣ ቀሳውስት፡ ዲያቆናት፡ እንደ፡ ጋለ፡ ብረት፡ ናቸው፤ አንድም፣ ነፍስቱሂ፡ ጳጳሳት፡ ኤጲስ፡ ቆጾሳት፣ ገጹሂ፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፣ አዕይንቲሁ፡ ጳጳሳት፡ ቀሳውስት፣

እደዊሁ፡ ዲያቆናት፡ ወእገሪሁ፡ ምዕመናን፡ እንደ፡ ጋለ፡ ብረት፡ ናቸው፡ ወቃለ፡ ነገሩ፡ በቃሉ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ያስፈራል፤

፯፤ ወርኢኩ፡ አነ፡ ዳንኤል፡ ባሕቲትየ፡ ዘ፡ ራእየ፣

ይኸን፡ ራእይ፡ እኔ፡ ዳንኤል፡ ብቻዬን፡ አየሁ፤

ወዕደው፡ እለ፡ ምስሌየ፡ ኢርእዩ፡ ዘ፡ ራእየ፣

ከኔ፡ ጋራ፡ ያሉ፡ ሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ ይህን፡ ራእይ፡ አላዩም፣ ሠለስቱ፡ ደቂቅስ፡ አይተዋል፡ ብሎ፡ ሌሎች፡ ይህን፡ ራእይ፡ አላዩም፤

ዳዕሙ፡ ዓቢይ፡ ድንጋፄ፡ አኃዞሙ፣

ፅኑዕ፡ ድንጋፄ፡ አገኛቸው፡ እንጂ፤

ወእምፍርሃት፡ ጐዩ፣

ከፍርሃት፡ የተነሣ፡ ሸሹ፤

፰፤ ወአነ፡ ባሕቲትየ፡ ተረፍኩ፣

[illegible]

ወርኢኩ፡ ዘ፡ ራዕየ፡ ዓቢየ፣

ይህን፡ ደግ፡ ራእይ፡ አየሁ፤

ወኢተርፈ፡ ላዕሌየ፡ ኃይልየ፣

አእምሮዬ፡ ተለየኝ፤

ወክብርየ፡ ተወለጠ፡ በላዕሌየ፣

በኔ፡ ላይ፡ ያለ፡ መልኬ፡ ተለወጠ፤

ወኢአኃዝኩ፡ ኃይለ፣

ዕውቀት፡ አላገኘሁም፤

፱፤ ወሰማዕኩ፡ ቃለ፡ ነገሩ፣

የነገሩን፡ ፍሬ፡ ሰማሁ፤

ወሰሚዕየ፡ ደንገፅኩ፡ ወወደቁ፡ በገጽየ፡ ውስተ፡ ምድር፣

የሚያስፈራ፡ ነገሩን፡ ሰምቼ፡ ደነገጥሁ፣ በግምባሬ፡ ፍግም፡ ብዬ፡ ወደቅሁ፤

፲፤ ወናሁ፡ እድ፡ እደውየ፡ አኀዘኒ፣

እነሆ፡ የመልአኩ፡ እጅ፡ እጄን፡ ያዘኝ፤ አንድም፡ መልአኩ፡ በእጁ፡ እጄን፡ ያዘኝ፤

ወአቀመኒ፡ በብረክየ፣

በእግሬ፡ አቆመኝ፣ በምን፡ ያቆመው፡ ኑሯል፡ ቢሉ፡ በዕውቀት፡ አፀናኝ፡ ሲል፡ ነው፤

፲፩፤ ወይቤለኒ፡ ዳንኤል፡ ብእሴ፡ ፍትወት፡ አንተ፣

ሊነግሩህ፡ የምትወድ፡ ሊነግሩህ፡ የምትወደድ፡ አንተ፡ ዳንኤል፤

ለቡ፡ ዘ፡ ነገረ፡ ዘእነግረከ፡ አነ፣

እኔ፡ የምነግርህን፡ ይህን፡ ነገር፡ ልብ፡ አድርግ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወቁም፡ በኃይልከ፤

በአእምሮህ፡ ጽና፤

እስመ፡ ይእዜ፡ ተፈናኩ፡ ኀቤከ፤

ዛሬ፡ ወደ፡ አንተ፡ ተልኬያለሁና፤

ወሶበ፡ ይቤለኒ፡ ዘ፡ ነገረ፡ ተንሣእኩ፡ እንዘ፡ እርእድ፤

ይህን፡ ነገር፡ በነገረኝ፡ ጊዜ፡ እየራድሁ፡ እየተንቀጠቀጥሁ፡ ተነሣሁ፤

፲፪፤ ወይቤለኒ፡ ኢትፍራኍ፡ ዳንኤል፤

ዳንኤል፡ አትፍራ፡ አለኝ፤

እስመ፡ እምቀዳሚት፡ ዕለት፡ ዘአግባዕከ፡ ልበከ፤ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ትሠራኂ፡ ፍኖትከ፡ ወትለቡ፡ በገጸ፡ አምላክከ፤

ቀኖና፡ ከገባህበት፡ ቀን፡ ጀምሮ፡ በቀኖና፡ ትክናወን፡ ዘንድ፡ ገጸ፡ ረድኤቱን፡ ለማግኘት፤ አንድም፡ የፈጣሪህን፡ ፊት፡ ታይ፡ ዘንድ፤

ተሰምዐ፡ ነገርከ፤

ነገርህ፡ ተሰማ፤

ወአነ፡ መጻእኩ፡ በእንተ፡ ቃልከ

እኔ፡ ስለተናገርኸው፡ ነገር፡ መጣሁ፤

፲፫፤ ወመልአከ፡ ንጉሠ፡ ፋርስ፡ ይቀውም፡ ቅድሜየ፡ ፳ወ፩ደ፡ ዕለተ፤

እስከዛሬም፡ ድረስ፡ አለመምጣቴ፡ የፋርስን፡ ንጉሥ፡ ጣዖት፡ የሚያስመልክ፡ ዲያብሎስ፡ ሀያ፡ አንድ፡ ቀን፡ በፊቴ፡ ቢቆም፡ ነው፤ እርሱን፡ እንደምን፡ ጥየው፡ ልምጣ፡ ብዬ፡ ሰነበትሁ፤ አንድም፡ የፋርስን፡ ንጉሥ፡ የሚገዛ፡ ቅዱስ፡ ሚካኤልን፡ ተክቼ፡ መጣሁ፤

ወናሁ፡ ሚካኤል፡ ፩ዱ፡ እመላእክት፡ ቀደምት፡ መጽአ፡ ይርድአኒ፤

ከቀደሙ፡ መላእክት፡ አንዱ፡ ሚካኤል፡ እነሆ፡ ሊረዳኝ፡ መጣ፤

ወኪያሁ፡ ኃደጉ፡ ህየ፡ ምስለ፡ መልአከ፡ ንጉሠ፡ ፋርስ፤

እሱን፡ ተክቼ፡ መጣሁ፤ የፋርስን፡ ንጉሥ፡ ጣዖት፡ የሚያስመልክ፡ ዲያብሎስ፤

፲፬፤ ወመጻእኩ፡ እንግርከ፡ ዘይረክቦሙ፡ ለሕዝብከ፡ በደኃሪ፡ መዋዕል፤

በኋላ፡ ዘመን፡ ወገኖችህን፡ የሚያገኛቸውን፡ እነግርህ፡ ዘንድ፡ መጣሁ፤

እስመ፡ ራእይ፡ በዕለቱ፤

ራእዩ፡ በጊዜው፡ ጊዜ፡ ይደረጋልና፤

፲፭፤ ወሶበ፡ ነገረኒ፡ ዘ፡ ነገረ፡ ሜጥኩ፡ ገጽየ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ወብህምኩ፤

ይህን፡ ነገር፡ በነገረኝ፡ ጊዜ፡ ፊቴን፡ ወደምድር፡ መለስሁ፤ መናገር፡ ተሳነኝ፤

፲፮፤ ወናሁ፡ ከመ፡ በአምሳለ፡ ወልደ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው፡ ገሠሠኒ፡ ከናፍርየ፤

እነሆ፡ በሰው፡ አምሳል፡ መጥቶ፡ ከንፈሬን፡ [illegible]



ወከሠትኩ፡ አፉየ፡ ወነበብኩ፤

አፌን፡ ገልጬ፡ ተናገርሁ፤

ወእቤሎ፡ ለዘይቀውም፡ ቅድሜየ፡ እግዚኦ፡ እምራእይከ፡ ተገፍትዓት፡ ነፍስየ፡ በላዕሌየ፡ ወኃጣእኩ፡ ኃይለ፤

በፊቴ፡ የቆመውን፡ እንዲህ፡ አልሁት፤ አቤቱ፡ መልክህን፡ ከማየቴ፡ የተነሣ፡ በእኔ፡ ላይ፡ ያለች፡ ሰውነቴ፡ ግልብጥብጥ፡ አለች፤ አእምሮ፡ አጣሁ፤

፲፯፤ ወእፎ፡ ይክል፡ ገብርከ፡ ተናግሮ፡ ምስለ፡ እግዚእየ፤

እኔ፡ ባሪያህ፡ ከጌታዬ፡ ጋር፡ ለመናገር፡ እንደምን፡ ይቻለኛል፤

ወአነሂ፡ እምይእዜ፡ ኢይቀውም፡ ኃይልየ፤

ከዛሬ፡ ጀምሮ፡ ኃይሌ፡ አይጸናም፤

ወኢተርፈ፡ እምነ፡ መንፈስየ፤

ከአእምሮዬ፡ የቀረ፡ የለም፤

፲፰፤ ወዳግመ፡ ገሠሠኒ፡ ከመ፡ ራእየ፡ ብእሲ፡ ወአጽንዓኒ፤

ዳግመኛ፡ በሰው፡ አምሳል፡ መጥቶ፡ ቀሰቀሰኝ፡ በአእምሮ፡ አጸናኝ፤

፲፱፤ ወይቤለኒ፡ ኢትፍራህ፡ ብእሴ፡ ፍትወት፡ አንተ፤

ሊነግሩህ፡ የምትወድ፤ ሊነግሩህ፡ የምትወደድ፡ አንተ፡ አትፍራ፡ [illegible]

ሰላም፡ ለከ፡ ጽናዕ፡ ወኃይል፤

ፍቅር፡ አንድነት፡ ይገባሃል፡ ጽና፡ በርታ፤

ወእንዘ፡ ይትናገረኒ፡ ጸናዕኩ፤

ሲናገረኝ፡ ጸናሁ፤

ወእቤሎ፡ ንግረኒ፡ እግዚእየ፡ እስመ፡ አፅናዕከኒ፤

ጌታዬ፡ አጽንተኸኛልና፡ ንገረኝ፡ አልሁት፤

፳፤ ወይቤለኒ፡ ሶበሰ፡ አእመርከ፡ ለምንት፡ መጻእኩ፡ ኀቤከ፤

ባታውቅ፡ ልነግርህ፡ መጣሁ፡ እንጂ፡ ስታውቅ፡ ልነግርህ፡ መጣሁ? አንድም፡ ብታውቅስ፡ ልነግርህ፡ መጣሁ፡ እንጂ፡ ለምን፡ መጣሁ?

ወይእዜኒ፡ እትመየጥ፡ ከመ፡ ዕፅብዖ፡ ለመልአከ፡ ንጉሠ፡ ፋርስ፤

አሁንም፡ የፋርስን፡ ንጉሥ፡ ጣዖት፡ የሚያስመልክ፡ ሰይጣንን፡ እጣላው፡ ዘንድ፡ እመለሳለሁ፤

ወእንዘ፡ እወጽእ፡ አነ፡ ናሁ፡ መጽአ፡ መልአከ፡ አረማውያን፤

በሩን፡ ስወጣ፡ ሰይጣን፡ መጣ፤ አንድም፡ መልአክ፡ አራምያን፡ ይላል፤ የአረማውያን፡ መቅጫ፡ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ መጣ፤

፳፩፤ ወዳዕሙ፡ እነግረከ፡ ትእዛዘ፡ ዘተአዘዘ፡ በመጽሐፈ፡ ጽድቅ፤

ዘተጽሕፈ፡ ሲል፡ ነው፤ ነገር፡ ግን፡ በኦሪት፡ የተጻፈውን፡ እነግርሃለሁ፤ ወአዘዘኒ፡ ትእዛዘ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘዜነዎ፡ በመጽሐፈ፡ ጽድቅ፤
የሚል፡ይገኛል፤በአራት፡ዘኍልቍ፤
ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ ለበልዓም፡
የነገረውን፡ ለዳንኤል፡ ነገረው፡
ብሎ፡ አዘዘኝ፤ የአክዩ፡ አሶር፡
በዕብራውያን፡ ያለውን፡ ነው፤

ወአልቦ፡ መኑሂ፡ ዘየዓብየኒ፡ በዝንቱ፡ ዳዕሙ፡ ሚካኤል፡ መልአክክሙ፤

እስራኤልን፡ በመራዳት፡ ማንም፡
ማን፡ የሚበልጠኝ፡ የለም፤ እንጂ፡
ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ እንደሆነ፡ ነው፡
እንጂ፤ አንድም፡ ቅዱስ፡ ሚካ
ኤል፡ ነው፡ እንጂ፡ ማንም፡ ማን፡
የሚበልጠኝ፡ የለም፡ መጋቤ፡
ብሉይ፡ ነውና፡፡

## ምዕራፍ፡ ፲ወ፩

### ጉባዔ፤

፩፤ ወአነ፡ በዓመት፡ ቀዳሚ፡ ዘዳርዮስ፡ ሜዶናዊ፤

የሜዶን፡ ሰው፡ ዳርዮስ፡ በነገሠ፡
በመጀመሪያው፡ ዘመን፤ አን
ድም፡ ወኮነ፡ በዓመት፡ ቀዳሚ፡
ዘዳርዮስ፡ ይላል፤ አንድም፡ ወኮነ፡
በሣልት፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡
ለቂሮስ፡ ይላል፤

ቆምኩ፡ ለአኃይሎቱ፡ ወለረድኤቱ፤

ኮነ፡ ያለውን፡ ቆምኩ፡ ብሎ፡
አመጣው፤ ዳርዮስን፡ ላበረታ
ታው፡ ልረዳው፡ ቆምሁ፤ አን
ድም፡ ለአኃይሎትከ፡ ወለረድ
ኤትከ፡ ይላል፤ አንተን፡ ላበረ
ታህ፡ ልረዳህ፤ አንድም፡ በኃይል፡
ወበጽንዕ፡ ቆምኩ፡ ይላል፤ እስ
ራኤልን፡ ለመርዳት፡ ለማበረታ
ታት፡ በኃይል፡ በጽንዕ፡ ቆምሁ፤

፪፤ ወይእዜኒ፡ ጽድቀ፡ እነግረከ፤

አሁንም፡ እውነት፡ ነገር፡ እነግ
ርኻለሁ፤ አንድም፡ ጽድቀ፡
ባለው፡ ፍትሐ፡ ይላል፤ ፍርድ፡
እነግርሃለሁ፡ ፍርዱ፡ እስራኤ
ልን፡ ማዳን፡ አሕዛብን፡ ፈርዶ፡
ማጥፋት፤

ናሁ፡ እንከ፡ ሠለስቱ፡ ነገሥት፡ ይትነሥኡ፡ ውስተ፡ ፋርስ፤

እነሆ፡ በፋርስ፡ ሦስት፡ ነገሥ
ታት፡ ይነሣሉ፤ ዳርዮስ፡ ቂሮስ፡
፩ዱ፡ እምሰብእ፡ ሰገል፤

ወራብዖሙስ፡ ይብዕል፡ ብዕለ፡ ዓቢየ፡ እምኵሉ፤

አራተኛው፡ ግን፡ ከሁሉ፡ ይከብ
ራል፤ (ይበልጣል)፡ እስክንድር፡
ነው፤ አንድም፡ ዳርዮስ፡ ወልደ፡
አህሻዊሮስ፤



ዓመት፡ ኂውውት፤ ዳርዮስ፡
ወልደ፡ ይጸፍ፡ ራብዖሙ፡ ራብ
ዕዳራ፤ አንድም፡ ዳርዮስ፡ ቂሮስ፤
ዳርዮስ፡ ቂሮስ፤ ዳርዮስ፡ ቂሮስ፤
የሚባሉ፡ ሦስት፡ ነገሥታት፡
ይነግሣሉ፤ ከቂሮስ፡ ዳርዮስ፡ ስለ
ተወለዱ፡ ዳርዮስ፡ ቂሮስ፡ አላ
ቸው፤ ራብዖሙ፡ ራብዕዳራ፤ አን
ድም፡ ይዞት፡ የሚሄድ፡ እስክን
ድርን፡ ነው፤

ወበአጽንዖተ፡ ብዕሉ፡ ያሥተናስእሙ፡ ለኵሎሙ፡ ነገሥት፡ አረማውያን፤

ባለጸግነቱን፡ በማጽናቱ፤ አን
ድም፡ ወበአብጽሖተ፡ ብዕሉ፡
ባለጸግነቱን፡ ከሁሉ፡ በማዳ
ረሱ፤ አንድም፡ ወበአብፅዖተ፡
ብዕሉ፡ ባለጸግነቱን፡ በማስመስ
ገኑ፤ አንድም፡ እምድኅረ፡ አፅን
ዖተ፡ ብዕሉ፡ ባለጸግነቱን፡ ካጸና፡
በኋላ፤ አንድም፡ እምድኅረ፡ አብ
ጽሖተ፡ ብዕሉ፡ ባለጸግነቱን፡
ከሁሉም፡ ከአደረሰ፡ በኋላ፤
አንድም፡ እምድኅረ፡ አብፅዖተ፡
ብዕሉ፤ ባለጸግነቱን፡ ከአስመሰ
ገነ፡ በኋላ፡ ነገሥታቱን፡ እንዲ
ገዙለት፡ ያደርጋቸዋል፤

፫፤ ወይትነሣእ፡ ንጉሥ፡ ኃያል፤

ኃያል፡ ንጉሥ፡ እስክንድር፡

ወይኴንን፡ ምኵናነ፡ ብዙኃ፡ ወይገብር፡ ዘፈቀደ፤

ብዙ፡ አገዛዝን፡ ይገዛል፤ የወደደ
ውን፡ ያደርጋል፤

፬፤ ወሶበ፡ ተንሥአ፡ መንግሥቱ፡ ትትቀጠቀጥ፤

እስክንድር፡ በመንግሥት፡ በተ
ነሣ፡ ጊዜ፤ አንድም፡ ወደሮም፡
በሄደ፡ ጊዜ፡ መንግሥቱ፡ ትጠ
ፋለች፤ እስክንድር፡ መንግሥት፡
ለማዳረስ፡ ወደሮም፡ ሲሄድ፡
ዖፍ፡ ትሞታለህ፡ ብላ፡ ነፋች
በት፤ አራቱን፡ ነገሥታት፡ አን
ግሦ፡ ተመልሷል፤ አንጥያኮስን፡
በፅርዕ፤ በጥሊሞስን፡ በግብፅ፤
ስልፎስን፡ በአንጾኪያ፤ ደማጥር
ያኖስን፡ በባቢሎን፡ አንግሷቸ
ዋል፤ አንድም፡ በከበረ፡ በገነነ፡
ጊዜ፤ አንድም፡ ከፅርዕ፡ ወደ፡
ባቢሎን፡ በሔደ፡ ጊዜ፡ እስክን
ድር፡ መንግሥት፡ ለማዳረስ፡
ከፅርዕ፡ ወደ፡ ባቢሎን፡ ሲሔድ፡
ዖፍ፡ ትሞታለህ፡ ብላ፡ ጮኸ
ችበት፡ በቋንቋ፡ አውቀው፡ ትሞ
ታለህ፡ አትሒድ፡ ተመለስ፡
አሉት፤ የሚሞት፡ ሰው፡ ቢነግ
ሩት፡ አይሰማምና፡ እምቢ፡ ብሎ፡
ሔደ፤ ሲበጸበጽበት፡ የዋለው፡
ጠጅ፡ መልከኛው፡ (አዛገ) መድ

www.ethiopianorthodox.org

ኃኒት፡ አጠጥቶ፡ ገድሎታል፤ ሲሞት፡ ዕርዕን፡ ለአንጥያኮስ፤ ግብፅን፡ ለበጥሊሞስ፤ ሦርያን፤ አንጾኪያን፡ ለሰልፎስ፤ ባቢሎንን፡ ለደማጥርያኖስ፡ ሰጥቷቸዋል።

ወትዘርኦ፡ ውስተ፡ አርባዕቱ፡ ነፋሳተ፡ ሰማይ፤

ከአራቱ፡ ነገሥታት፡ ትከፈላለች፤

ኢበደኃሪቱ፡ ወኢበከመ፡ ምኵናኑ፡ አልቦ፡ ዘኮነ፤

ከሱም፡ በፊት፡ ሁኖ፡ ከሱም፡ በኋላ፡ ሁኖ፡ እንደሱ፡ አድርጎ፡ የገዛ፡ የለም፤

እስመ፡ ትትመላሕ፡ መንግሥቱ፤

መንግሥቱ፡ ትጠፋለችና። አንድም፡ እስከ፡ ትትመላሕ፡ መንግሥቱ፡ እስክትጠፋ፡ ድረስ።

ወለባዕዳን፡ ትትወሀብ፤

ለሌሎች፡ ትሰጣለችና። አንድም፡ ለሌሎች፡ እስክትሰጥ፡ ድረስ። አንድም፡ ወእምእሉ፡ ትትወሀብ፡ ለባዕዳን፡ ይላል፤ ለሮማውያን፡ ትሰጣለች፤

፳። ወእምእሉ፡ ይጸንዕ፡ ንጉሠ፡ ዓዜብ፤

ከእሊህም፡ የግብፅ፡ ንጉሥ፡ በጥሊሞስ፡ ይጸናል።

ወይፅዱ፡ እመላእክቲሁ፡ ይጸንዕ፡ ላዕሌሁ፤

በጥሊሞስ፡ በዓቢይ፡ አንጥያኮስ። አንድም፡ ዓቢይ፡ አንጥያኮስ፡ በበጥሊሞስ፤ ይጸናል።

ወይኴንን፡ ምኵናነ፡ ብዙኃ፤

በጥሊሞስ። አንድም፡ ዓቢይ፡ አንጥያኮስ፡ ብዙ፡ አገዛዝን፡ ይገዛል።

፳፩። ወእምድኅረ፡ ብዙኅ፡ ዓመታት፡ ይዴመሩ፤

ከብዙ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ በጥሊሞስና፡ ዓቢይ፡ አንጥያኮስ፡ በግቢ፡ አንድ፡ ይሆናሉ።

ወወለተ፡ ንጉሠ፡ ዓዜብ፡ ትበውዕ፡ ኀበ፡ ንጉሠ፡ መስዕ፤

የበጥሊሞስ፡ ልጅ፡ አክላውባጥራን፡ የዓቢይ፡ አንጥያኮስ፡ ልጅ፡ ወሬዛ፡ እስክንድር፡ ያገባታል፤ አክላውባጥራ፡ ማለት፡ ዘትበኪ፡ ላዕለ፡ ኵኵሕ፡ ማለት፡ ነው፤ ተድራ፡ ስትሄድ፡ ብእሲተ፡ ሎጥ፡ ሐውልተ፡ ጨው፡ ከሆነችበት፡ ደረሰች፤ ይሔ፡ ምንድነው? ብላ፡ ጠየቀች፤ እንደ፡ አንቺ፡ ያለች፡ ሴት፡ ነበረች፡ አገርሽን፡ ዞረሽ፡ አትይ፡ ቢሏት፡ ዞራ፡ አይታ፡ እንዲህ፡ ሆነች፡ አሏት፤ አውርዱኝ፡ ብላ፡ አልቅሳለችና፤ ዘትበኪ፡ ላዕለ፡ ኵኵሕ፡ አለ። አንድም፡ ጽንዕት፡ ማለት፡ ነው፡ በጥርዓ፡ [illegible]



ከመ፡ ትግበር፡ ቀተተ፡ ምስሌሁ፤

ፍቅረ፡ ጕሕሉተ፡ ምስሌሁ፡ ሲል፡ ነው። ከሱ፡ ጋራ፡ ፍቅር፡ የምታደርግ፡ መስላ። አንድም፤ ከመ፡ ትግበር፡ ቀትለ፡ ይላል። ታስገድለው፡ ዘንድ።

ወኢይጸንዕ፡ ኃይለ፡ መዝራዕታ፤

ለወሬዛ፡ እስክንድር፡ አትወልድለትም። አንድም፡ ወኢይጸንዕ፡ ኃይለ፡ መዝራዕቱ፡ ቢል፡ ወሬዛ፡ እስክንድር፡ ከርሷ፡ ልጅ፡ አይወልድም። አንድም፡ ወይፀንዕ፡ ኃይለ፡ መዝራዕታ፡ ለደማጥርያኖስ፡ ልጅ፡ ትወልድለታለች። አንድም፡ ወይጸንዕ፡ ኃይለ፡ መዝራዕቱ፡ ደማጥርያኖስ፡ ከሷ፡ ልጅ፡ ይወልዳል።

ወኢይቀውም፡ ዘርዓ፤

ለወሬዛ፡ እስክንድር፡ አትወልድለትም። አንድም፡ ወኢይቀውም፡ ዘርዑ፤ ወሬዛ፡ እስክንድር፡ ከሷ፡ አይወልድም። አንድም፡ ወይቀውም፡ ዘርዓ፡ ለደማጥርያኖስ፡ ልጅ፡ ትወልድለታለች። አንድም፡ ወይቀውም፡ ዘርዑ፤ ደማጥርያኖስ፡ ከርሷ፡ ልጅ፡ ይወልዳል።

ወኢይትወሀብ፡ ላቲ፤

ለወሬዛ፡ እስክንድር፡ ልጅ፡ አትወልድለትም። አንድም፡ ወኢይ[illegible] እስክንድር፡ ከሷ፡ አይወልድም። አንድም፡ ወይትወሀብ፡ ላቲ፡ ለደማጥርያኖስ፡ ልጅ፡ ትወልድለታለች፡ አንድም፡ ደማጥርያኖስ፡ ከሷ፡ ይወልዳል።

ወእስሃ፡ አምጽእዋ፡ ለወለተ፡ ንጉሠ፡ ዓዜብ፤

ይፈርሁ፡ ይደነግፁ፡ ያለበት፡ ነው፤ የበጥሊሞስን፡ ልጅ፡ አክላውባጥራን፡ ያመጧት፡ ሰዎች፡ ይደነግጣሉ፡ ይፈራሉ።

ወዘያጸንዓሂ፡ በመዋዕል፤

እንደ፡ አሥርት፡ ባለው፡ የሚያጸናት፡ ሥር፡ ሚዜው፡ ይፈራል፡ ይደነግጣል፤

፳፪። ወኢይቀውም፡ እምጕንደ፡ ሥርዋ፡ ዕኑዕ፤

ጕንድ፡ ማኅፀኗ፡ ሥርዋ፡ ሰውነቷ፡ ነው። ለወሬዛ፡ እስክንድር፡ አትወልድለትም። አንድም፡ ወሬዛ፡ እስክንድር፡ ከሷ፡ አይወልድም። አንድም፡ ለደማጥርያኖስ፡ ትወልድለታለች። አንድም፡ ደማጥርያኖስ፡ ከሷ፡ ልጅ፡ ይወልዳል።

ወይመጽእ፡ በኃይል፡ ወይበውዕ፡ ኀበ፡ ምስካቡ፡ ለንጉሠ፡ መስዕ፤

በጥሊሞስ፡ በኃይሉ፡ ይመጣል፡ ወደ፡ ዓቢይ፡ አንጥያኮስ፡ አገር፡ ይገባል።

www.ethiopianorthodox.org

ወይገብር፡ ቦሙ፤

ክፉ፡ ነገር፡ ያደርግባቸዋል፤

ወያጸንዖሙ፤

አጽንቶ፡ ይጣላቸዋል፤

አምላኮሙኒ፤

ይቀጠቅጥ፡ ያለበት፡ ነው፤ አምላካቸውን፡ ይቀጠቅጠዋል፤

፰፤ ወይገፌትዖሙ፡ ምስለ፡ መላእክቲሆሙ፤

ከአለቆቻቸው፡ ጋራ፤

ወምስለ፡ አማልክቲሆሙ፤

ከጣዖታቱ፡ ጋራ፤

ወምስለ፡ መኳንንቲሆሙ፤

ከመኳንንቱ፡ ጋራ፤

ወምስለ፡ ኵሉ፡ ንዋይ፡ መፍትው፤

ከአማረው፡ ከተወደደው፡ ገንዘብ፡ ጋራ፡ ያጠፋቸዋል፤

ወርቆሙ፡ ወብሩሮሙ፡ በዔዋ፡ ይወስድ፡ ግብፀ፤

ወርቃቸውን፡ ብራቸውን፡ ምርኮ፡ አድርጎ፡ ወደ፡ ግብፅ፡ ይወስደዋል፤ አንድም፡ ወይመጽእ፡ በኃይል፡ ብለህ፡ መልስ፤ ዓቢይ፡ አንጥያኮስ፡ በኃይል፡ ይመጣል፤ ወይበውዕ፡ ኀበ፡ ምስካቡ፡ ለንጉሠ፡ ዓዜብ፡ ሲል፡ ነው፤ ወደበጥሊሞስ፡ አገር፡ ይገባል፤ ክፉ፡ ነገር፡ ያደርጋል፤ አጽንቶ፡ ይጣላቸዋል፤ አምላካቸውንም፡ ይቀጠቅጠዋል፤ ከአለቆቻቸው፡ ጋራ፡ ከጣዖታቱ፡ ጋራ፡ ከመኳንንቱ፡ ጋራ፡ ከገንዘቡ፡ ጋራ፡ ያጠፋቸዋል፤ በግብፅ፡ የነበረውን፡ ወርቁን፡ ብሩን፡ ምርኮ፡ አድርጎ፡ ወደ፡ ዕርዕ፡ ይወስደዋል፤

ወውእቱ፡ ይቀውም፡ በእንተ፡ ቀትለ፡ ንጉሠ፡ መስዕ፤

ደማጥርያኖስ፡ ከዳግም፡ አንጥያኮስ፡ ጋራ፡ ለመዋጋት፡ ይጸናል፤

፱፤ ወይበውዕ፡ ውስተ፡ መንግሥቱ፡ ለንጉሠ፡ ዓዜብ፤

ደማጥርያኖስ፡ በበጥሊሞስ፡ መንግሥት፡ ተገብቶ፤

ወይሠወጥ፡ ብሔሮ፤

ደማጥርያኖስ፡ ድል፡ ነሥቶ፡ ወደ፡ ሀገሩ፡ ይመለሳል፤ አንድም፡ ዳግም፡ አንጥያኮስ፡ ድል፡ ተነሥቶ፡ ወደ፡ ሀገሩ፡ ይመለሳል፤ አንድም፡ ወውእቱ፡ ዳግም፡ እምንጉሠ፡ ሰሜን፡ የሚል፡ ይገኛል፤ ዳግምነቱ፡ ዓቢይ፡ አንጥያኮስ፡ ወሬዛ፡ እስክንድርን፡ ይወልዳል፤ ወሬዛ፡ እስክንድር፡ ዳግም፡ አንጥያኮስን፡ ይወልዳል፤ ዳግም፡ አንጥያኮስ፡ አውፊፋኖስ፡ አንጥያኮስን፡ ይወልዳል፤ ዳግም፡ ማለቱ፡ በስም፡ ያሉ፡ እንደሆነ፡ ለዓቢይ፡ አንጥያኮስ፤ በመንግሥት፡ ያሉ፡ እንደሆነ፡ ለወሬዛ፡ እስክንድር፡ ነው፤



ወይበውዕ፡ ውስተ፡ መንግሥቱ፡ ለንጉሠ፡ ዓዜብ፤

ዳግም፡ አንጥያኮስ፡ ከበጥሊሞስ፡ ጋራ፡ ለመዋጋት፡ ወደ፡ ግብፅ፡ ይሄዳል፤

ወይሠወጥ፡ ብሔሮ፤

ድል፡ ነሥቶ፡ ይመለሳል፤ አንድም፡ ደማጥርያኖስ፡ ድል፡ ተነሥቶ፡ ይመለሳል፤

፲፤ ወደቂቁ፡ ይፃብዑ፤

እስክንድር፡ በመንግሥት፡ የወለዳቸው፡ ዓቢይ፡ አንጥያኮስና፡ በጥሊሞስ፡ ይጣላሉ፤ አንድም፡ የደማጥርያኖስ፡ ሠራዊቶች፡ ይዋጋሉ፤

ወያስተጋብዕ፡ አሕዛበ፡ ወሠራዊተ፡ ብዙኃነ፤

ደማጥርያኖስ፡ ብዙ፡ ሠራዊት፡ ብዙ፡ አሕዛብን፡ ይሰበስባል፤

ይመጽእ፡ ወይትቃተል፡ ምስለ፡ ንጉሠ፡ መስዕ፤

ደማጥርያኖስ፡ ከዳግም፡ አንጥያኮስ፡ ጋራ፡ ለመዋጋት፡ ይመጣል፤

፲፩፤ ወያቀውም፡ ብዙኃነ፡ አሕዛበ፤

ደማጥርያኖስ፡ ብዙ፡ ሠራዊት፡ ይሰበስባል፤

ወይትዓረወይ፡ ንጉሠ፡ ዓዜብ፡ ላዕለ፡ ንጉሠ፡ መስዕ፤

ደማጥርያኖስ፡ በዳግም፡ አንጥያኮስ፡ ጋራ፡ ይዋጋል፤

ወይወጽእ፡ ወይትቃተል፡ ምስለ፡ ንጉሠ፡ መስዕ፤

ደማጥርያኖስ፡ መጥቶ፡ ከአንጥያኮስ፡ ጋራ፡ ይዋጋል፤

ወይገብዑ፡ ውስተ፡ እዴሁ፡ ሰብኡ፤

የአንጥያኮስ፡ ሰዎች፡ በደማጥርያኖስ፡ እጅ፡ ይያዛሉ፤ አንድም፡ የደማጥርያኖስ፡ ሰዎች፡ በአንጥያኮስ፡ እጅ፡ ይያዛሉ፤ አንድም፡ በበጥሊሞስ፡ ጊዜ፡ የተማረኩት፡ ይመለሳሉ፤ አንድም፡ ጧት፡ የተማረኩት፡ ማታ፡ ይመለሳሉ፤ አንድም፡ ወደቂቁ፡ ይፃብዑ፡ ብለህ፡ መልስ፤ የአጥንያኮስ፡ ሠራዊት፡ ይዋጋሉ፤

ወያስተጋብዕ፤

አንጥያኮስ፡ ብዙ፡ ሠራዊት፡ ይዞ፡ ይመጣል፤ ከበጥሊሞስ፡ ጋራ፡ ይዋጋል፤ አንጥያኮስ፡ በበጥሊሞስ፡ ይበረታበታል፤ የደማጥርያኖስ፡ ሰዎች፡ በአንጥያኮስ፡ እጅ፡ ይያዛሉ፤ አንድም፡ በዓቢይ፡ አንጥያኮስ፡ ጊዜ፡ የተማረኩት፤ አንድም፡ ጧት፡ የተማረኩት፡ ማታ፡ ይመለሳሉ፤

፲፪፤ ወይነሥእ፡ ሕዘቢሁ፡ ወየዓቢ፡ ልቦ፤

ደማጥርያኖስ፡ ሠራዊቶቹን፡ ይዞ፡ ልቡናውን፡ ያስታብያል፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፤ ወእምዝ፡ ይመይጥ፡ ገጾ፡ ውስተ፡ ደሰያት፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ ወሬዛ፡ እስክን ድር፡ ወደ፡ ደሴቱ፡ ፊቱን፡ ይመ ልሳል፤ አንድም፡ ዳግም፡ አንጥ ያኮስ፡ ወደሚገዛው፡ አገር፡ ፊቱን፡ ይመልሳል፤

ወይእኅዝ፡ ብዙኃነ፤

ብዙ፡ ሰዎችን፡ ይይዛል፤

ወይሥዕር፡ መኳንንተ፡ ኃፍረቱ፡ ሎቱ፤

ወሬዛ፡ እስክንድር፡ ድል፡ ተነ ሥተው፡ ያሳፈሩት፡ መኳንን ቱን፡ ይሽራቸዋል፤ እንደ፡ አሞዩ፤ አንድም፡ አባቱ፡ ዓቢይ፡ አንጥ ያኮስ፡ አክብሮ፡ ያኖራቸው፡ የነ በረውን፡ መኳንንቱን፡ ይሽራ ቸዋል፤

ወዘእንበለ፡ ኃፍረት፡ ይትመየጥ፤

ድል፡ ነሥቶ፡ ሳያፍር፡ ወደሀ ገሩ፡ ይመለሳል፤

፲፱፤ ወይመይጥ፡ ገጾ፡ ለአጽንዖተ፡ ምድሩ፤

ሀገሩን፡ ለማጽናት፡ ፊቱን፡ ይመ ልሳል፤

ወይደክም፡ ወይወድቅ፤

ኋላ፡ ግን፡ ይደክማል፡ ይጠፋል፤

ወኢይትረከብ፤

፳፤ ወይትነሣእ፡ ወይነብር፡ ዲበ፡ መንበሩ፤

ዳግም፡ አንጥያኮስ፡ በመንግ ሥት፡ ይነሣል፤ እግዚአብሔር፡ በሰጠው፡ ዙፋን፡ ይቀመጣል፤

ወይሥእር፡ ሥልጣነ፤

መኳንንቱን፡ ይሽራል፤

ወሠናየ፡ መንግሥታት፤

ነገሥታቱን፡ ያጠፋል፤

ወእምድኅረ፡ ብዙኅ፡ መዋዕል፡ ይሠበር፤

ከብዙ፡ ቀን፡ በኋላ፡ በጥሊሞስ፡ ድል፡ ይነሣል፤ በጥሊሞስስ፡ ይዞት፡ ያልመጣ፡ ነው፤ ሳይነ ግሥ፡ አይሞትም፡ አለ፡ ብሎ፤

ይትነሣእ፡ ወይነብር፡ በመንበሩ፤

በጥሊሞስ፡ በመንግሥት፡ ይነ ሣል፤ በዙፋን፡ ይቀመጣል፤ ወይ ሥዕር፡ ሥልጣነ፡ መኳንንቱን፡ ይሽራል፤ ወሠናየ፡ መንግሥ ታት፡ ነገሥታቱን፡ ያጠፋል፡ ከብዙ፡ ዘመን፡ በኋላ፡ በጥሊ ሞስ፡ ይሞታል፤

አኮ፡ በመዓት፤

እንደ፡ አንጥያኮስ፡ ቍስለ፡ ሥጋ፡ ታሞ፡ የሞተ፡ አይደለም፤

ወአኮ፡ በፀ[illegible]



፳፩፤ ወይቀውም፡ ዲበ፡ መንበሩ፡ ኅሡር፤

ደማጥርያኖስ፡ በዙፋኑ፡ ይቀመ ጣል፤ ኅሡር፡ አለው፡ ናታን፡ ዘሞአ፡ ይለዋልና፤

ወኢይሁብዎ፡ ክብረ፡ መንግሥት፤

ሽህ፡ ዓመት፡ ያንግሥህ፡ አይሉ ትም፤ አንድም፡ ግብር፡ አይሰ ጡትም፤ አይገብሩለትም፤

ወይመጽእ፡ በኅድዓት፤

በጸጥታ፡ ይመጣል፤

ወይጸንዕ፡ መንግሥቱ፡ በሁከት፤

መንግሥቱ፡ በሁከት፡ ይጸናል፡ አለ፤ በጥሊሞስና፡ ዓቢይ፡ አን ጥያኮስ፡ ይጣሉበታል፤

በደኃሪ፡ መዋዕል፡ ይትነሥኡ፡ ላዕለ፡ ንጉሠ፡ ዓዜብ፡ በኃይል፡ ወይትቃተሎ፡ ለንጉሠ፡ ዓዜብ፤

በኋላ፡ ዘመን፡ እነ፡ አንጥያኮስ፡ በደማጥርያኖስ፡ ላይ፡ በኃይል፡ ይነሣሉ፤ ደማጥርያኖስ፡ ይዋ ጋዋል፤

፳፪፤ ወእምቅድሜሁ፡ ይትቀጠቀጡ፡ መጋብያነ፡ ሕግሂ፤

ከዚህ፡ አስቀድሞ፡ መቃብያንን፡ ጥቂት፡ ጥቂት፡ እያለ፡ ይወ ጋቸዋል፤

፳፫፤ ወእምእለ፡ ይሳተፍዎ፡ ይገብሩ፡ ላዕሌሁ፡ ጽልሁተ፤

[illegible] ፍጥር፡

ወየዓርግ፡ ወይጸንዕ፡ በሕዝብ፡ ንዑስ፤

አፊፋኖስ፡ አንጥያኮስ፡ ይዘም ታል፡ በመቃብያን፡ ይጸናባቸዋል፤

፳፬፤ ወበብሔር፡ ጥሉል፤

እንተ፡ ታውኅዝ፡ ሀሊበ፡ ወመ ዓረ፡ በሚላት፡ በኢየሩሳሌም፡ ክፉ፡ ነገር፡ ያደርጋል፤

ይመጽእ፡ ወይገብር፡ ዘኢገብሩ፡ አበዊሁ፤

መጥቶ፡ አባቶቹ፡ እነ፡ ወሬዛ፡ እስክንድር፡ ያላደረጉትን፡ ያደ ርጋል፤

ወአበው፡ አበዊሁ፤

አያቶቹ፡ እነዓቢይ፡ አንጥያኮስ፡ ያላደረጉትን፡ ያደርጋል፤

ወይመሀርክ፡ ወይዔውው፤

ሰውን፡ ከብቱን፡ ይማርካል፤

ወይነድዕ፡ እንስሳሆሙ፤

ከብታቸውን፡ ይነዳል፤

ወላዕለ፡ ፀወናቲሆሙ፤ ይሔሊ፡ ሕሊና፡ እኩየ፤ እስከ፡ ዕድሜሁ፤

ሦስት፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፡ በአ ምባቸው፡ ላይ፡ ክፉ፡ ነገር፡ ያስ ባል፤ አንድም፡ በአርበኞች፡ ላይ፡ ክፉ፡ ነገር፡ ያስባል፤

፳፭፤ ወይነሥእ፡ ኃይሎ፤

ዳግም፡ አንጥያኮስ፡ ሠራዊቱን፡

www.ethiopianorthodox.org

ወልቡ፡ ላዕለ፡ ንጉሠ፡ ዓዜብ፡ ለተዓብዮ፡ በሠራዊት፡ ዓቢይ።

ብዙ፡ ሠራዊት፡ ይዞ፡ መጥቶ፡ በደማጥርያኖስ፡ ላይ፡ ልቡን፡ ያስታብያል።

ወንጉሠ፡ ዓዜብ፡ ይጸንዕ፡ በሠራዊት፡ ዓቢይ።

ምስለ፡ ሠራዊት፡ ዓቢይ፡ ሲል፡ ነው፣ ከብዙ፡ ሠራዊት፡ ጋራ፡ ለመዋጋት፡ ጸንቶ፡ ይመጣል።

ወጽኑዕ፡ ጥቀ።

እጅግ፡ ጽኑዕ፡ ነው።

ወኢይጸንዕ።

አይጸናም።

፳፮። እስመ፡ ይሔልዩ፡ ሕሊና፡ እለ፡ ይበልዑ፡ ውስተ፡ ማዕዱ።

ማዕዱን፡ የሚበሉ፡ ጠርፎስ፡ አውፋጥር፡ ድል፡ ይነሣል፡ ብለው፡ ይላላኩበታልና።

ወይቀጠቅጥዎ፡ ኃይሎ።

አይሆንልህም፡ እያሉ፡ ኃይሉን፡ ያደክሙታል።

ወይወድቁ፡ ቅቱላን፡ ብዙኃን፡ በኵናት።

ብዙ፡ ሰዎች፡ በጦር፡ ይሞታሉ።

፳፯። ወ፪ቱ፡ ነገሥት፡ የአክዩ፡ ልቦሙ።

አውፋጥር፡ ጠርፎስ፡ ልባቸውን፡ ወደክፋት፡ ይመልሳሉ። አንድም፡ በጥሊሞስና፡ አንጥ

ወበአሐቲ፡ ማዕድ፡ ይትናገሩ፡ ሐሰተ።

ደማጥርያኖስና፡ አንጥያኮስ፡ በአንድ፡ በመንግሥተ፡ እስክንድር፡ ሳሉ፡ አሰት፡ ይናገራሉ።

ወኢያረትዑ፡ እስመ፡ ዓዲ፡ ኢበጽሐ፡ ዕድሜሁ።

ጊዜው፡ ገና፡ አልደረሰምና፡ እውነት፡ ነገር፡ አይናገሩም። አንድም፡ ኢይትፋቀሩ፡ ይላል፡ አይፋቀሩም።

፳፰። ወየአቱ፡ ብሔሮ፡ ምስለ፡ ብዙኀ፡ ንዋይ።

አንጥያኮስ፡ ድል፡ ነሥቶ፡ ከብዙ፡ ገንዘብ፡ ጋራ፡ አገሩ፡ ይገባል።

ወልቡሰ፡ ላዕለ፡ ሥርዓተ፡ ቅድስት።

ልቡ፡ ግን፡ ሥርዓተ፡ ኦሪትን፡ ለማጥፋት፡ ነው። አንድም፣ ላዕለ፡ ሥርዓት፡ ቅድስት፡ ይላል።

ወይገብር፡ ወይትመየጥ፡ ኀበ፡ ምድሩ።

የወደደውን፡ ያደርጋል፡ ወደ፡ ሀገሩ፡ ይመለሳል።

፳፱። ወበዕድሜሁ፡ ይትመየጥ።

በጊዜው፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ሀገሩ፡ ይመለሳል።

ወይመጽእ፡ ውስተ፡ ዓዜብ።

አውፊፋኖስ፡ ወደ፡ ግብፅ፡ ይመጣል።

ወኢይከውኖ፡ በቅድሜሁ፡ ወበደኃሪቱ።

ከሱም፡ በፊት፡ ሁኖ፡ ከሱም፡ በኋላ፡ ሁኖ፡ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org



፴። ወይመጽኡ፡ ቦቱ፡ ኪ.ም፡ ወከይተም፡ ወኔባ።

ግብፅ፡ ሮም፡ ፋስቆሎ፡ ማይጓን፡ ወደሱ፡ ይመጡበታል።

ይትመየጥ፡ ወይትመአዕ፡ ላዕለ፡ ሥርዓተ፡ ቅድስት።

ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ይመለሳል፡ በንዋየ፡ ቅድሳቱ፡ ይበሳጫል።

ይትመየጥ፡ ወይገብር።

ወደኢየሩሳሌም፡ ይመለሳል፡ የወደደውን፡ ያደርጋል።

ወያረኵስ፡ መቅደሰ፡ በኃይል።

በኃይል፡ መጥቶ፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ያረክሳል፣ ሥዕለ፡ ፀሐይ፡ ያቆምባታል።

ወይበረብር።

ገንዘባቸውን፡ ይበዘብዛል።

ወያኀብር፡ ጣዖተ፡ ዲበ፡ እለ፡ የኃድጉ፡ ሥርዓተ፡ ቅድስት።

ሕግን፡ በጣሉ፡ በሦስቱ፡ ካህናት፡ ምክር፡ መጥቶ፡ ሥዕለ፡ ፀሐይን፡ ያቆማል። አንድም፡ በሦስቱ፡ ካህናት፡ ላይ፡ ጣዖቱን፡ ያኖራል፡ ማለት፡ ያሽክማቸዋል።

፴፩። ወዘርዖሙ፡ ይትነሥኡ፡ እምኔሆሙ።

ከነሱ፡ ወገን፡ የሚሆኑ፡ ሦስት፡ ካህናት፡ [illegible]

ወያረኵሱ፡ መቅደሰ።

ቤተ፡ መቅደስን፡ ያረክሳሉ። አንድም፡ ሰውነታቸውን፡ ያረክሳሉ።

፴፪። ወእለሂ፡ ይዔምፁ፡ ሥርዓተ፡ ያመጽኡ፡ ዳኅፀ።

ሥርዓተ፡ ኦሪትን፡ የሚያፈርሱ፡ ሦስቱ፡ ካህናት፡ መከራ፡ ያመጣሉ።

ወሕዝብ፡ ዘየአምሩ፡ አምልኮ፡ ያጸንዑ፡ ወይገብሩ።

አምልኮተ፡ እግዚአብሔርን፡ የሚያውቁ፡ ወገኖች፡ በሕግ፡ ጸንተው፡ በጎ፡ ሥራ፡ ይሠራሉ።

፴፫። ወጠቢባን፡ ሕዝብ፡ ይሌብዉ፡ ብዙኃ።

አዋቆች፡ ወገኖች፡ ሕገ፡ እግዚብሔርን፡ ይረዳሉ።

ወይደክሙ፡ በኵናት

በጦር፡ ይጠፋሉ፣ አራቱ፡ ዕልፍ፡ ታርደዋል።

ወበእሳት።

አራቱ፡ ዕልፍ፡ ተሰደው፡ በስለት፡ አልቀዋል።

ወበተዔውዎ።

አራቱ፡ ዕልፍ፡ ተማርከዋል።

ወይትበረበሩ፡ ብዙኃ፡ መዋዕለ።

ሦስት፣ ዓመት፡ ከመንፈቅ፡ ገንዘባቸው፡ ተበዘበዘ።

፴፬፤ ወበደዌሆሙ፡ ይረድዕዎሙ፡ ረድኤተ፡ ኅዳጠ፤

የታረዱት፤ የተሰደዱት፤ የተማረኩት፡ መከራ፡ በተቀበሉ፡ ጊዜ፡ ሥላሴ፡ ይረዷቸዋል፤ አንድም፡ የተሰደዱት፡ በጸሎት፡ ይረዷቸዋል፤

ወይትዌሰኩ፡ ላዕሌሆሙ፡ ብዙኃን፡ በዳኅፃተ፡ሆሙ፤

በክፉዎች፡ ኃጢአት፡ በጎዎች፡ ሰዎች፡ ተጨምረው፡ ይሄዳሉ፤ የኃጥዕ፡ ዳፉ፡ ጻድቅን፡ ይደፋ፡ እንዲሉ፤

፴፭፤ ወይደውዩ፡ እምጠቢባን፤

ከመቃብያን፡ ወገን፡ የሚሆኑ፡ መከራ፡ ይቀበላሉ፤

ከመ፡ ያርስንዎሙ፤

በመከራ፡ ያግኗቸው፡ ዘንድ፤

ወያጽርይዎሙ፤

ያከብሯቸው፡ ዘንድ፤

ወያንጽሕዎሙ፡ እስከ፡ ጊዜሁ፤

ሦስት፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፤ ቆይተው፡ ያነጽዋቸው፡ ዘንድ፤

እስመ፡ ዓዲ፡ ኢበጽሐ፡ ዕድሜሁ፤

ጊዜው፡ ገና፡ አልደረሰምና፤

ወዘይቀውም፡ ውስተ፡ መካን፡ ቅዱስ፡ ወዘ ያነብብ፡ መጽሐፈ፡ ዳንኤል፡ ለይለቡ፤

በቤተ፡ መቅደስ፡ የሚቆም፡ መጽሐፈ፡ ዳንኤልን፡ የሚመለከት፡ ሰው፡ የጥጦስ፤ አንድም፡ የሐሳዊ፡ መሢሕ፡ ነገር፡ እንዳይቀር፡ ይወቅ፤ አንድም፡ መከራ፡ ቢበዛ፡ ጸጋ፡ ክብር፡ እንዲበዛ፡ ይወቅ፤

፴፮፤ ወይገብር፡ ንጉሥ፡ በከመ፡ ፈቀደ፤

አንጥያኮስ፡ እንደወደደ፡ ያደርጋል፤

ወይትዔበይ፡ ወይዜኃር፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ አምላክ፤

ይታበያል፡ በሁሉ፡ ላይ፡ አምላክ፡ ነኝ፡ ይላል፤

ወላዕለ፡ አምላከ፡ አማልክት፡ ይነብብ፡ በትዕቢት፤

በአማልክት፡ አምላክ፡ በጌታ፡ ላይ፡ ደፍሮ፡ የእስራኤል፡ አምላክ፡ ምን፡ አምላክ፡ ነው፡ እያለ፡ ይናገራል፤

ወይረትዕ፡ እስከ፡ የሐልቅ፡ መዓት፤

ሦስቱ፡ ዓመት፡ ከመንፈቅ፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፡ ይቀናል፤ ያረትዕ፡ቢል፡ ሕገ፡ ጣዖትን፡ ያቀናል፤

ወእስከ፡ ምንዳቤ፡ ተገብረት፤

መከራ፡ በመቃብያን፡ እስኪፈጸም፡ ድረስ፡ ይቀናል፤ አንድም፡ ወያረትዕ፤ መንግሥቱን፡ ያጸናል፡ መከራ፡ በመቃብያን፡ ተፈጽማለችና



፴፯፤ ወላዕለ፡ አምላከ፡ አበዊሁ፡ ኢያእመረ፤

የአባቶቹ፡ ፈጣሪ፡ ከጣዖቱ፡ በላይ፡ ያለ፡ ጌታን፡ አላወቀውም፤

ወበፍትወተ፡ አንስት፤

ይደዊ፡ ያለበት፡ ነው፤ ሴትን፡ በመውደድ፡ በደዌ፡ ይጨነቃል፤ ቡኒ፡ ወለተ፡ ዳራ፡ ይላታል፤ አውፊፋኖስ፡ አንጥያኮስ፡ ላግባሽ፡ ብሎ፡ ላከባት፤ እሷም፡ በተንኮል፡ እሺ፡ ጥቂት፡ ሰው፡ ሆነህ፡ ና፡ ብላ፡ ላከችበት፤ በአንድ፡ ወገን፡ ብዙ፡ ሰው፡ ሰብስባ፡ በሚመጣበት፡ መንገድ፡ አስጠበቀችው፤ ሲመጣ፡ አይተው፡ ተነሡበት፤ እሱ፡ እየሸሸ፡ እነዚያ፡ እየተከተሉ፡ ጉንድ፡ ዕቡር፡ ጉንድ፡ ስቡር፡ ከሚባል፡ ሲደርስ፡ ከፈረስ፡ ወደቀ፡ ሰይጣንጢቅ፡ አለበት፤ ደዌ፡ ሥጋ፡ ታመመ፡ አንደበቱ፡ ተቆራርጦ፡ ሙቷል፤

ወላዕለ፡ ኵሉ፡ አምላክ፤

በሁሉ፡ ላይ፡ አምላክ፡ ነኝ፡ ይላል፤

ኢየአምር፡ እስመ፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ ይትዔበይ፤

ጌታን፡ አያውቅም፡ በሁሉ፡ ላይ፡ [illegible]

፴፰፤ ወለእግዚአብሔር፡ አዚዝ፡ ዲበ፡ መንበሩ፡ ይዜኃር፤

በእግዚአብሔር፡ ሥልጣን፡ ላይ፡ ይታበያል፡ ማለት፤ የእስራኤል፡ አምላክ፡ ምን፡ አምላክ፡ ነው፡ ይላል፤ አንድም፡ እግዚአብሔር፡ በሰጠው፡ ዙፋን፡ ላይ፡ ተቀምጦ፡ ይታበያል፤

ወለእግዚአብሔር፡ ዘኢየአምርዎ፡ አበዊሁ፡ ያከብር፡ በወርቅ፡ ወበብሩር፡ ወበዕንቍ፡ ሠናይ፤

አባቶቹ፡ የማያውቁት፡ ጌታን፡ በወርቅ፡ በብር፡ በዕንቍ፡ ያከብረዋል፤ ነቢያተ፡ ሐሰት፡ ይህ፡ ሁሉ፡ መከራ፡ የመጣብህ፡ ሕጉን፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ብታፈርስ፡ አይደለም? አሉት፤ ከአዳነኝስ፡ ሕጉን፡ አጸናለሁ፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ በወርቅ፡ በብር፡ በዕንቍ፡ እሠራለሁ፡ ብኋልና፡ እንዲህ፡ አለ፤

፴፱፤ ወይገብር፡ ለአህጉር፡ ጽኑዓት፡ ምስለ፡ አምላክ፡ ነኪር፤

ጣዖቱን፡ እየሠራ፡ ጽኑዓን፡ በሆኑ፡ አገሮች፡ ይሰዳል፤

ዘየአምር፡ ክብረ፤

ክብርን፡ የሚያውቅ፡ ማለት፡ ያከብሩታልና፤

ወሥልጣነ፡ ላዕለ፡ ብዙኃን፤

በብዙ፡ ሰዎች፡ ላይ፡ ሠልጥኗልና፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይከፍል፡ ምድረ፡ በሤጥ፤

ለካህናቱ፡ አስበ፡ ተልዕኳቸውን፡ ምድርን፡ እየከፈለ፡ ይሰጣቸዋል፤ አንድም፡ የሰለባቸውን፡ ዋጋ፡ ለመኳንንቱ፡ እየከፈለ፡ ይሰጣቸዋል፤

፵፤ ወበጊዜ፡ ዕድሜሁ፡ ይፀብዮ፡ ለንጉሠ፡ ዓዜብ፤

በተጣሉ፡ ጊዜ፡ ደማጥርያኖስን፡ ይወጋዋል፤

ወይተሐወክ፡ ላዕሌሁ፡ ንጉሠ፡ መስዕ፤

አንጥያኮስ፡ በደማጥርያኖስ፡ ይነሣበታል፤

በሠረገላት፡ ወበአፍራስ፡ ወበአሕማር፡ ብዙኃት፤

በሠረገላ፡ በፈረስ፡ በመርከብ፡ ሁኖ፡ ይሄዳል፤

ወይበውዕ፡ ውስተ፡ አምዳሮት፤

ምድር፡ ያለውን፡ አምዳሮት፡ ብሎ፡ አበዛ፤ በየሀገሩ፡ ይገባል፤

፵፩፤ ይትመየጥ፡ ወይበውዕ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ሠናይት፤

ተመልሶ፡ ወደግብፅ፡ ይገባል፤ አንድም፡ እንተ፡ ትውኅዝ፡ ወደ ሚላት፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ይመለሳል፤

ወብዙኃን፡ ይደክሙ፤

ብዙ፡ ሰዎች፡ መቃብያን፡ ይደክማሉ፤

ወእሙንቱ፡ ይድኅኑ፡ እምእዴሁ፡ ሞዓብ፡ ወኤዶም፡ ወደቂቀ፡ አሞን፤

ሞዓብ፡ ኤዶም፡ የአሞን፡ ልጆች፡ እነዚህ፡ ገብረው፡ ከሱ፡ እጅ፡ ይድናሉ፤ አንድም፡ ኢይድኅኑ፡ ይላል፤ አንገብርም፡ ብለው፡ ከሱ፡ እጅ፡ አይድኑም፤

ወምድረ፡ ግብፅሰ፡ ኢትድኅን፡ እም እዴሁ፤

ግብፅ፡ ግን፡ ከእጁ፡ አትድንም፤ ባትገብር፡ ባትቀቅል፤

፵፪፤ ወይፌኑ፡ እዴሁ፡ ውስተ፡ አምዳሮት፤

በየሀገሩ፡ ቃሉን፡ ሥልጣኑን፡ ይሰዳል፡ ብትገብሩ፡ ገብሩ፡ ያለ ዚያ፡ እወጋችኋለሁ፡ እያለ፤ አን ድም፡ ሠራዊቶቹን፡ ይሰዳል፤

፵፫፤ ወይሜልጥ፡ ላዕለ፡ ብዙኅ፡ መዛግብት፡ ዘወርቅ፡ ወዘብሩር፤

በወርቁ፡ በብሩ፡ ሣጥን፡ ላይ፡ ይሠለጥናል፤

ወላዕለ፡ ኵሉ፡ ፍትወተ፡ ግብፅ፤

የግብፅ፡ ሰዎች፡ በሚወዱት፡ ገንዘብ፡ ላይ፤ አንድም፡ ወላዕለ፡ ኵሉ፡ ፍትወት፡ ይላል፡ በሚወ ድደው፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ ላይ፡ ይሠለጥናል፤

ግብፅ፡ ወኖባ፡ ወኢትዮጵያ፡ ይከውንዎ፡ ረዳዕያነ፡ ሎቱ፤

የግብፅ፡ የኖባ፡ የኢትዮጵያ፡ ሰዎች፡ ረ[illegible]



፵፬፤ ወዜና፡ ይበጽሖ፤

ደማጥርያኖስ፡ አንተን፡ ሊወጋ፡ ጦር፡ ሰብስቦ፡ መጣ፡ የሚል፡ ወሬ፡ ደረሰለት፤

ወይጔጉዕ፡ እምሥራቅ፡ ወእምሰሜን፤

ከምሥራቅ፡ እስከ፡ ምዕራብ፡ ፈጥኖ፡ ይደርሳል፤

ወይወጽእ፡ በመዓት፡ ዓቢይ፤

በብዙ፡ ቁጣ፡ ይወጣል፤

ይቀትል፡ ወያጠፍዕ፡ ሰብአ፡ ብዙኃነ፤

ተቆጥቶ፡ ብዙ፡ ሰው፡ ያጠፋል፤

፵፭፤ ወይተክል፡ ደብተራሁ፡ ውስተ፡ መካን፡ ሠናይ፡ ማዕከለ፡ ባሕር፡ ወመ ቅደስ፤

በኤርትራና፡ በቤተ፡ መቅደስ፡ መሃከል፡ ድንኳኑን፡ ይተክላል፤ አንድም፡ በቤተ፡ መቅደስ፡ በኤር ትራና፡ በደብረ፡ ሲና፡ መካከል፡ ድንኳኑን፡ ይተክላል፤ አባትህ፡ እስክንድር፡ የቀበረው፡ ወርቅ፡ አለ፡ ብለው፡ ነግረውት፡ በአርስ ጣላብ፡ በመነጠር፡ በጠልሰም፡ ለማየት፡ ድንኳኑን፡ ይተክላል፤ አንድም፡ ዳዊት፡ ሰሎሞን፡ የቀ በሩት፡ ወርቅ፡ አለ፡ ብለው፡ ነግ ረውት፡ ድንኳኑን፡ ተክሎ፡ ሲያ ስቆፍር፡ ሰንብቷል፤

ወይፀንዕ፡ እስከ፡ ጊዜሁ፤

እስከ፡ ጊዜው፡ ድረስ፡ ይጸናል፤

ወአልቦ፡ ረዳኢ፡ ሎቱ፤

[illegible]

## ምዕራፍ፡ ፲ወ፪፤

### ጉባዔ፤

፩፤ ወውእተ፡ አሚረ፡ ይትነሣእ፡ ሚካኤል፡ መልአክ፡ ዓቢይ፡ ዘይቀውም፡ ለደቂቀ፡ ሕዝብከ፡ ወአልቦ፡ ረዳኢ፡ ሎቱ፤

ወዘይቀውም፡ ውስተ፡ መካን፡ ቅዱስ፡ ብሎ፡ ነበርና፡ ያን፡ ጊዜ፡ ለወገኖችህ፡ ለመቃብያን፡ ጠበቃ፡ ሁኖ፡ የሚቆም፡ ቅዱስ፡ ሚካ ኤል፡ ይነሣል፤ አንድም፡ በዕለተ፡ ምጽአት፡ ለምዕመናን፡ አጋዥ፡ ጠበቃ፡ የሚሆን፡ ቅዱስ፡ ሚካኤል፡ በዕለተ፡ ምጽአት፡ ይነሣል፤

ወይከውን፡ ሕማም፡ እምኔሁ፤

ከእሱ፡ ከመልኩ፡ የተነሣ፡ በፅር አውያን፡ መከራ፡ ይመጣል፤ አንድም፡ ከሱ፡ ንፍሐተ፡ ቀርን፡ የተነሣ፡ በኃጥአን፡ መከራ፡ ይመጣል፤

ወምንዳቤ፡ ዘኢኮነ፡ ከማሁ፡ እምአመ፡ ተፈጥሩ፡ አሕዛብ፡ ዲበ፡ ምድር፡ እስከ፡ ውእቱ፡ ጊዜ፤

አሕዛብ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ከተፈ ጠሩ፡ ጀምሮ፡ እስከዚያ፡ ድረስ፡ እንደዚህ፡ ያለ፡ ተደርጎ፡ የማያ ውቅ፡ መከራ፡ በፅርዓውያን፤ አንድም፡ በኃጥአን፡ ይመጣባቸ ዋል፤ መጽሐፍ፡ የደረሰበትን፡ ማጽናት፡ ልማዱ፡ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበውእቱ፡ መዋዕል፡ ይድኅኑ፡ ሕዝ
ብከ፡ ኵሉ፡ ዘተረክበ፡ ውስተ፡ መጽሐፈ፡
ሕይወት፤

በዚያ፡ ወራት፡ በመጽሐፍ፡ የተ
ጻፈውን፡ ቃል፡ የፈጸሙ፡ ወገኖ
ችህ፡ መቃብያን፡ ይድናሉ፤ አን
ድም፡ በልበ፡ ሥላሴ፡ የተቆጠሩ፡
ጻድቃን፡ በዕለተ፡ ምጽአት፡
ይድናሉ፤

፪፤ ውብዙኃን፡ እለ፡ ይነውሙ፡ ውስተ፡
መሬተ፡ ምድር፡ ይትነሥኡ፡ ለሕይወት፡
ዘለዓለም፤

በመከራ፡ የተያዙ፡ መቃብያን፡
በሕይወት፡ ለመኖር፡ ከኃሣር፡
ይነሣሉ፤ አንድም፤ እለሰ፡ ሠናየ፡
ገብሩ፡ ይትነሥኡ፡ ውስተ፡ ሕይ
ወት፡ ዘለዓለም፡ የተባሉ፡ ጻድ
ቃን፡ በሕይወት፡ ለመኖር፡ ከመ
ቃብር፡ ይነሣሉ፤

ወእልክቱሰ፡ ለኃሣር፡ ወለኃፍረት፡
ዘለዓለም፤

ፅርአውያን፡ ግን፡ ለኃሣር፡ ለተ
ዋርዶ፡ ይሆናሉ፤ አንድም፡ እለሰ፡
እኩየ፡ ገብሩ፡ የተባሉ፡ ኃጥአን፡
ግን፡ በመከራ፡ ለመኖር፡ ይነሣሉ፤

፫፤ ወእለሰ፡ ለበዉ፡ ይበርሁ፡ ከመ፡
ብርሃነ፡ ሰማይ፤

ሕጉን፡ የጠበቁ፡ መቃብያን፡ ግን፡
ብርሃን፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡
ይላቸዋል፤ አንድም፡ ሕጉን፡ የፈ
ጸሙ፡ ጻድቃን፡ እንደ፡ ፀሐይ፡
ያበራሉ፤ ምስብዒተ፡ ይበርህ፡
ገጾሙ፡ እንዲል፤

ወእምነ፡ ጻድቃን፡ ብዙኃን፡ ከመ፡ ከዋክ
ብተ፡ ሰማይ፡ እስከ፡ ለዓለም፤

ከመቃብያን፡ ወገን፡ ብዙ፡ ሰዎች፡
ኮከብ፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡
ይላቸዋል፤ አንድም፡ ከጻድቃን፡
ወገን፡ ብዙዎች፡ አንዱ፡ ከአ
ንዱ፡ በክብር፡ ይበልጣል፤ ኮከብ፡
እምኮከብ፡ ይኄይስ፡ ክብሩ፡
እንዲል፤

፬፤ ወዓዲ፡ አንተሂ፡ ዳንኤል፡ ዕፅዎ፡
ለዝ፡ ነገር፡ ወኅትም፡ መጽሐፎ፤

ዳንኤል፡ አንተ፡ ግን፡ ይህንን፡
ነገር፡ በልቡናህ፡ ሠውረህ፡ ያዘው፤
እንዲህ፡ ያለ፡ መከራማ፡ ካለብን፡
ብንወጣስ፡ ምን፡ እንረባለን፡
ምን፡ እንጠቅማለን፡ ብለው፡
እንዳይቀሩ፤

እስከ፡ ማኅለቅተ፡ ዓለም፤

ብዙ፡ ዘመን፡ ሠውረህ፡ ያዘው፤

ወእስከ፡ ይትሜሀሩ፡ ብዙኃን፤

ብዙ፡ ሰዎች፡ ሕገ፡ እግዚአብሔ
ርን፡ እስቲማሩ፡ ድረስ፤

ወትበዝኅ፡ ጥበብ፤

አምልኮተ፡ እግዚአብሔር፡ እስ
ክትበዛ፡ ድረስ፤

፭፤ በሣልስ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡
ለቂሮስ፡ ንጉሠ፡ ፋርስ፤

የፋርስ፡ ንጉሥ፡ ቂሮስ፡ በነገሠ፡
በሦስተኛው፡ ዘመን፤



ወነጸርኩ፡ አነ፡ ዳንኤል፤

እኔ፡ ዳንኤል፡ አየሁ፤

ወርኢኩ፡ ካልዓነ፡ ፪ተ፡ ይቀውሙ፤

ከሰው፡ ልዩ፡ የሆኑ፡ ሚካኤልና፡
ገብርኤልን፡ ቁመው፡ አየሁ፤

፩ዱ፡ እምለፌ፡ በድንጋገ፡ ፈለግ፤

አንዱ፡ በወንዙ፡ ዳር፡ ወዲህ፤

ወ፩ዱሂ፡ እምከህ፡ ድንጋገ፡ ፈለግ፤

አንዱ፡ በወንዙ፡ ዳር፡ ወዲያ፡
ቁሞ፡ አየሁ፤

፮፤ ወእቤሎ፡ ለብእሲ፡ ዘይለብስ፡
ጠብደነ፡ ዘሀሎ፡ መልዕልተ፡ ማየ፡
ፈለግ፤

ቀይ፡ ግምጃ፡ የለበሰውን፡ በአሸ
ዋው፡ ላይ፡ የቆመውን፡ እንዲህ፡
አልሁት፤

እስከ፡ ማእዜኑ፡ ማኅለቅቱ፡ ለዘትቤ፡
ትእምርት፤

የአክዩ፡ አሶር፡ በዕብራውያን፤
ወዕብራውያን፡ የአክዩ፡ በአሶር፡
ያልኸው፡ ፍጻሜው፡ እስከ፡ መቼ፡
ድረስ፡ ነው? አንድም፡ ሁለት፡
የተባሉ፡ ፈያታዊ፡ ዘየማንና፡ ፈያ
ታዊ፡ ዘጸጋም፡ ናቸው፤ ብእሲ፡
የተባለ፡ ጌታ፡ ነው፤

በፈያታዊ፡ ዘየማንና፡ በፈያታዊ፡
ዘጸጋም፡ መካከል፡ በመስቀል፡
ተሰቅሎ፡ አየሁት፤

፯፤ ወሰማዕክዎ፡ ለብእሲ፡ ዘይለ
ብስ፡ ጠብደነ፡ ዘሀሎ፡ ዲበ፡ ማየ፡ ፈለግ፤

ግምጃ፡ የለበሰ፡ በአሸዋው፡ ላይ፡
የቆመውን፡ ሰው፡ እንዲህ፡ ሲል፡
ሰማሁት፤

ወአልዓለ፡ የማኖ፡ ወጸጋሞ፤

ቀኝ፡ ግራ፡ እጁን፡ ወደሰማይ፡
ከፍ፡ ከፍ፡ አድርጎ፤

ወመሐለ፡ በዘሕያው፡ ለዓለም፤

ሕያው፡ አነ፡ አማንየ፡ ሲል፡ ሰማ
ሁት፤ አንድም፡ ጌታን፡ በመ
ስቀል፡ እጁን፡ ዘርግቶ፡ አየሁት፤

ከመ፡ በጊዜሁ፤

አንድ፡ ዓመት፤

ወበከመ፡ ዕድሜሁ፤

ሁለት፡ ዓመት፤

ወበመንፈቀ፡ ዓመት፤

የዓመቱ፡ እኩሌታ፤

ሶበ፡ ተፈጸመ፡ ዝርወቶሙ፡ ለሕዝብ፤

የመቃብያን፡ መበተናቸው፡ በተ
ፈጸመ፡ ጊዜ፤

የአምሩ፡ ዘንተ፡ ኵሎ፤

ይህን፡ ሁሉ፡ ያውቃሉ፤

፰፤ ወአነሂ፡ ሰማዕኩ፡ ወጠየቁ፡
ወእቤ፡ እግዚኦ፡ ምንት፡ ደኃሪቱ፡ ለዝንቱ፤

እኔም፡ አቤቱ፡ የዚህ፡ ፍጻሜው፡
ምንድነው፡ ብዬ፡ ጠየቅሁ፤

፱፤ ወይቤለኒ፡ ዓዲ፡ ሑር፡ ዳንኤል፤

ዳንኤል፡ ገና፡ ነውና፡ በሞት፡ ሂድ፡
አለኝ፤ አንድም፡ ዳንኤል፡ ነገሩ፡
ገና፡ ነው፡ አለኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወበውእቱ፡ መዋዕል፡ ይድኅኑ፡ ሕዝ
ብከ፡ ኵሉ፡ ዘተረክበ፡ ውስተ፡ መጽሐፈ፡
ሕይወት፤

በዚያ፡ ወራት፡ በመጽሐፍ፡ የተ
ጻፈውን፡ ቃል፡ የፈጸሙ፡ ወገኖ
ችህ፡ መቃብያን፡ ይድናሉ፤ አን
ድም፡ በልበ፡ ሥላሴ፡ የተቆጠሩ፡
ጻድቃን፡ በዕለተ፡ ምጽአት፡
ይድናሉ፤

፪፤ ውብዙኃን፡ እለ፡ ይነውሙ፡ ውስተ፡
መሬተ፡ ምድር፡ ይትነሥኡ፡ ለሕይወት፡
ዘለዓለም፤

በመከራ፡ የተያዙ፡ መቃብያን፡
በሕይወት፡ ለመኖር፡ ከኃሣር፡
ይነሣሉ፤ አንድም፤ እለሰ፡ ሠናየ፡
ገብሩ፡ ይትነሥኡ፡ ውስተ፡ ሕይ
ወት፡ ዘለዓለም፡ የተባሉ፡ ጻድ
ቃን፡ በሕይወት፡ ለመኖር፡ ከመ
ቃብር፡ ይነሣሉ፤

ወእልክቱሰ፡ ለኃሣር፡ ወለኃፍረት፡
ዘለዓለም፤

ፅርአውያን፡ ግን፡ ለኃሣር፡ ለተ
ዋርዶ፡ ይሆናሉ፤ አንድም፡ እለሰ፡
እኩየ፡ ገብሩ፡ የተባሉ፡ ኃጥአን፡
ግን፡ በመከራ፡ ለመኖር፡ ይነሣሉ፤

፫፤ ወእለሰ፡ ለበዉ፡ ይበርሁ፡ ከመ፡
ብርሃነ፡ ሰማይ፤

ሕጉን፡ የጠበቁ፡ መቃብያን፡ ግን፡
ብርሃን፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡
ይላቸዋል፤ አንድም፡ ሕጉን፡ የፈ

ያበራሉ፤ ምስብዒተ፡ ይበርህ፡
ገጸሙ፡ እንዲል፤

ወእምነ፡ ጻድቃን፡ ብዙኃን፡ ከመ፡ ከዋክ
ብተ፡ ሰማይ፡ እስከ፡ ለዓለም፤

ከመቃብያን፡ ወገን፡ ብዙ፡ ሰዎች፡
ኮከብ፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ ደስ፡
ይላቸዋል፤ አንድም፡ ከጻድቃን፡
ወገን፡ ብዙዎች፡ አንዱ፡ ከአ
ንዱ፡ በክብር፡ ይበልጣል፤ ኮከብ፡
እምኮከብ፡ ይኄይስ፡ ክብሩ፡
እንዲል፤

፬፤ ወዓዲ፡ አንተሂ፡ ዳንኤል፡ ዕፅዎ፡
ለዝ፡ ነገር፡ ወኅትም፡ መጽሐፎ፤

ዳንኤል፡ አንተ፡ ግን፡ ይህንን፡
ነገር፡ በልቡናህ፡ ሠውረህ፡ ያዘው፤
እንዲህ፡ ያለ፡ መከራማ፡ ካለብን፡
ብንወጣስ፡ ምን፡ እንረባለን፡
ምን፡ እንጠቀማለን፡ ብለው፡
እንዳይቀሩ፤

እስከ፡ ማኅለቅተ፡ ዓለም፤

ብዙ፡ ዘመን፡ ሠውረህ፡ ያዘው፤

ወእስከ፡ ይትሜሀሩ፡ ብዙኃን፤

ብዙ፡ ሰዎች፡ ሕገ፡ እግዚአብሔ
ርን፡ እስቲማሩ፡ ድረስ፤

ወትበዝኅ፡ ጥበብ፤

አምልኮተ፡ እግዚአብሔር፡ እስ
ክትበዛ፡ ድረስ፤

፩፤ በሣልስ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡
ለቂሮስ፡ ንጉሠ፡ ፋርስ፤

የፋርስ፡ ንጉሥ፡ ቂሮስ፡ በነገሠ፡
በሦስተኛው፡ ዘመን፡



ወነጸርኩ፡ አነ፡ ዳንኤል፤

እኔ፡ ዳንኤል፡ አየሁ፤

ወርኢኩ፡ ካልዓነ፡ ፪ተ፡ ይቀውሙ፤

ከሰው፡ ልዩ፡ የሆኑ፡ ሚካኤልና፡
ገብርኤልን፡ ቁመው፡ አየሁ፤

፩ዱ፡ እምለፌ፡ በድንጋገ፡ ፈለግ፤

አንዱ፡ በወንዙ፡ ዳር፡ ወዲህ፤

ወ፩ዱሂ፡ እምከሀ፡ ድንጋገ፡ ፈለግ፤

አንዱ፡ በወንዙ፡ ዳር፡ ወዲያ፡
ቁሞ፡ አየሁ፤

፮፤ ወእቤሎ፡ ለብእሲ፡ ዘይለብስ፡
ጠብደነ፡ ዘሀሎ፡ መልዕልተ፡ ማየ፡
ፈለግ፤

ቀይ፡ ግምጃ፡ የለበሰውን፡ በአሸ
ዋው፡ ላይ፡ የቆመውን፡ እንዲህ፡
አልሁት፤

እስከ፡ ማእዜኑ፡ ማኅለቅቱ፡ ለዘትቤ፡
ትእምርት፤

የአክዩ፡ አሶር፡ በዕብራውያን፤
ወዕብራውያን፡ የአክዩ፡ በአሶር፡
ያልኸው፡ ፍጻሜው፡ እስከ፡ መቼ፡
ድረስ፡ ነው? አንድም፡ ሁለት፡
የተባሉ፡ ፈያታዊ፡ ዘየማንና፡ ፈያ
ታዊ፡ ዘጸጋም፡ ናቸው፤ ብእሲ፡
የተባለ፡ ጌታ፡ ነው፤

በፈያታዊ፡ ዘየማንና፡ በፈያታዊ፡
ዘጸጋም፡ መካከል፡ በመስቀል፡
ተሰቅሎ፡ አየሁት፤

፯፤ ወሰማዕክዎ፡ ለብእሲ፡ ዘይለ
ብስ፡ ጠብደነ፡ ዘሀሎ፡ ዲበ፡ ማየ፡ ፈለግ፤

ግምጃ፡ የለበሰ፡ በአሸዋው፡ ላይ፡
የቆመውን፡ ሰው፡ እንዲህ፡ ሲል፡
ሰማሁት፤

ወአልዓለ፡ የማኖ፡ ወጸጋሞ፤

ቀኝ፡ ግራ፡ እጁን፡ ወደሰማይ፡
ከፍ፡ ከፍ፡ አድርጎ፤

ወመሐለ፡ በዘሕያው፡ ለዓለም፤

ሕያው፡ አነ፡ አማንየ፡ ሲል፡ ሰማ
ሁት፤ አንድም፡ ጌታን፡ በመ
ስቀል፡ እጁን፡ ዘርግቶ፡ አየሁት፤

ከመ፡ በጊዜሁ፤

አንድ፡ ዓመት፤

ወበከመ፡ ዕድሜሁ፤

ሁለት፡ ዓመት፤

ወበመንፈቀ፡ ዓመት፤

የዓመቱ፡ እኩሌታ፤

ሶበ፡ ተፈጸመ፡ ዝርወቶሙ፡ ለሕዝብ፤

የመቃብያን፡ መበተናቸው፡ በተ
ፈጸመ፡ ጊዜ፤

የአምሩ፡ ዘንተ፡ ኵሎ፤

ይህን፡ ሁሉ፡ ያውቃሉ፤

፰፤ ወአነሂ፡ ሰማዕኩ፡ ወጠየቁ፡
ወእቤ፡ እግዚኦ፡ ምንት፡ ደኃሪቱ፡ ለዝንቱ፤

እኔም፡ አቤቱ፡ የዚህ፡ ፍጻሜው፡
ምንድነው፡ ብዬ፡ ጠየቅሁ፤

፱፤ ወይቤለኒ፡ ዓዲ፡ ሑር፡ ዳንኤል፤

ዳንኤል፡ ገና፡ ነውና፡ በሞት፡ ሂድ፡
አለኝ፤ አንድም፡ ዳንኤል፡ ነገሩ፡
ገና፡ ነው፡ አለኝ፤

www.ethiopianorthodox.org

እስመ፡ ዕፅው፡ ወኅቱም፡ ነገሩ፡ እስከ፡ ማኅለቅተ፡ ዕድሜሁ፤

የአክዩ፡ አሶር፡ በዕብራውያን፡ ያለው፡ እስቲፈጸም፡ ድረስ፡ ነገሩ፡ ፈጽሞ፡ ተሠውሯልና፤

፲፡ ያጸርዩ፤

ሥላሴ፡ ያጠሯቸዋል፤

ወይፀዓድዉ፤

ያነጿቸዋል፤

ይቤይንዎሙ፤

በመከራ፡ ይለይዋቸዋል፤

ወያነጽሕዎሙ፤

ያነጿቸዋል፤

ወያረስንዎሙ፤

በመከራ፡ ያግሏቸዋል፤

ወይትቄደሱ፡ ብዙኃን፤

እነዓልአዛር፡ በነፍስ፡ ይከብራሉ፤

ወይስሕቱ፡ ጊጉያን፤

ሦስቱ፡ ካህናት፡ ይበድላሉ፡ ይስታሉ፤

ወኢይሌብዉ፡ ዓማፅያን፤

ፅርአውያን፡ ሕገ፡ እግዚአብሔርን፡ ልብ፡ አያደርጉም፤

ወይጤይቁ፡ ጠቢባን፡ ጊዜ፡ ሣህሉ፤

መቃብያን፡ ይቅር፡ የሚልበትን፡ ጊዜ፡ ያውቃሉ፤

ወሕዝብ፡ ይሌብዉ፡ ብዙኃ፡ እምዘወ ሀብክዎሙ፤

መቃብያን፡ ከሰጠኋቸው፡ ዕውቀት፡ የተነሣ፡ እነአንጥያኮስ፡ የሚሞቱበትን፡ ቀን፡ ያውቃሉ፤ አንድም፡ እምዘወሀብክዎ፡ ይላል፤

የሰጠሁት፡ ዕድሜ፡ ከመፈጸሙ፡ የተነሣ፡ አንጥያኮስ፡ የሚሞትበትን፡ ጊዜ፡ ያውቃል፤ አንድም፤ ከሰጠኋቸው፡ ዕውቀት፡ የተነሣ፡ ይቅርታዬን፡ ያውቃሉ፤

፲፩፤ ወእምጊዜ፡ ይሠዓር፡ መሥዋ ዕት፡ ለውሂበ፡ ርኩሰሙ፡ ሙስና፡ መዋ ዕል፡ ፲ቱ፡ ወ፪ቱ፡ ፻ወ፺፤

መሥዋዕተ፡ ኦሪት፡ ከጠፋ፡ ጀምሮ፡ ሙስና፡ ርኩስ፡ ጣዖት፡ ሊሰጥ፡ ሽህ፡ ከሁለት፡ መቶ፡ ዘጠና፡ ቀን፡ ቀርቷል፤ አንድም፡ ውስን፡ ይላል፡ መሥዋዕተ፡ ኦሪት፡ ከጠፋ፡ ጀምሮ፡ ውስን፡ ርኩስ፡ ጣዖት፡ ሊሰጥ፡ በሽህ፡ ሁለት፡ መቶ፡ ዘጠና፡ ቀን፡ ተወ ስኗል፤ አንድም፡ ለብዉሂ፡ ሙስነ፡ ርኩሰ፡ ሙስን፡ ርኩስ፡ ጣዖትን፡ እንዳታመልኩ፡ ሽህ፡ ሁለት፡ መቶ፡ ዘጠናውን፡ ቀን፡ ልብ፡ አድርጉ፤ አንድም፤ ሙስን፡ ርኩስ፡ ጣዖትን፡ እንዳታመልኩ፤ በሽህ፡ ሁለት፡ መቶ፡ ዘጠና፡ ቀን፡ ተወስኗል፤ ከመ፡ ይትበ ዋህ፡ ይትወሀብ፡ እምነ፡ ርኩ ሰሙ፡ የሚል፡ አብነት፡ ይገኛል፤ አሥራ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ይቀር፡ የለም፡ ቢሉ፡ መጣ፡ መጣ፡ ሲባል፡ የሄዱ፡ አሉና፤



፲፪፤ ብፁዕ፡ ዘተዐገሠ፡ ወበጽሐ፤

መከራውን፡ የታገሠ፡ ሰው፡ ንዑድ፡ ክቡር፡ ነው፤

አሠርተ፡ ምዕተ፡ ወሠለስተ፡ ምዕተ፡ ወሠ ላሳ፡ ወሐሙሰ፡ መዋዕለ፤

ሽህ፡ ከሦስት፡ መቶ፡ ሠላሳ፡ አምስቱን፡ ቀን፡ ደርሶ፡ መከራ ውን፡ የታገሠ፡ ንዑድ፡ ክቡር፡ ነው፤ አምሳ፡ ስምንት፡ ቀን፡ ይቀር፡ የለም፡ ቢሉ፡ መጣ፡ መጣ፡ ሲባል፡ የሄዱ፡ አሉና፤ አንድም፡ አምሳ፡ ስምንት፡ ቀን፡ ቆይተው፡ የተመለሱ፡ አሉና፤

፲፫፤ ወአንተሰ፡ ዳንኤል፡ ሑር፡ ለዕ ድሜ፡ ወአዕርፍ፤

ሙቶ፡ ብዙ፡ ዘመን፡ ለመኖር፡ በሞት፡ ሂድ፤ በሞትም፡ ታር ፋለህ፤

እስመ፡ ዓዲ፡ መዋዕል፡ ወሰንበታት፡ በዘ ይትፌጸም፡ ማኅለቅቱ፤

ዘመኑ፡ ብዙ፡ ነውና፡ ሱባዔው፡ በሚፈጸም፡ ገንዘብ፡ የሚፈጸም በት፡ ጊዜው፡ ገና፡ ነውና፡ በሞት፡ እረፍ፤

ወትትነሣእ፡ ውስተ፡ ርስትከ፡ በደኃሪ፡ መዋዕል፤

በኋላ፡ ዘመን፡ በገነት፡ በመንግ ሥተ፡ ሰማያት፡ ለመኖር፡ በም [illegible]

## ምዕራፍ፡ ፲፫፡

፩፡ ወሀሎ፡ ፩፡ ብእሲ፤ ዘይነብር፡ በባቢሎን፡ ዘስሙ፡ ኢዮአቄም፤

በባቢሎን፡ የሚኖር፡ ስሙ፡ ኢዮ አቄም፡ የሚባል፡ አንድ፡ ሰው፡ ነበረ፤ ስለምን፡ በዋዌ፡ ጀመረ፡ ቢሉ፡ መጻሕፍት፡ ይቀድሙታ ልና፤ አንዱ፡ መጽሐፍስ፡ ለአ ንዱ፡ መጽሐፍ፡ ዋዌ፡ አይሆነ ውም፡ ብሎ፡ መጽሐፍ፡ ምሥ ጢር፡ ይጠነቅቃል፡ እንጂ፡ አን ድና፡ ብዙ፤ ሩቅና፡ ቅርብ፤ ሴትና፡ ወንድ፡ አይጠነቅቅምና፡ ለመጻሕፍት፡ በዋዌ፡ መጀመር፡ ልማዳቸው፡ ነው፤ ወሀሎ፡ ፩ዱ፡ ብእሲ፡ በሀገረ፡ አውስጢድ፡ ዘስሙ፡ ኢዮብ፡ ዘይፈርሆ፡ ለእ ግዚአብሔር፡ እንዳለ፡ ወሀሎ፡ ፩ዱ፡ ብእሲ፡ ዘእምነ፡ አርማ ቴም፡ ዘመሴፋ፡ ዘስሙ፡ ሕል ቃና፡ እንዳለ፤ ፩፡ ሳሙ.፩፥፩፤

፪፤ ወአውሰበ፡ ብእሲተ፡ እንተ፡ ስማ፡ ሶስና፡ ወለተ፡ ኬልቅዩስ፤

የኬልቅዩስን፡ ልጅ፡ ስሟ፡ ሶስና፡ የምትባል፡ ሚስት፡ አገባ፤ ሶስና፡ ማለት፡ ዕድምተ፡ ስንዕ፤ ሠና ይተ፡ ስን፡ ማለት፡ ነው፤ አን ድም፡ ቀይ፡ አበባ፡ ጥቁር፡ አበባ፡ ሱሳን፡ ማለት፡ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ወሠናይት፡ ጥቀ

መልክ፡ ከደም፡ ግባት፡ አስተባ
ብራ፡ የያዘች፡ ነበረች፤ አሁን፡
ሁለቱ፡ መምህራን፡ ወደሷ፡ ሄዱ፡
የሚል፡ ነውና፤

ወትፈርህ፡ እግዚአብሔርሃ፤

እግዚአብሔርን፡ ትፈራ፡ ነበ
ረች፤ እምቢ፡ አለቻቸው፡ የሚል፡
ነውና፤

፫፤ ወአዝማዲሃኒ፡ ጻድቃን፡
እሙንቱ፤

እናት፡ አባቷ፡ ደጋጎች፡ ነበሩ፤
ወመሀርዋ፡ ለወለቶሙ፡ ኦሪተ፡
ሙሴ፡ የሚል፡ ነውና፤

ወመሀርዋ፡ ለወለቶሙ፡ ኦሪተ፡ ሙሴ፤

ስምንቱን፡ በሐውርተ፡ ኦሪት፤
አንድም፡ አሠርቱ፡ ቃላትን፡
ዳግም፡ ሕግን፡ ኢትዘሙን፡ አስ
ተምረዋት፡ ነበር፤

፬፤ ወኢዮአቄምሰ፡ ምታ፡ ባዕል፡
ጥቀ፤

ባሏ፡ ኢዮአቄም፡ ግን፡ እጅግ፡
ባለጸጋ፡ ነበር፤ ወይመጽኡ፡
ኀቤሁ፡ እለ፡ ይትኳነኑ፡ ብሎ፡
እንዲያመጣው፤

ወቦ፡ ዐፀደ፡ ሐምል፡ ኀረቤቱ፤

ስትታጠብ፡ አገኛት፡ የሚል፡
ነውና፤

ወይመጽኡ፡ ኀቤሁ፡ አይሁድ፤

አይሁድ፡ ወደሱ፡ ይመጡ፡
ነበር፤

እስመ፡ ውእቱ፡ ይከብር፡ እምኵሎሙ፤

ከሁሉ፡ እሱ፡ ይከብር፡ ነበርና፤

፭፤ ወአስተርአዩ፡ ፪ቱ፡ ረበናት፡
በውእቱ፡ ዓመት፡ እለ፡ በእንቲአሆሙ፡
ነገረ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ እምባቢ
ሎን፡ ወጽአት፡ ኃጢአት፤

ኃጢአት፡ ከባቢሎን፡ እንደ፡
ተገኘች፡ እግዚአብሔር፡ በሄ
ኖክ፡ አድሮ፡ ወጸውዓ፡ ፸፡ ኖላ
ውያነ፡ ካላቸው፡ ወገን፡ ናቸ
ውና፡ ብሎ፡ ያናገረባቸው፡ ሁለቱ፡
ረበናት፡ በዚያ፡ ወራት፡ በክ
ፋት፡ ታዩ፤ አንድም፡ ኃጢአት፡
ከባቢሎን፡ እንደተገኘች፡ በሕዝ
ቅኤል፡ የተናገረባቸው፡ ሁለቱ፡
ረበናት፡ በክፋት ታዩ፤ ወጸውዓ፡
፸፡ ኖላውያነ፡ ባለው፡ ዘዘከ
ሮሙ፡ ሕዝቅኤል፡ ይላል፤ አን
ድም፡ ከሕዝቅኤል፡ ይልቅ፡ ዳን
ኤል፡ በባቢሎን፡ ሳለ፡ የተናገረባ
ቸው፡ ሁለቱ፡ መምህራን፡ በክ
ፋት፡ ታዩ፤

ወእምሕዝብ፡ መደልዋን፡ እለ፡ ይብሉ፡
ነዓቅቦሙ፡



ለን፡ የሚሉ፡ ሁለቱ፡ ረበናት፡
በክፋት፡ ታዩ፤

፮፤ ወእሙንቱ፡ ይለምዱ፤

በኢዮአቄም፡ ቤት፡ የለመዱ፡
ነበሩ፤አንድም፡ ይፀመዱ፡ ይላል፤
በኢዮአቄም፡ ቤት፡ ያገለግሉ፤
ያስተምሩ፡ ነበር፤ ወፅሙዱስ፡
ሆሴዕ፡ ወልደ፡ ነዌ፡ እንዲል፤
ማገልገል፡ የደቀ፡ መዝሙር፡
ብቻ፡ አይደለም፤ መምህርም፡
በማስተማር፡ ያገለግላልና፤

ወይመጽኡ፡ ኀቤሁ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡
ይትኳነኑ፤

የሚፈራረዱ፡ ሁሉ፡ ወደሱ፡
ይመጡ፡ ነበር፤

፯፤ ወእምዝ፡ አቲዎሙ፡ ሕዝብ፡
ጊዜ፡ ቀትር፡ ትበውዕ፡ ሶስና፤

ሕዝቡ፡ ከገቡ፡ በኋላ፡ በቀትር፡
ጊዜ፡ ሶስና፡ ትገባ፡ ነበር፤

ወታንሶሱ፡ ውስተ፡ ዓፀደ፡ አቅማሕ፡
ዘምታ፤

የባሏ፡ ገንዘብ፡ በሚሆን፡ በተ
ክል፡ ቦታ፡ ትመላለስ፡ ነበር፤

፰፤ ወይሬእይዋ፡ ረበናት፡ ኵሎ፡
አሚረ፡ ሶበ፡ ትበውዕ፡ ወታንሶሱ፤

ወደተክሉ፡ ቦታ፡ ገብታ፡ ስትመ
ላለስ፡ ሁለቱ፡ ረበናት፡ ሁል፡
ጊዜ፡ ያይዋት፡ ነበር፤

፱፤ ወሜጡ፡ ልቦሙ፤

ልቡናቸውን፡ ወደ፡ ዝሙት፡ ወደ፡
ኃጢአት፡ መለሱ፤

ወገፍትዑ፡ አዕይንቲሆሙ፤

ዓይነ፡ ልቡናቸውን፡ ለዝሙት፡
ግልብጥብጥ፡ አደረጉ፤

ከመ፡ ኢይነጽሩ፡ ሰማየ፤

ሰማያዊ፡ ሕግን፡ እንዳይመለከቱ፤
አንድም፤ ሰማያዊ፡ እግዚአብ
ሔርን፡ እንዳያስቡ፤

ወኢተዘከሩ፡ ኵነኔ፡ ጽድቅ፤

እውነተኛ፡ ሕግ፡ ኢታምልክን፡
አላሰቡም፤ አንድም፡ ኢትሑር፡
ኀበ፡ ብእሲተ፡ ብእሲ፡ ያለውን፡
አላሰቡም፤

፲፤ ወ፪ኤሆሙ፡ አፍቀርዋ፤

ሁለቱም፡ ወደዷት፤

ወኢተናገሩ፡ በበይናቲሆሙ፡ ዘውስተ፡
ልቦሙ፤

የልቡናቸውን፡ ሐሳብ፡ እርስ፡
በርሳቸው፡ አልተነጋገሩም፤

እስመ፡ ኃፍሩ፡ ነጊረ፡ ፍትወቶሙ፤

ፈቃዳቸውን፡ መናገር፡ አፍ
ረዋልና፤

፲፩፤ ወይፈቅዱ፡ ይስክቡ፡ ምስሌሃ፤

ከሷ፡ ጋራ፡ ሊጫዋወቱ፡ ወደው፤

ወይፀንሕዋ፡ ኵሎ፡ አሚረ፡ ይርከብዋ፤

ያገኟት፡ ዘንድ፡ ሁል፡ ጊዜ፡
ይጠብቋት፡ ነበር፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ወይቤሎ፡ ፩ዱ፡ ለካልዑ፡ ንዕቱ፡ ቤተነ፤

አንዱ፡ አንዱን፡ ወደቤታችን፡ እንግባ፡ አለው፤ አንድም፡ ንን ሥት፡ ዐውደነ፡ ይላል፤ ጉባኤያ ችንን፡ እንፍታ፡ አለው፤

እስመ፡ ጊዜ፡ ምሳሕ፡ ውእቱ፤

የምሳ፡ ጊዜ፡ ነውና፤ በሀገራ ቸው፡ ጥዋት፡ አይበሉም፤ የሚ ጽፍ፡ ሲጽፍ፤ የሚደጉስ፡ ሲደ ጉስ፤ አርፍደው፡ የሚበሉት፡ በስድስት፡ ሰዓት፡ ነውና፤

ወኃለፉ፤

ሄዱ፤

ወተፋለጡ፡ በበይናቲሆሙ፤

እርስ፡ በርሳቸው፡ በጐዳና፡ ተለ ያዩ፤ አንድም፡ በነገር፡ ተለያዩ፤

፲፫፤ ወተሠውጡ፤

ተመለሱ፤

ወተራከቡ፡ ኅቡረ፤

በጎዳና፤ አንድም፤ በነገር፡ ተገናኙ፤

ወተናጸሩ፡ ፪ኤሆሙ፤

ሁለቱ፡ ተያዩ፤

ወሶቤሃ፡ ተናገሩ፡ ፍትወቶሙ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ፈቃዳቸውን፡ ተጨ ዋወቱ፤ የት፡ ትሄዳለህ? ወደ፡ ሶስና፤ እኔም፡ ወደ፡ ሶስና፤ ማንን፡ ትሻለህ? ሶስናን፤ እኔም፡ ሶስ ናን፤ ተባባሉ፤ ለአንድ፡ ያሉት፡ እንጂ፡ ለሁለት፡ ይበቃል፡ ብለው፡ በአንድነት፡ ሔደዋል፤

ወተዓደሙ፡ ጊዜ፡ ይክሉ፡ ረኪቦታ፡ ባሕቲታ፤

ብቻዋን፡ ማግኘት፡ የሚችሉበትን፡ ጊዜ፡ ተቃጠሩ፤

፲፬፤ ወእምዝ፡ እንዘ፡ ይፀንሕዋ፡ መዓልተ፡ ቦአት፡ ሶስና፡ ከመ፡ ዘልፍ፡ ምስለ፡ ፪ዔ፡ አዋልዲሃ፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ ቀን፡ ሲጠብቋት፡ ሶስና፡ ከሁለቱ፡ ገረዶቿ፡ ጋራ፡ እንደ፡ ወትሮው፡ ከተክል፡ ቦታ፡ ገባች፤ አዋልዲሃ፡ ባለው፡ ገዛዒሃ፡ ይላል፤

ወፈተወት፡ ትትሐፀብ፡ በውስተ፡ ገነት፤

በተክሉ፡ ውስጥ፡ ትታጠብ፡ ዘንድ፡ ወደደች፤

እስመ፡ ሐፈወት፤

ወዝታለችና፡ በቀትር፡ ጊዜ፡ ሰውነት፡ ይወዛልና፤

፲፭፤ ወአልቦ፡ ህየ፡ ወኢመኑሂ፡ ዘአ ንበለ፡ ፪ቱ፡ ረበናት፡ እለ፡ ይትኀበዑ፡ ይፀንሕዋ፤

ተሠውረው፡ ከሚጠብቋት፡ ከሁ ለቱ፡ ረበናት፡ በቀር፡ ከዚያ፡ ማንም፡ ማን፡ አልነበረም፤

፲፮፤ ወትቤሎን፡ ለአዋልዲሃ፡ ያም ጽኣ፡ ላቲ፡ ቅብአ፡ ወይሕፅባሃ፤

ገረዶቿን፡ ሽቱ፡ አምጥተው፡ ያጥቧት፡ ዘንድ፡ አዘዘቻቸው፤

ወይዕፅዋ፡ ኆኅተ፡ ገነት፡ ከመ፡ ትትሐፀብ፤

ስትታጠብ፡ የተክሉን፡ ደጅ፡ ይዘጉ፡ ዘንድ፡ አዘዘቻቸው፤



ወይዕፅዋ፡ ኆኅተ፡ ገነት፡ ወይ ሕፅባሃ፡ ሲል፡ ነው፤ የተክሉን፡ ደጅ፡ ዘግተው፡ ያጥቧት፡ ዘንድ፤

፲፯፤ ወገብራ፡ በከመ፡ አዘዞን፤

እንደ፡ አዘዘቻቸው፡ አደረጉ፤

ወአፀዋ፡ ኆኅተ፡ ገነት

የተክሉን፡ ደጅ፡ ዘጉ፤

ወወጽኣ፡ እንተ፡ መፍልስት፡ ከመ፡ ያም ጽኣ፡ ዘአዘዘቶን፤

ያዘዘቻቸውን፡ ያመጡ፡ ዘንድ፡ በሥርጥ፡ ጐዳና፡ ወጡ፤

ወኢርእያሆሙ፡ ለረበናት፡ እለ፡ ተኀብዑ፤

የተሠወሩ፡ ረበናትን፡ አላዩዋ ቸውም፤

፲፰፤ ወወጺኦን፡ እልክቱ፡ አዋልድ፡ ተንሥኡ፡ እልክቱ፡ ፪ቱ፡ ረበናት፤

ገረዶች፡ ከወጡ፡ በኋላ፡ እኒህ፡ ሁለቱ፡ ረበናት፡ ተነሡ፤

ወሮፁ፡ ኀቤሃ፤

ወደሷ፡ ፈጥነው፡ ሄዱ፤

፲፱፤ ወይቤልዋ፡ ናሁ፡ ዕፅው፡ ኆኅተ፡ ገነት፤

ሰው፡ ይደርስብናል፡ እንዳትዪ፡ እነሆ፡ የተክሉ፡ ደጅ፡ ተዘግ ቷል፡ አሏት፤

ወአልቦ፡ ዘይሬእየነ፤

ሰው፡ ያየናል፡ እንዳትዪ፡ የሚ ያየን፡ ሰው፡ የለም፤

ወንፈቱ፡ ንስክብ፡ ምስሌኪ፡ ወኦሆ፡ በልነ፤

ከአንቺ፡ ልንደርስ፡ እንወዳለን፤ እሽ፡ በጂ፡ በይን፤

፳፤ ወእመ፡ አኮ፡ ናስተዋድየኪ፡ ከመ፡ ረከብነ፡ ብእሴ፡ ምስሌኪ፤

አይሆንም፡ ብትዪን፡ ካንች፡ ጋራ፡ ሰው፡ እንዳገኘን፡ ነግረን፡ እና ጣላሻለን፤

ወበእንተ፡ ገዝ፡ ሰደድኪ፡ አዋልደኪ፡ እምኔኪ፤

ይምሰልን፡ አይምሰልን፡ በይዋ፡ ስለዚህ፡ ነገር፡ ገረዶችሽን፡ ከአ ንቺ፡ ለይተሽ፡ የሰደድሽ፡ አይ ደለምን፤

፳፩፤ ወበከየት፡ ሶስና፡ ወትቤ፡ ተመንደብኩ፡ ፈድፋደ፡ እምኵሉሄ፤

ሶስና፡ አለቀሰች፡ ከሁሉም፡ እጅግ፡ ተጨነቅሁ፡ አለች፤

እመኒ፡ ገበርኩ፡ እመውት፤

ዝሙቱንም፡ ባደርገው፡ እሞ ታለሁ፤

ወእመኒ፡ ኢገበርኩ፡ ኢይድኅን፤

ባላደርገውም፤ አልድንም፤

ወኢይክል፡ አምሥጠ፡ እምእዴክሙ፤

ከእጃችሁ፡ ማምለጥ፡ አልችልም፤

፳፪፤ ይኄይሰኒ፡ ኢገቢርየ፡ እደቅ፡ ውስተ፡ እዴክሙ፡ እምአብሶ፡ ቅድመ፡ እግዚአብሔር፤

በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ኃጢአት፡ ሠርቼ፡ ከምበድል፡ ዝሙቱን፡

www.ethiopianorthodox.org

ሳላደርግ፡ በናንተ፡ እጅ፡ መው ደቅ፡ ይሻለኛል፤

፳፫፤ ወአውየወት፡ ሶስና፡ በዓቢይ፡ ቃል፣

ሶስና፡ ቃሏን፡ አሰምታ፡ ጮኸች፤

ወአውየዉ፡ ረበናትሂ፡ ምስሌሃ፣

ረበናትም፡ ከሷ፡ ጋራ፡ ጮኹ፤ ተንኰል፡ ነው፡ ለማስመሰል፤

፳፬፤ ወሮፀ፡ ፩ዱ፡ ወአርኃወ፡ ኆኅተ፡ ገነት፣

አንዱ፡ ፈጥኖ፡ ሄዶ፡ የተክሉን፡ ደጅ፡ ከፈተ፣ አሁን፡ ሄደ፡ ለማለት፣

፳፭፤ ወሰሚያሙ፡ አውያተ፡ በው ስተ፡ ገነት፡ ወጽኡ፡ እለ፡ ውስተ፡ ቤታ፡ በጊዜሃ፣

በተክሉ፡ ውስጥ፡ ጩኸቱን፡ ሰምተው፡ በቤቷ፡ ያሉ፡ ሰዎች፡ ያን፡ ጊዜ፡ ወጡ፤

ወሮፁ፡ እንተ፡ መፍልስት፡ ከመ፡ ይር አዩ፡ ምንተ፡ ዘኮነ፣

የሆነው፡ ምን፡ እንደሆነ፡ ያዩ፡ ዘንድ፡ በሥርጥ፡ ጐዳና፡ ፈጥ ነው፡ ሄዱ፤

፳፮፤ ወሶበ፡ ተናገሩ፡ እልክቱ፡ ረበ ናት፡ ዘ፡ ነገረ፡ ተኃፍሩ፡ አግብርት፡ ጥቀ፣

እሊህ፡ ረበናት፡ ይህን፡ ነገር፡ በተናገሩ፡ ጊዜ፡ ባሮች፡ እጅግ፡ [illegible]

እስመ፡ ግሙራ፡ ኢተሰምዓ፡ ዘከመዝ፡ ነገር፡ ላዕለ፡ ሶስና፣

እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ በሶስና፡ ላይ፡ ፈጽሞ፡ አልተሰማምና፣

፳፯፤ ወበሳኒታ፡ ተጋቢያሙ፡ ሕዝብ፡ ኀበ፡ ምታ፡ ኢዮአቄም፣

ቀን፡ ቀጥሯቸዋል፤ በማግሥቱ፡ ሕዝቡ፡ ከባሏ፡ ከኢዮአቄም፡ ዘንድ፡ ተሰብስበው፡ ሳለ፤

መጽኡ፡ እልክቱ፡ ፪ቱ፡ ረበናት፡ ምስለ፡ ልቦሙ፡ ዘዓመፃ፣

ከክፋታቸው፡ ሳይመለሱ፣ ከሐ ሰታቸው፡ ሳይከፍሉ፡ እሊህ፡ ሁለቱ፡ መምህራን፡ መጡ፤

ከመ፡ ያቅትልዋ፡ ለሶስና፣

ሶስናን፡ ያስገድሏት፡ ዘንድ፤

፳፰፤ ወይቤሉ፡ ቅድመ፡ ሕዝብ፣

በሕዝቡ፡ ፊት፡ እንዲህ፡ አሉ፤

ለአኩ፡ ኀበ፡ ሶስና፡ ወለተ፡ ኬልቅዩስ፡ ብእሲተ፡ ኢዮአቄም፡ ያምጽእዋ፣

የኢዮአቄምን፡ ሚስት፡ የኬልቅ ዩስን፡ ልጅ፡ ሶስናን፡ ያመጧት፡ ዘንድ፡ ላኩባት፡ አሉ፤

ወለአኩ፡ ባቲ፣

ላኩባት፤

፳፱፤ ወመጽአት፡ ይእቲ፡ ወነገዳ፡ ወአዝማዲሃ፡ ወኲሉ፡ ዘመዳ፡ ወኲሉ፡ ዘየአምራ፣

ሶስና፡ መጣች፤ ነገዷ፣ እናት፡ አባቷ፣ ዘመዷ፡ ሁሉ፡ የሚያ ውቋት፡ ሁሉ፡ መጡ፤



፴፤ ወሶስናሰ፡ ላኅዩት፡ ጥቀ፡ ወሠ ናይ፡ ራእያ፣

ሶስና፡ ግን፡ መልክ፡ ከደም፡ ግባት፡ የያዘች፡ መልከ፡ መል ካም፡ ነበረች፤

፴፩፤ ወአዘዙ፡ እልክቱ፡ ዓማፅያን፡ ይክሥትዋ፡ ርእሳ፡ ከመ፡ ይጽገቡ፡ እምላህያ፣

እኒህ፡ ዓማፅያን፡ ሰርመዴዋን፡ ይገልጧት፡ ዘንድ፡ አዘዙ፣ ለጊ ዜው፡ እንደ፡ ሙሴ፡ ሥርዓት፡ ለማድረግ፡ ነው፤ ምሥጢሩ፡ ግን፡ ከመ፡ ይፅገቡ፡ አምላኅያ፡ ብሎ፡ እንዲያመጣው፡ መልኳን፡ አይተው፡ ይጠግቡ፡ ዘንድ፡ ነው፤

ወከሠትዋ

ሰርመዴዋን፡ ገለጧት፤

፴፪፤ ወበከዩ፡ አዝማዲሃ፣

ዘመዶቿ፤

ወሰብአ

ቤተሰቦቿ፤

ወኲሉ፡ ዘየአምራ፣

የሚያውቋት፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ አለቀሱ፤

፴፫፤ ወተንሥኡ፡ እልክቱ፡ ፪ቱ፡ ረበ ናት፡ ማዕከለ፡ ሕዝብ፣

እሊህ፡ ሁለቱ፡ ረበናት፡ በሕ ዝቡ፡ መካከል፡ ቆሙ፤

ወአንበሩ፡ እዴሆሙ፡ ላዕለ፡ ርእሳ፣

እጃቸውን፡ በራሷ፡ ላይ፡ ጫኑ፤ አሁንም፡ በጄ፡ ትዩን፡ እንደሆነ፡ እንደምንም፡ ብለን፡ እናድንሽ፡ ሲሉ፣

፴፬፤ ወይእቲሰ፡ እንዘ፡ ትበኪ፡ ነጸ ረት፡ ሰማየ፣

እሷ፡ ግን፡ እያለቀሰች፡ ሰማያዊ፡ እግዚአብሔርን፡ አሰበች፤

እስመ፡ ተወከለ፡ ልባ፡ በእግዚአብሔር፣

ልቧ፡ በእግዚአብሔር፡ ታም ኗልና፣

፴፭፤ ወይቤሉ፡ እልክቱ፡ ረበናት፡ እንዘ፡ ናንሶሱ፡ ውስተ፡ ገነት፡ ባሕቲተነ፣

እኒህ፡ ሁለቱ፡ ረበናት፡ በተክሉ፡ ውስጥ፡ ብቻችንን፡ ስንመላለስ፤

ቦአት፡ ይእቲ፡ ወ፪ቲ፡ ገዛኢሃ፣

እሷ፡ ሁለቱ፡ ደንገጡሮቿ፡ ገቡ፡ አሉ፤

ወዐፀዋ፡ ኆኅተ፡ ገነት፡ ወሖራ፣

የተክሉን፡ ደጅ፡ ዘግተው፡ ሄዱ፤

፴፮፤ ወእምድኅረዝ፡ ፈነወቶን፡ ለአዋልዲሃ፣

ከዚህ፡ በኋላ፡ ደንገጡሮቿን፡ ሰደደቻቸው፤

ወመጽአ፡ ኀቤሃ፡ ፩፡ ወሬዛ፡ እምወዕደ፡ ይትኀባዕ፣

ከተሠወረበት፡ ዘንድ፡ አንድ፡ ጐልማሳ፡ ወደሷ፡ መጣ፣

www.ethiopianorthodox.org

ወሰከበ፡ ምስሌሃ፤

ከሷ፡ ጋራ፡ ተጨዋወተ፤

፴፯፤ ወንሕነሰ፡ ውስተ፡ ማዕዘንተ፡ ገነት፡ ርኢነ፡ ኃጢአቶሙ፤

እኛ፡ ግን፡ በተክሉ፡ ቦታ፡ ማዕዘን፡ ሁነን፡ ኃጢአታቸውን፡ አየን፤

ወሮፅነ፡ ኀቤሆሙ፤

ፈጥነን፡ ወደነሱ፡ ሄድነ፤

ወረከብናሆሙ፡ ይሰክቡ፡ ኅቡረ፤

አንድ፡ ሁነው፡ ሲጨዋወቱ፡ አገኘናቸው፤

፴፰፤ ወንሕነሰ፡ ስዕናሁ፡ ሎቱ፡ እኂዞቶ፤

እኛ፡ ግን፡ በምግባር፡ በትሩፋት፡ ደክመናልና፡ እሱን፡ መያዝ፡ አልተቻለንም፤

ወአምሠጠነ፡ እስመ፡ ይኄይለነ፤

ይበረታታብናልና፡ አመለጠን፤

ወአርኃወ፡ ኆኅተ፡ ወወጽአ፤

በሩን፡ ከፍቶ፡ ሄደ፤

፴፱፤ ወኪያሃሰ፡ አኀዝናሃ፤

እሷን፡ ግን፡ ያዝናት፤

ወተስእልናሃ፡ መኑ፡ ብእሲሁ፡ ወኢያይድዓተነ፤

ሰውየው፡ ማነው፡ ብለን፡ ብን ጠይቃት፡ አልነገረችንም፤

፵፤ ወአምንዎሙ፡ ዓውድ፤

የጨረቃ፡ ሂያጅ፡ የምስክር፡ ፈራጅ፡ እንዲሉ፡ ሕዝቡ፡ አመኗቸው፤

እስመ፡ ረበናተ፡ ሕዝብ፡ ኮሙ፡ንቱ፤

ሐሰተኞች፡ እንዳይሏቸው፡ የሕዝቡ፡ መምህራን፡ ናቸውና፤

ወመኳንንት፤

በገንዘብ፡ ይታለላሉ፡ እንዳይሏቸው፡ ገዥዎች፡ ናቸውና፤

ወኰነንዋ፡ ትሙት

ትሞት፡ ዘንድ፡ ፈረዱባት፤

፵፩፤ ወዓውየወት፡ ሶስና፡ በዓቢይ፡ ቃል፤

ሶስና፡ ቃሏን፡ አሰምታ፡ ጮኸች፤ ጽራሐ፡ ልቡና፡ ነው፤ ወይቤሎ፡ ለሙሴ፡ ለምንት፡ ትጸርህ፡ ኀቤየ፡ በሎሙ፡ ለሕዝብ፡ ይንድዑ፡ እንስሳሆሙ፡ እንዲል፤

ወትቤ፡ ኦ፡ አምላክ፡ ዘለዓለም፤

ለዘለዓለም፡ የምትኖር፡ ፈጣሪ፤

ዘተአምር፡ ዘኅቡዕ፤

የተሠወረውን፡ የምታውቅ፡ አንተ፡ ነህ፤

ወዘተአምር፡ ኵሎ፡ ዘእንበለ፡ ይኩን፤

ሳይደረግ፡ ሁሉን፡ የምታውቅ፤

፵፪፤ አንተ፡ ተአምር፡ ከመ፡ ሐሰተ፡ አስተዋደዩኒ፤

በሐሰት፡ እንዳጣሉኝ፡ አንተ፡ ታውቃለህ



ወናሁ፡ እመውት፡ ዘአልብየ፡ ዘገበርኩ፤

ያደረግሁት፡ ሳይኖር፡ እነሆ፡ እሞታለሁ፤

በዘአሕሰሙ፡ ላዕሌየ፡ እሉ፡ ረበናት፤

እሊህ፡ ረበናት፡ በኔ፡ ላይ፡ ክፉ፡ ነገር፡ ባደረጉ፡ ገንዘብ፤

፵፫፤ ወሰምዓ፡ እግዚአብሔር፡ ቃላ፤

እግዚአብሔር፡ ልመናዋን፡ ሰማት፤

፵፬፤ ወእንዘ፡ ይወስድዋ፡ ይቅትልዋ፤

በደንጊያ፡ ወግረው፡ በእሳት፡ ጠብሰው፡ ሊገሏት፡ ሲወስዷት፤

አንሥአ፡ እግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ላዕለ፡ ወልድ፡ ወሬዛ፡ ዘስሙ፡ ዳንኤል፤

ስሙ፡ ዳንኤል፡ በሚባል፡ በአንድ፡ ጐልማሳ፡ ልጅ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ አሳደረበት፤ አንድም፡ የዳንኤልን፡ ልቡናውን፡ አነሣሳው፤

፵፭፤ ወከልሐ፡ በዓቢይ፡ ቃል፤

ቃሉን፡ አሰምቶ፡ ጮኸ፤

ወይቤ፡ ንጹሕ፡ አነ፡ እምደማ፡ ለዛቲ፡ ብእሲት፤

እኔ፡ ከዚች፡ ሴት፡ ደም፡ ንጹሕ፡ ነኝ፡ አለ፤ አንድም፡ ከነፍሷ፡ ፍዳ፡ ንጹሕ፡ ነኝ፤ ደምን፡ ነፍስ፡ አላት፤ እስመ፡ ነፍስ፡ ተኃድር፡ በደም፡ እንዲል፤ የበሉት፡ የጠጡት፡ ደም፡ ይሆናልና፤

፵፮፤ ወተመይጠ፡ ኵሉ፡ ሕዝብ፡ ኀቤሁ፤

ሕዝቡ፡ ሁሉ፡ ወደሱ፡ ተመለሱ፤

ወይቤሉ፡ ምንትኑ፡ ዝ፡ ነገር፡ ዘትብል፡ አንተ፤

አንተ፡ የምትናገረው፡ ይህ፡ ነገር፡ ምንድነው፡ አሉ፤

፵፯፤ ወቆመ፡ ማዕከሎሙ፤

በመካከላቸው፡ ቆመ፤

ወይቤሎሙ፡ ከመዝኑ፡ አንትሙ፡ ደቂቀ፡ እስራኤል፡ ዘእንበለ፡ ትሕትቱ፡ ወትጠይቁ፡ ትኴንኑ፡ ወለተ፡ እስራኤል፤

እናንተ፡ የእስራኤል፡ ልጆች፡ ሳትመረምሩ፤ ሳትረዱ፡ በእስራኤል፡ ልጅ፡ እንዲህን፡ ትፈርዳላችሁ? አንድም፡ ከመዝኑ፡ አብዳን፡ አንትሙ፤ እናንት፡ የእስራኤል፡ ልጆች፡ እንዲህን፡ አላዋቆች፡ ናችሁ? ሳትመረምሩ፡ ሳትረዱ፡ በእስራኤል፡ ልጅ፡ የምትፈርዱ፤

፵፰፤ ግብኡኬ፡ ውስተ፡ ዓውድ፤

ወደ፡ አደባባይ፡ ተመለሱ፤

እስመ፡ ሐሰዉ፡ አስተዋድዮታ፡ እሉ፤

እነዚህ፡ በሐሰት፡ አጣልተዋታልና፤

፵፱፤ ወተሠውጡ፡ ኵሉ፡ ሕዝብ፡ ውስተ፡ ዓውድ፡ እንዘ፡ ይረውፁ፤

ሕዝቡ፡ ሁሉ፡ ፈጥነው፡ ወደ፡ አደባባይ፡ ተመለሱ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤልዎ፡ ለዳንኤል፡ ሊቃናት፡ ነዓ፡ ንበር፡ ማዕከሌነ፡ ወንግረነ፤

ዳንኤልን፡ አለቆች፡ ና፡ በመካከላችን፡ ተቀምጠህ፡ ንገረን፡ አሉት።

እስመ፡ ኪያከ፡ አልሐቀ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ አንተን፡ በዕውቀት፡ አልቆሃልና።

፶፤ ወይቤሎሙ፡ ዳንኤል፡ አስተራሕቅዎሙ፤ ዘዘዚአሆሙ፡ ወእሕትቶሙ፤

እየራሳቸው፡ አራርቋቸው፤ ልመርምራቸው፡ አላቸው።

ወዓቀምዎሙ፡ ለለ፩ዱ፤

አንዱንም፡ አንዱንም፡ እየራሳቸው፡ አቆሟቸው።

፶፩፤ ወጸውዖ፡ ለ፩ዱ፡ እምኔሆሙ፤

ከነዚያ፡ አንዱን፡ ጠራው።

ወይቤሎ፡ ብሉይ፡ መዋዕሊከ፡ ወእኩያት፤

አስቀድሞ፡ ይዘልፈዋል፤ ብዙ፡ የሆኑ፡ ዘመኖችህ፡ ክፉዎች፡ ናቸው።

በጽሐ፡ ኃጣውኢከ፡ ዘገበርከ፡ ቀዲሙ፤

አስቀድመህ፡ የሠራኸው፡ ኃጢአትህ፡ ፍዳ፡ ይዞ፡ ደረሰብህ።

፶፪፤ እስመ፡ ኮነንከ፡ ፍትሐ፡ ዓመፃ፤

ሐሰት፡ ፍርድ፡ ፈርደሃልና።

ወአሕየውከ፡ ጊጉያነ፤

ይሞት፡ በቃውን፡ ይድን፡ በቃ፡ ብለሃልና።

ወቀተልከ፡ ንጹሐ፤

ይድን፡ በቃውን፡ ይሙት፡ በቃ፡ ብለሃልና።

ዘከልዓ፡ እግዚአብሔር፤

ወኃጥኣ፡ ኢታሕዩ፡ ያለውን፡ ነው።

ወይቤ፡ ጻድቀ፡ ወንጹሐ፡ ኢትቅትል፤

ጻድቁን፡ ንጹሑን፡ አትግደል፡ ያለውን፡ ለውጠሃልና።

፶፫፤ ወይእዜኒ፡ እመ፡ ርኢካሃ፡ ለዛቲ፤

ማየትስ፡ አላየሃትም፡ አሁንም፡ ይቺን፡ ሴት፡ አይታሃት፡ እንደሆነ።

ንግረኒ፡ በታሕተ፡ ዓይ፡ ዕፅ፡ ነበ፡ ርኢክሙ፡ ይትናገሩ፡ ፪ሆሙ፤

ሁለቱ፡ ሲጨዋወቱ፡ ያያችሁበት፡ ከምን፡ እንጨት፡ ሥር፡ ነው፡ ንገረኝ።

ወይቤ፡ ታሕተ፡ ዕፀ፡ ሰኪኖን፤

ሰኪኖን፡(ኮክ፡)ከሚባል፡እንጨት፡ ሥር፡ ነው። አንድም፡ ለውዝ፡ ከሚባል፡ እንጨት፡ ሥር፡ ነው። ሰኪኖን፡ ባለው፡ ዕፀ፡ ለውዝም፡ ይላል።

፶፬፤ ወይቤሎ፡ ዳንኤል፡ አማን፡ ሐሰውከ፤

ዳንኤል፡ በእውነት፡ ሐሰት፡ ተናገርህ፡ አለው።



ወደምከ፡ ላዕለ፡ ርእስከ፤

ደምህ፡ በራስህ፡ ላይ፡ ነው።

ናሁ፡ ወድዓ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ተአዚዞ፡ በኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ያንቅዕከ፡ እማዕከሌከ፤

እነሆ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ከሁለት፡ ይከፍልህ፡ ዘንድ፡ ከእግዚአብሔር፡ ታዘዘ፤ አንድም፤ ከማዕከለ፡ ዘመንህ፡ ይለይህ፡ ዘንድ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ታዘዘ።

፶፭፤ ወአግኃሦ፡ ኪያሁ፤

እሱን፡ አርቆ።

ወአዘዘ፡ ያምጽኡ፡ ካልዖ፤

ሁለተኛውን፡ ያመጡ፡ ዘንድ፡ አዘዘ።

ወአምጽእዎ፤

አመጡት።

ወይቤሎ፡ ዘርአ፡ ከነዓን፡ ወአኮ፡ ዘይሁዳ፤

ይህንንም፡ አስቀድሞ፡ ይዘልፈዋል። የይሁዳ፡ ያይደለ፡ አንተ፡ የከነዓን፡ ልጅ።

ላኅይ፡ አስሐተከ፤

ደም፡ ግባት፡ አሳተህ።

ወፍትወት፡ ገፍትዓ፡ ልበከ፤

ፈቲው፡ ልቡናህን፡ ግልብጥ ብጥ፡ አደረገው።

፶፮፤ ከመዝኑ፡ ትሬስዩ፡ ወለተ፡ እስራኤል፤

የእስራኤልን፡ ልጅ፡ እንዲህን፡ ታደርጋላችሁ?

እስመ፡ ይእቲ፡ ኢክህለት፡ ተዋቅሶተክሙ፤

ይች፡ እናንተን፡ መከራከር፡ አልተቻላትምና።

ወፈርሀት፡ ወለተ፡ ይሁዳ፤

የይሁዳ፡ ልጅ፡ ፈርታለችና፤

ወተዓገሠት፡ ዕዕለተክሙ፤

ስድባችሁን፡ ታገሠች።

፶፯፤ ይእዜኒ፡ ንግረኒ፡ ምንት፡ ዕፀ፡ ነበ፡ ረከብክሙ፡ እንዘ፡ ይትናገሩ፡ ፪ሆሙ፤

ሁለቱ፡ ሲጨዋወቱ፡ ያገኛችሁበት፡ ዛፉ፡ ምንድነው፡ እስቲ፡ ንገረኝ።

ወይቤ፡ ታሕተ፡ ዕፀ፡ ጽርዮን፤

ሮማን፡ ከሚባል፡ እንጨት፡ ሥር፡ ነው። አንድም፡ ገውዝ፡ ማለት፡ ነው። እነዚያ፡ በዝሙት፡ ተናድደዋልና፤ ይሰክቡ፡ ይሰክቡ፡ ይላሉ። እሱ፡ ግን፡ የለበትምና፡ ይትናገሩ፡ ይትናገሩ፡ ይላል።

፶፰፤ ወይቤሎ፡ ዳንኤል፡ አማን፡ ሐሰውከ፡ አንተኒ፡ ላዕለ፡ ርእስከ፤

በውነት፡ በራስህ፡ ላይ፡ አንተም፡ ሐሰት፡ ተናገርክ፡ አለው።

ናሁ፡ ጽኑሕ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ በሰይፍ፡ ይሥፅርከ፡ እመንፈቅከ፤

እነሆ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ በሰይፍ፡ ከሁለት፡ ይከፍልሕ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ፡ ደጅ፡ ይጠናሃል፤ አንድም፡ ከማዕከለ፡ ዘመንህ፡ ሊለይህ፡ ይጠብቀሃል፤

ከመ፡ ይሥሩከ፤

ሊያጠፉህ፡ ወዶ፤

፳፱፤ ወከልሐ፡ ኵሉ፡ ሕዝብ፡ በዓ
ቢይ፡ ቃል፤

ሕዝቡ፡ ሁሉ፡ ቃላቸውን፡ አሰ ምተው፡ ጮሁ፤

ወባረክዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘአድኃና፡ ለሶስና፡ ዘተወከለት፡ ቦቱ፤

ያመነችበት፡ ሶስናን፡ ያዳናት፡ እግዚአብሔርን፡ አመሰገኑት፤

፴፤ ወተንሥኡ፡ ሕዝብ፡ ላዕለ፡ እል
ክቱ፡ ፪ቱ፡ ረበናት፤

ሕዝቡ፡ በሁለቱ፡ ረበናት፡ ላይ፡ በጠላትነት፡ ተነሡ፤

እስመ፡ አርስሐሙ፡ ዳንኤል፡ እም ቃሎሙ፤

ከቃላቸው፡ የተነሣ፡ ዳንኤል፡ አስነቅፏቸዋልና፤

ወሐሰዎሙ፡ ስምየሙ፤

ምስክርነታቸውንም፡ ሐሰት፡ አድርጎባቸዋልና፤

ወገብሩ፡ እኩየ፡ ላዕሌሆሙ፡ በከመ፡ ገብሩ፡ እኩየ፡ ዲበ፡ ቢጾሙ፡ በሕገ፡ ሙሴ፤

በሶስና፡ ላይ፡ ክፉ፡ ነገር፡ እንዳደ ረጉ፡ በሙሴ፡ ሥርዓት፡ በነ ዚያ፡ ላይ፡ ክፉ፡ ነገር፡ አደረ ጉባቸው፤

፴፩፤ ወአድኃኑ፡ ደመ፡ ንጹሐ፡ በይ
እቲ፡ ዕለት፤

በዚያች፡ ቀን፡ ንጹሕ፡ ደምን፡ ከማፍሰስ፡ አዳኑ፤

፴፪፤ ወአእኰትዎ፡ ለእግዚአብሔር፡
ኬልቅዩስ፡ ወብእሲቱ፡ በእንተ፡ ወለ ቶሙ፡ ሶስና፡ ምስለ፡ ኢዮአቄም፡ ምታ፡ ወኵሎሙ፡ አዝማዲሃ፤

ከባሏ፡ ከኢዮአቄም፡ ከዘመዶቿ፡ ሁሉ፡ ጋራ፡ ስለ፡ ልጃቸው፡ ስለ፡ ሶስና፡ ኬልቅዩስና፡ ሚስቱ፡ እግ ዚአብሔርን፡ አመሰገኑት፤

እስመ፡ ኢተረክበ፡ እኩይ፡ ላዕሌሃ፤

በሷ፡ ላይ፡ ክፉ፡ ሥራ፡ አል ተገኘምና፤

፴፫፤ ወኮነ፡ ዳንኤል፡ ዓቢየ፡ በቅድመ፡
ሕዝብ፡ እምይእቲ፡ ዕለት፡ ወለዝላፉ፤

ከዚች፡ ቀን፡ ጀምሮ፡ ዳንኤል፡ ለዘለዓለሙ፡ በሕዝቡ፡ ፊት፡ ከበረ፤ ገነነ፡፡

## ምዕራፍ፡ ፲ወ፬

ወእምድኅረ፡ ሞተ፡ ንጉሥ፡ አስጥያዴስ፤

አስጥያዴስ፡ አስጥያጊስ፡ አስጥ ያግስ፡ ይላል፤ አስጥያዴስ፡ ከሞተ፡ በኋላ፤

ወተቀብረ፡ ኀበ፡ ተቀብሩ፡ አበዊሁ፤

አባቶቹ፡ ከተቀበሩበት፡ ቦታ፡ ከተ ቀበረ፡ በኋላ፤

ነሥአ፡ ቂሮስ፡ ፋርሳዊ፡ መንግሥቶ፤

የፋርስ፡ ሰው፡ ቂሮስ፡ መንግሥ ቱን፡ ያዘ፤



፩፤ ወሀሎ፡ ዳንኤል፡ ደቀ፡ ጽርሑ፡
ለንጉሥ፤

የንጉሥ፡ ባለሟል፡ ዳንኤል፡ ነበረ፤

ወይከብር፡ እምኵሉ፡ አዕርክቲሁ፤

ከባልንጀሮቹ፡ ሁሉ፡ እሱ፡ ይከ ብር፡ ነበር፤

፪፤ ወሀሎ፡ ምስል፡ ዘያመልክዎ፡
ሰብአ፡ ባቢሎን፤

የባቢሎን፡ ሰዎች፡ የሚያመል ኩት፡ ምስል፡ ነበር፤

ወያስተዋጽኡ፡ ኵሎ፡ አሚረ፡ ሲሳዮ፡ ሥን ዳሌ፡ ዕሥረ፡ ካዕበ፡ በመሥፈርት፡ አርጣባስ፤

ቻል፡ በሚባል፡ ማድጋ፡ ዕለት፡ ዕለት፡ ሀያ፡ ሀያ፡ ማድጋ፡ ሕጾ፡ ጉርዶ፡ የወጣ፡ ስንዴ፡ ያወጡ ለት፡ ነበር፤ አንድም፡ ዕሥረ፡ ወካዕበ፡ ይላል፤

ወአባግዓ፡ አርባዕተ፤

አራት፡ በግ፤

ወወይነ፡ ፮ተ፡ መስፈርተ፤

ሰባት፡ ፊቀን፡ ወይን፡ ያወጣጡ ለት፡ ነበር፤

፫፤ ወያመልኮ፡ ንጉሥ፡ ወየሐውር፡
ኵሎ፡ አሚረ፡ ወይሰግድ፡ ሎቱ፤

ንጉሥ፡ ያመልከው፡ ነበር፤ ሁል፡ ጊዜም፡ እየሄደ፡ ይሰግድለት፡ ነበር፤

ወዳንኤልሰ፡ ይሰግድ፡ ለአምላኩ፤

ዳንኤል፡ ግን፡ ለፈጣሪው፡ ይሰ ግድ፡ ነበር፤

ወይቤሎ፡ ንጉሥ፡ ለዳንኤል፡ ለምንት፡ ኢትሰግድ፡ ለቤል፤

ንጉሥ፡ ዳንኤልን፡ ለቤል፡ ለምን፡ አትሰግድም፡ አለው፤

፬፤ ወይቤ፡ ዳንኤል፡ ኢያመልክ፡
ጣዖተ፤

ጣዖት፡ አላመልክም፡ አለ፤

ወግብረ፡ እደ፡ ሰብእ፤

ይኸውም፡ የሰው፡ እጅ፡ ሥራ፡ ነው፤ አንድም፡ ጣዖተ፡ ግብረ፡ እደ፡ ሰብእ፤ ሰው፡ ሠራሽ፡ ጣዖ ትን፡ አላመልክም፡ አለ፤

ዘእንበለ፡ ዳዕሙ፡ ለአምላክ፡ ሕያው፡ ዘፈጠረ፡ ሰማየ፡ ወምድረ፤

ሰማይን፡ ምድርን፡ የፈጠረ፡ ሕያው፡ አምላክን፡ አመልካለሁ፡ እንጂ፤ አንድም፡ ሰማይን፡ ምድ ርን፡ ከፈጠረ፡ ከሕያው፡ አም ላክ፡ በቀር፡ ጣዖትን፡ አላመ ልክም፤

ወመኰንን፡ ውእቱ፡ ለኵሉ፡ ዘነፍስ፤

ለሥጋዊ፡ ለደማዊ፡ ሁሉ፡ ገዥ፡ እሱ፡ ነውና፤

፭፤ ወይቤሎ፡ ንጉሥ፡ ይመስለ
ከኑ፡ ዘኢኮነ፡ ሕያወ፡ አምላከ፡ ቤል፤

ንጉሥ፡ እንዲህ፡ አለው፤ ቤል፡ ሕያው፡ አምላክ፡ ያይደለ፡ ይመ ስልሃልን፤

www.ethiopianorthodox.org

ኢትሬኢኑ፡ መጠነ፡ ይበልዕ፡ ወይሰቲ፡ እንተ፡ ጸብሐት፤

ዕለት፡ ዕለት፡ የሚበላውን፡ የሚ ጠጣውን፡ መጠን፡ አታውቀው ምን፤ አንድም፡ እንዲበላ፡ እን ዲጠጣ፡ አታውቅምን፤

፮፤ ወሰሐቆ፡ ዳንኤል፤

ዳንኤል፡ ሳቀበት፤

ወይቤ፡ ኢያስሕቱከ፡ ኦ፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ ሆይ፡ አያስቱሕ፡ አለ፤

ዝሰ፡ ውስጡ፡ ፅቡር፡ ወአፍአሁ፡ ብርት፤

ይህስ፡ ውስጡ፡ ጭቃ፡ አፍአው፡ (ውጭው)፡ ብርት፡ ነው፤ በፊት፡ ጭቃውን፡ መስለው፡ በላይ፡ ብርቱን፡ ያፈሱታልና፤ አንድም፡ ጥንቱን፡ ጭቃ፡ ነውና፡ መስ ለው፡ ያፈሱታልና፤

ኢይበልዕ፡ ወኢይሰቲ፡ ግሙራ፤

ፈጽሞ፡ አይበላም፡ አይጠጣም፤

፯፤ ወተምዓ፡ ንጉሥ፡ ወጸውዖሙ፡ ለገነውተ፡ ቤል፤

ንጉሥ፡ ተቆጥቶ፡ ካህናተ፡ ጣዖ ቱን፡ ጠራቸው፤

ወይቤሎሙ፡ እመ፡ ኢነገርክሙኒ፡ መኑ፡ ዘይበልዕ፡ ዘንተ፡ ሲሳዮ፡ ትመውቱ፤

ይህነን፡ ምግቡን፡ የሚበላው፡ ማን፡ እንደሆነ፡ ካልነገራችሁኝ፡ ትሞታላችሁ፤

፰፤ ወእመሰ፡ አብጸሕክሙ፡ ሊተ፡ ከመ፡ ቤል፡ ይበልዕ፡ ይመውት፡ ዳንኤል፡ ዘፀረፈ፡ ላዕለ፡ ቤል፤

ቤል፡ እንዲበላ፡ ብትረቱ፡ ግን፡ ቤልን፡ የሰደበ፡ ዳንኤል፡ ይሞታል፤

ወይቤሎ፡ ዳንኤል፡ ለንጉሥ፡ ለይኩን፡ በከመ፡ ትቤ፤

ዳንኤል፡ ንጉሥን፡ እንዳልህ፡ ይሁን፡ አለው፤

፱፤ ወየአክሉ፡ ገነውቱ፡ ለቤል፡ ፸፡ ዘእንበለ፡ አንስት፡ ወደቅ፤

ከሴት፡ ከሕፃናት፡ በቀር፡ ካህናተ፡ ጣዖቱ፡ ሰባ፡ ያህሉ፡ ነበር፤

ወሖሩ፡ ንጉሥ፡ ወዳንኤል፡ ቤተ፡ ቤል፤

ንጉሡና፡ ዳንኤል፡ ወደ፡ ጣዖቱ፡ ቤት፡ ሄዱ፤

፲፤ ወይቤሉ፡ ገነውተ፡ ቤል፡ ናሁ፡ ንሕነ፡ ነሐውር፡ አፍኣ፤

ካህናተ፡ ጣዖቱ፡ እንሆ፡ እኛ፡ ወደ፡ ውጭ፡ እንሄዳለን፤

አንተ፡ ንጉሥ፡ ሥራዕ፡ ማዕዳቲሁ፡ ወቅ ዱሕ፡ ወይኖ፡ ወአስተናብር፡ ወዕፁ፡ ኆኅቶ፡ ወኅትም፡ በማኅተምከ፤

ንጉሥ፡ አንተ፡ ማዕዱን፡ ሠር ተህ፤ ወይኑን፡ ቀድተህ፡ አዘጋ ጅተህ፡ ደጁን፡ ዘግተህ፡ በማኅ ተም፡ ቆልፈው፡ አሉ፤



፲፩፤ ወጊሥ፡ በጽባሕ፡ ለእመ፡ ረከ ብከ፡ በዘኢበልዐ፡ ኵሎ፡ ቤል፡ ንመውት፡ ንሕነ፤

ማለዳ፡ ገሥግሠህ፡ ሂድ፡ ቤል፡ በልቶ፡ እንጂ፡ ያልበላ፡ ሁኖ፡ ቢገኝ፡ እኛ፡ እንሞታለን፤

ወእመ፡ አኮሰ፡ ዳንኤል፡ ዘሐሰወ፡ ላዕሌነ፡ ይመውት፤

ያልበላ፡ ሁኖ፡ እንጂ፡ በልቶ፡ ቢገኝ፡ በኛ፡ ላይ፡ ሐሰት፡ የተና ገረ፡ ዳንኤል፡ ይሞታል፤

፲፪፤ ወእሙንቱሰ፡ የአምሩ፡ ዘይገ ብሩ፡ በታሕተ፡ ማዕድ፡ ቦሙ፡ ፍኖት፡ ኅቡዕ፤

እነዚያ፡ ግን፡ የሚያደርጉትን፡ ያውቁ፡ ነበር፤ ከማዕዱ፡ በታች፡ ውስጥ፡ ለውስጥ፡ የሚሄዱበት፡ ሥርጥ፡ ጉዳና፡ ነበራቸው፤

ወእንተ፡ ህየ፡ ይበውዑ፡ ዘልፈ፡ ወይበልዑ፡ ወይሰትዩ፤

እነዚያ፡ ግን፡ ሁል፡ ጊዜ፡ በሥ ርጡ፡ ጎዳና፡ እየገቡ፡ ይበሉ፡ ይጠጡ፡ ነበር፤

፲፫፤ ወወጺኦሙ፡ እሙንቱ፡ ሠርዐ፡ ንጉሥ፡ ለቤል፡ ዘይበልዕ፤

እነዚያ፡ ከወጡ፡ በኋላ፡ ንጉሥ፡ ለቤል፡ የሚበላውን፡ አዘጋጀ፤

ወአዘዞ፡ ዳንኤል፡ ለቍልዔሁ፡ ያምጽእ፡ ሐመደ፤

ዳንኤል፡ አመዱን፡ ያመጣ፡ ዘንድ፡ ብላቴናውን፡ አዘዘ፤

ወረበቦ፡ ውስተ፡ ቤቱ፡ ለቤል፡ በቅድመ፡ ንጉሥ፡ ባሕቲቱ፤

በንጉሥ፡ ፊት፡ ብቻ፡ አመዱን፡ በጣዖቱ፡ ቤት፡ ነሰነሰው፤

ወወጺኦሙ፡ አፀዉ፡ ኆኅተ፤

ወጥተው፡ ደጁን፡ ዘጉ፤

ወኀተሙ፡ ማኅተመ፡ ንጉሥ፡ ወዳንኤል፤

ንጉሥና፡ ዳንኤል፡ ቍልፉን፡ ቆለፉ፤

፲፬፤ ወኃለፎሙ፡ ቦኡ፡ ገነውተ፡ ቤል፡ በሌሊት፡ በከመ፡ ያለምዱ፡ ምስለ፡ አንስ ቲሆሙ፡ ወደቂቆሙ፡ በልዑ፡ ወሰትዩ፡ ኵሎሙ፤

ንጉሥና፡ ዳንኤል፡ ከሄዱ፡ በኋላ፡ ካህናተ፡ ጣዖቱ፡ እንደለመዱ፡ ሌሊት፡ ገብተው፡ ከሚስቶቻቸው፡ ከልጆቻቸው፡ ጋራ፡ ሁሉን፡ በሉ፡ ጠጡ፤

፲፭፤ ወጌሡ፡ በጽባሕ፡ ንጉሥ፡ ወዳ ንኤል፤

ንጉሥና፡ ዳንኤል፡ ማልደው፡ ሄዱ፤

፲፮፤ ወይቤ፡ ንጉሥ፡ ዳኅንኑ፡ ማኅ ተምከ፡ ዳንኤል፡ ወይቤ፡ ዳንኤል፡ እወ፡ ዳኅን፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ ዳንኤልን፡ ማኅተምህ፡ ደህና፡ ነው? አለው፤ ዳንኤልም፡ ንጉሥ፡ አዎን፡ ደህና፡ ነው፤ አለው፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፤ ወእምዝ፡ ሶበ፡ አርኃው፡ ኆኅተ፡ ነጸረ፡ ንጉሥ፡ በዘወድዑ፡ ማዕደ፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ ደጁን፡ በከፈተ፡ ጊዜ፡ ንጉሥ፡ ማዕዱን፡ በፈጸሙት፡ ገንዘብ፡ ፈጽመውት፡ አየ፤

ወወውዓ፡ በዓቢይ፡ ቃል፤

ቃሉን፡ አሰምቶ፡ ተናገረ፤

ወይቤ፡ ዓቢይ፡ አንተ፡ ቤል፡ ወአልብከ፡ ትምይንት፤

ቤል፡ አንተ፡ ደግ፡ ገናና፡ ነህ፡ ሐሰት፡ ሽንገላ፡ ተንኮል፡ የለብ ህም፡ አለ፤

፲፰፤ ወሰሐቀ፡ ዳንኤል፤

ዳንኤል፡ ነገሩን፡ ናቀበት፤

ወአኃዞ፡ ለንጉሥ፡ ወከልኦ፡ ኢይባዕ፡ ውስጠ፤

ወደውስጥ፡ እንዳይገባ፡ ንጉሡን፡ ይዞ፡ ከለከለው፤

ወይቤሎ፡ ነጽር፡ ምድረ፡ ወርኢ፡ አሠረ፡ ምንት፡ ዝንቱ፤

ምድሩን፡ ተመልከት፡ ይህ፡ የምን፡ ፍለጋ (ዱካ) ነው? አለው፤

፲፱፤ ወይቤ፡ ንጉሥ፡ እሬኢ፡ ዓሠረ፡ ዕደው፡ ወአንስት፡ ወደቅ፤

ንጉሥ፡ እንዲህ፡ አለ፤ የወንዶ ችን፡ የሴቶችን፡ የልጆችን፡ ጫማ፡ ኢያለሁ፡ የሴቶች፡ ጫማ፡ ጠመም፡ ጠመም፡ ብሎ፤ የሕፃናቱ፡ ታና ናሽ፡ ሁኖ፡ ይታወቃልና፤

ወተምዓ፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ ተቆጣ፤

፳፤ ወአኃዞሙ፡ ሶቤሃ፡ ለገነውተ፡ ቤል፡ ወለአንስቶሙ፡ ወለደቂቆሙ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ካህናተ፡ ጣዖቱን፤ ሴቶችን፤ ልጆችን፡ ያዛቸው፤

ወአርአይዎ፡ ኆኅተ፡ ኅቡዓ፡ እንተ፡ ነበ፡ ይበውዑ፡ ወይበልዑ፡ ዘውስተ፡ ማዕድ፤

በማዕድ፡ ውስጥ፡ እየገቡ፡ የሚ በሉበትን፡ ሥርጥ፡ ጕዳና፡ አሳዩት፤

፳፩፤ ወቀተሎሙ፡ ንጉሥ፤

ንጉሥ፡ ገደላቸው፤

ወወሀቦ፡ ቤልሃ፡ ወመጠዎ፡ ለዳንኤል፡ ወቀጥቀጦ፡ ወነሠተ፡ ቤቶ፤

ቤልን፡ ለዳንኤል፡ ሰጠው፡ ቀጠ ቀጠው፡ ቤተ፡ ጣዖቱንም፡ አፈ ረሰው፤

፳፪፤ ወሀሎ፡ ከይሲ፡ ዓቢይ፡ ዘያ መልክዎ፡ ሰብአ፡ ባቢሎን፤

የባቢሎን፡ ሰዎች፡ የሚያመል ኩት፡ ታላቅ፡ ዘንዶ፡ ነበረ፤

፳፫፤ ወይቤሎ፡ ንጉሥ፡ ለዳንኤል፡ ዝንቱኬ፡ ብርትኑ፡ ውእቱ፡ ትብሎ፤

ንጉሥ፡ ዳንኤልን፡ ይህንንም፡ ብርት፡ ነው፡ ትለዋለህ? አለው፤

ናሁ፡ ሕያው፡ ይበልዕ፡ ወይሰቲ፤

እነሆ፡ ሕያው፡ ነው፡ ይበላል፡ ይጠጣል፤



ወኢትክል፡ ብሂሎቶ፡ ኢኮነ፡ ሕያወ፡ አምላከ፡ ወስግድ፡ ሎቱ፤

ደህነኛ፡ አምላክ፡ አይደለም፡ ማለት፡ አይቻልህም፡ ስገድለት፤

፳፬፤ ወይቤ፡ ዳንኤል፡ ለእግዚአብ ሔር፡ አምላኪየ፡ እሰግድ፡ እስመ፡ ውእቱ፡ አምላክ፡ ሕያው፤

ዳንኤል፡ ለፈጣሪዬ፡ ለእግ ዚአብሔር፡ እሰግዳለሁ፡ አለ፤ ሕያው፡ አምላክ፡ እሱ፡ ነውና፤

፳፭፤ ወአንተ፡ ንጉሥ፡ አብኃኒ፡ እቅ ትሎ፡ ለዝ፡ ከይሲ፡ ዘእንበለ፡ መጥባሕት፡ ወበትር፤

ያለብትር፡ ያለሰይፍ፡ ይህን፡ ዘንዶ፡ እገድለው፡ ዘንድ፡ ንጉሥ፡ አሰና ብተኝ፡ አለው፤

ወይቤሎ፡ ንጉሥ፡ ለዳንኤል፡ አባሕኩከ፤

ንጉሥ፡ ዳንኤልን፡ አሰናብቼሃ ለሁ፡ ግደለው፡ አለው፤

፳፮፤ ወነሥአ፡ ዳንኤል፡ ፒሳ፡ ወሥ ዕርተ፡ ወስብሐ፤

ዳንኤል፡ ስቡን፤ ሰም፤ አደሮ ማር፤ ጠጕር፡ አመጣ፤

ወአብሰሎ፡ ኅቡረ፤

አንድ፡ አድርጎ፡ ቀቀለው፡ ጠበሰው፤

ወገብሮ፡ ልሕሉሃ፤

ልሕሰህ፡ (ልል)፡ አደረገው፤

ወአፍአሞ፡ ለከይሲ፡ ውስተ፡ አፉሁ፤

አለሎውን፡ ደንጋይ፡ በዚህ፡ ጠቅሎ፡ ለዘንዶው፡ በአፉ፡ አጐረሰው፤

ወውኂጦ፡ ነቅዓ፡ ውእቱ፡ ከይሲ፤

ዘንዶው፡ ይኸንን፡ ውጦ፡ ተሰነ ጠቀ፤ ይኸም፡ ለጊዜው፡ ተደር ጓል፤ ለኋላው፡ ምሳሌ፡ ነው፤ ዕብን፡ የወልደ፡ እግዚአብሔር፤ አደሮማር፤ ሙጫ፤ ስብ፤ ጠጕር፡ አንድ፡ ወገን፤ የትስብእት፤ ከይሲ፡ የዲያብሎስ፤ አንድም፡ ከይሲ፡ የመቃብር፤ ስብ፡ አደሮማር፡ የወልደ፡ እግዚአብሔር፤

ወይቤሎሙ፡ ዳንኤል፡ ርእዩ፡ አም ላከክሙ፤

ዳንኤል፡ ፈጣሪያችሁን፡ እዩ፡ አላቸው፤

፳፯፤ ወእምዝ፡ ሰሚዖሙ፡ ሰብአ፡ ባቢሎን፡ ተምዑ፡ ጥቀ፤

ከዚህ፡ በኋላ፡ የባቢሎን፡ ሰዎች፡ ሰምተው፡ ፈጽመው፡ ተቆጡ፤

ወተመይጡ፡ ላዕለ፡ ንጉሥ፤

ወደንጉሡ፡ ተመለሱ፤

ወይቤሉ፡ ተኃይደ፡ ንጉሥ፡ ተኃይደ፤

ንጉሥ፡ መንግሥቱን፡ ተቀማ፡ ተቀማ፡ አሉ፤

ቤልሃኒ፡ ቀጥቀጠ፤

ቤልን፡ ቀጠቀጠ፡ ትኸ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወገነውተኒ፡ ቀተለ፤

ካህናቱን፡ ገደለ፤ ትች፤

ወከይሴኒ፡ ቀተለ፤

ዘንዶውን፡ ገደለ፡ ትች፤

፳፰፤ ወይቤሉ፡ ንዑ፡ ንሑር፡ ኀበ፡ ንጉሥ፡ የሀበነ፡ ዳንኤልሃ፤

ዳንኤልን፡ ይሰጠን፡ ዘንድ፡ ኑ፡ ወደ፡ ንጉሥ፡ እንሂድ፡ አሉ፤

ወእመ፡ አኮ፡ ንቀትለከ፡ ንብሎ፤

ዳንኤልን፡ ካልሰጠኸን፡ እንገ ድልሃለን፤

ወቤተከሂ፡ ናውዒ፡ በእሳት፤

ቤትህን፡ በእሳት፡ እናቃጥለዋ ለን፤ አንድም፡ ንበረብሮ፡ ይላል፤ ቤትህን፡ እንበዘብዘዋለን፡ እን ለዋለን፡ አሉ፤

፳፱፤ ወርእዮ፡ ንጉሥ፡ ከመ፡ ጥቀ፡ ያጠውቅዎ፤

ንጉሥ፡ እጅግ፡ እንዳስጨነቁት፡ አይቶ፤

ሶቤሃ፡ በግብር፡ ኮኖ፡ ለንጉሥ፡ መጠ ዎሙ፡ ዳንኤልሃ፤

አገር፡ ቢያብር፡ ለንጉሥ፡ ያስቸ ግር፤ ፈትል፡ ቢያብር፡ አንበሳ፡ ያሥር፡ እንዲሉ፡ የዳንኤል፡ ሞት፡ ግድ፡ በሆነበት፡ ጊዜ፡ ዳንኤልን፡ ሰጣቸው፤

፴፤ ወወሰድዎ፡ ወወደይዎ፡ ውስተ፡ ግበ፡ አናብስት፤

ወስደው፡ ከአንበሳ፡ ጉድጓድ፡ ጣሉት፤

ወነበረ፡ ህየ፡ ፮ተ፡ ዕለተ፤

በዚያ፡ ስድስት፡ ቀን፡ ተቀመጠ፤

፴፩፤ ወሀለዉ፡ ውስተ፡ ግብ፡፯ቱ፡ አናብስት፤

በጉድጓዱ፡ ውስጥ፡ ሰባት፡ አና ብስት፡ ነበሩ፤

ወዘሎሙ፡ አሚረ፡ ይሴስይዎሙ፡ ፪ተ፡ ሰብአ፡ ወ፪ተ፡ አባግዓ፤

ዕለት፡ ዕለት፡ ሁለት፡ ሰው፤ ሁለት፡ በግ፡ ይመግቧቸው፡ ነበር፤ ይሞት፡ በቃ፡ የተፈረ ደበት፡ ሰው፡ ነው፤

ወአሜሁሰ፡ ኢወሀብዎሙ፡ ምንተኒ፡ ከመ፡ ይብልዕዎ፡ ለዳንኤል፤

ያን፡ ጊዜ፡ ግን፡ ዳንኤልን፡ ይበ ሉት፡ ዘንድ፡ አልሰጧቸውም፡ ነበር፤

፴፪፤ ወሀሎ፡ ዕንባቆም፡ ነቢይ፡ በይሁዳ፤

ሀሎ፡ በፍልስጥኤም፡ ነው፤ ነቢዩ፡ ዕንባቆም፡ በፍልስጥኤም፡ ነበር፤

ወአብሰለ፡ ተብሲለ፡ ወኀብስተ፤

ንፍሮውን፡ ቀቅሎ፡ እንጀራው ንም፡ ይዞ፤

ወወደየ፡ ውስተ፡ አስፈሬዳ፤

በቅርጫት፤ አንድም፡ በመሶብ፡ አድርጎ፤

ወወፈረ፡ ውስተ፡ ሐቅል፡ ይሰድ፡ ለእለ፡ የዓፅዱ፤

ለአጫጆች፡ ይወስድ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ምድረ፡ በዳው፡ ሄደ፤



፴፫፤ ወይቤሎ፡ መልአከ፡ እግዚአብ ሔር፡ ለዕንባቆም፤

መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ዕንባ ቆምን፡ እንዲህ፡ አለው፤

ሰድ፡ ዘንተ፡ ምሳሐ፡ ለዳንኤል፡ ውስተ፡ ብሔረ፡ ባቢሎን፡ ኀበ፡ ግበ፡ አናብስት፤

ይህንን፡ ምሳ፡ በግበ፡ አናብስት፡ ላለ፡ ለዳንኤል፡ ወደ፡ ባቢሎን፡ ውሰድ፡ አለው፤

፴፬፤ ወይቤሎ፡ ዕንባቆም፡ እግዚኦ፡ ኢየአምር፡ ባቢሎንሃ፤

ዕንባቆምም፡ አቤቱ፡ ባቢሎንን፡ አላውቅም፡ አለው፤

ወኢርኢኩ፡ ግበ፡ አናብስት፡ አይቴ፡ ውእቱ፤

ግበ፡ አናብስት፡ ወዴትም፡ እን ደሆነ፡ አላየሁም፤

፴፭፤ ወአኃዞ፡ መልአከ፡ እግዚአ ብሔር፡ በድማሁ

መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ በመ ሀል፡ ራሱ፡ ያዘው፤ አንድም፡ በመ ልአኩ፡ ራስ፡ ያዘው፤

ወፆሮ፡ በስእርተ፡ ርእሱ፤

በአንዲት፡ ጠጉሩ፡ አንጠልጥሎ፤

ወአብጽሖ፡ ኀበ፡ ግበ፡ አናብስት፡ ዘባቢ ሎን፡ በኃይለ፡ መንፈስ፤

በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ኃይል፡ በባ ቢሎን፡ ባለ፡ አንበሳ፡ ጉድጓድ፡ አደረሰው፤ አንድም፡ በነፋሱ፡ ኃይል፤ አንድም፡ በመልአኩ፡ ኃይል፡ ከአንበሳ፡ ጉድጓድ፡ አደረሰው፤

፴፮፤ ወከልሀ፡ ዕንባቆም፡ ወይቤ፡ ዳንኤል፡ ዳንኤል፡ ንሣእ፡ ምሳሐ፡ ዘፈ ነወ፡ ለከ፡ እግዚአብሔር፤

ዕንባቆም፡ ቃሉን፡ አሰምቶ፡ ዳን ኤል፡ ዳንኤል፡ አለ፤ እግዚአብ ሔር፡ የሰደደልህን፡ ምሳ፡ ተቀበል፤

፴፯፤ ወይቤ፡ ዳንኤል፡ ተዘከረኒኑ፡ እግዚአብሔር፡ ወኢየኀድጎሙ፡ ለእለ፡ ያፈቅርዎ፤

ዳንኤልም፡ የሚወዱትን፡ ሰዎች፡ የማይተዋቸው፡ እግዚአብሔር፡ እኔንም፡ በምግብ፡ አሰበኝን፤ አንድም፡ ትንኝንስ፡ ስንኳ፡ በም ግብ፡ የሚያስብ፡ እግዚአብሔር፡ እኔንም፡ አሰበኝን፡ አለ፡ ራሱን፡ ከትንኝ፡ ቆጥሮ፤

፴፰፤ ውተንሥአ፡ ዳንኤል፡ ወበልዐ፤

ዳንኤል፡ ተነሥቶ፡ በላ፤

ወአግብኦ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ለዕንባ ቆም፡ ብሔሮ፡ ሶቤሃ፤

ያን፡ ጊዜ፡ መልአከ፡ እግዚአብ ሔር፡ ዕንባቆምን፡ ወደ፡ ሀገሩ፡ መለሰው፤ ይህም፡ ለጊዜው፡ ተደርጓል፤ ለኋላው፡ ምሳሌ፡ ነው፤ ዳንኤል፡ የምዕመናን፤ ምግቡ፡ የሥጋ፡ ወደሙ፤ ግበ፡ አናብስት፡ የአመቤታችን፤ ዕን ባቆም፡ የወልደ፡ እግዚአብሔር፡ ምሳሌ፡ ነው፤ ሳይከፍት፡ ገብቶ፡ ሳይከፍት፡ መውጣቱ፡ ጌታ፡ በኅቱም፡ ድንግልና፡ ተፀንሶ፡ በኅቱም፡ ድንግልና፡ ለመወለዱ፡ ምሳሌ፡ ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ዳል፣ ይወለዳል፣ ይሞታል፡ ተብሎ፡ ተናግሯል።

በአሕዛብስ፡ ስለአራት፡ ነገር፡ እንደምነው፡ ቢሉ፣ አሕዛብ፡ አምላክ፡ ሕዝብ፡ ነው፡ እንጂ፡ አምላክ፡ አሕዛብ፡ አይደለም፡ ይላሉ፤ ግድ፡ አምላክ፡ አሕዛብ፡ ወሕዝብ፡ እንደሆነ፡ ተናግሮባቸዋልና፣ ሁለተኛ፡ በደብያት፡ እንዲጠፉ፡ ተናግሮባቸዋል፤ በፍዳ፡ ማለቱ ነው፤ ሦስተኛ፡ አፍርሆ፡ ነው፤ እስራኤል በአሕዛብ፡ መከራ፡ ሲያጸናባቸው፡ አይተው፡ ሕግ፡ ባልተሠራላቸው፡ በአሕዛብ፡ እንዲህ፡ መከራ፡ ያጸናባቸው፡ በደብረ፡ ሲና፡ የተሠራልንን፡ ሕግ፡ ብናፈርስ፡ መከራውን፡ እንዴት፡ ያጸናብን፡ ይሆን፡ ብለው፡ ይፈራሉና።

አራተኛ፡ ትእምርት፡- (ትምህርት) ነቢዩ፡ ሕዝቡም፡ አሕዛቡም፡ ይጠፋሉ፡ ብሎ፡ ይናገራል፤ ኋላ፡ እስራኤል፡ አሕዛብ፡ ሲጠፉ፡ አይተው፡ ያ፡ ነቢይ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ አልቀረም፤ እኒያ፡ አሕዛብ፡ ጠፉ፣ እኛም፡እንጠፋ፡ይሆናል፡ ብለው፡ ምልክት፡ ያደርጓቸዋልና፡ እንዲህ፡ አለ፤ ይህስ፡ አይደለም፤ አፍርሆና፡ ትእምርትስ፡ (ትምህርትስ) አንድ፡ ወገን፡ ናቸው፡ ይጐራበታሉ ብሎ፡ አራተኛ፡ በነቢይ፡ በካህን፡ ሳያናግር፡ እንዳያጠፋቸው፡ ተናግሮባቸዋል።

ሰረይነ፡ ሰብአ፡ ወኢያህየውነ፡ ወኮነ ጽድቅነ፡ ከመ፡ ጸርቀ፡ ትክቶ፡ ፈወስናሃ ለባቢሎን፡ ወኢተፈወሰት፡ እንዲል፣ ይኸም፡ ተጽፎ፡ ሲነበብ፡ ሲተረጐም፡ ከነቢያት፡ እስከ፡ ሐዋርያት፡ ደረሰ፤ ሐዋርያትም፡ ለቀሌምንጦስ፡ ሰማንያ፡ አንዱን፡ መጽሐፍ፡ ቈጥረው፡ ሲሰጡት፡ ዐሥራ፡ ሁለት፡ ደቂቀ፡ ነቢያት፡ ብለው፡ ቆጥረው፡ ሰጥተውታል፤ ደቂቀ፡ ነቢያት፡ መባላቸው፡ የነቢያት፡ ልጆች፡ ሁነው፡ አይደለም፤ ከነቢያት፡ ወገን፡ ስለተወለዱ፤ አንድም፡ ከነቢያት፡ ስለተማሩ፡ ደቂቀ፡ ነቢያት፡ ተብለዋል፤ አንድም፡ ትንቢታቸው፣ ትምህርታቸው፡ ስለ፡ አጠረ፡ ደቂቀ፡ ነቢያት፡ ተብለዋል።

ይህንንም፡ የሚያስረዳ፡ አሞፅ፡ የኢሳይያስ፡ አባት፡ ነው፤ ኢሳይያስን፡ ከዓበይት፡ ነቢያት፡ አሞጽን፡ ከደቂቀ፡



ነቢያት፡ ጋራ፡ ይቈጥረዋል፤ አንድም፡ በእውነት፡ የነቢያት፡ ልጆች፡ ናቸው፤ ከደቂቀ፡ ነቢያት፡ አንዱ፡ አሞፅ፡ አንስ፡ ኢኮንኩ፡ ነቢየ፡ ወኢወልደ፡ ነቢይ፡ አለሳ፡ ቢሉ፣ እሱ፡ ባይሆን፡ ሌሎች፡ ናቸው፤ አንድም፡ እሱ፡ ራሱ፡ ትምህርቱን፡ ትንቢቱን፡ እንደ፡ አጥንት፡ እንደ፡ ጅማት፡ ከእናት፡ ከአባቱ፡ አላገኘሁትም፡ ሲል፡ ነው፡ እንጂ፡ የነቢይ፡ ልጅ፡ ነው፤ ትውልዱም፡ ከነገደ፡ ኤፍሬም፡ ነው፤

አሌ፡ ሎ፡ ኤፍሬም፡ ሥጋየ፡ ውእቱ፡ በማለቱ፡ ይታወቃል፤ ይኸም፡ ለከንቱ፡ አልተጻፈም፤ እኛ፡ ልንመከርበት፣ እኛ፡ ልንገሠጽበት፡ ነው፤ ወኵሉ፡ ዘተጽሕፈ፡ ለተግሣጸ፡ ዚአነ፡ ተጽሕፈ፡ ከመ፡ በትዕግሥትነ፡ ወበተወክሎተ፡ መጽሐፍ፡ ንርከብ፡ ተስፋነ፡ እንዲል፤ ሮሜ.፲፭-፬፤

እስከዚህ፡ አርእስት፡ ነው፤ ሠለስቱ፡ ምእት፡ ለመጻሕፍት፡ አርእስት፡ ሲሰጡ፡ አርእስት፡ ሰጥተውታል፣ እሱ፡ ግን፡ ነገሩን፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ብሎ፡ ያመጣል።

## - ምዕራፍ ፩ -

፩፤ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ኀበ፡ ሆሴዕ፡ ወልደ፡ ብኤርም፣

ዘሆሴዕ፡ ያሉ፡ ሠለስቱ፡ ምእት፡ ናቸው፣ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ያሉ፡ በኋላ፡ የተነሡ፡ ናቸው፤ አንድም፡ ዘሆሴዕ፡ ያሉ፡ በኋላ፡ የተነሡ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ያሉ፡ ሠለስቱ፡ ምእት፡ ናቸው፤ እሱ፡ ግን፡ ቀዳሜ፡ ቃሉ፡ ብሎ፡ ይጀምራል፤

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡ ነው፤ ከብኤርም፡ ልጅ፡ ከሆሴዕ፡ ዘንድ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ይህ፡ ነው፤

በመዋዕለ፡ ያዝያን፡ ወኢዮአታም፡ ወአካዝ፡ ወሕዝቅያስ፡ ነገሥተ፡ ይሁዳ፣

እለ፡ ነግሡ፡ በይሁዳ፡ እለ፡ ነግሡ፡ ለይሁዳ፡ ነገሥታተ፡ ይሁዳ፡ ይላል፤

በይሁዳ፡ በነገሡ፡ በነዚህ፡ ዘመን፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ ስለምን፡ እነዚህን፡ አነሣቸው፡ ቢሉ፡ መነሣቱ፡ በሊህ፡ ዘመን፡ ነውና፤ አንድም፡ በነዚህ፡ ዘመን፡ ብመከራቸው፡ ባስተምራቸው፡ አንሰማም፡ ብለው፡ ተማረኩ፡ ለማለት፤

www.ethiopianorthodox.org